የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት

ዓመታዊ ሪፖርት

ጥራዝ 1

ግንቦት/2010

አዲስ አበባ

ማውጫ

		ገጽ
1.	መግቢያ	1
2.	ኦዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report/	4
3.	የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በዘርፍ የተጠቃለለ ኦዲት ሪፖርት	
3.1	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን	39
3.2	የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች	57
3.3	የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	91
3.4	የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	136
3.5	የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች	178
3.6	የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	231

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

I. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲያስችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በእንጌጅሜንት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ6 የኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች፤የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች እና በ2 የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፤ እንዲሁም በክልል መንግስታት የተከናወነው የመሰረታዊ አገልገሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ለማከናወን በ1 የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በመደራጀት የኦዲቱ ስራ ተከናውኗል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት የስጋት ደረጃ እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

በሪፖርት ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፣ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም ስጋትን ያማከለ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መንግስት መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን ምላሽና አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡

መ/ቤታችን በሚከተለው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከየካቲት 1/2009 እስከ ጥር 30/2010 ዓ.ም (በጊዜያዊነት የተስተካከለ) የ172 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት፤ በመከናወን የኦዲት ሪፖርቶቹ ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፤ በዚህ ጥራዝ የተጠቃለለ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ዋና ዋና ግኝቶች ቀርቧል፡፡

II. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 39 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ 5 መ/ቤቶች ብር 927,522.46 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 2 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ3 መ/ቤቶች ብር 2,953,621.96 በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-2/1 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በተለያዩ መ/ቤቶችና ተጠሪ የሆኑ ቅ/ጽ/ቤቶች በርካታ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ-3/ሀ-ሐ እና አባሪ-4 እና 4/1 ተመልክቷል፡፡

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፤

- በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ እጅ መያዝ ከሚገባው በላይ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት የተገኘ በ1 መ/ቤትና የተለያዩ መ/ቤቶች በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 767,077.37፤
- የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ ያላስገቡ በ2 መ/ቤቶች ብር 3,474,137.59 መገኘቱ፣
- የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ 2 መ/ቤቶች፤
- የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ /ዴቢት/ በ1 መ/ቤትና በ7 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 167,543,104.87 መገኘቱ እና በ2 መ/ቤት ብር 14,788,427.82 መደበኛ ሚዛን ያልሆነ- (መክፈቻ ሚዛን) (ክሬዲት ባላንስ) ያለው የጥሬ ገንዘብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ ላይ በየወቅቱ ቁጥጥር በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲተገበር፤ በኦዲት የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንዲተካ፤ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2 <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

2.1 <u>በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ116 መ/ቤቶች እና በ15 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 5,835,334,951.52 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /በዝርዝሩ በአባሪ-6 እና አባሪ-6/1 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	52,074,277.63
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	3,682,154,951.75
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	510,191,429.81
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,172,375,148.70
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	318,249,742.67
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	100,289,400.96
ጠ/ድምር	ብር	**5,835,334,951.52**

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 1,004,811,500.39 ፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 3,745,300,525.75 ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 264,830,787.34 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 111,142,869.56 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 709,249,268.48 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ ነው፡፡ በተጨማሪም በ10 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,332,235,294.08 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከውዝፍ ተሰብሳቡ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ያዙት የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር3,526,111,909.99፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 572,280,328.63፤ የውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 194,467,448.89፤ ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር173,651,200.77፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 112,701,810.27፤ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት 6 ተጠሪ ተቋማት ብር 90,694,883.75፤ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 78,256,261.03 የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 58,763,114.41 ፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 67,156,467.64 እና ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤትና 9 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 52,074,277.63 ይገኙበታል፡፡የተሰብሳቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሳብም የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 1,215,751,975.22 እና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 54,687,040.37 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም፤ ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ12 መ/ቤቶች ብር 151,669,167.02 መሆኑ፣
- በአንድ መ/ቤት ያለአግባብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ የተሰረዘ ብር 500,231.72 መኖሩ፤ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ-7 ሀ እስከ ሐ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ /እንዲሰበሰቡ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3 የገቢ ሂሳብ

3.1 በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ ተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ ሰባት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,463,463,992.66 ፤በሌሎች በ49 መ/ቤቶች ብር 49,295,431.76 በድምሩ ብር 1,512,759,424.42 የገቢ ግብር፣

ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ/VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax)፤ የአክስዮን ትርፍ ድርሻ፤ እና በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበ እና በሌሎች 22 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ቅጣት ሂሳብ ብር 77,082,375.48 እና ገቢ ያልተደረገ የውል ማስከበሪያ ብር 1,256,965.48.00 ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በሁለት መ/ቤቶች ብር 8,132.60 እና በአንድ መ/ቤት የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ የወጪ መጋራት ሂሳብ ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-9 እና 9/1 እስከ አባሪ - 9/3 ተመልክቷል/

ገቢ ለመሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበው ሂሳብ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	1,463,463,992.66
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	375,886.11
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	14,784,874.29
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	33,017,042.07
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	753,095.85
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	364,533.44
ጠ/ድምር	ብር	1,512,759,424.42

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 985,860,257.77፣ ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 119,398,319.73፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 86,691,742.14፣ ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 70,980,332.17፣ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 41,581,761.09፤ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 37,911,841.04 ሲሆን ፤ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,473,484.63፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 6,054,599.28፤ ሀዋሳ ኒቨርሲቲ ብር 5,783,522.79 እና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,542,798.37 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code)

ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ፣ ማራገፊና ኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፊያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዥ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ</u>

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስር ባሉት ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 6,220,131,548.44 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ እና በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ባለመሰጠቱ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን 2 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ግብር፤ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 1,619,812,240.90 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 8 እና 8/1 ተመልክቷል/

በተጨማሪም ከሱቅና የቢሮ ኪራይና ሌሎች ውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ ሂሳብ ወለድና ቅጣት በ3 መ/ቤቶች ብር 6,431,747.45 እና ከሰጡት አገልግሎት ሽያጭ ላይ ውዝፍ ሂሳብ በ4 መ/ቤቶች ብር 64,695,033.19 በወቅቱ /በአባሪ- 8/2/ ያልተሰበሰበ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

ውዝፍ ገቢ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,922,242,000.48 ፤ የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 620,102,798.87 ፣ በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 333,325,596.16 እና ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 121,824,984.30 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የዱቤ ሽያጭ በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 58,070,344.30 ከፍተኛ ሲሆን፤ የዱቤ ሽያጭን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውዝፍ የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል ፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 32,840,678.91 ፤እንዲሁም በ7 መ/ቤቶች የማስከፈያ የዋጋ ተመን/ታሪፍ ሳይኖር የተሰበሰበ ገቢ ብር 14,333,161.16 እና በሌሎች 2 መ/ቤቶች በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። /ዝርዝራቸው በአባሪ-10 እና አባሪ-14 ተመልክቷል/

ዋና ዋና ምክንያቶቹም አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ መግቢያ ደረሰኝ (ማንኛውም እቃ ሲመጣ የሚመዘገብበት) ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ፤የውስጥ ገቢ ሂሳብ ምዝገባ ባለመካሄዱ እና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ እንቅስቃሴን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች እና መግለጫዎች ባለመዘጋጀታቸው፤

ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በሌላም በኩል ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያለሳወቁ 95 ግብር ከፋዮች ፤የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 36 ግብር ከፋዮች እና ኤክሳይስ ታክስና ተርኦቨር ታክስ ያለሳወቁ 26 ግብር ከፋዮች የተገኙ ሲሆን፤በድምሩ 157 ግብራቸውን ያላሳወቁ በመሆኑ፤ የሚፈለግባቸው ግብር ምን ያህል እንደሆነም፤ ስለመክፈላቸው/ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 በገቢ ያልመዘገቡና በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተተ የገቢ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ13 መ/ቤቶች ብር 367,716,599.48 እና በሌላ አንድ መ/ቤት በገንዘብ መጠን ያልተገለጸ የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ያልመዘገቡና ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት እና በሶስት መ/ቤቶች በብር 1,044,169.02 የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-11 እና አባሪ-13 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	6,925,512.52
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	354,156,078.28
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	6,635,008.68
በድምር	ብር	**367,716,599.48**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣

ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 <u>የተሰበሰበው ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች</u>

በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜውና በሰኔ 30/2009 የሚታየው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት /ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች ብር 165,597,719.82 ለማዕከላዊ ግምጃቤት ፈሰስ ያልተደረገ የባንክ ሂሳብና በአንድ መ/ቤት ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ብር 264,072.40 ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-5 እና አባሪ-12 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈሰስ መሆን እንዳለበት፣ ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.6 <u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

3.6.1 በገቢዎችና ጉምሩክ ባላስልጣንና ቅ/ጽ/ቤቶች

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል አራት ምዕራፍ አንድ አንቀፅ 96/1/ሀ/5 ዕቃዎች በአየር የተጓጓዙ በሚሆኑበት ጊዜ ለአየር ትራንስፖርት የተከፈለውን አንድ ሶስተኛ(1/3) ወጪ መወሰድ እንዳለበት እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 111/08 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 14(1)(መ) መሰረት ሌሎች ወጪዎች ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበ ከሆነ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተካተው ቀረጥና ታክሱ እንደሚሰላ ይደነግጋል፡፡ ***የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*** በዚህ አዋጅ እና

መመሪያ መሰረት ገቢ ዕቃዎችን እያስተናገደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለናሙና ባየናቸው ዲክላራሲዮኖች አማካኝነት ወደ ሀገር የገቡት ዕቃዎች የትራንስፖርት ወጪው በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የተካተተው ከሌሎች ወጪዎች ጋር በመደመር እና የሁለቱንም ድምር አንድ ሶስተኛውን በመውሰድ ሲሆን ነገር ግን በአዋጁ መሰረት የትራንስፖርት ወጪን ብቻ አንድ ሶስተኛ ወስዶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መደመርና እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን ለብቻው ወስዶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተደምሮ እንዲሰራ ያልተደረገ ሲሆን ይህንን የአሰራር ክፍተት አስመልክቶ በ2007 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየታችን ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድበት ተብሎ የተገለጸ ቢሆንም ቅ/ጽ/ቤቱ ለአሰራር ክፍተቱ የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ የቆየ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶቹ እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አስመጪዎቹ በየቅ/ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ነገር ግን ቀረጥና ታክሳቸው በገቢ ዕቃዎች ቡድን ሳይሰላላቸው /Assess ሳይደረግ የቆዩ ቢሆንም ዲክላራንቱ ያቀረበው የቀረጥና ታክስ መጠን በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 26,803,896.09 ትክክለኛ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ /Assess ያልተደረገ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን ከአሲኩዳ የመረጃ ዘዴ ከወስድነው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2007 አንቀጽ 71 እና 73 መሰረት እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ በጊዜያዊነት ሊገቡ እንደሚችሉና በአዋጁ በተደነገገዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን እቃዉ አገር ዉስጥ የሚቆይበት ጊዜ ከተጠናቀቀ እና ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና ወይም በቦንድ ያስያዘዉ ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መሆን እንዳለበት ወይም ዋስትናው መታደስ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከአዋጁ አንጻር በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢዉ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑንና በአዋጁ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር በማይወጡት እቃዎች ላይ በዋስትና የተያዘዉ

ገንዘብ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ መሆኑን ወይም ዋስትናው እንዲታደስ ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 235,177,463.32 ዋስትናው ያልታደረሰ ወይም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ሲሆን በተጨማሪ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በ2008 በጀት ዓመት ሰነድ ያልተገኘላቸው የዋስትና ሂሳቦች ብር 32,470,457.32 እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም ተገቢ እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ ታይቷል፡፡

- በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀፅ 10 (3 እና 5) መሰረት በቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ወደ አገር የገባ ጥሬ እቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጪ ገበያ መላክ እንዳለበት ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጥሬ እቃውን ባህሪ መሰረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ሊፈቅድ እንደሚችል ነገር ግን የመጠቀሚያ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ወይም ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ 50% እንዲከፍል እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ባስገቧቸው ጥሬ እቃዎች ልክ በአዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ ምርት ለውጪ ገበያ የሚያቀርቡ መሆኑን፣ ይህ ካልሆነ ግን ከቀረጥና ታክስ ነፃ አስገብተው ጥቅም ላይ ባላዋሉት ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በወቅቱ የሚሰበሰብ መሆኑን፣ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ***በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት*** በኩል በተለያዩ አስመጪዎች አማካኝነት ወደ ሀገር የገቡ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ጥሬ ዕቃዎች በቫውቸር ስርአት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ቢሆንም በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ በመሆኑ በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ (1)ሀ-ኘ በተገጸው መሰረት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች ከገቢ ላይ አለመቀነሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ወጪዎች በትክክል ከገቢ ላይ የሚቀናነሱ ስለመሆኑ አስፈላጊው

መረጃ ሳይኖር ከገቢ ላይ እንዲቀናነስ የተደረገ ወጪ በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 13,741,882.62 ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ወይም ተቀባይነት ያላቸው ወጪዎች ስለመሆናቸው ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እና ተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 79/1995 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ በአግባቡ መቅረቡን፣ ተቀናንሶ መሰላቱን እንዲሁም የተመላሽ ሂሳብ በትክክል ወደ ሚቀጥለው ወር መተላለፉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ተመላሽ ሂሳቦች ወደሚቀጥለው ወር ሲተላለፉ በአግባቡ የማይተላለፉ በመሆኑ በብልጫ የዞረ የተጨማሪ እሴት ታክስ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብምሩ ብር 4,070,094.00 መኖሩ ታውቋል፡፡
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ምዕራፍ 1 ክፍል 1 አንቀጽ 4 ማንኛውም በዚህ ህግ የሚሸፈን ገቢ ያገኘ ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት ግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ግብር ከፋዮቹን ለይቶ በመመዝገብ ግብር እንዲከፍሉ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ከደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት በተገኘው መረጃ መሰረት በግብር ከፋይነት ተመዝግበው የሚታወቁት ግብር ከፋዮች በግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት በኩል ተመዝግበው ከተያዙት ጋር ሲነጻጸር 12 ልዩነት የሚያሳይ በመሆኑ በልዩነት የታዩትን 12 ግብር ከፋዮች የግብር አወሳሰን አሰባሰብና ክትትል የስራ ሂደት መዝግቦ ያልያዛቸው በመሆኑ ግብር ከፋዮቹ ገቢያቸውን እያሳወቁ የሚከፍሉ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በየቅ/ጽ/ቤቱ ግብር የሚከፍሉ ድርጅቶች በተደጋጋሚ ኪሳራ በሚያሳውቁበት ጊዜ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ለናሙና ከመረጥናቸው ግብር ከፋዮች ውስጥ በጅማ ቅ/ጽ/ቤት 2 ግብር ከፋዮች ከ2004 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም እስከ ለ3 እና ለ4 ዓመታት ኪሳራ ያሳወቁ ቢሆንም ምንም ዓይነት ክትትል እና ማጣራት አለመደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የሽያጭ መመዝገቢያ የሚጠቀም ማንኛውም ንግድ ድርጅት ዓመታዊ እና ወርሃዊ ግብር በሚከፍልበት ጊዜ በሽያጭ ማጠቃለያ/ዜድ ሪፖርት ላይ ባሳየው ሽያጭ መጠን መሰረት ዓመታዊ ንግድ ትርፍም ሆነ ወርሃዊ ተጨማሪ እሴት ታክስ

የሚከፍል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲያሳውቁ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በተገኘ ወርሃዊ ማጠቃለያ ዜድ ሪፖርት (summery report) መሰረት ስለመሆኑ ከሰነዱ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ በ 2 ቅ/ ጽቤቶች በድምሩ 12 ግብር ከፋዮች በማስረጃው መሰረት አሳውቀው ስለመክፈላቸው ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.6.2 ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

➢ **በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ**

በአገር ዉስጥ ገንዘብ የሚሰበሰበው ገቢ በገቢ ደረሰኝ መሂ/1 ወይም ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ በሚታተም ደረሰኝ ብቻ መሆን እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ከሐምሌ 1/2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በገቢ ሂሳብ ሂሳብ መደቦች 1443 እና 1489 ብር 4,623,489.88 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ የሰበሰበ መሆኑ፣

➢ **በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጥቁር አንበሣ ሆስፒታል**

መድሃኒት በመደበኛ በጀት የሚገዛ እና ከመድሃኒቱ ሽያጭ በበጀት ዓመቱ ብር 18,376,464.77 እንደተሰበሰበ በሂሳብ ሪፖርት ላይ የተመለከተ ሲሆን መድሃኒቱ በመደበኛ በጀት የተገዛ በመሆኑ በመልሶ መሸጥ የተገኘው ገቢ ሂሳብ ለበጀት መተኪያ ተደርጎ መመለስ ሲገባው አላግባብ ወደ ሆስፒታሉ የውስጥ ገቢ ሂሳብ አካውንት ገቢ የተደረገ መሆኑ፤

➢ የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ከእንስሳትን አባላዘር፣ የፈሳሽ ናይትሮጅን በሽያጭ የሚያቀርብ ሲሆን የምርት መሸጫ ዋጋ ተመን ሐምሌ 21 ቀን 1985 ዓ.ም ከምርት ማዳቀል አገልግሎት ዋና ክፍል ለአባላዘርና ፈሰሽ ናይትሮጅን ማምረቻና ማከፋፈያ ዋና ክፍል በተጻፈው ማስታወሻ መሰረት ተመኑ የማምረቻ ዋጋ ጥናት ተደርጎ የመሸጫ ተመን እስኪወሰን ድረስ ሥራ ላይ የሚውል መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ማዕከሉ ለሚያመርታቸው ምርቶች የማምረቻ ዋጋ ጥናት በማድረግ የሽያጭ ዋጋ ተመን ያላዘጋጀና በሚመለከተው አካል ያላጸደቀ መሆኑ፤

በኦዲቱ ተረጋግጧል።

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፣ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ላይ የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ አንዳንዶቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3.7 የገቢ ሂሳብ ዕቅድ አፈጻጸም

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በዕቅድ የያዙትን ገቢዎች የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ሀ/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት፡-ብር 25,871,660,000.00 (13%)

ለ/ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 144,854,097.14 (29%)

ሐ/ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 23,903,871.70 (18%)

መ/ የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ ብር 2,718,181.42 (21%)

ከዕቅዱ በታች መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ለመ/ቤቶቹ የገቢ ዕቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

4 የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ19 መ/ቤቶች ብር 110,033,859.03 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	382,811.47
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	45,625,308.47

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	275,219.17
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	248,497.22
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	63,502,022.70
በድምር	**ብር**	**110,033,859.03**

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው፣ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,575,478.53 ፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 22,123,507.92 ፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 27,044,750.71 እና የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር ብር 11,274,464.87 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ68 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 506,026,502.67 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	47,387,440.09
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	30,809.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	259,472.31
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	46,362,033.19
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	382,858,985.30
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	29,127,762.78
በድምር	ብር	**506,026,502.67**

ሆኖ ተገኝቷል ።

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች፤ ትምህርት ሚኒስቴር ብር157,383,533.13፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 60,183,740.86፣ አክሱም ዩኒቨርስቲ ብር 52,804,956.36፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 46,209,145.83፤ ውጭ ጉዳዩ ሚኒስቴር ብር27,350,000.00 እና ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 20,426,334.68 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ፤ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጐላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣ በ98 መ/ቤቶችና በ14 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 189,895,337.99 እና በአሜሪካ ዶላር በድምሩ $ 49,990.00 ከደንብና መመሪያ ውጭ ያለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	13,842,066.47
በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	19,581,842.40
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	53,305,483.52
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	77,263,498.42

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	22,356,415.38
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	3,546,031.80
በድምር	**ብር**	**189,895,337.99**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 40,253,397.51 እና በአሜሪካ ዶላር $12,400.00 ፤የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ብር 19,175,755.52፣ ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 18,799,243.82፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,268,727.60፣ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,491,954.72 እና የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 9,624,735.53 እና የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ብር 8,186,199.07 ሲሆኑ፤ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም፣ ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ ለውጭ ጉዞ ከወሰዱት የውሎ አበል ሂሳብ በመመሪያው መሰረት መመለስ ሲገባቸው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም፣ መ/ቤቱን ለለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት በሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ በ6 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብር 10,518,758.51 የስራው ባህሪ በቋሚነት ወይም ቀጠይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ እና በ15 መ/ቤቶች ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 24,184,740.66 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-19/1 እና አባሪ- 19/2 ተመልክቷል/

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ገንዘብ ከሚመለከታቸው ወደ መንግስት ካዝናተመላሽ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

4.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 9,724,581.41 እና በ27 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 10,362,826.73 በጠቅላላው ብር 20,087,408.14 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፤ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.5 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች</u>

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ97 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች 487,958,696.75 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	30,317,650.23
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	6,110,576.53
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	16,680,513.56
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	191,198,092.46

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	ብር	198,603,552.67
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	45,048,311.30
በድምር	**ብር**	**487,958,696.75**

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡-ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር 193,896,805.57፣ መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 92,502,156.98፣ ግልጽ ጨረታ መውጣት ሲገበው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ ብር 30,272,104.00፣ የዋጋ ወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 21,440,931.65 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 149,329,074.05 ናቸው፡፡

ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር 61,168,638.68፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 61,085,880.38፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ብር 43,283,741.84፣ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 39,164,123.08፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,059,148.78፣ መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,687,300.80፣ የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ ብር 21,174,423.27፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 17,696,548.64 እና ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,964,399.77 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ በ5 መ/ቤቶች የብር 13,026,244.39 መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ-21/1 ተመልክቷል፡፡/

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶችና በአንድ ቅ/ጽ/ቤት በብር 83,593,320.38 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ2 መ/ቤቶች ብር 1,102,109,933.36 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-22 እና አባሪ- 22/1 ተመልክቷል/

ገቢ ያልሆነው ንብረት ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	37,506.00
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	72,552,517.99
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	9,396,307.55
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	<u>1,606,988.84</u>
በድምር	ብር	<u>**83,593,320.38**</u>

ከዚህም ውስጥ የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማትኢንስቲትዩት ብር 71,128,769.99፣ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,383,772.80፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,662,342.75፣ ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ ብር 1,396,148.00 እና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ብር 1,364,859.58 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ወይም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ ማስረጃ ካላቀረቡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸውም፣ የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ብር 1,090,989,091.41 እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ብር 11,120,841.95 ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው

በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ10 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 41,966,889.32 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 28 ተመልክቷል/

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8 የወጪ የሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ82 መ/ቤቶች ብር 986,372,435.29 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች		16,662,458.29
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	ብር	282,669,321.13
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	92,563,479.26
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	569,766,564.97
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	24,710,611.64
በድምር	ብር	**986,372,435.29**

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 168,489,008.43፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 74,626,574.30፣ ወላይታ ዩኒቨርስቲ ብር 34,470,720.73 እና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,491,835.02፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 21,895,096.81 እና የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 20,426,911.53 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ38 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 85,400,239.14 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2009 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	22,233,142.37
የፋይናንስን ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	3,859,112.27
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	56,698,992.36
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	<u>2,608,992.14</u>
በድምር	ብር	<u>**85,400,239.14**</u>

ሲሆን፣ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 <u>በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ</u>

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ/ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶችና ሁለት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ

ብር 24,767,649.35 ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ወይም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/ ከዚሁ የሂሳብ ሪፖርት ጋር በተያያዘ በ2 መ/ቤቶች ብር 844,611.60 በድጋሚ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ እና ብር 1,444,970.18 በብልጫ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 <u>ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች፤</u>

ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የወጡ የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተከናወኑ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ሥምምነት ያልቀረበለትና በአዋጁ መሠረት በዋና ውል ላይ 25% በማስላት ብቻ ተጨማሪ ውል መግባት ሲገባው፣ ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ውል የተገባ በ5 መ/ቤቶች ብር 16,319,714.09 ፤ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ያልተፈረመ በ1 መ/ቤት ብር 4,025,000.00 በድምሩ በብር 20,344,714.09 ተከፍሎ መገኘቱ፤
- ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ፤በ2 መ/ቤቶች ብር 3,576,138.91፤
- በ5 መ/ቤቶች ብር 267,085,966.34 ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያ ሠርትፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ መገኘቱ፤

- በአማካሪ ባልጸደቀ የምስክር ወረቀት የተፈጸመ የግንባታ ሂሳብ ብር 6,325,575.80
- በ3 መ/ቤቶች ብር 23,130,699.31 በተከፋይነት ያልተያዘ ፤ በጀት ሳይፈቀደለት የመያዣ ሂሳብ መከፈሉ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-20/1 እስከ አባሪ-20/5 ተመልክቷል/

በመሰረቱ ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለበቸው፡፡ የግንባታ ክፍያ በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት መቀነስ ነበረበት፡፡ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ አገልግሎት ሳይገኝ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

በመሆኑም የማማከሪ ስራዎችም ገለልተኛና የሙያ ብቃት በተሰጣቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን፤ተጨማሪ ውል ሲያስፈልግም ሕጉ በሚፈቅደው ልክ እንዲሆንና በአጠቃላይ የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

4.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ ተመዘገቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ12 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 18,051,060.71 እና በቦርድ ያልጸደቀ ብር 39,648,133.82 ፤በ2 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 8,279,360.54 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ እና በ7 መ/ቤቶችና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ሳይፈቀድ የተፈፀሙ ክፍያዎች ብር211,225,466.81 መገኘቱ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-26 እና 26/1 እና አባሪ-33/ለ ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል።

4.13 ሌሎች ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዘ የሚታዩ ችግሮች

4.13.1 የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ

የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ከተለያዩ የግንባታ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን የተጠናቀቁት የግንባታ ሥራዎች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ኮሌጁ ከአሊ ሞሚን ጠቅላላ የውሀ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ጋር ለውሀ መስመር ዝርጋታ ግንባታ በብር 7,379,375.32 ውል የፈጸመና ሥራውም ተጠናቆ ከተቋራጩ ጋር ጊዜያዊ ርክክብ የፈጸመ ቢሆንም፡-
- በውሀ መስመሩ ላይ ተዘርግተው የነበሩት በርካታ የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች ከመሀል የተነሱና በገዋኔ ከተማ በሚገኘው ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ግቢ ውስጥ ሜዳ ላይ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን፣ በውሀ መስመሩ ላይ የቀሩት የውሀ ማስተላለፊያ ቧንቧዎችም ቢሆኑ አልፎ አልፎ የወላለቁ መሆኑ፤
- ኮሌጁ የውሃ መስመሩን ዝርጋት ርክክቡ ከፈጸመበት ከመስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 60,000.00 የውሀ ማመላለሻ ቦቴ መኪና ተከራይቶ በድምሩ ብር 540,000.00 ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ ከመሆኑም በላይ ወጪው አሁንም የቀጠለ መሆኑ፤
- ኮሌጁ ከሁሴን ኢብራሂም ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር በብር 9,221,913.25 የመኖሪያ ቤት ግንባታ ውል የፈጸመና ሥራው ተጠናቆ ርክክብ የተከናወነ ቢሆንም ለግንባታው የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ማስወገጃ አብሮ ስላልተገነባለት ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመታት በላይ ተቆልፎ የሚገኝ መሆኑ፤
- ኮሌጁ ኤፍ ኤ ዋይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር በብር 5,468,710.00 የህንጻ ጥገና ግንባታ ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ጥገናው ከመጋቢት 2006 ዓ.ም ጀምሮ በስምንት ወራት ውስጥ ማለቅ እንዳለበት ቢጠቀስም ግንባታው ከመዘግየቱም በተጨማሪ የጥገናው ሥራ ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ በተቋራጩ ላይ ምንም ዓይነት ህጋዊ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

- በትምህርት ሚኒስቴር የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታና መሰረተ ልማት እስከ ሰኔ 30/2009 ለኦዲት በቀን 12/12/2009 በቀረበው ዝርዝር መግለጫ መሰረት የአዳቡሉቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ

ለማከናወን ከ11 ህንጻና የግንባታ ስራ ተቋራጮች ጋር በቀን 20/08/2008 እና ከአንድ የመሰረተ ልማት ተቋራጭ ጋር በቀን 05/07/2009 ውል የተያዘ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው ግንባታ የሚውል የቦታ ርክክብ ሳይደረግና ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባበት አካባቢ ላሉ ተነሺዎች የካሳ ግምት ሳይቀርብና ካሳ ሳይከፈላቸው አስቀድሞ ውል ከመያዙ በተጨማሪ የህንጻ የስራ ተቋራጮች የቦታ ርክክብ ሳያደርጉና ወደ ስራ ሳይገቡ ቅድመ ክፍያ ለ9 ኮንትራክተሮች የዋናውን ውል 20% በ2008 በጀት ዓመት በድምር ብር 40,594,366.64 ከአንድ ዓመት በላይ እና ለአንድ ኮንትራክተር በ2009 15% ብር 31,442,798.11 ከሶስት ወር በላይ ምንም ዓይነት ስራ ሳይሰራ የተከፈለ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 በድምር ብር 72,037,164.75 የመንግስት ገንዘብ በህንጻ ግንባታና መሰረተ ልማት ስራ ተቋራጭ ድርጅቶች እየተጠቀሙበት መሆኑ፤ ኒሐም ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የብር 14,699,675.00 ፒፒስ ሲሚንቶ ለማቅረብ ውል የተገባ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው የውሉን ጠቅላላ ዋጋ ×30% (14,699,675.00×30%) = ብር 4,409,902.50 ቅድሚያ ክፍያ መስጠት ሲገባ ብር 14,699,675.00 ሙሉውን ጠቅላላ የውሉን ዋጋ ተሰጥቶ የተገኘ መሆኑ፤

- በትምህርት ሚኒስቴር የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታና መሰረተ ልማት እስከ ሰኔ 30/2009 ለኦዲት በቀን 12/12/2009 በቀረበው ዝርዝር መግለጫ መሰረት የኦዳቡሉቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ለማከናወን ከ11 ህንጻና የግንባታ ስራ ተቋራጮች ጋር በቀን 20/08/2008 እና ከአንድ የመሰረተ ልማት ተቋራጭ ጋር በቀን 05/07/2009 ውል የተያዘ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው ግንባታ የሚውል የቦታ ርክክብ ሳይደረግና ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባበት አካባቢ ላሉ ተነሺዎች የካሳ ግምት ሳይቀርብና ካሳ ሳይከፈላቸው አስቀድሞ ውል ከመያዙ በተጨማሪ የህንጻ የስራ ተቋራጮች የቦታ ርክክብ ሳያደርጉና ወደ ስራ ሳይገቡ ቅድመ ክፍያ ለ9 ኮንትራክተሮች የዋናውን ውል 20% በ2008 በጀት ዓመት በድምር ብር 40,594,366.64 ከአንድ ዓመት በላይ እና ለአንድ ኮንትራክተር በ2009 15% ብር 31,442,798.11 ከሶስት ወር በላይ ምንም ዓይነት ስራ ሳይሰራ የተከፈለ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 በድምር ብር 72,037,164.75 የመንግስት ገንዘብ በህንጻ ግንባታና መሰረተ ልማት ስራ ተቋራጭ ድርጅቶች እየተጠቀሙበት መሆኑበቅድሚያ የተከፈለው ጥሬ ገንዘብ፤ ተመላሽ የተደረገው እና ያልተመለሰ ቅድሚያ ክፍያ፤ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በዓይነት የተሰጡ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች /Material

Advance/ ተመላሽ የተደረገው ገንዘብና እና ያልተመለሰ፣ቀሪ ዕዳ፣እያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ለሚያከናውናቸው ግንባታዎች በመያዣነት ገቢ ያደረገው የመልካም ስራ ዋስትና ገንዘብ እንዲሁም ግንባታ ክፍሉ ከGIZ-IS የተረከባቸው ሰነዶቹ ለሂሳብ ክፍል ተላልፈው በእያንዳንዱ የህንጻ ስራ ተቋራጭ ስም ሂሳቡ እንዲመዘገብ ስለመደረጉ፤ እንዲሁም ስራው የደረሰበት ደረጃ፣ ያቋረጡ ካሉ በእነሱ ላይ የተወሰደ እርምጃ ካለ፤ ከስራ ተቋራጮቹ የሚፈለገውን የተሰብሳቢ እና የመያዣ ሂሳብ የሚያሳይ ተቀጽላ ሌጀር ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብና እየተደረገ ስላለውም ክትትል ለማወቅ የሚያስችል በቂ ምላሽ የሚሰጥ አካል ባለመገኘቱ የሂሳቡን ሁኔታ ማጣራት አለመቻሉ፤

በወላይታ ዩኒቨርሲቲ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 11 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

- በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 4 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ በውሉ በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሠረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 8 የህንጻ ተቋራጮች መኖራቸው ታውቋል፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱት አሰራሮች እንዲስተካከሉ የተጀመሩት ግንባታዎች በጊዜያቸው እንዲጠናቀቁና በውል በተቀመጠው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው የደረሰው የጉዳት ካሳ እንዲጠየቅበት አሳስበናል፡፡

5 <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ት/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ74 መ/ቤቶችና በ12 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 789,616,771.63 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	91,229,531.87
የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	33,769,155.94
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	70,006,646.80
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	561,748,905.23
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	340,571.66
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	32,521,960.13
ድምር	ብር	**789,616,771.63**

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 46,920,159.94 ፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 113,557,523.40 ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 15,796,869.41 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 32,993,267.39 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 580,348,951.46 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ያልተለየ ሂሳብ ነው፡፡ በተጨማሪም በ6 መ/ቤቶችና በ6 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 177,292,636.49 በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ለማን እንደሚከፈል፤ መቼ እንደተከሰተ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 444,126,372.81፣ በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 53,982,806.33፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ብር34,323,631.25፣ በገ/ጉ ባ/ሞጆ ቅ/ጽ ቤት ብር 22,431,939.13፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,401,956.01 እና የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ብር 18,402,285.79 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የተከፋዩን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለባቸው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 95,816,056.39 እና በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 32,302,818.25 እና ሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ብር 22,649,840.58 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑ እየተጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ሌሎች ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ያልተመዘገበ የግንባታ የቅድመ ክፍያ ተመላሽ በሶስት መ/ቤቶች ብር 5,318,289.92 እና የመያዣ ተከፋይ ሂሳብ ያልተመዘገበ በአንድ መ/ቤት ብር 392,974.88 መገኘቱ፣
- ከግዥ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ ያልተመዘገበ ቅዲሚያ ክፍያ ብር 2,835,538.85 እና መያዣ ሂሳብ ብር 23,136,063.64 መገኘቱ፤
- በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ በ2 መ/ቤቶች ብር 505,688.91 መገኘቱ፣ (አባሪ-27/1)
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ8 መ/ቤቶችን ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 42,013,985.99 መኖሩ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ3 መ/ቤቶች ብር 82,444,473.66 ተገኝቷል፡፡
- መደበኛ የመነሻ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ (ዴቢት ሚዛን) የተከፋይ ሂሳብ በ3 መ/ቤትና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,301,372.12 መኖሩ፤

/ዝርዝሩ በአባሪ-32 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6 <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ41 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ ከመደበኛ በጀትና የውስጥ ገቢ ብር 765,807,523.17 እና ከካፒታል በጀት ብር 132,675,821.28 በድምሩ ብር 898,483,344.45 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	3,120,487.35
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	339,537,427.65
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	202,875,267.40
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		6,729,691.39
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	346,220,470.66
ጠ/ድምር	**ብር**	**898,483,344.45**

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 330,099,679.28፣ የፌ/ቴክኒክና ሙያ ት/ትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 184,334,927.00፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብር 75,535,092.74፣ የወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 48,993,357.87፣ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 43,493,792.01፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ብር 36,092,729.98 እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 29,382,001.57 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ7 መ/ቤቶች እና ሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 211,225,466.81 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ክፍያዎች እና በ2 መ/ቤቶች ብር2,363,085.86 ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበን ሂሳብ በጀት ሳያስፈቅዱ ወጪ ያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 ያልተሰራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በ150 መ/ቤቶች በጀት ብር 2,718,103,111.41 እና ካፒታል ብር 4,060,527,838.33 በድምሩ ብር 6,778,630,949.74 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	816,712,645.58
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	291,074,233.48
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	659,899,212.60
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	1,328,728,994.66
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	2,124,338,098.30
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,557,877,765.12
ጠ/ድምር	ብር	**6,778,630,949.74**

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- ትምህርት ሚኒስቴር ብር 552,751,378.98፣ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 442,587,357.18፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 444,892,606.80፣ የአ.አ.ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 373,137,325.30፣ አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 347,481,497.23፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 291,074,233.48፣ ቤተ መንግስት አስተዳደር ብር 254,352,530.36 እና አምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 248,701,428.64 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7 የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-34/ሀ እስከ አ ተመልክቷል፡፡/

የግኝቶች መግለጫ	መ/ቤቶች	ቅ/ጽ/ቤቶች
ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	30	8
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገበ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	18	2
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	19	
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	19	
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	9	7
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	18	4
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	45	13
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	17	
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	1	
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው:- 59 የተለያዩ ተሽከሪካሪዎችና 63 ሞተር ብስክሌቶች ሲሆን፤ በ4ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት ያልተገለጸ		7
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ (በርካታ ንብረቶች በገንዘብ ያልተገለጹ እና ሌሎች በዋጋ የተቀመጡ ብር131,538.68 ይገኙበታል)	8	
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤	1	
የንብረት ጉድለት የተገኘባቸው ፤ ዋጋቸው ብር 38,073.53 እና 1 ታብሌት ኮምፒዩተር፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሞዴል 22 ወጪ ሆኖ በአካል በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ያልተገኘ የመሮጫ ትራክ ዋጋው ብር 1,649,999.99	4	
በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	1 መ/ቤት	
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	7	2

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በኦዲታችን ወቅት ታይቷል። እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸውና ሊወገዱ የሚገባ የተለያዩ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች በበርካታ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>ተሽከርካሪ</u>

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

የግኝቶች መግለጫ	ብዛት		
	የመ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች	ሞተር ብስክሌቶች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	25	120	38
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	31	325	37
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	9	21	25
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	16	119	2
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	2	8	
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	1	2	

የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ	4	39	2
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	1		
በኃላፊ ተወስዶ ተመላሽ ያልተደረገ ተሽከርካሪ(1 ኒሳን ፓትሮል መኪና)	1	1	
ሊብሬው ብቻ ኖሮ ተሽከርካሪው በአካል የሌለ	1	1	

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 /ሀ እስከ ቀ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልገሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፣ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣላቸውና ሰሌዳ የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8 <u>ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ</u>

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

በ67 መ/ቤቶች እና 11 ቅ/ጽ/ቤቶች/ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱና አሁንም ትኩረት እንዲሰጥበቸው ያህል /ዝርዝሩ በአባሪ-36/1 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየዘርፉና በየመ/ቤቶቹ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ በመጀመሪያ በቀረበው እያንዳንዱ ሪፖርት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

9 <u>ልዩ ልዩ ፤</u>

የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፡-

ዩኒቨርስቲው እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በትምህርት ላይ ያሉ 163 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ጊዜ የማይታወቅ መሆኑን፣ 166 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ተቋም (የት እንደሚማሩ) የማይተወቅ መሆኑን፣ 174

መምህራን ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደሥራ የሚመለሱበት ጊዜ የማይታወቅ (በውሉ ያልተቀመጠ) መሆኑን፣

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲው ለትምህርት የተላኩ 14 መምህራን በቀነ ገደቡ ያልተመለሱ ሲሆን ዩኒቨርሲቲውም በውሉ መሰረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

ፋይናስና ኮሚዩኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት

በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል

1. እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ዋርዊክ ዩኒቨርስቲ 37 የሁለተኛ ዲግሪ 13 የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች እንዲሁም አሜሪካን አገር ከሚገኘው አላባማ ዩኒቨርስቲ 19 ተማሪዎች በሁለተኛ ዲግሩ 4 ተማሪዎች በሶስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ቢገለጽም ትምህርታቸውን አጠናቀው የተመረቁት ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲማሩ ወደላካቸው ተቋም ወይም መ/ቤት በመመለስ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ለመስጠታቸው ማረጋገጫ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
2. እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ዋርዊክ ዩኒቨርስቲ አራት የሁለተኛ ዲግሪ አራት የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያቋረጡ እንዳሉ ተገልጿል፡፡ይሁን እንጂ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ተከፍሎላቸው ነገር ግን ትምህርታቸውን ባላጠናቀቁ ተማሪዎች ላይ የተወሰደ እርምጃ ለመኖሩ ማስረጃ ተጠይቆ ለኦዲት ሊቀርብ አለመቻሉ፣
3. ትምህርታቸውን አጠናቀው ከተመረቁ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን እንዲማሩ ወደላካቸው ተቋም ወይም መ/ቤት ያልተመለሱ እና የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ሳይሰጡ በገዛ ፍቃዳቸው የተሰናበቱ ሰራተኞች የስም ዝርዝራቸው እና ለትምህርት አገልግሎት የተከፈለላቸው ገንዘብና ሌሎች ወጪዎች የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ እንዲሁም በገቡት የግዴታ ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው የተወሰደ እርምጃ ለመኖሩ ማረጋገጫ ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
4. እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ዋርዊክ ዩኒቨርስቲ አንድ የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ እንዲሁም አሜሪካን አገር ከሚገኘው አላባማ ዩኒቨርስቲ ሁለት የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች አሁንም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ መሆኑ ተገልጿል፡፡ይሁን እንጂ እነዚህ ተማሪዎች ትምህርቱን ማጠናቀቅ በሚገባቸው ጊዜ ውስጥ ባለማጠናቀቃቸው ማዕከሉ ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ አመራር ሲሆን፤ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 984/2008 ለመቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የባለስልጣን መ/ቤቱ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግለት በደ.ቁ 2-4-6/78/10 ህዳር 05 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለመ/ቤታችን ያቀረበውን የሂሳብ መግለጫ የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን እና የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ ኦዲቱ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ባለስልጣኑና 18 ቅ/ጽ/ቤቶቹ ያቀረቧቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የባለስልጣን መ/ቤቱ የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ተከናውኖ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 96 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/4 በተደነገገው መሰረት እቃዎች እስከ ኢትዮጲያ የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የትራንስፖርት፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያ፣ የመንከባከቢያና የኢንሹራንስ ወጪ በግብይት ዋጋ መካተት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭ መረጃ እና ማስረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ በመመሪያ ቁጥር 111/2008 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4(ከ ሀ እስከ ሐ) በተደነገገው መሰረት እቃዎችን እስከ ኢትዮጲያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት 5 በመቶ፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያና የመንከባከቢያ ወጪ 5 በመቶ፣ የኢንሹራንስ ወጪ 2 በመቶ ዲክሌር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ፎብ ዋጋ ላይ በመጨመር በቀረጥና ታክስ ዋጋ ላይ እንደሚካተት በተጨማሪም በደብዳቤ ቁጥር 3.1.0/492/08 በቀን 17 ህዳር 2008 ከጅቡቲ ወደብ እስከ መዳረሻ ደረቅ ወደብ ድረስ ለማድረስ በተላለፈው የወጪ ተመን ሰርኩላር መሰረት ወጪዎቹ በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መካተት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ቅ/ጽ/ቤቶቹ በአዋጁና መመሪያው መሰረት ባለመሰራቱ በ 10 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር <u>9,737,113.73</u> ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ መገኘቱ፣
2. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከጎረቤት ሀገር ተገዝተው ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች በዲክላራሲዮን አቅራቢው (በኢንቮይሱ) የቀረበው የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ ከስሪት

ሀገር ሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ አንሶ ከተገኘ ዕቃው የተሰራበት ሀገር ሲገዛ ባለው አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ መሰረት እንዲስተናገድ የሚደረግ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ ከጎረቤት ሀገር ግዢ ተፈጽሞ ወደ ሀገር ለገቡት ዕቃ የተያዘላቸው የግብይት ዋጋ የስሪት ሀገሩ ኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋ በመሆኑ የስሪት ሀገር ሲ.አይ.ኤፍ ላይ ለመድረስ የባህር መጓጓዣ ኢንሹራንስ ወጪ(marine insurance cost) ከስሪት ሀገር ወደብ እስከ ጅቡቲ ወደብ ድረስ ላለው ሽፋን የተከፈለው የኢንሹራንስ ሰነድ ያልቀረበ በመሆኑ በንዑስ አንቀጽ 4/ሐ መሰረት በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የኤፍ.ኦ.ቢ. ዋጋን 2 በመቶ ታክሎበት ያልተሰራ ባለመሰራቱ በአንድ ቅ/ጽ/ቤት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፡- ብር 2,586,237.87 መገኘቱ፣

3. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 102 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ወደ ሀገር ከገቡ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) እና በትክክለኛው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ኮድ (CPC) ያልተመደቡ በመኖራቸው ምክንያት በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,111,978.51 መገኘቱ፣
4. የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2/መ መሰረት በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የእያንዳንዱ የዕቃ ዋጋ እና በጉምሩክ የዋጋ መረጃ ዳታ ቤዝ (ECVS) ውስጥ የሚገኙ የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃዎች አማካይ ዋጋ ሲነጻጸር ያለው ልዩነት በማነስ ከ10% በላይ ከሆነ የቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ ተቀባይነት እንደማይኖረው ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በአስመጪዎች በቀረበው የኢንቮይስ ዋጋ እና በጉምሩክ ዳታ ቤዝ(ECVS) ውስጥ ያለው የአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ ዋጋ ልዩነታቸው ከ10% በላይ በመሆኑና በጉምሩክ ዳታ ቤዝ ውስጥ ባለው ዋጋ መሰረት እንዲስተናገዱ ባለመደረጉ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 15,236,030.55 መኖሩ ፣
5. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 ምዕራፍ 5 አንቀጽ 25 ን.አ 2 ሰ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ዲክላራሲዮን በመሙላት የዕቃውን ዋጋ ለመተመን አስፈላጊ የሆኑ መግለጫና መረጃዎችን የተሽከርካሪ ስም፣ ዓይነት፣ ሞዴል ቁጥር፣ ምርት ዘመን፣ ሞተር ቁጥር፣

ሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር/የሲሊንደር ጉልበት (cylinder capacity/cc) የመሳሰሉትን በመሙላት ለባለስልጣን መ/ቤቱ ማቅረብ እንዳለበት ቢደነገግም ለቀረጥና ታክስ ማስከፈያነት ከሚያገለግሉ መረጃዎች ዋና የሆነው የሞተር ጉልበት መጠን ወይም የመጫን አቅሙ (carrying capacity or cc) በዲክላራሲዮኑም ሆነ በዕቃ ዝርዝር መግለጫ(VDD) ላይ ያልተገለጸ በመሆኑ ***በአንድ ቅ/ጽ/ቤት*** የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 943,433.55 ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

6. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 በአንቀፅ 27(3)(ለ) መሰረት ***በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል ወደ አገር ለገቡ እቃዎች*** እቃው ከተላከበት አገር ወደብ እስኪደርስ ድረስ የወጣው ትክክለኛ የመጓጓዣ ወጪ/የትራንስፖርት (freight) ክፍያዎች ማስረጃ ከዲክላራሲዮኑ ጋር የቀረቡ ቢሆንም በክፍያ ደረሰኙ ላይ የተመለከተው (የተከፈለው) የትራንስፖርት ወጪ በእጅ ተሰርዞ ሌላ ያነሰ ዋጋ በመጻፍ እንደ ትራንስፖርት ወጪ በመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 432,485.07 መገኘቱ፣

7. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል አራት ምዕራፍ አንድ አንቀፅ 96/1/ሀ/5 ዕቃዎች በአየር የተጓጓዙ በሚሆኑበት ጊዜ ለአየር ትራንስፖርት የተከፈለውን አንድ ሶስተኛ(1/3) ወጪ መወሰድ እንዳለበት እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 111/08 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 14(1)(መ) መሰረት ሌሎች ወጪዎች ስለመከፈላቸው ግልጽ መረጃ የቀረበ ከሆነ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተካተው ቀረጥና ታክሱ መስት ሲኖርበት ***በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*** ወደ ሀገር ለገቡት ዕቃዎች ግን የትራንስፖርት ወጪው በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የተካተተው ከሌሎች ወጪዎች ጋር በመደመር እና የሁለቱንም ድምር አንድ ሶስተኛውን በመውሰድ ሲሆን ነገር ግን በአዋጁ መሰረት የትራንስፖርት ወጪን ብቻ አንድ ሶስተኛ ወስዶ በቀርጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ መደመርና እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን ለብቻው ወስዶ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ተደምሮ እንዲሰራ ያልተደረገ ሲሆን ይህንን የአሰራር ክፍተት አስመልክቶ በ2007 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየታችን ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድበት ቢገለጽም ቅ/ጽ/ቤቱ ግን ለአሰራር ከፍተቱ የእርምት እርምጃ ሳይወሰድ አሰራሩን የቀጠለ መሆኑ ፣

8. በመመሪያ ቁጥር 111/2008 ምዕራፍ 3 አንቀፅ 19 (1) ለአገለገሉ ተሽከርካሪዎች የእርጅና ቅናሽ የሚደረገዉ ተሽከርካሪዉ የምርት ዘመንና አገልግሎት የሰጠ መሆኑን

ከሚያስረዱ መረጃዎች በመነሳት እስከ 3ኛ አመት መጨረሻ ድረስ ከፎብ ዋጋ ላይ በየአመቱ የሚደረግ 10% ተቀናሽ ሲሆን ከ30% እንደማይበልጥ ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ተሽከርከርካሪዎች እና ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ ምንም አይነት አገልግሎት ወይም ጥቅም ላይ ሳይውሉ ከአንድ አመት በላይ የቆዩ ቢሆኑም የእርጅና ቅናሽ ሳይደረግባቸው አዲስ በነበሩበት ጊዜ ባለው ዋጋ የቀረጥና ታክስ ማስከፊያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል ብሎ ይደነግጋል፡፡ ***በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት*** ግን ወደ ሀገር የገቡ ተሽከርካሪዎች ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ ያገለገሉ/used በማለት እንዲስተናገዱ በመደረጉ እና ያለአግባብ የእርጅና ቅናሽ ከዋጋው ላይ እንዲቀነስ በመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,792,857.10 መኖሩ ፣

9. ለኦዲት ሥራ እንዲቀርቡ ከተጠየቁ ዲክላራሲዮኖች ውስጥ ***በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት*** 2 ዲክላራሲዮኖች ያልቀረቡ በመሆኑ የተሰበሰበው ብር 245,631.97 ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

10. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 15(1) ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 51(1) ላይ እንደተደነገገው ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነስርአት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት እንዳለበት ያዛል፡፡ ***በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት*** በአሲኩዳ ምዝገባ መሰረት በመንገደኞች በኩል የ2016 /2017 ሰነዶች የቆይታ ግዜያቸው ከሀምሌ 1/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 (ከአንድ ወር እስከ አስራ ሁለት ወራት) ያስቆጠሩ በ70 ዲክላራሲዮኖች የተገለጹ የደንበኛ ንብረቶች ያልወጡ/ያልተዘጉ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም ንብረቶቹም በውርስ መጋዘንም ሆነ በጉምሩክ መጋዘን ባለመገኘታቸውና እና በወቅቱ መሰብሰብ የነበረበት ቀረጥና ታክስ (Assed but not paid) ብር 392,972.73 አለመሰብሰቡ፣

11. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ

ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 51(1) ላይ እንደተደነገገው ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ስነስርአት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት እንዳለበት ያዛል፡፡ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ወደ ሀገር ለገቡ ዕቃዎች ብር 27,121,029.36 ቀረጥና ታክሳቸው የተሰላ(assessed) ቢሆንም የቀረጥና ታክስ ክፍያ ሳይፈጸምበት ወይም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት መገኘቱ፣

12. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2014 አንቀጽ 15(1) እና በመመሪያ ቁጥር 118/2008 ክፍል ስምንት አንቀጽ 20/1/ ላይ እንደተገለጸው ዲክላራስዮን አቅራቢው የዕቃ ዲክላራስዮን ከተመዘገበበት ወይም የክፍያ ማስታወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት የስራ ቀናት ድረስ ቀጣይ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ካልጀመረ ዲክላራስዮኑ እንዲሰረዝ ሊደረግ ይችላል በማለት ደንግጓል፡፡ በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች የተመዘገቡና ዲክላራንቱ ባቀረበው መሰረት ብር 26,803,896.09 የቀረጥና ታክስ መጠን ትክክለኛ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ /Assess ያልተደረገ እና ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን፣

13. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 1 ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች ታክስ የሚጣልበት በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የሚከፍለውን ቀረጥና ታክስ ጨምሮ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት በጉምሩክ የሚወሰነው የዕቃዎች ዋጋ ስለመሆኑ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 133/1993 አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የዕቃው ዋጋ የመድን አረቦን እንዲሁም የማስጫኛ ወጪ (ሲ.አይ.ኤፍ) እና ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ የተ.እ.ታክስ እና ኤክሳይዝ ታክስ ድምር መሰረት መሆን እንዳለበት ቢገለጽም በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች ወደ ሀገር ውስጥ የገቡት እቃዎች በትክክለኛ የታክስ ስሌት መነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰላቱ ምክንያት ብር 797,161.08 ያልተሰበሰበ ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሱር ታክስ መገኘቱ ፣

14. ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የ2008 በጀት ዓመት የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ከ2008 በጀት ዓመት የ 12 ወራት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ ጋር ሲነፃፀር

በትርፍና ኪሳራ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ያነሰ በመሆኑና ለልዩነቱም አሳማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምክንያት በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች ውሳኔ ያልወጣለት የንግድ ትርፍ ግብር ብር 36,838,851.13_ና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 65,303,657.63 መኖሩ፣

15. አጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ አያያዝ መርህ (GAAP) መሰረት በ2007 የግብር ዘመን የሂሳብ መግለጫ ላይ በአመቱ መጨረሻ ሳይሸጥ የቀረ ዕቃ(ending inventory) በ2008 የግብር ዘመን ላይ እንደ መነሻ ሚዛን(begging inventory) አድርጎ በተመሳሳይ መጠን ማዞር ሲገባው በብልጫ በመዞሩ ምክንያት በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች ሳይሰበሰብ የቀረ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 304,546.8 መኖሩ፣

16. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ (1) ሀ እስከ ኘ በተገለጸው መሰረት ከገቢ ላይ መቀናነስ የሌለባቸው ወጪዎች እንዲቀነሱ የተደረገ በመሆኑ በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 10,265,278.35 መኖሩ፣

17. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ሐምሌ 30/2005 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/3 ባወጣው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3.4 መሰረት ኩባንያዎች ያገኙትን ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ያከፋፈሉ ወይም የኩባንያውን ካፒታል መዋጮ ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት እና ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ማቅረብ እንዳለባቸውና ማስረጃውን ያላቀረቡ ኩባንያዎች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ ለባለአክሲዮኖች እንዳከፋፈሉ ተቆጥሮ ግብሩን መክፈል እንዳለባቸው በተገለጸው መሰረት ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የቀረበ ማስረጃ በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 11,990,829.61 መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ መገኘቱ፣

18. የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ክፍል 7 አንቀጽ 21 እና 26 ተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስከፈል በወጣው በደንብ ቁጥር 79/1995 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ በአግባቡ መቅረብ፣ ተቀናንሶ መሰላት እንዲሁም የተመላሽ ሂሳብ በትክክል ወደ ሚቀጥለው ወር መተላለፍ ሲኖርበት የከፈሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመክፈል ካሳወቁት ያነሰ በመሆኑ እንዲሁም በገዢው በተያዘው የተጨማሪ

እሴት ታክስ ተከፋይ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገ ባለመሆኑ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 500,215.81 ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስናተመላሽ ሂሳቦች ወደሚቀጥለው ወር ሲተላለፉ በአግባቡ ባለመተላለፉ በብልጫ የዞረ የተጨማሪ እሴት ታክስ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,070,094.00 መኖሩ፣

19. በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያስታወቁት የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠን በሽያጭ ማጠቃለያ/ Z-Report ላይ ካስታወቁት ያነሰ በመሆኑና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ባለመቅረቡና በሽያጭ ማጠቃለያ ላይ በተገለጸው መሰረት እንዲከፍሉ ያልተደረገ በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,366,021.82 መኖሩ፣

20. በህግ ግብርን ቀንሶ የማስቀረት ስልጣን የተሰጣቸው ድርጅቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረቡ ድርጅቶች ግዢ ሲፈጽሙ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 91 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30 በመቶ መቀነስ ሲገባቸው 2 በመቶ ብቻ ተቀናሽ ያደረጉ በመሆኑ እና ከግብር ከፋዩ ላይ ተቀናሽ የተደረገው ተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ በተደረገው መጠን ገቢ እንዲሆን ባለመደረጉ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ቅድመ ግብር ከ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 3,699,991.15 መኖሩ፣

21. ግብር ከፋዮች የ2008 በጀት ዓመት ንግድ ትርፍ መግለጫ ላይ መታየት ያለበት የዓመቱ ጠቀላላ ሽያጭ ቢያንስ (የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ ≥ ቅድመ ግብር X 50) መሆን ሲገባው ግብር ከፋዮቹ ያሳወቁት የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ ከዚህ በታች በመሆኑ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ከ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 21,451,462.61 መኖሩ ፣

22. ግብር ከፋዮች ባቀረቡት በንግድ ሥራ ግብር ማሳወቂያ ላይ የተመለከተው ጠቅላላ ሽያጭ በአመታዊ ማጠቃለያ (Z-Report) ላይ ከታየው ሽያጭ ልዩነት በመኖሩ ምክንያትና ለልዩነቱም አጥጋቢ ምክንያት ውሳኔ ያልወጣለት ንግድ ትርፍ ግብር ብር 2,650,787.58 መኖሩ ፣

23. በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 55 እንደተገለጸውና በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈጸም የዕቃ ግዥ የገንዘብ መጠኑ ከቀን 12/4/2008ዓ/ም ተፈፃሚ የሚሆነው መመሪያው ለማሻሻል በወጣ ሰርኩላር መሰረት እስከ ብር 200,000.00 መሆኑንና የገንዘብ መጠኑ ከብር 200,000.00 በላይ ደግሞ የዕቃ ግዥ በግልጽ ጨረታ የሚፈጸም መሆኑን በሚያዘው መሰረት ባለመሰራቱ በዋጋ ማቅረቢያ በማወዳደር እንዲሁም

በግልጽ ጨረታ መከናወን የነበረበት ግዥ በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,152,264.93 ከመመሪያና ደንብ ውጭ ግዥ ተፈጽሞ መገኘቱ ፣

24.የፌደራል መንግሰት ግዥና የንብረት አሰተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2009 አንቀጽ 43/8/ሀ መሰረት በጨረታው አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው በጨረታ ግምገማ ቴክኒክ መመዘኛ ማሟላቱን የተረጋገጠ እና ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ባቀረበበት ዋጋ መገዛት ሲገባቸው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት በመግዛታቸው በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች በብር 1,435,878.00 በብልጫ ግዥው መከናወኑ፣

25.የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሊደረጉ የሚገባ ጥንቃቄዎች በሚለው አንቀጽ 9 ስር በተዘረዘረው መሰረት ስራዎች ባለመሰራታቸው ግምገማ ላይ የተሳተፉ ሰራተኞች ስለመሳተፋቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ስለመኖሩ፣ ወጪው በመመሪያ መሰረት ስለመሆኑ፣ እቃው በገቢ ደረሰኝ ስለመግባቱ ሳይረጋገጥ፣ የቋሚ ዕቃ ግዥ በዕቅድ ሳይያዝ፣ የግዥ መጠየቂያ ወይም የግዢ ትዕዛዝ እና የወጪ ማስረጃ ሳይኖር በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር **3,958,311.60** ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

26.ሰኔ ወር 2004 ዓ/ም በወጣው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ወሎ አበል የአከፋፈል መመሪያ አንቀጽ 8 (1ሀ-ሐ) ላይ በተመለከተው መሰረት ባለመሰራቱ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው ለቀጠራቸው ባለሙያዎች እና ከሚሰሩበት መ/ቤት ሠራተኛ መሆናቸውንና የወር ደመወዝ መጠን የሚገልፅ ደብዳቤ ሳይኖር እንዲሁም ሠራተኞቹ ለስራ የተጓዙት ሞጆ ሆኖ ሳለ የአበል ክፍያው አዳማ እንደሄዱ ተደርጎ በመከፈሉ የውሎ አበል መመሪያ ያልተከተለ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 313,962.59 ያለ አግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ሂሳብ መኖሩ ፣

27.በመደበኛ የወጪ በጀት ተይዞለት መገዛት ሲኖርበት ያለ በጀት የተገዛ እና ለመንግስት ስራ ተገቢ መሆኑን የተፈቀደበት ሰነድ ሳይኖር በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች በብር 116,043.96 ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣

28.የህገ ወጥ ዕቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ፣ አመዘጋገብና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 78/2004 ክፍል አምስት አንቀፅ 29 ን.አ 1 እና 2 መሰረት ህገ ወጥ ዕቃ ተይዞ ለባለስልጣኑ ገቢ ከሆነበት ግዜ ጀምሮ በ 6 ወር ጊዜ ዉስጥ የክፍያ ጥያቄ ካልቀረበ መብቱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ቢገለጽም ***በጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት*** በ2005 በጀት ዓመት በጥቆማ ለተያዘ እቃ በ2009

በጀት ዓመት በባንክ ክፍያ ማሳወቂያ መሰረት የይርጋ ገደቡ ካለፈ ከሶስት ዓመታት በላይ መሆኑ እየታወቀ ያለአግባብ ብር 18,786,184.38 የጥቆማና የወሮታ ክፍያዎችን የተፈጸመ መሆኑ፣

29. የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በጊዜ ገደቡ የማይወራረድ ከሆነ ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ የአለበት መሆኑንና በዚህ መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ይሁን እንጂ በ9 ቅ/ጽ/ቤቶች በሰኔ 30/2009 የሂሳብ መግለጫቸው ሪፖርት ከተደረጉት ተሰብሳቢ ሂሳቦች ውስጥ ብር 48,444,108.39 ሂሳብ በቂ ማስረጃ የሌላቸው ሲሆኑ አብዛኞቹ ሂሳቦች በባለፉት ዓመታት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መሆኑና እርምጃ ሳይወሰድባቸው የቆዩ ሲሆን ይህም ሂሳብ በተጠቃለለው መግለጫ ላይ በድምር ተይዞ መገኘቱ ፣

30. የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈፀምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚኖርበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች ከተመለከተው ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የብር 79,470,004.62 ተከፋይ ሂሳብ ማስረጃ ሳይኖረው በሂሳብ ሪፖርት ላይ ሪፖርት ተደርጎ መገኘቱ፣

31. በ2009 በጀት ዓመት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ተጠቃሎ መቅረብ ሲገባው ፤ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተላከው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ፣

- የወጪ ሂሳብ ብር 12,183.80 በመብለጥ እና ብር 11,538.80 በማነስ፣
- በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ በድምር ብር 488,654.68 በማነስ እና ብር 6,901,617.54 በመብለጥ፣
- በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ በድምር ብር 7,043,961.69 በመብለጥ፣ ብር 21,379.07 በማነስ፣

- የገቢ ሂሳብ በድምር ብር 76,227,364.01 በመብለጥ፣
- የጥሬ ገንዘብ እና ባንክ ሂሳብ ብር 1,099,881.12 ዴቢት በማነስ ፣ እንዲሁም ብር ብር 1,873,765.63 ዴቢት በመብለጥ፣
- የተጣራ ሀብት የሂሳብ መግለጫ ድምር ብር 37,840,864.05 በክሬዲት በማነስና 42,613,421.78 ዴቢት በማነስ፣

የሚያሳይ መሆኑ ፣

32. በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በ 8 ቅ/ጽ/ቤቶች ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ሪፖርት በተደረገው የሂሳብ መግለጫ ላይ ግን ያልተለመደ ሚዛን(abnormal balance) የሚያሳዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 167,544,565.83 መኖሩንና ይህም ሂሳብ በተጠቃለለው ሂሳብ ላይ ተካክሶ ሪፖርት መደረጉ፣
33. የመንግስት ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት (8) (መ) የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ እንዳለበት ያዛል፡፡ በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች የተዘጋጁ ሂሳብ ሪፖርቶች ግን ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በተዘጋጀው የባንክ ሂሰብ ማስታረቂያ(bank reconciliation) ላይ በመዝግብ ሚዛንና ባንክ ሚዛን መካከል የብር 858,906,466.18 ልዩነት የሚታይ ሲሆን የልዩነቱ ምክንያት ባለመታወቁ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
34. በባለስልጣኑ ***ዋና መ/ቤት*** ለክልሎች እና ለከተማ መስተዳደር ለመክፈል ከቅ/ጽ/ቤቶች እና ሌሎች መ/ቤቶች የሰበሰበው የአደራ ሂሳብ በአደራ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 010019104192 ላይ ብር 110,622,643.26 የሚታይ ሲሆን በ5026 ለክልሎች እና ከተማ መስተዳደር ድርሻ ገቢ በተከፋይ በሪፖርት የተያዘው ሂሳብ ግን ብር 97,920,344.00 በመሆኑ በልዩነት ብር 12,702,299.06 በአደራ ባንክ ሂሳብ የሚታይ ነገር ግን በሂሳብ መግለጫ በተከፋይ ያልተያዘ መገኘቱ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1-34 በተገለጹት ሁኔታዎች ምክንያት የባለስልጣን መ/ቤቱ የ2009 በጀት ዓመት የተጠቃለለው ሂሳብ የሂሣብ መግለጫዎች የመ/ቤቱን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት አመቱን የስራ እንቅስቃሴ በሚያሳይ ሁኔታ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ

እንዲሁም በሂሳብ አያያዝ ማእቀፍ መሰረት ያልተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት ትክክለኛውን ሁኔታ አያሳይም፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፣

ምንም እንኳን የኦዲት አሰተያየታችንን ሊያስለውጡ ባይችሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና አፋጣኝ የእርምት እርምጃ የሚፈልጉ ናቸው፡፡

1. በጥሬ ገንዘብ የሚሰጥ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ....ወዘተ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 እንዲሁም ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 11 በተገለጸው ሰንጠረዥ ሀ መሰረት ግብር የሚከፈልባቸው መሆኑን መስከረም 19/2008 በደብዳቤ ቁጥር 3.5.0/165/09 በገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በ16 ቅ/ጽ/ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት እና ባለፉት የኦዲት አመት እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበት እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ ብር 1,287,630.52 ከቤት እና ከሙያ አበል ያልተቀነሰ የስራ ግብር መኖሩ ፣
2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የትርፍ ስዓት ክፍያና የማካካሻ እረፍት አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 104/2007 አንቀፅ 16 ንኡስ አንቀፅ 2 ላይ በተገለፀው መሰረት የትርፍ ስዓት ስራ የማይከናወንባቸው የስራ መደቦች ወይም የስራ ዝርዝር በተላከው ደብዳቤ መሰረት ተግባራዊ እዲደረግ ያዛል፡፡ በተጨማሪ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ/ም በወጣ የፌደራል መንግስት ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች፣ስለክፍያው መጠን እና የማካከሻ ዕረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ አንቀፅ 10.2 አንድን ሰራተኛ በወር ዉስጥ እጅግ ቢበዛ ከ60 ሰዓት በላይ ትርፍ ሰዓት ማሰራት እንደማይቻል በሚደነግገው መሰረት መሰራት ሲኖርበት ፣ የተሰራ ስራ ሳይገለጽ፣ በሚመለከተው የስራ ክፍል ሳይፈቀድና ሳይጸድቅ በመደበኛ የሰራ ሰዓት ሊሰሩ የሚችሉና የትርፍ ሰዓት ላልተፈቀደ የሥራ መደቦች የተከፈለ ትርፍ ስዓት ***በጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 318,346.42 መገኘቱ ፣
3. በየቅ/ጽ/ቤቶቹ በጊዜ ገደቡ ሳይሰበሰብ የቆየ በ2009 በጀት ዓመት እና በባለፉት ዓመታት እንዲሰበሰብ ተብሎ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ውዝፍ የግብር እና

ታክስ ዕዳ ከ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 7,533,167,277.70 በተለያየ ደረጃ እንጥልጥል ላይ ያለ መሆኑን፣

4. በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢዉ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑንና በአዋጁ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ተመልሰዉ ከአገር በማይወጡት እቃዎች ላይ በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ለመንግስት ገቢ የሚደረግ ወይም ዋስትናው እንዲታደስ ክትትል መደረግ ቢኖርበትም በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 235,177,463.32 ዋስትናው ያልታደረሰ ወይም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተቀየረ ሲሆን በተጨማሪ በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በ2008 በጀት ዓመት ሰነድ ያልተገኘላቸው የዋስትና ሂሳቦች ብር 32,470,457.32 እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም አሁንም ተገቢ እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ፣

5. በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርአት አዋጅ ቁጥር 768/2004 አንቀፅ 10(3 እና 5) መሰረት በቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ወደ አገር የገባ ጥሬ እቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጪ ገበያ መላክ እንዳለበት ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የጥሬ እቃውን ባህሪ መሰረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ሊፈቅድ እንደሚችል ነገር ግን የመጠቀሚያ የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ወይም ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ እቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ 50% እንዲከፍል እንደሚደረግ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ***በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት*** በኩል በተለያዩ አስመጪዎች አማካኝነት ወደ ሀገር የገቡ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ጥሬ ዕቃዎች በቫውቸር ስርአት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ቢሆንም በአዋጁ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ በመሆኑ በጥሬ እቃው ላይ ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑን፣

6. በቅ/ፅ/ቤቱ በተግባር ላይ ያለው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሁለት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎችና ዓይነቶች በአንቀጽ 6 እና 7 በተዘረዘሩት የቁጥጥር ደረጃዎች ዕይታ

የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ቁጥጥር የሚካሄድበትና ማመዛዘኛ መሰራት የሚገባ ቢሆንም የቀረጥ ሂሳብ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ/REMOVAL/ ከዋና መ/ቤት ተከታታይ ቁጥር ተሰጥቶት ወደ ቅ/ፅ/ቤቶች የሚላክ ቢሆንም ***በሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና በመቀሌ ቅ/ጽጽቤት*** በሞዴል 19 እና 22 ገቢና ወጪ የማይሆን ከመሆኑም በተጨማሪ የተሰራበትንና ያልተሰራበትን ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል መልኩ የተዘረጋ የቁጥጥር ስርዓት ባለመኖሩና የደረሰኝ ማመዛዘኛ ለመስራት ባለመቻሉ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

7. በ2009 በጀት ዓመት የገቢ ሂሳብ ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው ብር185,949,250,000.00 ሲሆን ፣የተሰበሰበው ደግሞ ብር 160,077,590,000.00 በመሆኑ እቅዱ ከክንውኑ ጋር ሲነጻጸር ክንውኑ በብር 25,871,660,000.00(13%) አንሶ ተገኝቷል፡፡በተጨማሪም በተለያዩ የሂሳብ መደብ በመቶኛ ከ10% በላይ ከዕቅድ በታች ክንውን በ75 የገቢ ሂሳብ መደብ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ውስጥ ብር 26,430,907,214.20 ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ፣
8. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት ቢታወቅም ከ 1999 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ ከ 10 ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ ተሰብሳቢ ሂሳብ በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 52,074,280.63 መኖሩ፣
9. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከ ሀ-ሠ በተዘረዘረው መሰረት በየቅ/ጽ/ቤቱ በሂሳብ መግለጫ ላይ ለታየው ተከፋይ ሂሳቦች የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶለት ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ እንዲወራረዱ ክትትል መደረግ ቢኖርበትም ከ 2001 እስከ 2009 ዓ.ም ከ9 ኣመታት በላይ ሳይወራረዱ የቆዩ የተከፋይ ሂሳቦች በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 33,769,154.94 መኖሩ፣
10. በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 6/1 ረ እና አንቀጽ 10/ሀ መሰረት ለመንግስት ንብረት የተሟላ የቁጥጥር ስርአት የተዘረጋ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በውርስ መጋዘን ውስጥ በሚገኙና በመደበኛ

በጀት በተገዙ ንብረቶች ላይ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ለንብረት ተገቢው የቁጥጥር ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑ ፣ ከፍተኛ ክፍተቶች የሚታዩ መሆኑን፣

11.በፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 አንቀጽ 17(3) መሰረት ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገኙ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በባለፉት በጀት ዓመታት በተገኙ ግኝቶች ላይ ለተሰጡ የኦዲት አስተያየቶች መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው መገኘታቸው፣ሁኔታውም እንደሚከተለው ነው፣

<u>በሀገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ</u>

- የእርጅና ቅናሽ በትክክል ባለመሰላቱ እና የመጨረሻ ሚዛን በትክክል ወደ ሚቀጥለው ዓመት ያልተላለፈ እንዲሁም የጥገናና የማሻሻያ የወጪ ስሌታቸው በትክክል ባለመቀመጡ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 479,671.99 መኖሩ፣
- የ2007 እና 2008 ዓመታዊ ንግድ ትርፍ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ኤክሳይስ ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክሳቸውን በወቅቱ ያላሳወቁ በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች 20 ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ያላሳወቁ መሆኑ፣
- በንግድ ትርፍ መግለጫ እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ መካከል በታየ ልዩነት በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 22,684,650.33 ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ፣
- የሽያጭ ገቢን በማሳነስ ***ባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 10,916.438,018.16 ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ መኖሩ፣
- ማስረጃ ሳይቀርብለት ተቀናሽ የተደረገ ቅድመ ግብር (withholding tax) እና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስ (Withholding Tax) ትክክለኛ ስሌት መሰረት በንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያ ላይ ያላሳወቁ በመሆኑ በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 4,995,905.81 ያሳወቁት ሽያጭ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ፣
- የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ዓመታዊ ንግድ ትርፍ ከዜድ ሪፖርት ጋር በታየ ልዩነት ***ምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 47,910.35 መኖሩ፣

- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ያልተቀነሰ ግብር ***ምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት*** ብር 151,613.99 መኖሩ፣
- ከግብር ከፋዮች ያልተሰበሰበ የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር ምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 259,513.51 መኖሩ፣
- የታክስ ማዕከል ያልተቀየረላቸው ***በጅማ ቅ/ጽ/ቤት*** 221 ግብር ከፋዮች መኖሩ፣
- ***ምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት*** በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ መሰረት ያልተሰበሰበ ግብር ብር **31,151,339.07** መኖሩ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ በብልጫ ብር 365,849.22 ተቀናሽ የተደረገ ስለመኖሩ እና የውሳኔ ማስታወቂያ ያልወጣለትና ግብሩም ያልተሰበሰበ ብር 2,121,118.39 መኖሩ ፣

<u>የጉምሩክ ገቢ ሂሳብን በተመለከተ</u>

<u>*የኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት*</u>

<u>ጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ሳይፈቀድ የገባ USED LAUNDARY MACHIN በህግ አግባብ ጉዳዩ ተቋጭቶ መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ ሳይሰበሰብና ውሳኔ ሳያገኝ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ መሆኑ፣
- በተለያየ ምክንያት ያልተሰበሰበ ብር 401,501.71 እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠበት ቀረጥና ታክስ ያለ መሆኑ፣

በአጠቃላይ እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

<u>የወጪ ሂሳብን በተመለከተ</u>

<u>ዋና መ/ቤት</u>

- አቅራቢው በወቅቱ ባለማቅረቡ ለዘገየበት የተያዘ የቅጣት ሂሳብ ያለአግባብ የተከፈለው ብር 403,137.20 በህግ ክርክር ላይ መሆኑ፣
- ከመመሪያው ውጪ የተከፈለ የምሳ አበልን ብር 1,989.50 ተመላሽ አለመደረጉ፣
- መመሪያው ከሚፈቅደው ወጪ ያለአግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ብር 60,545.00 እርምጃ አለመወሰዱ፣

- በዱቤ ከተሸጡ የተወረሱ ዕቃዎችን ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 621,050,644.38 መኖሩን፣
- የተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ወይም ጉዳያቸው ያላለቀ 19 ተሽከርካሪዎች መኖራቸን፣
- በስራ ላልተገኙ ሰራተኞች ያለአግባብ ከተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ ያልተደረገ ብር 324.12 መኖሩ፣
- በማነስ ተመዝግቦ የተገኘው እስካሁን የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት በብር 2,080,670.72 መኖሩ፣
- የሰሌዳ ቁጥር 4-14310፣ 4-12137፣ 4-15028፣ 4-16059 የሆነ መኪና ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ከ6 ወር በጥገና ላይ ያሉ ተብሎ የተገለጸው በአሁን ሰዓት በግቢ ውስጥ ቆሞ የሚገኝ አገልግሎት የማይሰጥ 4-15028 ሲሆን 4-14310 እና 4-16059 የሚወገዱ ተብለው በሰነድ የተያዙ ነገር ግን ያልተወገዱ የሰሌዳ ቁጥር 4-12137 ተሸከርካሪ አሁንም በጥገና ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

<u>ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት</u>

ከሰራተኞች መቆረጥ የሚገባው የደመወዝ የስራ ግብር ብር 34,109.40 ያልተሰበሰበ ስለመሆኑ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን ተገቢውር እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ ፣

<u>ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ሳይመዘገብ የገባ የውጭ ምንዛሬ ማስረጃ ያልቀረበለት በዩሮ 211,220.00 እና በዶላር 1,700.00 በወቅቱ ባለው የሀገር ውስጥ ምንዛሬ በአጠቃላይ በድምሩ ብር 4,876,186.20 እንዲሁም 4.336 ኪ.ግ ወርቅን ያለአግባብ ተመላሽ የተደረገው የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
- ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኞች የተከፈለ የደመወዝ ክፍያ ብር 2,663.45 ተመላሽ አለመደረጉ፣

<u>የጅግጅጋ ቅ/ጽ/ቤት</u>

ሂሳቡ እንዲሰበሰብ ወይም ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት የተሰጠ የያዥና ጠቋሚ አበል ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ያልቀረበ ብር 105,630.10 መኖሩ፣

ሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት

- ከዋና መ/ቤት ለመጡ የተከፈለ የውሎ አበል እንዲከፈል ደብዳቤም ሆነ ማስረጃ ካለ ያልቀረበ እንዲሁም ገንዘቡ መሰብሰብ ያለበት ከሆነም ያልተሰበሰበ ብር 1,719.90 መኖሩ
- በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000026238537 በሂሳብ መደብ 5051 የጉምሩክ የመያዣ ተከፋይ ሂሳብ ብር 411,469.09 ማስረጃ አልተገኘለትም ተብሎ የነበረውን ወደ ቀጥታ ገቢ ያስገቡት ሲሆን ወደ ቀጥታ ገቢ እንዲገባ የማኔጅመንት ውሳኔ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፣

በአጠቃላይ እርምጃ እንዲወሰድበት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድበት የቆየ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ የተመለከተውን ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች ዋና ዋናዎቹ በተዘጋጀው አባሪ የገቦዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና ቅ/ጽ/ቤቶች ስር የተመለከቱ ሲሆን፤ በዝርዝር ደግም በስራ አመራር ሪፖርት ውስጥ ስለተገለጹ መመመልከት ይቻላል፡፡

የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2009/10 የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት

1.1 የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር

ተ.ቁ	ኦዲት የተደራጊው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር	448,422,900.37	338,700,000.00	787,122,900.37
2	የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት	26,529,436.00	30,000,000.00	56,529,436.00
3	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	23,421,640.00	3,571,020.00	26,992,660.00
4	የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር	44,434,519.41	-	44,434,519.41
5	የብሄራዊ ስነ ልክ ኢንስትቲዩት	31,813,675.14	-	31,813,675.14
6	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ	13,938,110.00	-	13,938,110.00
7	ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ	45,885,995.00	80,000,000.00	125,885,995.00
8	ብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን	46,788,143.10	-	46,788,143.10
9	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	9,205,025.00	-	9,205,025.00
10	ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	56,224,569.33	20,635,000.00	76,859,569.33
11	የፌዴሬሽን ም/ቤት	56,375,626.00	9,480,234.07	65,855,860.07
12	የኢትዮጵያ ባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት	20,964,000.00	33,000,000.00	53,964,000.00
13	የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ	24,926,114.00	-	24,926,114.00
14	የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	21,460,000.00	-	21,460,000.00
15	ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	68,918,334.86		68,918,334.86
16	ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት	11,853,184.74	-	11,853,184.74
17	የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ	47,108,350.00	-	47,108,350.00
18	የትምህርት ስትራቴጂ ማእከል	26,342,690.00	14,157,000.00	40,499,690.00
19	የህብረት ስራ ኤጀንሲ	40,548,770.00	-	40,548,770.00

20	የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ	9,294,405.64	-	9,294,405.64
21	የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት	167,257,954.47	600,152.59	167,858,107.06
22	ፕሬስ ድርጅት	133,750,680.00	-	133,750,680.00
23	የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባህል ማዕከል	23,471,610.00	-	23,471,610.00
24	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	581,485,378.85	-	581,485,378.85
25	የኢትዮጵያ ወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ	62,977,000.00	10,000,000.00	72,977,000.00
26	ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	80,174,877.96	-	80,174,877.96
27	የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	16,663,470.00	-	16,663,470.00
28	የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	56,110,440.00		56,110,440.00
29	የኢትዮጵያ ካይዘን ኢኒስቲትዮት	33,554,142.00	-	33,554,142.00
30	ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ	150,655,999.58	639,945,819.23	790,601,818.81
31	የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን	35,735,440.00	77,096,749.30	112,832,189.30
32	የቤተመንግስት አስተዳደር	172,858,956.58	410,177,125.13	583,036,081.71
33	ፕሬዚደንት ጽ/ቤት	68,838,223.00		68,838,223.00
34	ካርታ ስራ ድርጅት	34,204,610.00	20,000,000.00	54,204,610.00
35	ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት	240,505,016.12		240,505,016.12
36	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቤት	26,364,022.48	36,900,000.00	63,264,022.48
37	የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	58,720,334.65	-	58,720,334.65
38	ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን	8,931,415,064.62	-	8,931,415,064.62
39	የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	419,671,400.00	125,837,900.00	545,509,300.00
40	መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ	153,103,142.69	8,316,000.00	161,419,142.69
41	የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን	54,767,406.00	-	54,767,406.00
42	ሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	33,610,301.03	-	33,610,301.03
43	የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ ሂሳብ			
	ድምር	**12,610,350,958.6**	**1,858,417,000**	**14,468,767,959**

1.3 የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

- ነቀፌታ የሌለበት Clean Opinion - 2 መ/ቤቶች
- በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) -36 መ/ቤቶች
- የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ /Adverse opinion/- 2 መ/ቤቶች
- ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች (Disclaimer opinion- 1 መ/ቤት

ናቸው፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-1 ተመልክቶል፡፡/

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሂሳብ ሰራተኛ የነበሩት ከነሀሴ 12/2009 ጀምሮ በመደበኛ ስራቸው ላይ ባለመገኘታቸው ከስራ የተሰናበቱ ቢሆንም ለሥራ ማስኬጃ በተለያየ ጊዜ ከወሰዱት ውስጥ ቀሪ ብር 10,092.95 ጥሬ ገንዘብ ለጽ/ቤቱ ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም ሰራተኛው የወሰዱትን ጥሬ ገንዘብ ተመላሽ እንዲያደርጉ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ29 መ/ቤቶች 3,682,154,951.75 ያልተወራረደ ሂሳብ ተገኝቶል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለማወራረድ ለመንግስት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ለረጅም ዓመታት ሳይወራረዱ የተገኙት ሂሳቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ ፣ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግስት መመሪያ መሰረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሣብ

3.1 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6(ሐ) እና አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8(ሠ) በፋይናንስ ምንጮች የተመዘገቡ ሂሳቦች ሚዛን ተወስዶ ወርሀዊ ዓመታዊ ሪፖርቶች ማዘጋጀት እና የተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረብ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

- ከውጭ ሀገር የሚመጡ ተመራማሪዎች ለምርምር ከሚከፈላቸው ሂሳብ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ገቢ ያደረጉት ሂሳብ ------------------ ብር 6,718,714.45
- ለጥናትና ምርምር የማመልከቻ ፎርም ------------ ብር 148,816.31

በድምሩ ብር 6,867,530.76 ብሄራዊ ባንክ በሚገኘው የባንክ ሂሳብ ቁጥር 0100181040093 ገቢ የተደረገ ቢሆንም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ እና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚያቀርበው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተሰበሰበው ገቢ በሙሉ ወደ ባንክ ገቢ መደረጉ እና ያለአግባብ ወጪ ያልተደረገ መሆኑ ተጣርቶ ፈሰስ ሊደረግ እንደሚገባና ማንኛውም የመንግስት ገቢ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ተመዝግቦ ሪፖርት ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

3.2 <u>ለማስታወቂያ አገልግሎት እና የተለያዩ የጋዜጣ እና መጽሔት ሽያጭ በዱቤ ተሰጥቶ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ሂሳብ</u>

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት</u>

ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች አገልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ እስከ 2009 ዓ.ም ከተላለፈው ማስታወቂያ መሰብሰብ የነበረበት ብር 5,871,507.84 እንዲሁም ለተለያዩ ወኪል አከፋፋዮች በዱቤ ከተሸጠ ጋዜጣና መጽሂት ብር 20,374.50 በድምሩ ብር **5,891,882.34** ከደንበኞች ሊሰበስብ ይገባው የነበረውን ውዝፍ ሂሳብ አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡ስለሆነም ያልተሰበሰበው ሂሳብ እንዲሰበሰብ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን</u>

ከ2002 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ ለተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በዱቤ ከሰጠው የማስታወቂያ አገልግሎት ውስጥ ያልተሰበሰበ ብር 58,070,344.30 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰብ የተገኘው ሂሣብ እንዲሰበሰብ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ሊሰበሰብ የማይችል ተሰብሳቢ ተለይቶ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዝ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.3 <u>በእቅድ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ</u>

የፌዴራል መንግሥት በጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ቁጥር 3 የፌዴራል መንግስት የገቢና ወጪ ግምት ዕቅድ ዝግጅት ታሣቢዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፡-</u>

ድርጅቱ ከሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች **በ2009** በጀት ዓመት ብር 133,625,476.00 ለመሰብሰብ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም መሰብሰብ የተቻለው ብር 109,721,604.30 (82%) በመሆኑ የተሰበሰበው ገቢ ከገቢ እቅዱ በብር 23,903,871.70 በማነስ የሚታይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን</u>

በ2009 በጀት ዓመት ውስጥ ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ የስራ ዘርፎች ብር 500,000,000.00 /አምስት መቶ ሚሊዮን/ ለመሰብሰብ የታቀደ ቢሆንም ብር 355,145,902.86 ብቻ በመሰብሰቡ ክንውኑ ከዕቅድ ጋር ሲነጻጸር በብር 144,854,097.14 ወይም (29%) በማነስ የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ</u>

በ2009 በጀት ዓመት ኤጀንሲው ከሚሰጣቸው የተለያዩ አገልግሎቶች ብር 13,500,000.00 ለመሰብሰብ የታቀደ ቢሆንም መሰብሰብ የተቻለው ብር 10,781,818.58 (79%) በመሆኑ ክንውኑ ከዕቅዱ በብር 2,718,181.42 (21%) የሚያንስ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ ዕቅድና ዝግጅት በጥናትና በመረጃ የተደገፈ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.4 ማስረጃ ሳይቀርብለት ከገቢ የተሰረዘ ሂሳብ

የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

መስሪያ ቤቱ የሰበሰባቸውን የተለያዩ ገቢዎች በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ በናሙና ለኦዲት ከተመረጡት ውስጥ በድምሩ ብር 12,322,088.90 ከተንቀሳቃሽ እና ተንቀሳቃሽ ካልሆኑ ንብረቶች ሽያጭ የተገኘ ገቢ እንዲሁም ብር 20,920,555.30 ልዩ ልዩ ገቢዎች በአጠቃላይ ብር 33,242,644.20 የያዙ በቁጥር 203 የገቢ ትራንዛክሽኖች በIFMIS የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተከታታይ የገቢ ደረሰኝ ቁጥር ተሰጥቷቸው በክሬዲት የተመዘገቡ ቢሆንም የሰነድ ማስረጃ ሳይቀርብና መግለጫ ሳይሰጥ ብር 33,242,644.20 በዴቢት በመመዝገብ በገቢ የተመዘገበው ሂሳብ እንዲጠፋ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም አስቀድሞ በገቢ የተመዘገበው ሂሳብ እንዲጠፋ የተደረገበትን ምክንያት የሚገልጹ የሰነድ ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 የውስጥ ገቢ የማስከፈያ የዋጋ ተመን የሌለ መሆኑ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ስለፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል 4.21.1 የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት አዲስ ተመን/ ዋጋ ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በኃላፊው በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማስፀደቅ እንደሚኖርባቸው ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

የቤተ-መንግስት አስተዳደር

በ2009 በጀት ዓመት ከፈረስ ስፖርት መዝናኛ አገልግሎት ፣ ከመቀሌ ቤተመንግስት የሙዝየም ጉብኝት እና ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎች ብር 2,005,933.77 ገቢ የተሰበሰበ ቢሆንም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ የአገልግሎት አይነቶች ዝርዝር (source of revenues) እና ለእያንዳንዱ አገልግሎት የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ (Charge Rates) የሚገልጽና በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጸደቀ ሰነድ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

የካርታ ስራ ኤጀንሲ

በ2009 በጀት ዓመት ከአየር ፎቶግራፍ፤ ከቅየሳ እና የካርታ አነሳስ አገልግሎት ብር 10,781,818.58 የተሰበሰበ ቢሆንም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ የአገልግሎት

የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ (Charge Rates) የሚገልጽ ሰነድ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን</u>

በቡና ጥራት ምርምርና ሰርቴፊኬሽን ማዕከል ከኤክስፖርት ቡና ምርምራ እና ከአቅም ግንባታ ስልጠና አገልግሎት ገቢዎች በ2009 በጀት ዓመት ብር 7,611,560.57 የተገኘ ቢሆንም ባለሰልጣኑ ለሚሰበስበው ገቢ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ አገልግሎት የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ (Charge Rates) የሚገልጽ ሰነድ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም መ/ቤቶቹ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ዝርዝር እና ለእያንዳንዱ አገልግሎት የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ የሚገልጽ ሰነድ በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ስራ ላይ እንዲውል የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል ፡፡

3.6 በተከፋይ ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ገቢ

<u>የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ</u>

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ቁጥር 3 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸው ተለይተው በሂሳብ መለያ ቁጥሮች መሰረት ሂሳባቸው መመዝገብ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው IGAD Climate Predication and Application Center ከሚባል ተቋም ጋር በገባው ውል መሰረት ለሰጠው አገልግሎት ገቢ ከተደረገው ውስጥ ብር 57,981.76 በገቢ ሂሳብ ርዕስ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው በሂሳብ አርዕስት 5002 እንደተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ በመሆኑ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም በተከፋይ ለተያዘው ሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራለት ሆኖ በዚሁ መሰረት የሂሳብ መግለጫዎቹ እንዲስተካከሉና ለወደፊቱም ኤጀንሲው ለሰጠው አገልግሎት ገቢ የተደረገ ገንዘብ በገቢ ተመዝግቦ ሪፖርት ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

4.1 ያለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ

<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ 4/2003 አንቀጽ 10 ተራ ቁጥር 5 መሠረት በጡረታ፣ በሞትና በሌሎች ምክንያት ከሥራ ለተለዩ ሠራተኞች ደመወዝ እንዳይከፈል ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በተለያየ ምክንያት ሥራ ለለቀቁ 5 ሰራተኞች ሥራ ላይ ላልተገኙበት ቀናት በጠቅላላ ብር **4,516.46** አላግባብ የተከፈለ በመሆኑ ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በገዛ ፍቃዳቸው ከስራ ለተሰናበቱ ሰራተኛ በስራ ላይ ያልነበሩበት የ19 ቀን ደመወዝ ብር 2,733.46 ያለአግባብ የተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 2 አገልግሎቱ በተፈለገው ስፔስፊኬሽን መሠረት መቅረቡ ወይም አገልግሎቱ መሰጠቱ ሲረጋገጥ እና እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ተ.ቁ 2/ለ መሰረት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ተጠቅሷል፡፡ ይሁን እንጂ የወጪ ሂሳብ ትክክለ ኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ16 መ/ቤቶች ብር 47,387,440.09 የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቶል/

የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሊመዘገብ እና ማስረጃ ሲቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ሊደረግ እንደሚገባና በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ደጋፊ የክፍያ ማስረጃ እንዲቀርብ እና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጸም ጥንቃቄ እንዲደረግ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡

ለመስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ በስብሰባም ሆነ በስልጠና የተሳተፉት ሰራተኞች ብዛትና የስም ዝርዝር የሚገልጽ የሰዓት መቆጣጠሪያ ሠነድ ለኦዲት ባለመቅረቡ ምክንያት ሂሳቡን በዝርዝር ኦዲት ለማድረግና የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ

ለወደፊቱ ማንኛውም የወጪ ሂሳብ ከመመዝገቡ በፊት የተሟላና ተገቢ ማስረጃ የቀረበለት መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

4.3 ምንም ዓይነት የሰነድ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዘገበ ሂሳብ

የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

ለአየር ትኬት ግዥ ብር 214,366.00፣ ለማስታወቂያ አገልግሎት ብር 4,579.00፣ እንዲሁም ለተለያዩ ወጪዎች ብር 50,000.00 በድምሩ ብር 268,945.00 የያዙ የወጪ ሰነዶችና ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ አልቻሉም፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ

ለትርፍ ሰዓት የተከፈለ ተብሎ በትራንዛክሽን ሬጂስተር ላይ ብር 6,274.17 የተመዘገበ እና በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ የተካተተ ቢሆንም ደጋፊ የክፍያ ማስረጃ ሰነድ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

4.3 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ታህሳስ 2008 በተሻሻለው የፌዴራል የመንግሥት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ከብር 150,000.00 በላይ የሚፈጸሙ የአገልግሎት ግዥዎች እና ከብር 200,000.00 በላይ የሆኑ የዕቃዎች ግዥ በግልጽ ጨረታ መከናወን እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሰኔ 2/2002 ክፍል 4 አንቀፅ 24.3 የመንግስት መ/ቤቶች በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ ግዥ ሲፈጽሙ አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ከተመዘገቡ መካከል ቢያንስ ከሦስቱ የዋጋ ማቅረቢያ በመጠየቅ ዋጋቸው ተወዳድሮ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበው ተመርጦ በበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክላቸው ሰዎች እንዲፀድቅ በማድረግ ግዥ ማከናወን እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡ ሆኖም የግዥ ደንብ እና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ ግዥ በ26 መ/ቤቶች ብር 30,317,650.23 ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-21 ተመልክቷል/

ስለሆነም ማንኛውም ግዥ በመንግሥት የግዥ መመሪያ መሰረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡

4.4 በግዥ መመሪያ ለጥቃቃቅን ዕቃዎች ግዥ ከተመደበው የገንዘብ መጠን በላይ የተፈጸመ ቀጥታ ግዥ

የቤተመንግስት አስተዳደር

ለኦዲት ስራ በናሙና በተመረጡ የወጪ ቫውቸሮች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከብር 5,000.00 ያልበለጡ ነገር ግን በድምሩ ብር 761,613.66 የሚያወጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከተፈቀደው በላይ ቀጥታ ግዥ የተከናወነ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከብር 5,000.00 ያልበለጡ ነገር ግን በድምሩ ብር 473,448.9 የሚያወጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ግዥ ሲፈጸም የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትሎ መሆን እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.5 በብልጫ የተከፈለ

የመ/ቤት ስም	ምክንያት	የገንዘቡ ልክ
የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል	ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት በመግዛቱ	20,629.25
የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት በመግዛቱ	255,085.14
የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን	በመመሪያ ከተፈቀደው የወተት አበል ተመን በላይ የተከፈለ ብር 30,774.50 እና በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል ብር 26,676.00	57,450.50
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	ለትርፍ ሰአት፣ከማዕቀፍ ግዥ ውጭ በብልጫ የተከፈለ	9072.50
የህዝብተወካዮችም/ቤት	ከተመን በላይ ለስልክ የተከፈለ	9,575.39
የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	ከተመን በላይ ለስልክ የተከፈለ	4,684.61
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት በመግዛቱ በብል	41,742.70
ድምር		**398,240.09**

ማንኛውም ግዢ በግዥ መመሪያ መሠረት ፍትሀዊና ግልፅ በሆነ አሰራር ሊፈፀም እና የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዳይደረግ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ መደረግ እንደሚኖርበት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

4.6 በተጋነነ ዋጋ የተፈፀመ ግዥ

<u>የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 ክፍል 2 አንቀፅ 6 ንዑስ 22 በተለይ በዋጋ ማቅረቢያ የሚፈፀሙ ግዥዎችን በሚመለከት በአሸናፊነት የሚመረጡ አቅራቢዎች ዋጋ የገበያ ዋጋ መሆኑን ሊረጋገጥ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ከኢትኮም ኢንተርፕራይዝ ኃላ.የተ.የግል ማህበር አንድ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር በብር 54,000.00 እና ከኔክ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኃ.የተ.የግል.ማ አንድ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር በብር 65,000.00 ግዥ የተፈጸመ በመሆኑ በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ግዢ በመፈፀም የመንግስትን ሀብት ከብክነት ለመከላከል በስራ አመራሩ ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ የማሻሻያ ተሰጥቷል፡፡

4.7 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች

የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ	በ2008 በጀት ዓመት ጥሩ የስራ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ሰራተኞች የማበረታቻ ሽልማት	38,100.00
የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት	አገልግሎት መስጠት ላልጀመሩ ደሴ፣ ጅማ እና ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሠራተኛ ደመወዝ እና ለቤት ኪራይ የተከፈለ	440,120.00
የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	ባልፀደቀ የትምህርት እና ስልጠና መመሪያ ላይ በተዘጋጀው ስልጠና በአወያይነት እና በፅሁፍ አቅራቢነት ለተሣተፉበት የተከፈለ	75,000.00
የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	የመመረቂያ ፅሁፍ ማዘጋጃ ለ16 ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸዉ ብር9,000.00 (16*9000.00) በድምሩ ብር 144,000.00 እና ለሁለተኛ፣ድግሪ/Masters/ተማሪዎች የመመረቂያ ፅሁፍ ግምገማ ላደረጉ አድቫይዘሮች ለእያንዳንዳቸዉ በቀን ብር 700.00 ብር ብር 42,000.00	186,000.00
ብሮድካስት ባለስልጣን	ለማበረታቻ ሽልማት የተከፈለ	71,500.00

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን	ለተለያዩ ሰራተኞች ለህክምና አገልግሎትና ለመድኃኒት ግዥ የተከፈለ ብር 50,901.15	50,901.15
ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ	በ5 ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ሳይፈቀድ ለካርታ ስራ ሰራተኞች የኪስ ገንዘብ ተብሎ የተከፈለ	1,719,396.50
የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን	የሠራተኞች የሥራ ልብስና ሥራ መሥሪያ አሰጣጥና አጠቃቀም እንዲሁም የአፈጻጸም መመሪያ ሳይዘጋጅ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች የደንብ ልብስ ብር 1,365,435.53 ግዥ ያከናወነ መሆኑ	1,365,435.53
የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን	ሳይፈቀድ ለህክምና አገልግሎት ብር 50,901.15 ለትርፍ ሠዓት አገልግሎት ብር 14,194.20 የተከፈለ	65095.35
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	ትርፍ ሰአት ክፍያ	2,729.40
የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	ለሥልጠና የምሳ አበል	60,087.50
ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	ወደሌላ መ/ቤት ለተዛወሩ	9,000.00
የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ	ለማበረታቻና ሽልማት፣ትራንስፖርት አበል	242,618.45
የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	ነዳጅና አበል	4,364.24
የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ	ለሠራተኞች በየቀኑ የሻይ ቡና መስተንግዶ እና ለ ACCA መፈተኛ	108,990.94
የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል	ልዩልዩ	4,917.00
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	ማበረታቻ፣የትፍ ሰኣት ክፍያ	196,864.42
የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	ልዩልዩ	253,741.26
ድምር		**4,894,861.74**

ያለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ሳይፈቀድ ለተከፈለውም ፈቃድ ሊኖረው እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.8 በመመሪያ መሰረት ያልተከፈለ ውሎ አበል፤

የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያና የሚኒስትሮች ም/ቤት ታህሳስ 27/2003 ዓ.ም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2001 አንቀጽ 10/1/ሀ መሰረት ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛው ስራው ውጭ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ ሲመለስ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው ቦታዎች (ክልል/ዞን/ወረዳ) ከተማ መሰረት ተከፋፍሎ መከፈል እንዳለበት የደነገገ እና የፌዴራል መንግስት ሰኔ 2004 ዓ.ም ክፍል 2 አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 3 መስሪያ ቤቱ የምግብ ወይም የመኝታ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ የሰጠው አገልግሎት ሂሳብ በተፈቀደው ተመን መሰረት ከውሎ አበል ተቀናሽ መደረግ እንዳለበት የገለጸ ቢሆንም ቀጥሎ በተመለከቱት መ/ቤቶች ከውሎ አበል መመሪያ ውጭ የተከፈለ ውሎአበል ተገኝቷል፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት	የቁርስና የምሳ አገልግሎት ያገኙበት ከተማ በውሎ አበል ቅፅ ላይ ሳይጠቀስ በሠራተኛው መዳረሻ ቦታ ብቻ በማስላት የውሎ አበል ክፍያ መፈፀሙ እና አላግባብ የተከፈለውን የውሎ አበል ለማስላትም ሆነ ትክክለኛውን የገንዘብ ልክ ለማረጋገጥ አለመቻሉ	313,235.80
የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	ለስልጠና ተሳታፊዎቹ የምሳ መስተንግዶ የቀረበላቸው ቢሆንም አለአግባብ የምሳ አበል በድጋሚ የተከፈላቸው	34,479.50
ብሔራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት	ለህዳሴ ግድብ ጉብኝት ለተጓዙ 119 ሰራተኞች የ4 ቀናት ብቻ መክፈል ሲገባ አለአግባብ የ10 ቀናት አበል የተከፈለ	205,353.17
የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የውሎ አበል	77,433.05
ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የውሎ አበል	5,658.00
የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ	አላግባብ የተከፈለ ውሎአበል	4,821.08
የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የውሎ አበል	1,431.00

የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል	ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የውሎ አበል	116.35
የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የውሎ አበል	2,555.00
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር	በስልጠና ላይ ለተሳተፉ የመ/ቤቱ ሰራተኞች ለምሳ አበልና ለትራንስፖርት የተከፈለ	210,900.00
የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ልማትና ግብይት ባለስልጣን	ከቆይታ ቀናት በላይ በብልጫ ብር 26,676.00 እና የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ አላግባብ ለውሎ አበል የተከፈለ ብር 16,250.00 በትርፍ ሰዓት ለተሰጠ አገልግሎት የተከፈለ ውሎ አበል ብር 14,194.20	57,120.20
የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ	ከቆይታ ቀናት በላይ በብልጫ ብር 12,587.00 እና አላግባብ የተከፈለ ብር 5,930.55 በትርፍ ሰዓት ለተሰጠ አገልግሎት የተከፈለ ውሎአበል ብር 25,558.00	44075.55
ድምር		**957,178.70**

ስለሆነም ያለአግባብ የተከፈለው ውሎ አበል ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 አገልግሎቱ ሳይገኝ ያለአግባብ ለቤት ኪራይ የተከፈለ

የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

የፌዴራል መንግሥት ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ቁጥር 4 ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት ያዛል ፡፡ ይሁን እንጂ ለቤት ኪራይ አገልግሎት የዘጠኝ ወር ቅድመ ክፍያ ብር 8,259,300.00 የተከፈለ ቢሆንም እስከ ግንቦት/2009 ድረስ ለ9 ወር ያህል ህንጻው አገልግሎት ላይ ያልዋለ መሆኑ በተጨማሪም ከአከራዩ ጋር የስምምነት ውል የተፈረመ ቢሆንም ስምምነቱ ጸንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብም ሆነ ስምምነቱ የሚጠናቀቅበትና የሚያበቃበት ጊዜ በውሉ ላይ ያልተገለጸ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ከፍያው ለተቋሙ ጥቅም የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ አስገንዝበናል፡፡

4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ የወጪ ሂሳብ

<u>የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ</u>

ለ30 ሠራተኞች ለህዳሴ ግድብ ጉብኝት ለውሎ አበል በማለት ብር 30,000 እና ለ30 ሠራተኞች ለአልጋ በማለት ብር 24,199.76 በድምሩ ብር 54,199.76 ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ሂሳቡ በተገቢው የወጪ አርዕስት ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተከፋይ ሂሳብ ርዕስ 6171101 በወጪ (ዴቢት) የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

ያለአግባብ በተከፋይ ሂሳብ ለተያዘው የወጪ ሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራ ሆኖ በማስተካከያው መሰረት የሂሳብ መግለጫዎቹ እንዲስተካከሉ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 ከመኖሪያ ቤት አበል፣ ከትርፍ ሰዓት ክፍያ ከተመራማሪ ልጆች የት/ቤት ክፍያ ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራ ግብር

የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ ልክ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር	5,505.00
የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	306,296.66
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	14,372.55
የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	31,670.80
ድምር	**357,845.01**

ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.13 <u>ተቀናሽ ያልተደረገ ቅድመ ታክስ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 9,020.55</u>

<u>የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ</u>

- <u>የደሴ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት</u> በተለያዩ የወጪ ቫውቸሮች የዕቃና አገልግሎቶች ግዥ ክፍያ ሲፈጽም ቅድመ ታክስ ብር 793.14 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 7,805.41 በድምሩ ብር 8,598.55

- አርባ ምንጭ ቅ/ጽ/ቤት ከ2 ድርጅቶች ተቀናሽ ቅድመ ታክስ ብር 422.00 በጠቅላላ ብር 9,020.55, ቅድመ ታክስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል።

ያልተሰበሰበው ቅድመ ታክስ ክፍያና የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ተሰብስቦ ለመንግስት ፈሰስ እንዲደረግና ለወደፊቱም ኤጀንሲው መሰብሰብ የሚገባውን ታክስ በጥንቃቄ ሊሰበስብ እና የተሰጠውን ሀላፊነት በአግባቡ ሊወጣ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.14 ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ሳይረጋገጥ የተከፈለ ቀረጥ ሂሳብ

ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተለያየ ጊዜ ለኮሚሽኑ በተፃፈለት ደብዳቤ መሠረት በድምሩ ብር 1,090,989,091.41 የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ የተከናወነ ቢሆንም ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ገቢ ለመደረጋቸዉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲሁም የዕቃዎቹን ዝርዝር እና የሚከፈለውን የቀረጥ መጠን የያዘ ዲክላራሲዮን እና የመጫኛ ሰነዶች ለኦዲት ሊቀርብ አልቻለም፡፡

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ለሞኒተሪንግ መሣሪዎች ግዥ ብር11,120,841.95 የቀረጥ ሂሳብ የተከፈለ ሲሆን ንብረቶቹ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ለመሆናቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ ተውቋል፡፡

በመሆኑም ቀረጥ የተከፈለላቸው ብብረቶች ገቢ ለሆናቸው ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

4.15 ትክክለኛ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ወጪ

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ በ19 መ/ቤቶች ብር 16,662,458.29 የሂሳብ መደቡን ያል ጠበቀ ወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል /ዝርዝሩ በአባሪ-25 ተመልክቷል/

ስለሆነም የገንዘብ ኢኮኖሚትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ከላይ ለተጠቀሱት የወጪ ሂሳብ ምዝገባዎች አስፈላጊዉ ማስተካከያ እንዲደረግ፤

ለወደፊቱም ምዝገባዎቹ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱን ተከትለው ለመመዝገባቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.15 የበጀት አመቱን ያልጠበቀ ወጪ

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 6./1 እና 2 ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የመደበኛም ሆነ የካፒታል ክፍያዎችን በሚፈፅምበት ወቅት በበጀት ዓመቱ በመ/ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተካተተና ወጪው በጀት ዓመቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም በ7 መ/ቤቶች ብር 3,859,112.27 ከበጀት ዓመቱ ውጭ የተመዘገበ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ስለሆነም ማንኛውም ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ደጋፊ የክፍያ ማስረጃዎችና ሰነዶች የበጀት ዓመቱን የጠበቁ መሆናቸው ሊረጋገጥ እና የበጀት አመታቸውን ጠብቀው ሊከፈሉ እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

6. ያለአግባብ የተሰሩ የሂሳብ ማስተካከያዎች

በበጀት ዓመት ውስጥ የተሰሩ የሂሳብ ማስተካከያዎች በፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት መሰረት የተከናወኑ መሆናቸውን እንዲሁም የመንግሥትን መመሪያና ደንብ የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤በሚከተሉት መ/ቤቶች አስቀድሞ የተደረገው ስህተትም ሆነ የትኛውን ሂሳብ ለማስተካከል የተደረገ የሂሳብ ማስተካከያ እንደሆነ የሚገልጽ አጣቃሽ ቁጥር፤ደጋፊ ሰነድም ሆነ መግለጫ የሌለው በመሆኑ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ ልክ
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	46,145.86
የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	508,202.83
የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ	418,902.81
የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር	376,315.57
የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	4,569,501.76
የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	31,292.00
ድምር	**5,904,214.97**

ስለሆነም ከላይ የተገለጹት የሂሳብ ማስተካከያዎች የተሰሩበት ምክንያትና አጣቃሽ ቁጥር እንዲሁም የሂሳብ ሰነዶች እንዲቀርቡ ካልሆነም የተሰሩት ማስተካከያዎች እንዲሰረዙ ሆኖ የሂሳብ መግለጫዎቹም ሊስተካከሉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7. ተቀጽላ ሌጀር የሌለው ሂሳብ

የቤተመንግስት አስተዳደር

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 8/5 ለእያንንዱ የተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት ክትትል ማድረግ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ፡-

የተለያዩ አካሎች በቤተመንግስት አስተዳደር መስተንግዶ እንዲደረግላቸው ለመስተንግዶ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ እና ከዚሁ ገንዘብ ላይ ለመስተንግዶ የወጣው ብር 540,452.93 ለመስተንግዶ የሚሆን ጥሬ እቃ የተገዛበት ብር 1,132,505.90 በድምሩ ብር 1,672,958.83 ለብቻ ተለይቶ የሚያዝበት መከታተያ (ሌጀር) ያልተዘጋጀ በመሆኑ ለእያንዳንዱ መስተንግዶ ገቢ የተደረገው ገንዘብና ለመስተንግዶ የወጣው ወጪ እንዲሁም ከወጪ ቀሪው እየተመዛዘነ የማይረጋገጥ መሆኑ ታውቋል፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

ለመስተንግዶ ገቢ እና ወጪ ለሆነው ለእያንዳንዱ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር በማዘጋጀት ገቢና ወጪው እንዲሁም ከወጪ ቀሪ ሂሳብ መረጋገጥ እንደሚገባው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የመንግሥት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መ/ቤቶች ለግዥ ተብሎ በአገልግሎቱ አካውንት ገቢ ለሚደረገው እና ለሚከፈለው ሂሳብ በየመ/ቤቶቹ ስም የተከፈተ ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ የሂሳቡን እንቅስቃሴ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለማን እንደሚከፈል በግልጽ መታወቅ እንደሚኖርበት የስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

8. የተከፋይ ሂሳብ

8.1 ለባለጥቅሙ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ

በ20 መ/ቤቶች ብር 91,229,531.87 ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 30 ተመልክቷል/

ስለሆነም ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ መከፈል እንደሚኖርባቸው አሳስበናል፡፡

9. የበጀት አጠቃቀም

<u>9.1 ለየሂሳብ መደቡ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ</u>

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 30 ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በ5 መ/ቤቶች ለየሂሳብ መደቡ ከተደለደለው በጀት በላይ ብር3,120,487.35 ወጪ የሆነ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 33 ተመልክቶል/

ለሥራው ተጨማሪ በጀት ካስፈለገ በመመሪያው መሠረት የበጀት ዝውውር ማስፈቀድ እንደሚገባ እና በበጀት አጠቃቀምና አፈፃፀም ላይ ተገቢውን ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር መድረግ እንደሚኖርበት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

9.1 <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት /ከ10% በላይ ልዩነት ያለው</u>

የበጀት ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በመደበኛ ሂሳብ በ41 መ/ቤቶች ብር 436,556,359.47 እና ካፒታል በጀት ብር 380,156,286.11 በድምሩ ብር 816,712,645.58 ስራ ላይ ያልዋለ ተገኝቶል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-33 ተመልክቷል/

ስለሆነም የተፈቀደውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል እንዲቻል በጥናትና በመረጃ የተደገፈ የበጀት እቅድና ዝግጅት እንዲዘጋጅ በተላከው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10. የዕቃና ንብረት አስተዳደር

10.1 <u>ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት</u>

የንብረት አያያዝ ኦዲት ሲደረግ፤- በርካታ የንብረት አያያዝ ችግሮች መኖራቸው ተረጋግጦል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 34 ተመልክቷል፡፡/

ስለሆነም ያልተወገዱ ንብረቶች በአግባቡ እንዲወገዱ የንብረት ምዝገባ እንዲከናወን ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር እንዲሰጥ፤ የቆጠራ ውጤቱ ከመዝገብ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ለንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10.3 በመ/ቤቶች ውስጥ ያልተገኙ ንብረቶች

<u>የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ</u>

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሁለት ተ.ቁ 6 ከሀ-ሰ በተገለፀው መሠረት በኤጀንሲው ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች በአግባቡ ተጠብቀው የሚገኙ መሆናቸውን ለከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ከመንግስት ከኪራይ ነጻ ለተሰጣቸው መኖሪያ ቤት ከመንግሥት በጀት ወጪ ተደርጎ የቤት ቁሳቁስ እንዲሟላ የሚፈቅድ የሚንስትሮች ምክር ቤት መመሪያም ሆነ ውሳኔ የሌለ መሆኑን ከሚንስትሮች ምክር ቤት ለፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በ26/04/2010 በቁጥር መ30-23/484/23 በተፃፈ ደብዳቤ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በዋና ዳይሬክተር አንድ የብረት ጠረጴዛ እና በምክትል ዋና ዳይሬክተር አንድ አልጋና ፍራሽ ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፤

<u>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት</u>

በቀድሞ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች እጅ የሚገኙ ብር 304,436.93 የሚያወጡ የተለያዩ የቢሮ መገልገያዎች (ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች) እና 1 ጄኔሬተር ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም አለአግባብ የተወሰዱ ንብረቶች እንዲመለሱ፣ ንብረቶች በሚመለከተው ኃላፊ እየተፈቀዱ ወጪ እንዲደረጉ፣ ላልተመዘገቡ ንብረቶች ምዝገባ እንዲከናወንላቸው አሳስበናል፡፡

10.4 በጉድለት የተገኙ ንብረቶች

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት</u>

- ለስራ ማከናወኛ በተለያየ ጊዜ በየክፍሉ የሚገኙ ሰራተኞች ወጪ ያደረጉዋቸዉ ቋሚ ንብረት የሆኑ ብር ብር 439.13 ዋጋ ያለው 1 ዲጅታል ወክማን ቴፕ፤ ብር 400 ዋጋ ያለው 1 ራዲዮ ካሴት ፤ ብር 8,344፣ ዋጋ ያለው 1ተንቀሳቃሽ ስልክ ቀፎ (ሞባይል የስልክ ቀፎ) እና ዋጋው ያልታወቀየማኪና ጎማ ከነቸርኬው

በጠቅላላ ብር 9,183.13 የሚያወጡ ንብረቶች የጠፉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- መ/ቤቱን ከለቀቁ ሰራተኞች ላይ የሚፈለጉ1 ዲጂታል ወክማን ቴፕ ብር 3,340.00፣ 1 ዲጂታል ካሜራ ብር 4,499.99 እና 1 ዲክሽነሪ መፅሐፍ ብር 380.00፣11 ዲጂታል ወክማን ቴፕ ብር 21,595.55፣ 1 ዲጂታል ካሜራ ብር 4,499.99፣ 2 ላፕቶፕ ኮምፒውተር ብር 31,098.30፣ 1 ሞባይል ቀፎ ብር 2,912.00፣ ሲ ዲ ኤም ብር 500፣ እና ማስመሪያ ብር 6.00 በድምሩ ብር 68,831.83 ዋጋ ያላቸው እቃዎች ተመላሽ ሳያደርጉ ድርጅቱን የለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ዋናው መ/ቤት</u>

- ተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ በ(UC) ተመዝግበው 1 Flash 4GB፣ 2 የኮምፒውተር ስፒከር፣ 2 ላፕቶፕ ኮምፒዩተር፣ 3 በለ 32GB ፍላሽ ዲስክ፣ 1 መካከለኛ ወንበር፣ 1 ሌኖቮ ላፕቶፕ፣ 1 IPAD AIR 2 TOUCHID 1 ሳምሰንግ ታፕ Tab A ንብረቶቹ በሠራተኞች እጅ ላይ ያልተገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ሰኔ 2009 የባለስልጣን መ/ቤቱ የቋሚ እና አላቂ ንብረት ቆጠራ የተካሄደ በቆጠራው መግለጫ መሰረት 1 Insulator Rubber፣ 4 Oil filter፣ 10 7.00x16 አዲስ ጎማ፣ 1 Bar code scanner፣ 17 Screen protecter፣ 13 middle chair፣ 14 conference chair፣ 1Expert Table፣1 Conference table፣ 1 Managerial table፣ 1 Guest Chair፣ 1 insulator exhaust pipe 15 ባለ ብር 50 የሞባይል ካርድ በገንዘብ ብር 712.50

እንዲሁም 242 ባለ ብር 100 የሞባይል ካርድ በገንዘብ ብር 22,900.00 በጉድለት የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ነቀምት ቅ/ጽ/ቤት</u>

አንድ ታብሌት ኮምፒውተር በጉድለት የተገኘ መሆኑ፤

ስለሆነም በጉድለት የተገኙ ንብረቶች እንዲተኩ እርምጅ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

10.5 ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች የታዩባቸው መቤቶች

<u>የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን</u>

በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) በተመለከተው መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባ ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ በቅድመ ታሪክ አርክኦሎጂ እና ፒሊዮንቶሎጅ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ቅርሶች የውሃ እና የሽንት ቤት ፍሳሽ እየተንጠባጠበባቸው መሆኑ፣ ከህንፃው እየተላጠ የሚወድቀው ፍርስራሽ የሚገኝ መሆኑ የኤክስሬይ ክፍል የነበረው በሽንት ቤቱ ፍሳሽ ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፡ በተጨማሪም በዋናው የጎብኝዎች ሙዚየም የሚገኙት ቅርሶች የንጽህና ጉድለት የሚታይባቸውና በአቧራ የተሸፈኑ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ ስለሆነም ለመንግስት ንብረት ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ዋና መ/ቤት</u>

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ሀምሌ 19/2008 በቁጥር 6/ወስሚ/ሰጠ-75/16 ለኢትዮጵያ ወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ በፃፈው ደብዳቤ የአካዳሚውን እና የማእከሉን ግንባታ እና ቋሚ እቃዎች የያዘ 17 ገፅ የርክክብ ሰነድ የላከ ቢሆንም ከተገለጹት ንብረቶች ውስጥ የገንዘብ መጠናቸው ብር 16,307,028.87 የሆኑ የቢሮ መገልገያ ተንቀሳቃሽ እቃዎች እና ዋጋቸው ያልተጠቀሱ የጂምናዚየም እቃዎች እና ወርክሾፕ ያሉ የጅምናዚየም እቃዎች(መሳሪያዎች)፣ ቋሚ እቃዎች ርክክብ ሳይፈጸምባቸው አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ መሆኑና ንብረቶቹ በትክክል ለመኖራቸው ተረጋግጦ በፌደራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የንብረት ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር በቀን 13/6/09 በደብዳቤ ቁጥር 6/ወስሚ/ስጠ-75/16 በተፃፈ ደብዳቤ ሚኒስትር መ/ቤቱ የአካዳሚውን ጠቅላላ ግንባታ አጠናቆ የመጨረሻ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን ጠቅሶ 200m3 የውሀ ዋና እና 2-ጄነሬተሮች ርክክብ እንዲፈፀምባቸው የጠየቀ ቢሆንም አካዳሚው የንብረት ርክክብ ያልፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በስፖርት አካዳሚው ርክክብ የተፈፀመባቸው የተሟላና ዘመናዊ የሲኒማ ቤት እና 12 ሱቆች ያለምንም አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣

<u>የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ አሰላ በሚገኘው ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማዕከል</u>

- ከወጣቶችና ስፖርት ሚኒስትር ባለ 1.50 ሜትር 24 ሞዝቮልድ አልጋ፣5 ባለ ሜትር ሞዝቮልድ አልጋ፣73 ባለ 2 ሜትር የብረት መደርደር፣30 ቁመቱ ረጅም የምግብ ቤት ትንሽ ጠረጴዛ፣118 መካከለኛ የምግብ ቤት ጠረጴዛ፣5 የምግብ ቤት ወጥ መስሪያ

ጉልቻ፤5 የምግብ ቤት የእንጀራ መጋገርያ ጉልቻ ያለምንም ርክክብ በስፖርት ማዕከሉ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- በአራት ካርቶን የተቀመጡ 19 ተገጣጣሚ ባለቆዳ የእንግዳ መቀመጫ ወንበሮች፤ አንድ ተሽከርካሪ ወንበር፤አንድ የአዳራሽ ወንበር ያለምንም ርክክብ በስፖርት ማዕከሉ ተከማችቶ የሚገኙ መሆኑ፤
- ከግዢ ትእዛዝ በላይ የገቡ 21 የእቃ መደርደርያ(ሼልፎች) በጂምናዚየም አዳራሽ የሚገኙ መሆኑና ምንም አይነት ህጋዊ ርክክብ በስፖርት ሚኒስቴሩና በስፖርት አካዳሚው ያልተፈፀመባቸው መሆኑ፡
- የኢፌዲሪ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ሀምሌ 19/2008 በቁጥር 6/ወስሚ/ሰጠ-75/16 ለኢትዮጵያ ወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ በፃፈው ደብዳቤ የአካዳሚውን እና የማእከሉን ግንባታ እና ቋሚ እቃዎች የያዘ 17 ገፅ ሰነድ እና እንዲሁም የመጨረሻ ክፍያ የተፈፀመበትን የክፍያ ሰርተፍኬት አያይዞ የላከ መሆኑን ቢገልፅም የስፖርት ማእከሉ የቋሚ ንብረት ምዝገባ ያላከናወነ መሆኑ፤
- ስለሆነም መተካት ያለባቸው ንብረቶች እንዲተኩ እንዲሁም ርክክብና ምዝገባ ያልተደረገላቸው ንብረቶች በአግባቡ ርክክብ ተደርጎ መመዝገብ እንደሚኖርበት የስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

<u>የቤተመንግስት አስተዳደር</u>

የፈረስ ስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት የውስጥ አሰራሩ በሚታይበት ወቅት፡-

- ለእያንዳንዱ ፈረስ ለመለያነት የሚያገለግል ቁጥር (ታግ) የሌለው መሆኑ፤
- ለግለሰብ ፈረስ የጋጣ ኪራይ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን የመቆጣጠሪያ ዘዴ ያለመኖሩ፤
- ለፈረስ ስፖርት አባላት አባል ስለመሆናቸው መለያ (መታወቂያ) የሌላቸው እና ወርሀዊ ክፍያውን መከታተያ የሌለ መሆኑ፤
- የባልደራስ አክስዮን ማህበር የሰረገላ አገልግሎት በሚፈልጉበት ወቅት የአገልግሎት ጥያቄ በስልክ የሚቀርብ በመሆኑ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

በፈረስ ስፖርት መዝናኛ ላይ አስተማማኝ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ ሆኖ በአፈጻጸሙ ላይ ወቅታዊ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚገባው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን</u>

- የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ መሂ/1፣ የወጪ ማስመስከሪያ እና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ደረሰኞች በስቶክ ካርድ ተለይተው የማይመዘገቡ መሆኑ እንዲሁም ከባለፈው ዓመት የዞረ፣ በበጀት ዓመቱ ወደ ንብረት ክፍል ተገዝተው የገቡ ወይም ወደ ሂሳብ ክፍል የተላለፉና ከወጪ ቀሪ ያለውን በቀላሉ ማመዛዘን አለመቻሉ፤
- ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው እቃዎች ለምሳሌ ቪድዮ ካሜራ እንደ ሞዴላቸው ተለይቶ ስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለአግልግሎት ሲወጡ እና ተመላሽ ሲደረጉ መለያ/ሴርያል ቁጥራቸው የማይመዘገብ መሆኑ፤
- ለመ/ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊዎች ለአገልግሎት የተሰጡ ዲስክቶፕ ኮምፒውተሮች፣ ቴሌቪዥኖች ስቶክ ካርድ ላይም ሆነ የተጠቃሚዎች ካርድ (UC) ላይ ሴርያል ቁጥራቸው የማይመዘገብ መሆኑ፤

<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር</u>

- የቴአትር ቤቱ ቋሚ ንብረት የባህላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- ታሪካዊ የቴአትር ልብሶች ፣ የሮማውያን ብረታ ብረቶች፣የሮማውያን ኮፊያዎች ፣ የጦር መሳሪያዎች እና ለቴአትር መስሪያ የሚያስፈልጉ የተለያዩ መሳሪያዎች ለአገልግሎት ሲወጡና ተመላሽ ሲደረጉ መከታተያ መዘክር ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፣

10.6 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም

የመ/ቤቶች የተሽከሪካሪ አጠቃቀም ሲታይ፤ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች በአባሪ -35 ዝርዝሩ ተመልክቷል/

<u>የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ</u>

የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-03102 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር በቡናና ሻይ ባለስልጣን ስም የተመዘገበ መሆኑ፤ኮድ 4-02893 የእጽዋት ዘር ኢንዱስትሪ ንብረት መሆኑ እና ኮድ4-0291 ሞተር ሳይክል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር</u>

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ዳይሬክተር የነበሩት አቶ ሰሎሞን ታደሰ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ንብረት የሆነውን ኒሳን ፓትሮል የሰሌዳ ቁጥር 4-14327 የሻንሲ ቁጥር

JNITCSY6IZ0573390 የሞተር TD42-210291 በትውስት የወሰዱ ቢሆንም ስራ አስኪያጁ ከስራ ሲሰናበቱ በትውስት ወስደው የነበረውን መኪና ያልመለሱ መሆኑ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ንብረቱን ለማስመለስ ምንም አይነት እርምጃ ያላደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም በብልሽት ምክንያት የቆሙት ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ መደረግ እንደሚኖርበት እንዲሁም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው/በሌላ መ/ቤት ስም ያለው ተገቢውን በመፈጸም በመ/ቤቱ ስም መዞር እንደሚኖርበት የስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

11.ልዩ ልዩ

11.1 የውስጥ ኦዲት

በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 ክፍል ሁለት ቁጥር 8/2 መሰረት የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የማደራጀትና በቂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያካበተ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ መመደብ እንዳለበት እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 በክፍል 5 ተራ ቁጥር 3 የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ማቅረቢያ የግዜ ሰሌዳ 1ኛ ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 30/2009፤ የሁለተኛ ሩብ አመት እስከ ጥር 30፤ የሶስተኛ ሩብ አመት እስከ ሚያዚያ 30 እንዲሁም የአራተኛ ሩብ አመት እስከ ነሃሴ 15 ድረስ መቅረብ እንደሚኖርበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የውስጥ ኦዲት ግምገማ ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከተው ተገኝቷል፡፡

የመ/ቤቱ ስም	በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የሰው ኃይል ያልተሟላ	በተወሰነው የጊዜ ገደብ/ወቅቱ ያልቀረበ ሪፖርት
የብሄራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ	✓	✓
የኢትዮጵያ ባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	✓	✓
የመንግስት ልማት ድርጅቶች ባለአደራቦርድ	✓	✓
የጨረራ መከላከያ ባለሥልጣን	✓	✓
የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ	✓	✓
የፌዴሬሽን ምክር ቤት	✓	✓
የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት		✓

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር		✓
የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ		✓
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር		✓
የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	✓	✓
የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን	✓	✓

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ስራውን በአግባቡ ለማከናወን እንዲረዳው በመዋቅሩ መሰረት የተፈቀደለት የሰው ኃይል እንዲሟላ እንዲሁም በመመሪያው መሰረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ኦዲቱ እንዲከናወን ጥረት ሊደረግ እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

11.2 በቅጥርና በዕድገት እንዲሞሉ ያልተደረጉ ክፍት የስራ መደቦች ስለመኖራቸው

በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ክፍል 3 ምዕራፍ 1 አንቀጽ 12 ተራ ቁጥር 1 መሰረት ክፍት የስራ መደቦች በቅጥርና በዕድገት ማሟላት እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት፤

የመ/ቤቱ ስም	ክፍት የስራ መደብ ብዛት	በመቶኛ
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	191	41%
የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	108	38.84%
ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል	25	26.8%
የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ	183	74 %
የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	79	63.2%
የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ	58	33.14%
የቤተመንግስት አስተዳደር	631	59%
የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	196	46%
የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ	289	46%
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር	287	42%
የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	121	43%
የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን	313	43%

ስለሆነም መ/ቤቶቹ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችላቸው ዘንድ ክፍት የስራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲሞሉ ማድረግ እንደሚኖርባቸው በላክነው ሪፖርት አሳእበናል፡፡

11.3. <u>የተጣራ ሀብት (Net Asset Equity Account)</u>

<u>ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚታይ መሆኑ</u>

<u>የትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል</u>

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 (2ለ) መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ይሁን እንጂ በኦዲት እንደተረጋገጠው ሰኔ 30/2009 የተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የተጣራ ሂሳብ (Equity Account) ብር 1,157,984.38 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ</u>

ሰኔ 30/2009 የተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የተጣራ ሂሳብ (Equity Account) ብር 333,683.48 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባህል ማዕከል</u>

ሰኔ 30/2009 የተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የተጣራ ሂሳብ (Equity Account) ብር 64,210.02 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስለሆነም እያንዳንዱ የሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት የስራ አመራን አሳስበናል፡፡

11.4 በህግ ትምህርትና ስልጠና ማሻሻያ ፕሮግራም ስር የሚሰጠውን የውጭ ትምህርት በተመለከተ

<u>የትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል</u>

ማዕከሉ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ስራውን ከትምህርት ሚኒስቴር ተረክቦ የሚያስተዳደር ሲሆን ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ተማሪዎች እና ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በገቡት ውል መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1. እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ዊርዊክ ዩኒቨርስቲ 37 የሁለተኛ ዲግሪ 13 የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች እንዲሁም አሜሪካን አገር ከሚገኘው አላባማ ዩኒቨርስቲ 19 ተማሪዎች በሁለተኛ ዲግሩ 4 ተማሪዎች በሶስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ቢገለጽም ትምህርታቸውን አጠናቀው የተመረቁት ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲማሩ ወደላካቸው ተቋም ወይም መ/ቤት በመመለስ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ለመስጠታቸው ማረጋገጫ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
2. እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ዊርዊክ ዩኒቨርስቲ አራት የሁለተኛ ዲግሪ አራት የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያቋረጡ እንዳሉ ተገልጿል፡፡ይሁን እንጂ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ተከፍሎላቸው ነገር ግን ትምህርታቸውን ባላጠናቀቁ ተማሪዎች ላይ የተወሰደ እርምጃ ለመኖሩ ማስረጃ ተጠይቆ ለኦዲት ሊቀርብ አለመቻሉ፣
3. ትምህርታቸውን አጠናቀው ከተመረቁ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን እንዲማሩ ወደላካቸው ተቋም ወይም መ/ቤት ያልተመለሱ እና የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ሳይሰጡ በገዛ ፍቃዳቸው የተሰናበቱ ሰራተኞች የስም ዝርዝራቸው እና ለትምህርት አገልግሎት የተከፈለላቸው ገንዘብና ሌሎች ወጪዎች የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ እንዲሁም በገቡት የግዴታ ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው የተወሰደ እርምጃ ለመኖሩ ማረጋገጫ ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
4. እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ዊርዊክ ዩኒቨርስቲ አንድ የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ እንዲሁም አሜሪካን አገር ከሚገኘው አላባማ ዩኒቨርስቲ ሁለት የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች አሁንም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ መሆኑ ተገልጿል፡፡ይሁን እንጂ እነዚህ ተማሪዎች ትምህርቱን ማጠናቀቅ በሚገባቸው ጊዜ ውስጥ ባለማጠናቀቃቸው ማዕከሉ ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ተከፍሎላቸው ነገር ግን ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ያቋረጡ ተማሪዎች እንዲሁም ትምህርታቸውን አጠናቀው ከተመረቁ ተማሪዎች መካከል ትምህርቱን እንዲማሩ ወደላካቸው ተቋም ወይም መ/ቤት ያልተመለሱ እና የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ያልሰጡ ተማሪዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ የስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

11.5 ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች

<u>የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ</u>

ጥሩ የስራ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ሰራተኞች በጥሬ ገንዘብ ብር 62,500.00 የማበረታቻ ሽልማት ክፍያ አለአግባብ የተፈጸመ በመሆኑ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ እንዲደረግ እና ለወደፊቱም ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ክፍያ እንዳይፈጸም ጥንቃቄ መደረግ እንደሚኖርበት አስተያየት ቢሰጥበትም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር</u>

በ2008 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት መካከል ሥራ ለለቀቁ ሰራተኞች ሥራ ላይ ላልተገኙበት ቀናት የተከፈለው ብር 3,875.87 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

<u>የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን</u>

- **ያለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል**

በባህር ዳር ከተማ፣ በአዳማ ከተማ እና በሃዋሳ ከተማ በተለያዩ ጊዜያት በተደረገው ስልጠና ላይ ለተገኙ ተሳታፊዎች ምሳ ቀርቦላቸው እያለ የሙሉ ቀን የውሎ አበል በድምሩ ብር 19,514.00 አላግባብ በመከፈሉ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገንዘቡ ተመላሽ አልተደረገም፡፡

- **የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት**

በተለያየ ክልል ለሚገኙ ቅርሶች ጥገናና እድሳት ፣ ለቀን ሰራተኞች ምንዳ እና እርዳታ ቀጥሎ በተዘረዘሩት የሂሳብ መደቦች በባንክ በኩል የተላከው ሂሳብ ብር 12,660,000.00 ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ደጋፊ የሂሳብ ሰነዶችና ማስረጃዎች በባለስልጣኑ ስለማይጠበቁና ማስረጃዎቹን ሊያቀርብ ባለመቻሉ ሂሳቡን በዝርዝር ኦዲት ለማድረግም ሆነ ለክልሎች የተላከው ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲረጋገጥ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ እርምት አልተደረገም፡፡

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት</u>

- የስልጠና አበል በማለት አላግባብ ከተከፈለው ውስጥ ብር 7,722.30 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

- በድርጅቱ ውስጥ በቦርድ የሚተዳደሩ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ከተፈቀደላቸው የሥራ ክፍሎች ውጪ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቀድ ለፋይናንስ ሠራተኞች፣ ለእለት ገንዘብ ተቀባይ፣ ለትራንስፖርት ስምሪት፣ ለግዥ/ን/አስ/ጠ/አገልግሎት ሰራተኞች በምሳ ሰአትና በእረፍት ቀናት ለሰሩበት በድምሩ ብር 76,982.82 አላግባብ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

በበጀት ዓመት የታዩት የተከፋይ ሂሳብ ከወጪ ቀሪዎች ወደ ቀጣዩ በጀት ዓመት በትክክል መተላለፋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በሂሳብ መደብ በ6174299 (የአደራ ሂሳብ) የተመለከተው ከወጪ ቀሪ እና በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በተደረገው መካከል የሚታይ ልዩነት ብር 25,374,426.75 ተጣርቶ የሂሳብ ማስተካከያ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት

በኢንስቲትዩቱ ወጪ ለትምህርት ወደ ተለያዩ ሀገራት በመሄድ የተማሩ ሠራተኞች ከኢንስቲትዩቱ ጋር በገቡት ውል መሠረት ወደ ሥራ ገበታቸው ተመልሰው ኢንስቲትዩቱን የማገልገል ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ብር 352,002.67 እና USD 151,058.65 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ ብር 278,788.50 እና USD 29,205.10 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 73,214.17 እና USD 121,853.55 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ

ለ45 ሾፌሮች የአራት ቀን አበል አላአግባብ የተከፈለ ብር 11,250 ተመላሽ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባህል ማዕከል

- ሰራተኞች ከመስክ የተመለሱበት ትክክለኛ ሰዓት በቅጽ ላይ ሳይሞላ ከመስክ ለተመለሱ የመ/ቤቱ ሠራተኞች በሙሉ ለእራትና ለአልጋ አለአግባብ በብልጫ ከተከፈለው ውስጥ ብር 1,370.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ለአንድ ተሳታፊ ከውሎ አበል በተጨማሪ ለአልጋ ብር 150.00 በመከፈሉ ተመላሽ እንዲደረግአስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር

1. ከመንግስት መመሪያ ውጭ የተከፈለ የትርፍ ሰአት ክፍያ ብር 15,048 ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
2. አላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል በድምሩ ብር 96,035.10 ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
3. አዚዝ አህመድ ኘሮሞሽን ለተባለ ድርጅት በ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ ዝግጅት ውስጥ ሳይካተት፤ ከድርጅቱ ጋር የተደረገ የስምምነት ውል ሳይኖር፤ የአገልግሎት ግዥ ጥያቄ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያቀርብ እና ስለሚከፈለው ገንዘብ በሚመለከት አስቀድሞ በመረጃ የተደገፈ የዋጋ ጥናት ሳይደረግ አላግባብ የተከፈለው ብር ሂሳብ 400,000.00 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
4. ከደንብና መመሪያ ውጭ ለውሎ አበልና ትራንስፖረት እንዲሁም ለአሰልጣኞችና አስተባባሪዎች በድምሩ ብር 448,681.90 አላግባብ ተከፍሎ የተገኘው ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
5. በመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ከወጣው ታሪፍ በላይ በብልጫ የተከፈለ የትራንስፖርት ሂሳብ ብር 38,131.65 ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
6. ከአገር ውጭ ለስራ ጉዳይ ለወጡ ሰራተኛ ከተከፈለው የውሎ አበል ውስጥ ተመላሽ መደረግ ያለበት 339.66የአሜሪካ ዶላር (ብር 7,536.68) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
7. በመደበኛ የስራ ቦታ ለተሰሩስራዎች ለውሎ አበል የተከፈለ በድምሩ ብር 152,000.15 ለትርፍ ሰዓት ስራ ለተፈጸመ ክፍያ ብር 199,174.75 በመ/ቤቱ በተዘጋጀው የኦዲት መርሃ ግብር ላይ እርምጃ እንደተወሰደ ቢገለጽም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ (የ2007 በጀት ዓመት ኦዲት)

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት

- ለመልካ ቁንጥሬ እና ለፋሲል ቤተመንግስት እድሳት ብር 2,276,002.43 በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም ስራው ለመሰራቱም ሆነ ገንዘቡ ለታቀደለት ዓላማ ለመዋሉ ደጋፊ የክፍያ ሰነዶችና አግባብነት ያላቸው የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት

አልመቅረቡ የተጠቀሰ ሲሆን ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ለብር 1263839.48 ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ለቀሪው ብር 1,012,163.00 ማስረጃ አልቀረበም፡፡

- በተለያዩ 4 የወጪ ማስመስከሪያ ላይ ከተወራረደው ብር 398,489.30 ውስጥ ብር 115,837.06 በማተሚያ ቤት ያልታተመና ተከታታይ ቁጥር በሌለው ነጭ ወረቀት ሂሳቡ ተወራርዶና በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ

- በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በ 4 የተለያዩ የወጪ ቫውቸሮች የእቃና የአገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈፅም ከተከፋይ ላይ ብር 931.53 ዊዝሆልዲንግ ታክስ ቀንሶ ያላስቀረ በመሆኑ ያልተሰበሰበው ዊዝሆልዲንግ ታክስ ተሰብስቦ ለመንግስት ፈሰስ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ አለመወሰዱ፣
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በኩል በተሰጠ ካርታ ስራ ስልጠና ላይ የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ሰራተኞች ለ13 ቀን በብር 195.00 ሂሳብ (13*195*3) የተከፈለው ብር 7,605.00 ተመላሽ አለመደረጉ፡፡

የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት

- የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከተሾሙበት ቀን መስከረም 25/2008 ዓ.ም ጀምሮ በድምሩ ብር 3,780.36 ከደመወዝ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ የውጪ ሀገር ህክምና መዋጮ፤
- በ2008 በጀት ዓመት ለቤት አበል ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ከተከፈለው የቤት አበል ላይ በድምሩ ብር 10,972.50 የሥራ ግብር ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- በትርፍ ሰአት ከሚያሰራቸው ሰራተኞች ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ የስራ ግብር ብር 110,068.49 ላይ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

የቤተመንግስት አስተዳደር

- 4202 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 27,025.73 እንዲሁም በ4274 የሂሳብ አርዕስት ብር 8,288,747.56 (ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ) በወቅቱ ያልተሰበሰበ ሂሳብ በመገኘቱ በተሰብሳቢ ሂሣቦች ላይ ተገቢው ክትትል እየተደረገ በወቅቱ እንዲሰበሰቡና ሊወራረዱ የማይችሉ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በተመለከተ ደግሞ በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ አልተተካም፣

- በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 8/5 ለእያንንዱ የተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት ክትትል ማድረግ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ሆኖም ብር 1,471,036.74 ከግንባታ ክፍያ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገ የመያዣ ሂሳብ ገንዘቡን ያስያዘው የህንፃ ተቋራጭ ስም እና ያከናወነው ግንባታ ወይም የፕሮጀክቱ ዓይነት የሚገልጽ ተቀጽላ ሌጀር የሌለ በመሆኑ ለቁጥጥር እና ለክትትል እንዲያመች ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የተያዘ የመያዣ ሂሳብ ገንዘቡን ያስያዘው የህንፃ ተቋራጭ ስም እና ያከናወነው ግንባታ ወይም የፕሮጀክቱ ዓይነት ጊዜው ተቀጽላ ሌጀር በመክፈት ዝርዝር መረጃው ተመዝግቦ ሊያዝ እንደሚገባ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፣
- የንብረት ሥራንና ንብረት ገቢና ወጪ የማድረግ ኃላፊነት የፈረስ ስፖርት አሰልጣኝ ከዋና ስራቸው በተጨማሪ ስራውን ደርበው እንዲሰሩ የተደረገ መሆኑ፣
- በዋናው ቤተ መንግስት አስተዳደር ለሚገኙት ለውድ ጌጣጌጦቹና ቅርሳ ቅርሶቹ ለእያንዳንዳቸው የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ በቅርስ ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 209/92 ወይም በፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1.ሀ እና ረ መሰረት ተመዝግበው በየዓመቱ ቆጠራ እየተደረገ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፣
- በዋናው ቤተ መንግስት አስተዳደር የሚገኙት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ተሽከርካሪዎች ተለይተው ተጠግነው ለአገልግሎት እንዲበቁ፣ በቅርስነት ሊጠበቁ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች በባለሙያ እንዲለዩ እና ሊወገዱ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች ደግሞ በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፤

<u>የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ</u>

- የኤጀንሲው ሠራተኞች ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በበዓላት ቀንና በምሽት ለሰሩበት በሚል ከውል አበል የክፍያ መመሪያ ውጭ ብር 99,961.95 ለውል አበል አላግባብ የተከፈለ በመሆኑ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፡፡

የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት

- ለሥራው ተጨማሪ የሞባይል ካርድ እንዲወስዱ ከተፈቀደላቸው ሠራተኞች ውጭ ብር 2,150.00 የሞባይል ካርድ የወሰዱ መሆኑ፣
- ለሥራው ተጨማሪ የሞባይል ካርድ እንዲወስዱ ከተፈቀደላቸው መጠን በላይ ብር 300.00 የወሰዱ መሆኑ፣
- የሞባይል ካርድ እንዲወስዱ ከተፈቀደላቸው ዝርዝር የሌሉና ከስራው ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው በማመልከቻ በጠየቁት መሠረት ብር 1,800.00 የወሰዱ መሆኑ፣ እና ከኢንስቲትዩቱ ሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች ብር 775.00 የሞባይል ካርድ የወሰዱ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 5,025.00 አላግባብ የተከፈለ በመሆኑ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፡፡

የፕሬዚደንት ጽ/ቤት

በሂሳብ መደብ 4202 የተመለከተው ብር 12,697.87 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ሳይተካ ከአምስት ዓመት በላይ የቆየ በመሆኑ ሊሰበሰብ የማይችል መሆኑ ከተረጋገጠ በፋይናንስ ደንቡና መመሪያው መሠረት እንዲሰረዝ አስፈላጊው ክትትል መደረግ እንዳለበት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

ስለሆነም በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ አለመውሰድ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ ለግኝቶቹ መርሃግብር በመቅረጽ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ
መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን፣

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት፡-

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዕቅድና ክንውን፣

1.1 **የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር፣**

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	358,704,422.25	439,865,465.62	798,569,887.87
2	የመቱ ዩንቨርስቲ	5,776,497.02	-------	5,776,497.02
3	የቦንጋ ዩኒቨርስቲ	3,561,000.00	-------	3,561,000.00
4	የአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	603,300,398.40	380,545,001.00	983,845,399.40
5	የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ	79,070,948.89	-----	79,070,948.89
6	የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	32,759,612.72	67,795,941.19	100,555,553.91
7	የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	277,096,425.59	672,121,735.47	949,218,161.06
8	የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ	295,052,141.66	406,000,000.00	701,052,141.66
9	የወልድያ ዩኒቨርሲቲ	316,221,363.20	399,734,072.84	715,955,436.04
10	የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	46,532,899.16	44,239,559.01	90,772,458.17
11	የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር	187,835,904.50	-----	187,835,904.50
12	አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ	406,325,380.00	734,000,000.00	1,140,325,380.00
13	ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ	348,612,176.48	549,969,744.00	898,581,920.48
14	ወራቤ ዩኒቨርሲቲ	8,869,300.00	--	8,869,300.00
15	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን	35,549,430.00	--	35,549,430.00
16	ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ	360,246,818.95	--	360,246,818.95

17	ፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል	26,959,620.00	--	26,959,620.00
18	እንስሳት መዲሀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን	59,631,502.58	--	59,631,502.58
19	የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት	132,507,880.00	180,226,000.	312,733,880.00
20	የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	50,881,152.00	1,236,420.00	52,117,572.00
21	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ	226,666,200.00	158,121,000.00	384,787,200.00
22	አዲግራት ዩኒቨርሲቲ	392,768,068.88	500,000,000.00	892,768,068.88
23	የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት	54,973,950.96	27,587,854.00	82,561,804.96
24	ሣይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር	130,563,550.00	147,293,608.24	277,857,158.24
25	የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት	61,508,023.63	13,870,600.00	75,378,623.63
26	አሶሳ ዩኒቨርሲቲ	265,578,636.53	344,769,880.00	610,348,516.53
27	ደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ	38,325,000.53	------	38,325,000.53
28	የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	26,771,680.00	20,000,000.00	46,771,680.00
29	የፍትሕና የህግ ሥርዐት ምርምር ኢንስቲትዩት	14,567,639.23	-----	14,567,639.23
30	ብሔራዊ የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ መከላከያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት	47,048,359.56	2,500,000.00	49,548,359.56
31	የምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	48,160,268.60	6,342,200.00	54,502,468.60
32	ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	135,077,287.00	95,317,900.00	230,395,187.00
33	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር	40,455,496.15	----	40,455,496.15
34	የአካባቢ፤የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚ/ር	99,152,441.76	----	99,152,441.76
ድምር		**5,217,111,476.23**	**5,191,536,981.37**	**10,408,648,457.60**

1.2 የተሰጠው የኦዲት አስተያየት፣

- ነቀፌታ የሌለበት Clean Opinion - 2 መ/ቤቶች
- በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) -17 መ/ቤቶች
- ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች (Disclaimer opinion- 16 መ/ቤቶች

ናቸው፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-1 ተመልክቶል፡፡/

1.3 የድርጊት መርሐ ግብር የተጠየቁ መ/ቤቶች

መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ምላሽ የሰጡ

- የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ
- የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ
- የወልድያ ዩኒቨርሲቲ
- የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት
- አሶሳ ዩኒቨርሲቲ
- ሆቴሎችና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
- የአዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

1.3 ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣

1.3.1. የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ፣

1.3.1.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣

- **የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር፣** በመ/ቤቱ የፕሮጀክት ሂሳብ ገንዘብ ያዥ ስም የተያዘ የመደበኛ ሂሳብ ብር 13,873.15 እንዲሁም በግዥ ሠራተኛ ስም ብር 2,222.10 በድምሩ ብር 16,095.25 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- **የምግብ፣መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣**

የኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ የሂሳብ ሠራተኛ ለጥቃቅን ወጪዎች ከተረከቡት ብር 675.90 በጉድለት የተገኘ መሆኑ፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የጎደለውን ጥሬ ገንዘብ በአሽቸኳይ ከሚመለከታቸው አካላት ወይም ግለሰቦች ተመላሽ መሆን እንዳለበት እና የመንግሥትን ገንዘብ ከጥፋትና ከጉድለት ለመከላከል እንዲቻል ተቋሙ በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.1.2. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣

የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ፡-

- ከመመሪያ ውጭ በሳጥን መቀመጥ ካለበት በላይ የሰኔ 30/2009 ሂሳብ ሪፖርት ብር 256,073.78 በሳጥን የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ተቀምጦ መገኘቱ፣
- በዩኒቨርሲቲው "ቢ" ሂሳብ ቁጥር 10001711044158 ውስጥ ብር 7,481,706.59 ፈሰስ ሳይደረግ የሚገኝ መሆኑን፣
- ለመደበኛ የተፈቀደው በጀት በሰኔ 30 ሚዛኑ ዜሮ መሆን ሲገባው፣ የሰኔ 30/2009 ሂሳብ ሪፖርት በባንክ ያለ ገንዘብ ብር **1,932,793.46** የሚታይ ቢሆንም፣ የባንክ ስቴትመንት ላይ ምንም ገንዘብ የማይታይና ዜሮ ሚዛን ሲሆን፣ ሪፖርቱ እና ባንክ ስቴትመንቱ የማይጣጣም መሆኑን፣
- በሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ቋት ሚዛን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ ተዘጋጅቶ የማይመዛዘን መሆኑን፣
- በሳጥን የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ በየጊዜው ተቆጥሮ በሂሳብ ክፍል ከሚያዘው የጥሬ ገንዘብ ቋት ጋር መመዛዘን ቢገባውም ተቆጥሮ የማይመዛዘን መሆኑን፣
- **በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ** በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በ z ባንክ ሂሳብ ብር 14,495,060.20 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ፣**በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣**
- ከተለያዩ ገቢዎች የተሰበሰበ ገንዘብ ብር 70,712.04 የባንክ ገቢ ደረሰኝ ያልተያያዘለት መሆኑ፣
- በውስጥ ገቢ የተሰበሰበውን ገቢ በድምሩ ብር 3,200,050.17 በየዕለቱ ወይም በሚቀጥለው ቀን ወደ ባንክ ገቢ ሳይደረግ የቆየ መሆኑ፣
- በአዲግራት ዩኒቨርስቲ
- በውስጥ ገቢ የተሰበሰበውን ገቢ በድምሩ ብር 274,087.42 በየዕለቱ ወይም በሚቀጥለው ቀን ወደ ባንክ ገቢ ሳይደረግ የቆየ መሆኑ፣

- በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ በባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው በድምሩ ብር 521,920.86 ከሳጥን ወጪ ሆኖ የተከፈለ መሆኑ፣
- በቴክኒክና ሙያ ት/ሥ/ኤጀንሲ ለተቀጠሩ የውጪ አገር ዜጎች ደመወዝ ሲከፈል በባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው በድምሩ ብር 1,633,462.02 በጥሬ ገንዘብ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡
- በደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ዩኒቨርስቲው በቼክ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፣ በድምሩ ብር 12,026.10 ከሳጥን ወጪ ሆኖ ክፍያ መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- በሂሳብ ሪፖርት በሳጥን የታየው የገንዘብ መጠን ተጣርቶ ወደ ባንክ ገቢ መደረግ አለበት፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይከሰት ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ በሳጥን እንዳይያዝ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡
- ማንኛውም የተሰበሰበ ገቢ በልዩ ሁኔታ ተቋሙ እንዲጠቀምበት ከተፈቀደው እና በመደበኛ በጀት እንዲጠቀሙ ከተፈቀደው በስተቀር ተራፊ በጀት በመመሪያው መሰረት ወደ መንግስት ፈሰስ መደረግ አለበት፡፡
- የፋይናንስ ክፍሉ በየጊዜው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እያደረገ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ሠርተፊኬት የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡ የሥራ ክፍሉ የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ማዘጋጀት አለበት፡፡
- በአጠቃላይ እያንዳንዱ ተቋም ወይም መ/ቤት የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ የፋይናንስ ስርዓቱን ተከትሎ መስራት ይኖርበታል፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይከሰት እያንዳንዱ መ/ቤት ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>፣

2.1 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ

በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በሃያ አምስት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 510,191,429.81 ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ቀጥሎ በአባሪ-6 ቀርቧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም ተሰብሳቢ ሂሳብ በመንግስት መመሪያና ደንብ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪም በግለሰቦች እና በድርጅቶች እጅ የሚገኝ ተሰበሳቢ ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.2 **በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች፣**

- የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ በሂሳብ መደብ 4251 ለስራ ተቋራጮች የተያዘ የተሰብሳብ ሂሳብ ለያንዳንዱ ስራ ተቋራጮች የተከፈተ ተቀጽላ ቋት የሌለው በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፡፡
- የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሠሌዳ ቁጥር 4-14032 ጥገና እንዲደረግ ለኢትዮጵያ መድህን ድርጅት በጠየቀው መሠረት ድርጅቱ ባወጣው ጨረታ ዝቅተኛ ዋጋ ብር 926,473.72 ባቀረበው አሸናፊ ጋራዥ ጥገናው እንዲደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢያሳውቅም፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሞኤንኮ ጋራዥ እንዲጠገን በማስደረጉ ብር 1,498,573.36 እንዲከፈልና በልዩነት የሚታየውን ብር 572,099.64 የኢንሹራንስ ሽፋን እያለ ያለአግባብ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ካዝና በመብለጥ ተከፍሎ መገኘቱን፣
- የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ በመክፍቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተሰብሳቢ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት/ ሌጀሮች/ ብር 85,385,942.96 አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ፣
- የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 15,119,420.00 የተሰብሳቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል።
- የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተሰብሳቢ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት /ሌጀሮች/ ብር **11,129,206.79** አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ሂሳቡ የሚታይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 20,567,984.09 በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በተቀጽላ ሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ፣

- የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት በድምሩ ብር 2,485,585.48 በተሰብሳቢ ተይዞ መገኘቱንና ክፍያው ለመፈፀሙ ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቀረበው የተሰብሳቢ ሂሳብ መግለጫ በሂሳብ መደብ 4210 ከተያዘው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 21,460,692.49 መወራረዱ ቢገለፅም ማስረጃው ባለመቅረቡ ለማረጋገጥ አለመቻሉን፣
- ቴክኒክና ሙያ ት/ሥ/ ኤጀንሲ ብር 3,721,426.36 በተቀፅላ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ሂሰብ ከማን እንደሚሰበሰብ ባለቤቱ ተለይቶ ዝርዝር መግለጫ/ኤጂንግ አናላይስስ/ መቅረብ አለበት፡፡ ማስረጃ የለሌላቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተጣርቶ ለእያንዳንዱ ተቀጽላ ሌጀር ተከፍቶለት ከማን እንደሚሰበሰብ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ ተሰብሳቢ በትክክለኛው የሂሳብ ሚዛን ተመዝግቦ ሪፖርት መሆን አለበት፡፡

3. <u>የገቢ ሂሣብ</u>፣

3.1 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ</u>፣

- የወልቂጤ ዩኒቨርስቲው በውሉ መሠረት ዕቃውን ላዘገዩ ድርጅቶቹ ባለመቅጣቱ ገቢ መሆን የነበረበት የቅጣት ሂሳብ በድምሩ ብር 7,406.09 ገቢ ሳይሆን መገኘቱ፣
- የመቱ ዩኒቨርስቲ በውሉ መሠረት ዕቃውን ላላቀረቡና ላዘገዩ ድርጅቶች ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት በድምሩ ብር 29,657.39 የጉዳት ካሳ ገቢ አለመደረጉ፣
- የቦንጋ ዩኒቨርስቲው በውሉ መሠረት ዕቃውን ላዘገዩ ድርጅቶቹ መቅጣት ሲገባው እና ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት የቅጣት ሂሳብ በድምሩ ብር 44,737.25 ገቢ ሳይሆን መቅረቱ፣
- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች መከፈል የነበረበት የጉዳት ካሳ ብር 334,650.15 ተቀንሶ ገቢ አለመደረጉን፣
- የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ዩኒቨርስቲው ውስጥ ከተከራዩት ሰባቱ ማህበራት በውላቸው መሰረት በየወሩ የሚጠበቅባቸውን ወርሃዊ ኪራይ በድምሩ ብር 61,159.00 ያልተሰበሰበ መሆኑን፣

- የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ በግቢው ውስጥ የሚገኙትን የመመገቢያ ቤቶችን እና የኮንቴነር ሱቆች ለተለያዩ አገልግሎቶች በውል ያከራየ ቢሆንም በድምሩ ብር 22,215.47 ያልሰበሰበ መሆኑን፣

የወልድያ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ከሚመለከታቸው የተለያዩ ድርጅቶች እና ሰራተኞች መሰብሰበብ የነበረበትን የቅጣትና የኪራይ ገቢ በድምሩ ብር 2,853,542.37 ያልሰበሰበ መሆኑን፣
- ዩኒቨርስቲው በድምሩ ብር 294,581.03 ከተለያዩ አቅራቢዎች ላይ የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በብር 136,620.46 የተለያዩ አዋጆችና መመሪያዎች ለማሳተም ከMaster print (Mo) በ02/03/2009 ውል የገባና በውሉ መሠረት ዕቃውን የማሰረከቢያ ቀን ህዳር 10/2009 ሲሆን፣ በሞዴል 19 ቁጥር 234025 ገቢ የሆነው በ24/05/2009 ያለቅጣት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑና ውል ከገባበት ጊዜ በላይ ላዘገየበት 136,620.46 *1/1000*73= ብር 9,973.29 የጉዳት ካሳ ያልተቀነሰ መሆኑ፣
- የእንስሳት ውጤቶች፣ መድሀኒትና መኖ ጥራት ቁጥጥር ምርመራ ማዕከል በብር 125,436.14 ለቢሮ መገልገያ አገልግሎት የሚውል ፋይል ካቢኔትና የተለያዩ ተዛማጅ ዕቃዎች G.S.Y GENERAL WOOD WoRK PRODUCTION በ19/08/2009 ውል የገባና በውሉ መሠረት ዕቃውን የማሰረከቢያ ቀን ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ በ20 ቀናት ውሰጥ በ08/09/2009 ሲሆን፣ በሞዴል 19 ቁጥር 861051 ገቢ የሆነው በ21/10/2009 በመሆኑ ያለቅጣት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑና ውል ከገባበት ጊዜ በላይ ላዘገየበት 125436.14 *1/1000*41= ብር 5,142.88 የጉዳት ካሳ ያልተቀነሰ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 15,116.17 ያለቅጣት የተከፈለ መሆኑ፣

የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት የወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 0795980 የማሰተማሪያ እቃዎች ግዥ ከኤም ኤም አሰመጪ ዕቃው ተገዝቶ ክፍያ ተፈፅሟል ሆኖም ድርጅቱ ውል ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር 90 ቀናት ውሰጥ ዕቃውን ለማቅረብ ቢሰማማም አቅራቢው ዕቃውን የሚያቀርብበት የመጨረሻ ቀን ነሐሴ 24/2008 ሆኖ ውል የተፈረመው 25/09/2008 ዕቃው በሞዴል 19 ገቢ የሆነው ያለቅጣት

07/02/2009 በመሆኑ፡፡ ውል ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በላይ ላዘገየበት ብር 239,556.50*1/1000*41 = ብር **9,821.81** የጉዳት ካሣ ያልተቀነሰ በመሆኑ፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ሳይሰበሰብ የቀረው የኪራይ ይሁን የጉዳት ካሳ እና ሌሎች ገቢዎች ተሰብስቦው በየመስራቤቶቹ ገቢ ሊደረግ ይገባል፡፡ በፍርድ ውሳኔ ያገኘ የመንግሥትም ገንዘብ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሰራተኞችና ግለሰቦች ተሰብስቦ ገቢ እንዲሆን የሥራ አመራሩ እርምጃ በመውሰድ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ማናቸውም የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ ሁሉምን የመንግስት መ/ቤት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በአግባቡ ተሰብስቦና ተመዝግቦ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊትም መሰል ስህተት እንዳይፈጠር ዩኒቨርሲቲው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

3.2 **<u>በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ፣</u>**

የተለያዩ ገቢ ሂሳቦች በሕጉ መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ20 መ/ቤቶች ብር 14,784,874.29 በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ተገኝቶል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቶል/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

መቀነስ ሲገባው ያልተቀነሰ የስራ ግብር፣ የቅድመ ክፍያ ታክስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ከሚመለከተቸው ሰራተኞች እና ነጋዴዎች ተሰብስቦ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይደገም የገቢ ግብር አዋጅ፣ መመሪያና ደንቦችን መሰረት ያደረገ አሰራር ሊከተል ይኖርበታል፡፡

3.3 **<u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ፣</u>**

- የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ከተከታታይ ትምህርት ለትምህርት ክፍያ ተማሪዎቹ ባንክ አስገብተው ባንክ አድቫይስ ሲያመጡ ሂሳቡ የሚመዘገብ ቢሆንም፣ ብር 33,894.50 ተመዝግቦ ባንክ ገቢ የተደረገው የባንክ አድቫይስ ድምር 34,228.50 በመሆኑ በልዩነቱ ብር 167.00 ያልተመዘገበ ገቢ መሆኑን፣

የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ፡-

- በድምሩ ብር 5,083,210.00 ለዩኒቨርሲቲው በገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረገው ገቢም ሆነ ወጪው በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ በመሆኑ

ገቢ የሆነው ገንዘብ በትክክል ለታለመለት ዓላማ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በተከታታይ የትምህርት ፕሮግራም ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች የሰበሰበውን በድምሩ ብር 638,123.00 የገቢ ሂሳብ ገቢም ሆነ ወጪው ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ እና ስለወጪውም የሚገልጽ ምንም ማስረጃ የሌለው መሆኑን፣
- ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ 567001-567050 ብር 909,742.78 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከመደበኛ ተማሪዎች የሚሰበሰበው የመመዝገቢያ ክፍያ ከአንድ ተማሪ በሴምስተር ብር 375.00 የሚሰበሰብ ሲሆን በናሙና ሲታይ ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት ከመደበኛ ተማሪዎች የሰበሰበው የመመዝገቢያ ክፍያ በድምሩ ብር 670,487.00 ገቢ ወደ መደበኛው ሂሳብ ገቢ መደረግ ሲገባ ወደ ውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ የተደረገ መሆኑ፣
- በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,765.90 በገቢ ያልተያዘና በበጀት ዓመቱ የየገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ ሁሉምን የመንግስት መ/ቤት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በአግባቡ ተሰብስቦና ተመዝግቦ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊትም መሰል ስህተት እንዳይፈጠር ዩኒቨርሲቲው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

3.4 ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ፣

- በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብር 8,064.57 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በወራቤ ዩኒቨርሲቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብር 4,603.25 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ በውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000021168355 ሰኔ 30/2009 በቀረበው የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ የሚታይ ብር 6,627,408.44 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣

- በደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ሰኔ 30 2009 የሂሳብ ሚዛን ላይ የሚታየው ብር 53,128.33 ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ፈሰስ ያልተደረገ ተራፊ የገቢ ሂሳብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- **ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ** የዩኒቨርሰቲው የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከአቅራቢዎች የሰበሰበውን ከተከፋይ ተቀናሽ (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብር 47,926.57 እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 216,145.83 በድምሩ ብር 264,072.40 ለገቢዎችና ጉምሩክ ሳያስተላልፍ በሪፖርት ተመዝገቦ የታየ መሆኑ ተረጋግጧል::

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ማናቸውም የመንግስት መ/ቤት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ፈሰስ ያልተደረገ የገቢ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ተመዝግቦ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊትም መሰል ስህተት እንዳይፈጠር ማንኛውም መ/ቤት ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

3.5 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ የገቢውን ትክክልኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፣</u>

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲው የሚሰበሰብ ገቢ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በባንክ በኩል የገባ ተብሎ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት በድምሩ ብር 11,296,938.37 የገቢው ዓይነት፣ ገቢው ከማን እንደተገኘ፣ የገቢው ምክንያት እንዲሁም የማስከፈያ ተመን/ታሪፍ ባለመታወቁ የገቢውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፣

- የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል በድምር ብር 429,379.50 ለተሰበሰበው የገቢ ሂሳብ የገቢ ተመን (ታሪፍ) የሌለው መሆኑ፣
- የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን በአሚሪካን ዶላር የሰበሰበውን የዕለቱን የብር ምንዛሪ የተመን መጠን የሚገልጽ ማስረጃ በተሟላ ሁኔታ ሳይቀርብ ብር 73,928.28 በደረሰኙ ለመሰብሰቡ የተገለጸ መሆኑ፣

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፡-

- የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የሂሳብ ምዝገባ ያልተከናወነ እና ሪፖርትም ያልተደረገ በመሆኑ ኦዲት ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የዲፓርትመንቱ ስም እና የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት፣ የክሬዲት ብዛት፣ የትምህርት ዘመን እና ክፍለ ጊዜው በገቢ ደረሰኙ የማይጠቀሰ መሆኑ፣

- በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ብዛት ያላቸው ከፋዮች ባንክ ገቢ ያደረጉት ገንዘብ በጥቅል በአንድ ነጠላ የገቢ ደረሰኝ ወይም ቅጠል የሚዘጋጅ በመሆኑ ተፈላጊ መረጃዎችን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች አባሪ በማድረግ ከገቢ ደረሰኝ ቅጠል ጋር የማይያዙ መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት ለዩኒቨርስቲው ሥራ አመራርና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ያልቀረበ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በባንክ የገባ ተብሎ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት በድምሩ ብር 77,860.00 የገቢው ዓይነት፣ ገቢው ከማን እንደተገኘ፣ የገቢው ምክንያት እና የማስከፈያ ተመን (ታሪፍ) ባለመታወቁ የገቢውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

የገቢ ደረሰኝ ተፈላጊውን ማስረጃ አሟልቶ እንዲይዙ አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች እና የማስከፈያ ተመን (ታሪፍ) አባሪ በማድረግ ከገቢ ደረሰኝ ቅጠል ጋር እንዲያያዙ መደረግ አለበት፡፡ ለወደፊቱም የእርምት እርምጃ በመውሰድ አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.6 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች፣</u>

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

- ለእያንዳንዱ ኮርስ በክሬዲት ሰዓት የተተመነ የማስከፈያ ዋጋ ተመን/ታሪፍ በቦርድ ጸድቆ በሠነድ መልክ ሳይኖር ከማታ፣ ከሳምንት መጨረሻ፣ ከክረምት እና ከርቀት ተማሪዎች ገቢ የሚሰበስብ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው በናሙና ከታየው የውስጥ ገቢ ከተለያዩ ድርጅቶች በቅጣት መልክ በድምሩ ብር 534,919.98 የሰበሰበው የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑን፣
- በ2009 በጀት ዓመት ከተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ መጠን በዝርዝር የሚገልጽ የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን እና የገቢ እቅድ ከክንውን ጋር በማነጻጸር ለመገምገም እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብሰብ በሚገባው መጠን የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፣
- የውስጥ ገቢ የሳጥን ቋት (ሌጀር) ክሬዲቱ በብር 1,013,853.78 ዴቢቱን በልጦ የሚታይ ሲሆን፣ የመደበኛ የሳጥን ቋት ደግሞ በዚሁ የገንዘብ መጠን ዴቢቱ ክሬዲትን በልጦ የሚታይ መሆኑን፣

- የውስጥ ገቢ የባንክ ቋት (ሌጀር) ዴቢቱ በብር 13,786,885.12 ክሬዲቱን በልጦ የሚታይ ሲሆን፣ የመደበኛው የባንክ ቋት ደግሞ በዚሁ የገንዘብ መጠን ክሬዲቱ ዴቢቱን በልጦ የሚታይ መሆኑና የመደበኛ እና የውስጥ ገቢ ሂሳብ በትክክል ተለይቶ በፋይናንስ ምንጩ ተመዝግቦ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣
- የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 10000149251368 በየወሩ መጨረሻ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ /Bank Reconciliation/ የማይዘጋጅ በመሆኑ የባንክ ሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የዉስጥ ገቢ ሂሳብ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ተደርጎ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ የማይሰራ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ በማጠቃለያ ደረሰኝ መሂ/64 ተጠቃሎ መመዝገብ ሲገባው ህጋዊነትና በሌለው ወረቀት በማሳተም በማጠቃለል በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ብር 652,674.49 የተመዘገበ መሆኑና በውስጥ ገቢ መመዝገብ ሲገባው፣ በፋይናንስ ምንጭ በመደበኛ በጀት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገቢ ከረዳት ገንዘብ ያዥ ወደ ዋና ገንዘብ ያዥ ሲተላለፍ በሞዴል 64 ገቢ አለመደረጉን ይልቁንም በነጭ ወረቀት የሚጠቃለል መሆኑንና በወቅቱም ወደ ባንክ ገቢ የማይደረግ መሆኑን፡-

የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ

- ዩኒቨርስቲ ከተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎት የሚሆኑ የኮንቴነር ሱቆችን በውል ያከራየውን የገቢ ሂሳብ ለዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ህብረት እንዲሰበስብ በመደረጉ መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ ብር 32,100.00 እንዳያገኝ ያደረገ አሰራር መሆኑንና ገቢው በህጋዊ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ከጨረታ ሰነድ ሽያጭና ከቅጣት የተሰበሰበ ገንዘብ በድምሩ ብር 1,262,179.87 ለገንዘብና ትብብር ሚ/ር ገቢ መደረግ ሲገባው፣ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ገቢ መደረጉ፣

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን፡-

- ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ለሚሰበስበው ገቢ የገቢ ዕቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ፣

- የሂሳብ ማስረጃ እያላቸው የተከፋይ ተቀናሽና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 66,519.39 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡

ዋቸሞ ዩንቨርስቲ

- ለማህበረሰብ /ሠራተኛ እና ተማሪ/ ግልጋሎት ለመስጠት የተቋቋሙ መዝናኛዎች /ካፍቴሪያ፣ ስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ ሬስቶራንቶች ወዘተ/ የሚገኝ ገቢ የውስጥ ገቢ እንደሆነ የሚገልጽ ቢሆንም፣ ከዩኒቨርሲቲው መደበኛ ገቢ ጋር በመቀላቀል ብር 67,200.00 በገቢ ተይዞ የተገኘ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድረጅቶች ግዥ ሲፈጽም ከተከፋይ ሂሳብ ለተቀነሰ ገንዘብ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 170,604.15 ደረሰኝ ሳይቆረጥለት መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት፣

- ለሚሰበስበው ገቢ የገቢ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡
- ብር 8,214,759.93 ከትምህርት ክፍያ፣ የጨረታ ማስያዣ፣ ለፈተና መፈተኛ፣ ለቅጣትና ከሌሎች የተሰበሰበ ገቢ ኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መደብ (Chart Of Account) መሰረት የሙያና የትምህርት ተቋም የሚሰበሰብ ገቢ 1443 እና ከልዩ ልዩ የተሰበሰበ ገቢ ደግሞ 1489 ተለይተው መመዝገብ ሲገባው፣ ገቢው በሂሳብ መደብ 1489 በጥቅል ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር መ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ የሚሰበሰበውን ገቢ በዕቅድ ያልያዘ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከላይ የተዘረዘሩትን በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ድክመቶች እያንዳንዱ ተቋም ወይም መ/ቤት የገቢ ደንቡን መመሪያ ተከትለው መስራት ይኖርባቸዋለው፡፡ ለወደፊቱም የእርምት እርምጃ በመውሰድ አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

4 <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

4.1 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ፣</u>

የወጪ ሂሳብ ትክክለ ኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ19 መ/ቤቶች ብር 46,362,033.19 የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቶል/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም ከላይ ከተዘረዘሩት የመንግስት መ/ቤቶች ማንኛውም ክፍያ ሲፈጽሙ ሂሳቡ መወራረድ ያለበት በእጅ የእጅ ሽያጭ ደረሰኝ እንዲሁም አስፈላጊ የሆንቱን ደጋፊ ሰኖዶችን በሙሉ ያማሏ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ለተጠቀሰው ሂሳብ ደረሰኝ እና ሌሎች ደጋፊ ሰኖዶችን እንዲቀርብ በማድረግና ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይደገም የስራ ክፍሉ ትኩረት ሰጥቶበት ክፍያ ሲፈጸም የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ እና ሌሎች ደጋፊ ሰኖዶችን እንድቀርብ ማድረግ ይኖርበታል

4.2 <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣</u>

የወጪ ሂሳብ በመንግስት የወጡትን ደንብና መመሪያ ተከትለው የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ19 መ/ቤቶች ብር 13,842,066.47 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣ ተገኝቶል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-19 ተመልክቷል/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈፀሙ ክፍያዎች እያንዳንዱ ተቋም ወይም መ/ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ተመላሽ እንዲደረግ እንዲሁም ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

4.3 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፣</u>

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሐ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ26 መ/ቤች ብር 30,317,650.23 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፣ ተገኝቶል፡፡/ ዝርዝሩ በአባሪ-21 ተመልክቶል/

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማናቸውም የዕቃ ሆነ የአገልግሎት ግዥ ማከናወን ያለበት የመንግስትን ግዥ ደንብና መመሪያ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱም መሰል ስህተቶች እንዳይከሰቱ መመሪያን የተከተለ ግዥ እንዲከናወን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.4 በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ እና በሪፖርት ያልተካተተ ወጪ፣

- የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ብር 2,808,873.09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ተመዝግቦ ወጪ የሆነ ገንዘብ በሂሳብ እንቅስቃሰ መዝገብ (TR) ያልተመዘገበ እና በሪፖርት ያልተካተተ መሆኑን፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ማንኛውም ክፍያ ሲፈጸም በወጪ ሰነድ በተመዘገበው የገንዝብ መጠን በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ተመዝግቦ ሪፖርት ካልተደረገ ወጪን ከመደበቁ በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነት ስለሚያሰጣ ጉዳዩ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምት ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ለወደፊት መሰል ስህተት እንዳይፈጣር ዩኒቨርሲቲው እያንዳንዱን የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

4.5 በናሙናው መሠረት ለመግባቱና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ የግዥ ክፍያዎች፣

- የመቱ ዩኒቨርስቲ ለውሃ መስመር ዝርጋታ በሚል ብር 4,000.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ግለሰቡ በውሉ መሰረት መስራቱን የሚገልጽ የባለሙያዎች የጹሁፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፣
- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 4,400,406.55 የተገዙ ዕቃዎች በናሙናው መሰረት ገቢ ስለመሆናቸው የቴክኒክ ኮሚቴ ያረጋገጠበት ደብዳቤ ከክፍያ ሰነድ ጋር ያልተያያዘ መሆኑን፣

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ

- ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ በጀት የሚገዛው የተማሪዎች የምግብ ግብዓት እና ዕቃ በየቀኑ በተዘጋጀ የርክክብ ቅጽ በየቀኑ በትክክል ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን፣ ቆጥሮና አስመዝኖ በየእለቱ ተፈራርሞ ማስገባት ሲኖርበት የብር 3,659,245.43 የጥራት ቁጥጥር ኮሚቴው ሳይፈራረም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ በማድረግ ብቻ ለአቅራቢዎቹ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው ግዥ ሲፈጽም ከዕቃ ጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴዎች (ከባለሙያዎች) ስለትክክለኛነቱ ማስረጃ ሳይቀርብ የብር 4,359,605.44 ንብረት ክፍል ገቢ ተደርገው ክፍያ ለአቅራቢዎች የተፈጸመ መሆኑን፣
- የፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት በኢንስቲትዩቱ የተገዙ የተለያዩ ዕቃዎች በተፈላጊው መስፈርት መሰረት ገቢ መደረጋቸው በባለሙያ ሳይረጋገጥ በጠቅላላ ብር 207,186.97 መከፈሉ ታውቋል፡፡
- አዲግራት ዩኒቨርሲቲ ብር 395,800.00 ክፍያ ሲፈፀም በውሉ /በስፔስፊኬሽን/ መሰረት አገልግሎቱ በትክክል ስለመሰጠቱ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈፅሞ መገኘቱ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም ክፍያ ሲፈጸም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ስራው በውሉ መሠረት መጠናቀቁን ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የጹሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊት መሰል ስህተት እንዳይፈጣር ማንኛውም መ/ቤት እያንዳንዱን የሂሳብ እንቅስቃሴዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

4.6 <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ፣</u>

- የወጪ ሂሳቦች በተከፈሉበት በጀት ዓመት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ13 መ/ቤቶች ብር 22,233,142.37 የበጀት ዓመቱን /2009/ ያልጠበቀ ወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቶል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-24 ተመልክቶል/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በበጀት አመቱ ለተፈቀደለት በጀት ለታለመለት አላማ ሊያውል ይገባል፡፡ ስለዚህ ከደንብና መመሪያ ውጪ የሚከፈል ክፍያ ተገቢነት እንደሌለው ተውቆ ለወደፊት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሊስተካከል ይገባል፡፡

4.7 <u>በብልጫ የተከፈለ፣</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በተገኘው አገልግሎት ልክ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ7 መ/ቤቶች ብር 398,240.09 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቶል፡፡/ዝርዝሩ ባሪ-20 ተመልክቶል/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ከተፈቀደው ተመን በላይ ወጪ ሆኖ ለተለያዩ ጉዳዮች መከፈሉ አግባብነት ስለሌለው የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ሆኖ ወደ መንግስት ካዜና ገቢ ሊሆን ይገባል፡፡ ለወደፊትም መሰል ስህተት እንዳይፈጠር ማንኛውም ክፍያ በደንብና መመሪያ መሰረት መከናወን አለበት፡፡

4.8 <u>በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች፣</u>

ወጪ ሆነው የተከፈሉት ሂሳቦች በተፈቢው የሂሳብ መደብ መመዝገባቸውን ለማጠራት ኦዲት ሲደረግ በ19 መ/ቤቶች ብር 7,538,717.94 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች፣ ተገኝቷል ፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-25 ተመልክቷል/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ መደባቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም ጥንቃቄ ሊደረግና ማንኛውም ክፍያ ሲፈፀም የመንግስት የክፍያ መመሪያዎች ተጠብቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.9 <u>በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተያዘ ሂሳብ፣</u>

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የገንዘቡ ልክ
1	የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	17,993,749.61
2	የእንስሳት መድሀኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን	657,700.90
3	የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት	381,400.06
4	አዲግራት ዩኒቨርሲቲ	1,024,678.44
5	የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	1,536,778.73
6	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	387,460.00
7	የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ	1,146,840.73
ድምር		**23,128,608.47**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም የሂሳብ ምዝገባ በሰነዱ ላይ ተለይተው በተመዘገበው ሂሳብ መደብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ ስለዚህ በተሰብሳቢ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበው የማስተካከያ እርምት ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ለወደፊቱ እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይሰራ በፋይናንስ ህግ መሰረት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

4.10 <u>በወጪ መያዝ ሲገባው በተከፋይ የተያዘ ሂሳብ፣</u>

- የኦዳ ቡልቱም ብር 451,489.15 በወጪ መመዝገብ ሲገባው፣ ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ በተከፋይ ሂሳብ በመንግስት መ/ቤቶች መካከል ሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ተመላሽ በ5028 ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ማንኛውም የሂሳብ ምዝገባ በሰነዱ ላይ ተለይተው በተመዘገበው ሂሳብ መደብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ ስለዚህ በወጪ መመዝገብ ሲገባው በተከፋይ ተመላሽ ሂሳብ የተመዘገበው የማስተካከያ እርምት ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ለወደፊቱ እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይሰራ በፋይናንስ ህግ መሰረት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

4.11 <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ፣</u>

- የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 808,550.35 ለመስተንግዶ የተከፈለው የወጪውን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተጠቃሚ ብዛት፣ የተጠቃሚዎች ስም ዝርዝር፣ ተጠቃሚዎቹ ከየት እንደመጡ እና ለመጠቀማቸው በፊርማ ያረጋገጡበት የሚያሳይ ማስረጃ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመያያዙ የወጪውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑን፣
- የኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 476,221.57 የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ ሲሆን የተከፈላቸው ሰራተኞች ስለመስራታቸው የሚገልጽ የሰዓት መቆጣጣሪያ ቅጽ ከወጪ ሰነዱ ጋር ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 1,365,037.28 በግዥ ሂደት ውስጥ እንዳለፈ እና በውስጥ የጨረታ ዘዴ እንደተጠቀሙ ሰነዱ ቢያመለክትም የግዥ ሒደቱን የሚገልፅ የመነሻ ሰነዱ እንዲቀርብልን በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሊቀርብልን ባለመቻሉ ስለትክክለኛነቱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሠራተኞች ለድጋፍ ወደ ተለያዩ ክልሎች ሲሄዱ በዕቅድ ጊዜ በሚዘጋጀው (TOR) እና የዓመት እቅድን በወር ብዛት መሰረት በማድረግ የክፍሉ ተጠሪ ስለቆይታው ማረጋገጫ ባላቀረበበትና በመስክ ሥራ መሆናቸው ሳይረጋገጥ የአንድ ባለሞያ ብር 32,052.15 የውሎ አበል ክፍያን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን፣

ዋቸሞ በዩኒቨርሲቲ፣

- በዩኒቨርሲቲው ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተለያዩ ኮርሶችን ለሚሰጡ ዶክተሮች ውል በመግባት ለእያንዳንዳቸው በወር ብር 40,000.00 በድምሩ ብር 428,100.00 ለተከፈላቸው ክሬዲት ሰዓቱ ባለመገለጹ በውሉ መሠረት ስለመከፈሉ የክፍያዉን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የሂሳብ ማወራረጃ ቅፅ 2 ላይ መሞላት የሚገባቸው ሠራተኛው ለጉዞ የተነሳበት እና የደረሰበት ሰዓትና ቀን እንዲሁም ለሥራ የቆየባቸው ቦታዎች ሳይሞሉ በተሰብሳቢ የተያዘውን የገንዘብ መጠን ብቻ በመውሰድ በድምሩ ብር 209,279.00 በዋናው ግቢ እና በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተከፍሎ በመገኘቱ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ ማስተካከያ (Adjustment) በሚል ብር 96,728,320.73 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ (JV) ላይ የማስተካከያ ሂሳብ ከማለት በስተቀር ማስተካከያ የተሰራለትን የወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር፣ ቀንና የገንዘብ ልክ በመጥቀስ ማጣቀሻ ስላልተፃፈበት ማስተካከያ የተደረገውን ወጪ እና የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 38,938,099.53 የወጪ ሂሳብ ሰነዶች በድምሩ ብር 135,666,420.26 ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሊቀርቡ አልቻለም፡፡
- **የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት** በኢንስቲትዩቱ ወጪ ለሆነው ብር 3,182,405.12 ገንዘቡ ወጪ ለመሆኑ የወጪ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- **የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ** ለውሎ አበል የተከፈለ ብር 127,956.00 ወጪ ለመደረጉ በክፍያ ማወራረጃ ቅፅ ሠራተኛው ለጉዞ የተነሳበት እና የደረሰበት ሰዓት ባለመገለፁ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

- ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ከመከፈሉ በፊት የሂሳቡ ትክክለኛነት እና የተሟላ ማስረጃ ሲቀርብና የሚያረጋግጥ ሲሆን ብቻ ክፍያ ይፈፀማል፡፡ የመንግሥት ገንዘብ ከጥፋት ለመካላከልና አላግባብ ወጪ እንዳይሆን እያንዳንዱ ተቋም ወይም የመንግስት መ/ቤት በጉዳዩ ላይ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ማንኛዉም ክፍያዎች ከመፈጸሙ በፊት የክፍያዉን ትክክለኘነት

የሚያረጋግጡ የተሟላ የክፍያ ምስክር(ደጋፊ ሰነድ) ከወጪ ሰነዶች ጋር መቅረቡን አረጋግጦ ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

4.12 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበበት ወጪ ሂሳብ</u>

- የኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማትኢንስቲትዩት ብር 71,128,769.99 ለአቅራቢው ድርጅት ሙሉ በሙሉ መከፈሉን ባንኩ ማረጋገጫ የሰጠ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ዕቃዎቹን በንብረት ገቢ ደረስኝ ሞ/19 ገቢ ተደርጎ ሂሳቡን ማወራረድ ሲገባው ያልተወራረደ መሆኑን፣
- የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ በብር 1,396,148.00 ብዛቱ 4 ኮንቴይነር የህክምና ዕቃዎች ከሁማን ብሪጅ በእርዳታ ለመጣ የትራንስፖርት ወጪውን ለድርጅቱ ሲከፍል ንብረቱ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡
- **የፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት** የመኪና መለዋወጫ ዕቃ (Fuel Pump) ለተገዛበት ብር 27,600.00 የተከፈለ ሲሆን፣ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልተቆረጠ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

እያንዳንዱ የመንግስት በ/ቤት ንብረቶቹ ለመግባታቸው የሚገልፅ ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ መፈፀሙ የመንግስትን የግዥ መመሪያና ደንብ ከመጣሱም በላይ አሰራሩ የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት የሚያጋልጥ ስለሆነ ክፍያ የተፈፀመባቸው ንብረቶች ገቢ ለመሆናቸው የሚገልፅ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይፈጠር ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.13 <u>በወጪ ያልተመዘገበ እና በሂሣብ መግለጫ ያልተካተተ፣</u>

- **የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት** በወጪ ያልተመዘገበ እና በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ብር 27,570.00 መገኘቱን፣
- **የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ** በበጀት ዓመቱ በወጪ ከተያዘው ሂሳብ ብር 4,396.50 በወጪ ያልተመዘገበና በበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ፣

የማሻሻያ ሀሳብ፤

በክፍያ ማስመስከሪያዎች እና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች በወጪ የተያዘ ሂሳብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እንዲመዘገብ እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት እንዲደረግ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.14 በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ፣

- የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 65,641.48 ወጪውን ያዘዘው ባለሥልጣን ስምና ፊርማ ሳይኖር ክፍያ መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ወጪዎች ከመፈጸማቸው በፊት በሚመለከተው ኃላፊ መፈረሙን መከታተልና ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለወደፊትም እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንደይደገም ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.15 ከተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ያልተፈፀመ ግዥ፣

- **የፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት** 3 የሳምሰንግ ኤልዲ ቴሌቪዥኖች ለተገዙበት ብር 81,000.00 የተከፈለ ሲሆን፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆነ አቅራቢ ግዥው መፈፀም ሲገባው በተርን ኦቨር ታክስ እንዲገዛ መደረጉ፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ግዥዎች በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.16 የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ፣

4.16.1 ሌሎች ከግንባታዎች ጋር የተያየዙ ችግሮች፣

- የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 8,664,065.70 ድርጅቶቹ የግንባታ ሥራ የተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ (Retention) በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ(PV) በዴቢትና በክሬዲት ለማሳየት ብቻ የተያዘ እና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) በወጪ ሂሳብም ሆነ በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት እና የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት በዚሁ የገንዘብ መጠን በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣
- **የመቱ ዩኒቨርስቲ፡**
- የማስፋፊያ ፕሮጀክት ግንባታዎች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ9 እስከ 40 ቀናት የዘገዩ መሆናቸውን፣

- የማስፋፊያ ፕሮጀክት ግንባታዎች ላይ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መሆን የነበረበት የዋናው ውል 1/1000ኛ የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 2,177,872.16 ለዩኒቨርሲቲው ገቢ አለመደረጉ፣
- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በመመሪያው መሰረት በግቢ ውስጥ ለሚያስገነባቸው የተለያዩ የግንባታ ስራዎች ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል የአማካሪነት ፍቃድ ባለው አማካሪ ድርጅት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው በድምሩ ብር 71,295,914.67 በዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በአማካሪነት እና የክፍያ ሰርተፊኬት እንደሚያዘጋጅ በኦዲት የታወቀ መሆኑን፣
- የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ልዩ ልዩ ውል ፈጽሞ ድርድቶቹ በውሉ መሠረት ባለመፈጸማቸው ሊሰበስብ የሚገባ የጉዳት ካሣ በድምሩ ብር 10,057,217.40 ያልሰበሰበ መሆኑ፣

የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክቱን ከመረከቡ በፊት የነበሩ አግባብነት ያላቸው ሰነዶችና መረጃዎች ጉዳዩ ከሚመለከተው ከትምህርት ሚ/ር ርክክብ ባለመደረጉና በዩኒቨርሲቲው በመያዣነት የተመዘገበ ሂሳብ ሳይኖር ለአምደሚካኤል ተመስገን ጠ/ሥ/ተቋራጭ ምእራፍ 1 ሎት ኤ መሰረተ ልማት ግንባታውን አጠናቆ የመጨረሻ ዙር ርክክብ ስላደረገ በማለት የመያዣ ሂሳብ ብር 1,240,730.13 የተከፈለው መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲው ድርጅቱ የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ ምክንያት ብር 14,280,576.95 የጉዳት ካሣ /Liquidation Dameg/ ገቢ ሳያደርግ ወይም ሳይቀነስበት የተገኘ መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲው ለአባይ ደምሴ ህ/ሥራ ተቋራጭ Lab & Class Room ግንባታን በብር 30,168,566.27 ውል ያሰረ ሲሆን ተለዋጭ ሥራ /Variation Order/ የ30% ብር 9,050,569.88 መሆን ሲገባው፣ ብር 12,814,146.40 ከ30% በላይ በመሆኑ 12,814,146.40 - 9,050,569.88 = ብር 3,763,576.53 ለተለዋጭ ሥራ መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ ያለአግባብ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን፤

- በዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል/በኮንስትራክሽን ሚ/ር/ የተረጋገጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል ሰርተፊኬትና ፍቃድ ሳይኖራቸው የብር **70,679,377.44** ግንባታዎች የክፍያ ሰነዶችና የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ እያጸደቀ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣

የወልድያ ዩኒቨርስቲ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ እስከ 30 በመቶ የሚደርስ የቅድሚያ ክፍያ መፈጸም ሲገባው፣ በድምሩ ብር 20,403,854.50 ከግዥ መመሪያ ውጭ ሙሉ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው ድርጅቱ የፕሮጀክቱ ግንባታ በማዘግየቱ ምክንያት በድምሩ ብር 17,724,599.13 የጉዳት ካሣ /Liquidation Dameg/ ገቢ ሳያደርግ ወይም ሳይቀንስ የተገኘ መሆኑን፣
- **ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ** በድምር ብር **90,157,493.32** የግንባታ ሂሳብ ለተከፈለው ክፍያው በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት መሀንዲስ እና በህ/ሥ/ተቋራጮች በተዘጋጀ የክፍያ ሰርተፍኬት እና በሥራ አመራሩ ፀድቆ እንዲከፈል መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣

- በድምር ብር **27,592,730.23** በዩኒቨርስቲው የግንባታ ጽ/ቤት መሀንዲስ እና በህ/ሥ/ተቋራጮች በተዘጋጀ የክፍያ ሰርተፍኬት እና በሥራ አመራሩ ፀድቆ እንዲከፈል መደረጉ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡
- የዩኒቨርስቲው ኢንጅነሪንግና የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከሚመለከተው ክፍል የተሰጠ አማካሪ መሃንዲስ ለመሆን የሚያስችል የስራ ፍቃድ ሳይኖረው በስራ ተቋራጮች መከናወን የሚገባቸው ብር 154,766.67 ዋጋ ያላቸው ፕሮጀክቶች የማማከር፣ ዲዛይን የመስራት፣ ጨረታ የመገምገም ሥራዎች የሚያከናውን መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡
- በዩኒቨርስቲው የሚገኙ ግንባታዎች በመዝገብ አለመመዝገባቸው የተረጋገጠ መሆኑ፣
- እኳቶሪያል እንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን በተባለው ኃ/የግ/ማህበር የሚከናወነው ማዕከላዊ መጋዘን፤ የተማሪዎች ካፍቴሪያ፤ የጥበቃ ቤትና የልብስ ማጠቢያ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ

በ23/12/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 77.71 % መሆኑ፣

- ያሬድ ስዩም በተባለዉ ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው ሴሚናርና ላቦራቶሪ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ24/4/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 77.96 % መሆኑ፣
- ምዕሾ በተባለው ህንጸ ተቋራጭ የሚከናወነው የአጥር ሥራ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ08/9/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 10% መሆኑ፣
- ዩናይትድ በተባለዉ ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የተማሪዎች ካፍቴሪያ፤ የፕሬዝዳንትና የም/ፕሬዝዳንት በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ30/4/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 27% መሆኑ፣
- ሐዲሽ ተክሌ በተባለው ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የዶሪሚተረና ላውንደሪ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ30/3/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 39% መሆኑ፣
- አበበ ሙሉጌታ በተባለው ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የዶረሚተሪ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ24/3/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 10.50% መሆኑ፣
- ሸዋዬ በቀለ በተባለው ህንጻ ተቋራጭ የሚከናወነው የአስተደዳርና መምህራን ከፍቴሪያ በውል ስምምነት የተወሰነው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና ማስረከቢያ በ30/3/2008 ዓ/ም ቢሆንም የግንባታው ሥራ ደረጃ /Physical Status/ 40% መሆኑ እና በአጠቃላይ ግንባታው በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቀ መሆኑን የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሰጠው መግለጫ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት፣

- ላንድ ሰኬፕ (ለግቢ ማስዋቢያ) አገልግሎት በውሉ መሰረት መከፈል ያለበት ከቫት ጋር ብር 12,178,886.01 ሲሆን በተለያየ ወጪ ማስረጃ ተከፍሎ

የተገኘ ብር 14,418,471.37 ሲሆን የውሉ ጊዜ የተጠናቀቀው ቀን 27/04/09 ሲሆን ተጨማሪ ውል የተገባበት ሰነድ ሳይቀርብ እስከ 29/10/09 ክፍያ እየተፈፀመ ቆይቶ ከውል በላይ ብር 2,239,585.36 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

- ለነብዩ ማሞ ህንፃ ተቋራጭ ለላንድ ሰኬፕ አገልግሎት (ግቢ ማስዋብ) ለተከፈለው ሂሳብ ብር 12,178,886.01 ሲሆን ውሉ የተገባው 27/10/08 በውሉ መሰረት 180 ቀን (6 ወር) ሲሆን በዚህ መሰረት ውሉ የሚጠናቀቀው 27/04/09 ድረስ ስራውን አጠናቆ ማስረከብ ሲኖርበት እስከ 29/10/2009 ስራው ያልተጠናቀቀ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ ላጋጠመው መጓተት ተቋራጭ ላዘገየበት ስድስት ወር (180 ቀናት ቅጣት 180*0.001*12,178,886.01=ብር 2,192,199.40) የቅጣት ገንዘብ ነው ፡፡ ሆኖም የቅጣት ገንዘብ የውሉን 10% መብለጥ ስለሌለበት ብር 12,178,886.01*10= ብር **1,217,888.60** የቅጣት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ቀርቷል፡፡

በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ፣

- በባለሙያ ባልተረጋገጠ የክፍያ ምስክር ወረቀት በድምሩ ብር 4,414,048.24 ክፍያ መፈፀሙ፣
- በድምሩ ብር 32,624,108.96 ውል የተገባባቸው የግንባታ ሥራዎች የህንፃ ስራ ተቋራጮቹ ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረውን ውል ሲያቋርጡ ለአፈፃፀም የሚዘጋጅ የክፍያ ሠነድ (payment up on termination) ያላቀረቡ በመሆኑ የሥራ አፈፃፀሙንና የቀሪ ሥራውን መጠን ለመለየት አለመቻሉን፣
- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የህንፃ ሥራ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ በመከናወን ላይ የሚገኙት የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች በውላቸው መሠረት በወቅቱ ባለመጠናቀቃቸው ግንባታዎቹ ለዘገዩበት ተቋራጮች መክፈል የሚገባቸው በድምሩ ብር 759,069.39 የጉዳት ካሳ ገቢ አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡
- **የሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚ/ር፣** የግንባታ ሥራው በአግባቡ ስለመሰራቱ በባለሙያ ሳይረጋገጥ በህንፃ ተቋራጩ ተዘጋጅቶ እና ተረጋግጦ በቀረበ የክፍያ ምስክር ወረቀት ብር 988,657.20 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣

- ○ በተለያዩ የክፍያ ምስክር ወረቀቶች ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም ተቀናሽ የተደረገ የመያዣ ሂሳብ ብር 1,162,363.60 በተከፋይ ሂሳብ አለመያዙን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ○ ከሚመለከተው አካል የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባልተሰጣቸው በኤጀንሲው የምህንድስና ክፍል ሠራተኞች በተዘጋጀ የክፍያ የምስክር ወረቀት በድምሩ ብር 7,205,684.01 ለህንፃ ተቋራጭ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ማንኛውም ግንባታ ሲከናውን የግንባታው የክፍያ የምስክር ወረቀት /Payment Certificate/ መጽደቅ ያለበት ወይም የማማከር ስራው መሰራት ያለበት ፈቃድ ባለው አማካሪ መሃንዲስ መሆን ሲገባው አለመደረጉ ተገቢ ባለመሆኑ ለወደፊቱ ግንባታው የግንባታ ማማከር ፈቃድ በተሰጠው አማካሪ መሃንዲስ ሊጸድቅ ይገባል፡፡
- በወጣው የመንግሥት አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት ዩኒቨርሲቲው የግንባታ ሥራዎች እንዲከናወኑ በማድረግ የህዝብ ሀብት ለብክነት እንዳይጋለጥ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- በማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በመከናወን ላይ የሚገኙ ግንባታዎች ተጠናቀው ለተፈለጉበት ዓላማና አገልግሎት ለማዋል እንዲቻል ተቋራጮች በውል መሰረት ግንባታዎቹን አጠናቀው እንዲያስረክቡ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የጉዳት ካሳውም በውሉ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

4.17 **በሂሳብ መዝገብ (TR) በድጋሚ ተመዝግቦ የተገኘ የወጪ ሂሳብ፣**

ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ለዩኒቨርሲቲው አገልግሎት የሚውል የደንብ ልብስ የተገዛበት ብር 169,200.00 ፣ የጽዳት ዕቃዎች የተገዛበት ብር 87,018.12 እና የትርፍ ሰአት ክፍያ ብር 491,374.00 በድምሩ ብር 747,592.12 በሂሳብ መዝገብ (TR) ሁለት ግዜ በወጪ የተመዘገበ እና ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት ለወጪው በጀት መያዙንና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም አንድን

ወጪ ሁለት ጊዜ መዝግቦ ሪፖርት ማቅረብ የመንግስት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ ከወጪ ቀሪያቸውን እንዳያሳዩ እና የበጀት አጠቃቀሙንም የተዛባ እንዲሆን ሊያደርግ እና ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡ ስለዚህ ዩንቨርስቲው ወጪዎች ሁለት ጊዜ (በድጋሜ) እንዳይመዘገቡ ለሚመለከተው የስራ ክፍል በጥብቅ ማስገንዘብ ይኖርበታል፡፡

4.18 <u>የተሰረዘ የወጪ ቫውቸር በሂሳብ እንቅሰቃሴ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ፣</u>

የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት በኢንስቲትዩቱ በቀን 30/10/2009 በItem No 6872 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 534010 ብር 10,573.00 የተሰረዘው የወጪ ቫውቸር በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) የተመዘገበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት የተሰረዙት የወጪ ማስመሰከሪያዎች በትክክል የተሰረዙ መሆናቸውን በማረጋገጥ በጊዜው ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.19 <u>በወጪ ማስመስከሪያ በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተከፈለ፣</u>

- **የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት** ብር 5,519,082.08 በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ ታውቋል፡፡
- **በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ፣** በድምሩ ብር 7,459,377.57 ወጪ በተደረገባቸው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በየሂሳብ መደቦቹ ለተያዘው ወጪ በጀት መኖሩ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- **የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ** በድምሩ ብር 6,382,264.65 ወጪ በተደረገባቸው የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በየሂሳብ መደቦቹ ለተያዘው ወጪ በጀት መኖሩ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ወጪዎች ከመፈፀማቸው በፊት በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ኃላፊ መፈረሙ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የበጀት አፈፃፀሙን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ማስተዳደር እንዲቻል ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

4.20 <u>በውስጥ ገቢ የፋይናንስ ምንጭ መያዝ ሲገባው በመደበኛ ወጪ የተያዘ ሂሳብ፣</u>

- **የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት** ብር 4,651,000.00 ወጪ በውስጥ ገቢ የፋይናንስ ምንጭ 1900 በጀቱ በተፈቀደው መሰረት መያዝ ሲገባው ከመንግስት ግምጃ ቤት የፋይናንስ ምንጭ 1800 ከተፈቀደው ጋር ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

የውስጥ ገቢ ሂሳብ በፋይናንስ ምንጭ የውስጥ ገቢ 1900 ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው የመደበኛ እና የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት በአንድ ላይ በ1800 ሪፖርት ከተደረገ ሂሳቡ ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ከማድረጉም በተጨማሪ የ1800 የፋይናንስ ምንጭ የባንክ ሌጀር ከፍ እንዲል እና የ1900 የፋይናንስ ምንጭ የባንክ ሌጀር ዝቅ እንዲል ያደረገ በመሆኑም ለወደፊቱ ምዝገባ በሚከናወንበት ወቅት በፋይናንስ ምንጭ አመዘጋገብ ላይ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.21 <u>የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ፣</u>

- **የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ** በጠቅላላው ከሾፌሮች 13,095.27 ሊትር ነዳጅ በጉድለት የሚፈለግ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

በበጀት ዓመቱ ለተቋሙ ተሽከርካሪዎች ከተቀዳው ነዳጅ ውስጥ በጉድለት ከአሽከርካሪዎቹ የሚፈለገው ነዳጅ ተመላሽ እንዲደረግ እና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት አጠቃቀም እና ቁጥጥር በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆን የተቋሙ የስራ አመራር ተግባራዊነቱን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

5 <u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

5.1 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ</u>

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል በተገባው ውልና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ21 መ/ቤቶች ብር 70,006,646.80 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቶል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል/

የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ማናቸውም ተከፋይ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ማወራረድ አለበት፡፡ ለወደፊቱም የተከፋይ ሂሳብ ላይ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

5.2 **_በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች፣_**

- የመቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,691,403.20 የጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ሁለት ጊዜ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጅማ ቅርንጫፍ ገቢ የተደረገ መሆኑን፣
- የቦንጋ ዩኒቨርስቲ በብር **57,777.02** ቆርቆሮ እና ሚስማር የተገዛበት ለፍጹም ሳህሌ መርሻ የቤት እና የቢሮ ዕቃዎች ንግድ የተከፈለና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 7,536.13 ከድርጅቱ ቀንሶ የተያዘ ቢሆንም፣ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ብር 8,540.95 ተመዝግቦ ሪፖርት በመደረጉ በብር 1,004.82 በብልጫ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግቦ በመገኘቱ የተከፈይ ሂሳብ ሪፖርት በዚህ ገንዘብ መጠን ከፍ የተደረገ መሆኑን፣
- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በአጠቃላይ ብር **31,556,591.59** በመመሪያው መሰረት የመያዣ ሂሳብ ቋት እና ተቀጽላ ቋት ተከፍቶለት በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣
- የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ለአቅራቢዎች ብር 5,662.86፣ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች ብር 31,042.56፣ የተለያዩ ክፍያዎች ብር 355,987.62 እና የዋስትና ተከፋይ ብር 1,027,648.48 በጠቅላላው ብር 1,420,341.52 የተከፋይ ሂሳብ በሪፖርት የሚታይ ቢሆንም፣ ለማን ለማን እንደሚከፈልና ከመቼ ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ እንደሚታይ የሚገልጽ ሰነድ/ማስረጃ አለመቅረቡን፣
- **አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጅ ዩኒቨርሲቲ** በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተከፋይ ሂሳብ በተለያዩ ተቀጽላ ቋት /ሌጀሮች/ ብር **2,379,927.89** አግባብ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት የሚታይ መሆኑ፡፡
- **በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ** በተከፋይ የሂሳብ መደብ 5002 የተያዘ ብር 44,766.92 በተቀፅላ የሂሳብ ቋት (ሌጀር) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) ተመዝግቦ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡
- የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 176,421.92 ተሰብሳቢ የቆይታው ግዜው የማይታወቅ መሆኑን፣

- የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኢንስቲትዩት ብር 1,569,345.80 ተሰብሳቢ የቆይታው ግዜው የማይታወቅ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ለተያዘው የተከፋይ ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፡፡ ለወደፊም የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው እንዲረጋገጥ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6 <u>የበጀት አጠቃቀም፣</u>

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲመዛዘን፡- በ14 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 339,537,427.65 ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶቹ) ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 33 ተያይዟል)

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- በየወሩ በሥራ ክፍሉ በሚቀርበው የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት መሠረት ተራፊውን በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዳይቆይ በሌሎች መ/ቤቶች እንዲሰራበት ሪፖርት እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት መጠቀም ይኖርበታል፡፡
- ከተፈቀደለት በጀት በላይ መጠቀም አግባብነት የሌለው ስለሆነ የበጀት አጠቃቀም እና አወጣጥ ስርዓት ማኔጅመንቱ ትኩረት ሰጥቶ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከበጀት በላይ ጥቅም ላይ ውለው የታዩት በጀቶች የመንግስትን መመሪያ እና ደንብ ጥሰትን የሚያሳዩ ስለሆነ አስፈላጊው የበጀት ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

6.1 <u>በበጀት ዓመቱ የሂሳብ መግለጫ ያልተያዘ ተጨማሪ በጀት፣</u>

- **የአት.ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት** የኢንስቲትዩቱ የተስተካከለ በጀት ብር 75,378,623.63 ሲሆን በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ተጨማሪ በጀት ብር 5,828,792.63 ውስጥ ብር 1,305,252.40 በሂሳብ መግለጫ ባለመያዙ የበጀት ዓመቱ የተስተካከለ በጀት ድምር ብር 74,073,371.23 ሆኖ ሪፖርት መደረጉ ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በመመሪያው መሠረት በበጀት ዓመቱ የተፈቀደው እና በተጨማሪ በዝውውር ገቢ የተደረገው በጀት በአግባቡ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ እንዲገለፅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

7 የዕቃና ንብረት አስተዳደር፣

7.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፣

7.1.1 የመሥሪያ ቤቶች የንብረት አስተዳደር መንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በርካታ የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 3ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

የአሰራር ክፍተቶቹ የመንግሥት ንብረቶችን ለብክነት የሚያጋልጡ እና ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት መስተካከል እና መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

7.1.2 ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች የታዩባቸው መቤቶች፣

- **የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት** ኢንስቲትዩቱ መኪኖች ለአሽከርካሪው ሲሰጥ ለማን እንደተሰጠ በተሽከርካሪው የግል ማህደር /ፋይል/ ውስጥ የሌለ መሆኑንና በየጊዜው አሽከርካሪ በተቀያየረ ቁጥር ከንብረት ክፍል ገቢና ወጪ በተደጋጋሚ እንደሚደረግ እና ከስምሪት ክፍል አለመሆኑን፣
- **የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር** በንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል 22 ከንብረት ክፍል በግራውንድ (B2) 27 ጎማ፣19 ካለማደሪያ እና 15 ፍላፐ የተገኙና ንብረቶቹ ወጪ ሆነው የተቀመጠ መሆኑን፣
- **የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን** አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ጎማዎች፣ የመጋረጃ ሻተሮች፣ ኮምፒዩተሮች፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች እና የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች በመጋዘን ተቀምጠው መገኘታቸው፣
- **በአሶሳ ዩኒቨርስቲ**በድምሩ ብር 62,706.85 ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች ሳይመልሱ ሠራተኞች ዩኒቨርሲቲውን የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጧል።

የማሻሻያ ሀሳብ፣

ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ለአገልግሎት አመቺ እንዲሆኑ ተለይተው እንዲቀመጡ፣ተገቢው የንብረት አያያዝ እና የምዝገባ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ፣ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ተለይተው እንዲወገዱ እና ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉት ዕቃዎች ለአገልግሎት እንዲበቁ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ መ/ቤት የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ለቢሮ አገልግሎት እንዲውሉ የተሰጡ ቋሚ ዕቃዎች ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

7.1.3 በንብረት ቆጠራ ወቅት በጉድለት የተገኘ የሃይላንድ ውሃ፣

- **የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል** በ2009 በጀት ዓመት ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በውስጥ ኦዲት የንብረት ቆጠራ ሲካሄድ የሃይላንድ ውሃ ብዛት በቁጥር 1,664 x ያንዱ ዋጋ 3.60 = ብር 5,990.40 በንብረት ክፍል ተገኝቶ ያልተቆጠረ መሆኑ በውስጥ ኦዲት ሪፖርት መሠረት ተረጋግጧል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በቆጠራ የታየው ጉድለት እንዲተካ እና ለወደፊቱም በንብረት አያያዝ ሥርዓት ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

7.2 የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም፣

7.2.1 የመሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:- ሊቢሬ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው)፣በብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜያት የቆሙ ተሽከሪካሪዎችና ሌሎች የተሽከርካሪዎች አያያዝ ችግሮች እንዳሉ ተውቋል፡፡(ለዝርዝሩ አባሪ 35 ተያይዟል)

8. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣

የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፡-

- ከመንግስት መመሪያና ደንብ ውጪ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣
- በድምሩ ብር 1,777,374.15 የተለያዩ ዕቃዎች በዋጋ ማቅረቢያ የተገዛ መሆኑን፣
- በጠቅላላ የብር 4,209,386.47 በግልፅ በጨረታ መገዛት ሲገባው በቀጥታ የተፈጸመ ዩኒቨርሲቲው በ2008 ዓ.ቆጠራ ሲካሄድ ጠፍተዋል ተብለው የተገለፁ ንብረቶች ዴስክ

ቶፕ ኮምፒውተር ብዛት 29፣ ላፕ ቶፕ ብዛት 6፣የምግብ ቤት ጠረጴዛ ብዛት 13፣ ሚድየም ሀይ ባክ ወንበር ብዛት 12፣ ቴሌቭዥን ብዛት 3፣7 ኮምፒውተሮች፣ የሰባቱ RAM፣የኮምፒውተር ስፒከሮች (ብዛት 6)፣mouse(ብዛት 6)፣እንዲሁም አንድ LCD Projector፣ሪሲቨር ከፋሲሊቲ ልማት አስ/ዳ/ዳይሬክተር በቁጥር ወ/ዩ/5235/41/07 በቀን 20/08/07 ለወልቅጤ ከተማ ፖሊስ የተገለፀ ቢሆንም አሁን ድረስ መፍትሄ ያላገኘ መሆኑን፣

- ዩኒቨርሲቲው አጋፔ ካፍቴሪያ የቤት ኪራይ ከሚያዚያ 2007 እስከ ሰኔ 2007 ብር 46,732.62፣እንዲሁም ከጥቅምት 2008 እስከ ግንቦት 2008 ብር 124,620.32 በድምሩ 171,352.94 ያልተሰበሰበ ገቢ
- ዩኒቨርሲቲው ሽናት ሽቀጣ ሸቀጥ የተባለውም በ2007 እና 2008 ዓ.ም በድምሩ ብር 7,351.95 ለዩኒቨርሲቲው የቤት ኪራይ ገቢ ያላደረገ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው 2008 በጀት ዓመት ውስጥ ከካፍቴሪያ፣ከሸቀጣ ሸቀጥ፣ከውበት ሳሎን፣ከፅህፈትና ፎቶ ኮፒ አገልግሎት መሰብሰብ የነበረበት ብር 11,177.9 ተሰብስቦ ገቢ ያልተደረገ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው ብር 75,240.00 በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ በሚከበረው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት እና የ2007 ዓ.ም. የተማሪዎች ምረቃ በዓል በድምቀት ለማክበር በማለት የበዓሉ ቆይታ ጊዜው ሳይገለጽና የተሳታፊዎች ስማቸው ተመሳሳይ በሆነበት ሁኔታ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው ብር 104,376.00 ዩኒቨርሲቲው በመደበኛ የጥበቃ ሥራ ላይ ተሠማርተው ለሚሰሩ ሰራተኞች ሥራው በትክክል በትርፍ ሰዓታቸው ለመስራታቸው የሚያሳይ የሰዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ እና በቀን የሚከፈላቸው የገንዘብ መጠን በሌለበት እንዲሁም ለማን እና እንዴት እንደሚከፈል የሚያሳይ የተሟላ የሰነድ ማስረጃ ሳይኖር ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለመምህራን የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት ሰጥቷቸው እያለ በተጨማሪ ለ75 (ሰባ አምስት) መምህራን በየወሩ ሀምሌ 2007- ሰኔ 2008ዓ/ም ጠቅላላ ብር 615,600.00 የቤት አበል ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

የመቱ ዩኒቨርስቲ፡-

- የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ሳይታወቅ አላግባብ የዋጋ ማስተካከያ ተደርጎ እና በሂሳብ ስሌት ስህተት በድምሩ ብር 960,901.10 በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
- ኮንትራክተሮች የገንዘብ እጥረት ስላጋጠማቸው በሚል ብድር ተሰጥቶ መገኘቱ እና ለመውሰዳቸው ከድርጅቶቹ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የብር 451,511 ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ብር 23,210.00 የግንባታ ሥራ የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች አፈር በመድፋታቸው እና አፈሩን ለማስነሳት በሚል ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ከሶስተኛ ምእራፍ 1ኛዙር እና 2ኛ ዙር ግንባታ ላይ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መሆን የነበረበት የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 20,924,425.34 ለዩኒቨርሲቲው ገቢ አለመደረጉ፡፡
- ብር 40,000.00 ክፍያዎች የገንዘብ መቀበያ ደረሰኙ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ያልተያያዘ መሆኑን፣

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፡-

- የቤት አበል ላይ የቤት ተመን ዋጋ እየተቀነሰ ልዩነቱ የቤት አበል በሚል በድምሩ 162,650.00 ብር ያላግባብ ተከፈላቸው ተገኝቷል፡፡
- በውጭ ሀገር ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ መምህራን መመለስ በነበረባቸው ሳይመለሱ የቆዩ በድምሩ ብር 40,442.00 ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- በጠቅላላ ብር 1,035,900.00 ዩኒቨርሲቲው በራሱ የክፍያ ስርዓት በማውጣት ከመደበኛ በጀት ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለጥናትና ምርምር ማካሄጃ (Msc Thesis) ድጎማ አዲስ የሚገቡ ተማሪዎችን ለመፈተን ወደ ተለያዩ ክልሎች ለተጓዡ መምኅራን የሞያ አበል እና ካሪኩለም ሪቪዉ ወርክ ሾፕ (curriculum review work shop) ላይ ለተሳተፉ በሚል ብር 772,610.00 አላግባብ መሆኑ፣
- የብር 7,296,089.99 ወጪዎች የሂሳብ መደባቸውን መሰረት ያላደረገ መሆኑ፣
- በድምር ብር 913,544.48 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ መፈፀሙ ተረጋግጧል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ለአንድ ኮንትራክተርና ለአንድ አማካሪ ድርጅት በጠቅላላ ብር 28,906,495.29 ከመመሪያው ውጭ ከጠቅላላ ዋጋ ከ30% በላይ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል።
- በጠቅላላ ብር 39,697,017.64 ባላላቀ ስራ ከውሉ በላይ በብልጫ ተከፊሎ ተገኝቷል።

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፡-

- በ2008ዓ/ም የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑን፣

የደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፡-

- ብር 2,500,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመለት ዓላማ ውጭ ለሆነ የሥራ ዘርፍ ከመደበኛ ባልተፈቀደ በጀት ወጪ በማድረግ አለአግባብ የአክስዮን ግዥ መፈጸመ መሆኑና ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ፣
- በ27/01/2007 በቁጥር በጠ1/6/39 ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተላለፈ መመሪያ መሰረት በመንግስት ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ ተማሪዎች ካለው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ በመገምገም ከመስከረም 1ቀን 2007 ጀምሮ የምግብ በጀት ተመን በተማሪ በቀን ብር 15 እንዲሆን የተወሰነ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው ለ2ኛ እና ለ3ኛ ዓመት ህክምና አንስቴዥያን ሚድዋይፈሪ ተማሪዎች በቀን ብር 35 እንዲሰጣቸው በመደረጉ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ ብር 20 በተጨማሪ በመከፈሉ በድምሩ ብር 242,800.00 ከተመን በላይ ወጪ መደረጉና አለአግባብ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፣

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችል እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ቢወስንም ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 137,999.96 የማበረታቻ እና ሽልማት ክፍያ ፈፅሞ መገኘቱና አለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ፤

የወልድያ ዩኒቨርስቲ፡-

- ከተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች ጋር በገባው ውል መሠረት የግንባታ ሥራዎች በወቅቱ ባለመጠናቀቃቸው ገቢ መደረግ የሚገባው የጉዳት ካሣ በድምሩ ብር 53,759,140.43 መገኘቱን፤

- ዩኒቨርሲቲው ከኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ ጋር ውል በመግባት በብር 4,614,348.22 የጀነሬተር ግዥ የፈፀመ ሲሆን፤ በውሉ መሰረት ዕቃው በወቅቱ ገቢ ባለመደረጉ ላዘገየበት 463 ቀናት መከፈል የሚገባው የጉዳት ካሣ ብር 461,434.82 ገቢ መሆኑ፤
- የዩኒቨርሲቲው የግንባታ መሐንዲስ በቦታቸው በመሐንዲስነት የሚያገኙት ደመወዝ ሊከፈላቸው ሲገባ፣ በቦርዱ ውሳኔ በምክትል ስራ አስኪያጅ ደረጃ እንዲሰሩ በመደረጉ ለቦታው የሚከፈለው ደመወዝ እንደ ማበረታቻ (Top up) በየወሩ እንዲከፈላቸው የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በቁጥር ወዩ/1352/01-ፕ/06 ባሳወቀው መሰረት ከሰኔ/2006--ሰኔ30/2008 በድምሩ ብር 65,245.00 አለአግባብ ከመመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱን፤
- የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል ሰኔ 2004 ዓ.ም በወጣው መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 4 መሠረት መከፈል ሲገባው ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ለመጡ እና ሲምፖዝየም ላይ ንግግር ላደረጉ መምህራን ከተፈቀደው የውሎ አበል የክፍያ ተመን በላይ ከብር 2,000.00 እስከ ብር 5,000.00 እንዲከፈላቸው በመደረጉ በድምሩ ብር 49,000.00 ከመደበኛ የውሎ አበል በተጨማሪ ያለ አግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፤
- በትርፍ ሰዓት ለሚያስተምሩ መምህራን በየማዕረጋቸው በወጣው የክፍያ ተመን መሠረት በክሬዲት ሀወር (credit hours) ክፍያ እንደሚከፈል ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠ.ሚ ጽ/ቤት ጥር 13/2003 ዓ.ም በቁጥር ጠ80-አጠ52/02/13 በተጻፈ ደብዳቤ ቢገለፅም ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች በትርፍ ሰአት ለማስተማር ለመጡ መምህራን በአንድ የትምህርት ሰዓት (credit hour) እንዲከፈላቸው ከተፈቀደው የገንዘብ ተመን በላይ እንዲከፈላቸው በመደረጉ አለአግባብ ብር 43,082.00 ወጪ ሆኖ መገኘቱን፤
- የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር መ30/ጠ13/368/3 በሰኔ 29/2001 ዓ.ም ባስተላለፈው መመሪያ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ እንዲቆም በቁጥር መ30/ጠ13/37/820 በቀን 5/13/2001 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የተገለጸ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ ለሰሩበት በሚል የትርፍ ሰዓት ክፍያ በድምሩ ብር 1,691,768.94 ከመመሪያ ውጭ ያለአግባብ ክፍያ ፈፅሞ መገኘቱን፤
- የክረምት ክፍያ እንዲፈጸም የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ለአስተዳደር ቦርዱ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ቦርዱ ክፍያውን እንዲያፀድቀው እና በዩኒቨርሲቲው ሴኔት

እንዲወሰን በማድረግ የትምህርት መርሀ ግብርን ላስተባበሩ የአካዳሚክ ኃላፊዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች ከመደበኛ በጀት ብር 247,500.00 አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፤

- ለዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሾፌሮች ለመስክ ቆይታ በመደበኛ የቀን የውሎ አበል ላይ በተጨማሪ ለአልጋ በቀን ብር 100.00 ከውስጥ ገቢ ሂሳብ እየተደጎመ እንዲከፈል የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በ25/07/2005 በቃለ-ጉባኤ በወሰነው መሠረት በመከፈሉ በድምሩ ብር 272,786.19 ከመመሪያ ውጭ አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፣

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር፡-

- በ2008 የኦዲት አስተያየት መሠረት በተወሰኑ ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ አለመወሰዱን፣

የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል፣

- የመንግስት ሰራተኞች የቀን የውሎ አበል መመሪያ ሰኔ /2004 መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በኦዲት ሲደረግ የተገኘ ብር 261.00 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል የሚል አስተያየት ተሰጥቶ የነበረው አሁንም ገንዘቡ ተመላሽ አለመደረጉ፣

የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን፣

- በቅድሚያ የተከፈለ ብር 2,364,507.06 የንብረት ገቢ ሞ/19 ያልተያያዘ መሆኑ፣
- ብር 2,230.15 አለአግባብ ደመወዝ ተከፍሎ የተገኘው ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፤

የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ፣

- ዩኒቨርሲቲው በ2008 በጀት ዓመት ከልዩ ልዩ የውስጥ ገቢ ምንጮች የሚሰበስበውን በየሂሳብ ርዕሶቹ የሚመዘገብ ቢሆንም፣ በዝርዝር ሂሳብ መመዝገቢያ(TR) መሠረት ተመዝግቦ የተገኘው ብር 21,500,537.27 ሲሆን፣ በሂሳብ ቋት የተመዘገበው ደግሞ ብር 14,377,771.31 በመሆኑ በልዩነት ብር 7,122,765.96 የሚታይ መሆኑን፣ ዓመታዊ ሪፖርት የማይዘጋጅና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- ለ14 ሠራተኞች ከብር 1,500-20,000.00 በሥራ አመራሩ ውሳኔ የማበረታቻ ሽልማት ለቢ.ኤስ.ሲ ዕቅድ የሠሩ በሚል ብር 68,000.00 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- ዩኒቨርስቲው ሠራተኞች ሥራ ላይ ስለመሆናቸው ሳያረጋግጥ በድምሩ ብር 42,945.08 ሰራተኞቹ ዩኒቨርሲቲውን ከለቀቁ በኋላ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር ደመወዝ በሰራተኞች የግል የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ተደርጎ የተከፈለ መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲው ለለማ ኢንተርናሽናል ሆቴል ብር 40,026.55 መክፈል ሲገባው፣ ብር 10,213.53 በብልጫ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱ፤
- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ድርጅቶች ግዥ ሲፈጽም ብር 52,250.38 የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ብር 8,111.77 የተቀናሽ ተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 60,362.15 ከአቅራቢው ሳይቀነስ በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱና ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣

የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት፡-

- በተለያዩ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች እና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች በድምሩ ብር 3,168,870.89 የተከፈለው የወጪ ማስረጃዎች ያልቀረቡለት ሂሳብ መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣

- ብር 280,009.00 የገቢው ዓይነት፣ ገቢው ከማን እንደተገኘ፣ የገቢው ምክንያትና የማስከፈያ ተመን ታሪፍ በለመታወቁ የገቢ ትክክለኛ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- ውል ሳይታደስ የመኪና ጥገና ክፍያ ብር 265,658.50 ተፈፅሞ መገኘቱ፣
- በዩኒቨርስቲው ለትምህርት ውጪ ሃገር ሄደው በውሉ መሠረት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኃላ ወደ ስራቸው ያልተመለሱ የ3 መመህራን መኖራቸው፣
- በቋሚ ንብረት ክፍል ፣ 75 የሚሰሩ ዴል ሞኒተር፣ 1 የማይሰራ የምንጣፍ መጥረጊያ፣ 7 የማይሰሩ ኤልሲዲ ፕሮጀክተር፣ 85 ኪ-ቦርድ እና 1 የማይሰራ ሶኒ ቴሌቪዥን ሲሆኑ፣ በሌላው ሰራተኛ ስም የሚገኙ የማይሰሩ 18 philips lamp፣ 46 xerox፣ 71 dell-monitors፣ እና ሌሎች በርካታ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ተከማችተው ይገኛሉ፣
- በንብረት ክፍል ብዛታቸዉ 132 ፔርሙሶች በካርቶን የተቀመጡ መሆኑ፣
- በንበረት ክፍል ፣ ብዛት ያላቸው የጣሪያ ቆርቆሮዎች፣ ሽቦዎች፣ ፌሮዎች እና 2 ቲቢሲ ቱቦዎች ሳይወገዱ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፣

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣

- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ግዥ የፈጸመ ቢሆንም ነገር ግን አቅራቢ ድርጅቶቹ በጨረታ ያሸነፉት ንብረት በገቡት ውል መሠረት ገቢ ያላደረጉ መሆኑ ተረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም በግዥ

አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አዘግይቶ ላቀረቡ ድርጅቶች ቅጣት ሳይፈፀም ብር 332,443.84 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች መኝታ አገልግሎት የሚውል የብረት ቁም ሳጥን ለመግዛት ጨረታ ያወጣ ቢሆንም በጨረታው ሰነድ ላይ ከተገለጸው ስፔሲፍኬሽን ውጭ በብር 4,485,000.00 የእንጨት ቁም ሳጥን ግዥ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

አዲግራት ዩኒቨርሲቲ፣

- የዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ መደብ 4210 ብር 48,510.00፣ እንዲሁም በተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ መደብ 5054 ብር 360,395.50 በአጠቃላይ ቋት ቀሪ ሆኖ የሚታይ ሲሆን፣
- ተቀጽላ ቋት ያልተዘጋጀላቸው በመሆኑ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚታየውን ቀሪ ለማመሳከር አለመቻሉን፣
- በየሂሳብ መደቦቹ የታየው ቀሪ ሂሳብ ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ የሚታይ መሆኑንና በ2008 በጀት ዓመትም ሂሳቡ ሳይንቀሳቀስ መገኘቱን፣
- አንድ ትራክተር ተሸከርካሪ የሰሌዳ ቁጥርና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌለው ሆኖ መገኘቱን፣
- አቅራቢዎች ዕቃዎችን በወቅቱ ገቢ ባለማድረጋቸው ላዘገዩበት ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ማድረግ የሚገባቸው በድምሩ ብር 1,480,454.64 የጉዳት ካሣ ለዩኒቨርስቲው ገቢ አለመደረጉን በተመለከተ ከድርጅቶቹ ገቢ ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ዩኒቨርሲቲው እርምጃ ባለመውሰዱ ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉን፣
- ዩኒቨርሲቲው ለሚያስገነባው የተማሪዎች መመገቢያ ህንፃ ከመኮንን ገ/ኪዳን የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር በገባው ውል መሠረት ግንባታው በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ላዘገየበት ብር 112,586.76 የጉዳት ካሳ ገቢ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት የተገለፀ ቢሆንም የሥራ አመራሩ ገንዘቡ ገቢ እንዲደረግ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰዱን፣
- ዩኒቨርሲቲዉን ለለቀቁ 12 ሠራተኞች በድምሩ ብር 8,491.34 ላልሰሩባቸው ወራት እና ቀናት አለአግባብ ደመወዝ መከፈሉንና ከሠራተኞቹ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተመላሽ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

በማይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር፣

- ጥቅማ ጥቅም ለሚገባቸው የስራ ኃላፊዎች የቤት አበል፣ የኃላፊነት አበል እና አኑዋላይዜሽን ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣ ከደመወዝ ጋር ተደምሮ የስራ ግብር መቀነስ ሲገባው ብር 90,260.03 ያልተቀነሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር፣

- በ2008 የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑን፣

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣

- ከሐምሌ 2006 እስከ ሰኔ 2007 ዓ.ም ለቀጥታ ሥልክ ከተመን በላይ የተከፈለ ብር 2,224.22 ተመላሽ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡

የኢ.ት. ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት፣

- ባልታወቀ ምክንያት በፈቃዳቸው ሥራቸውን የለቀቁ ሰራተኞች በአጠቃላይ በሥራ ገበታቸው ላይ ላልተገኙ ለሶስት ሠራተኞች በድምሩ ብር 4,119.64 የደመወዝ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
- ለውሎ አበልና ለአልጋ ክፍያ ብር 1,707.00 በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
- የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ብር 2,727.27 ከተፈቀደላቸው የስልክ ሂሳብ ተመን በላይ ተጠቅመው የተገኙ መሆኑ፣

የቴክኒክና ሙያ ት/ሥ/ኤጀንሲ፣

- የኤጀንሲው ሠራተኞች ለመሠረታዊ የአሰራር ማሻሻያ (BPR) ሥልጠና በፊሊፒንስ ለቆዩበት ለእያንዳንዳቸው ለውሎ አበል ከተከፈላቸው ብር 368,320.01 በሚያቀርቡት የክፍያ ማስረጃ መወራረድ የሚገባው ብር 45,860.98 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ፣

- ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባቸው ህንፃዎች ከተለያዩ የህንፃ ስራ ተቋራጮች ጋር በገባው ውል መሰረት ግንባታዎቹ ባመጠናቀቃቸው መክፈል የሚገባው ብር 8,809,188.08 የጉዳት ካሣ ገቢ አለመደረጉን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም ባለፉት

ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት በኦዲት በተሰጡ አስተያየቶች መሠረት የእርምት እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት እንዲቀርብ በድጋሚ እናሳስባለን።

9 ልዩ ልዩ፣

የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፡-

- ዩኒቨርስቲው እስከ 2009 በጀት ዓመት መጨረሻ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በትምህርት ላይ ያሉ 163 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ጊዜ የማይታወቅ መሆኑን፣ 166 መምህራን ለትምህርት የሄዱበት ተቋም (የት እንደሚማሩ) የማይተወቅ መሆኑን፣ 174 መምህራን ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደሥራ የሚመለሱበት ጊዜ የማይታወቅ (በውሉ ያልተቀመጠ) መሆኑን፣

የመቱ ዩኒቨርሲቲ፡-

- የዓመቱ አጠቃላይ የምግብ ወጪ በ2009 ዓ/ም በበጀቱ በተፈቀደለት መሰረት የአንድ ተማሪ የምግብ በጀት ሲሰላ በቀን ብር 15.00 ሂሳብ መሆኑን ታውቀዋል፡፡ ነገር ግን በአዲሱ ሳያስፈቅዱ በጨመሩት በጀት ለነፍስ ወከፍ ተማሪ ሲሰላ ደግሞ ብር 18.13 መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አንድ ተማሪ ከተመደበለት በጀት በላይ በቀን 3.13(ወደፊት በወጪ መጋራት ከሚከፍለው በላይ) እየተመገበ መሆኑን፣
- ብር 15.00 ሁሉም ተማሪ ተመጋቢ ነው በሚል የታሰበ በመሆኑ፣ በዩኒቨርስቲው የተማሪዎች ምግብ ቤት የማይጠቀሙ (non-café) ተማሪዎች በቀን ብር 15.00 ሲከፈላቸው ተመጋቢ ተማሪዎች እስከ ብር 18.13 በቀን እንደሚመገቡና ይህም ተመጋቢ ያልሆኑ ተማሪዎች ተጎጂ መሆናቸውን፣
- የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች በተለያየ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች ዝርዝር፣ ትምህርት ያቋረጡበት ቀን፣ ወር እና ዓ.ም በየወሩ መረጃ ተሰብስቦ ባለመቀመጡ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች የተጠቀሙት እና ያልተጠቀሙት የምግብ ፍጆታ ማወቅ ያልተቻለ መሆኑን፣
- የዩኒቨርስቲው አስተማሪዎች ለትምህርትና ስልጠና ሄደው ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኃላ በቀነ ገደብ ያልተመለሱ 5 መምህራን መኖራቸው፣
- ዩኒቨርስቲው በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ አለአግባብ በነጻ የመንግስት ቤት ውስጥ የሚኖሩ የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች መኖራቸውን፣

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡-

- ኢንስቲትዩቱ ለኮሜሳ ሌዘር ኤንድ ሌዘር ፕሮዳክትስ ኢንስቲትዩት (COMESA) Leather and Leather Product Institute) ወ/ሮ ብርቅነሽ ጎንፋ ከሚያዚያ 23 ቀን 2009ዓ.ም ጀምሮ ህጉ ካስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውጭ ለ2 ዓመት በትውስት እንዲሄዱ መፃፉን፣
- ኢንስቲትዩቱ የስጋት ምንጮችን በመለየት የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ወይም ፍተሻ ያላደረገ መሆኑን፣
- የመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት የጸደቀ የአይሲቲ ፖሊሲ ወይም ተሰማሚ የአፈጻጸም መመሪያ የሌለው መሆኑን፣
- ኢንስቲትዩቱ የተፈቀደለት ሠራተኛ ብዛት 407 ሲሆን ያለው የሰው ሀይል 311 በመሆኑ አሁን ያለው የሰው ሀይል 76% ስለሆነ 24% ክፍት የስራ መደብ መኖሩ ስራዎች የስልጣን ገደብ የሌለው (Segregate Duty) አለመኖሩ፣
- ኢንስቲትዩቱ በሂሳብ ክፍል በቂ የሰው ሀይል ባለመኖሩ የክፍያ ማዘዥ የሚያዘጋጅ፣ የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ሰነድ የሚጠብቅ፣ ሰነድ የሚያዋቅር፣ የሂሳብ መዛግብትን IBEX SYSTEM ውስጥ የሚያስገባና የሂሳብ ሪፖርት የሚያወጣ አንድ ሰራተኛ መሆኑን፣
- ኢንስቲትዩቱ የተለያየ ክፍሎች ሰራተኞች ስራን ደርበው የሚሰሩ በመሆኑ የፋይል አደረጃጀት የወጪ ማስመስከሪያ(PV)፣ የባንክ ማስመስከሪያ(BPV)፣ የሂሳብ ማስተካከያ(JV)፣የገንዘብ መሰብሰቢያ(RV) አንድ ላይ የሚቀመጥ መሆኑ ለቦታው የሚፈቀደውን ስራዎች በተሳለጠ መንገድ እየተካሄደ አለመሆኑን፣

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር፡-

- የመደበኛው በጀት በተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት /IFMS/ የተመዘገበው በብር 30,000.00 በማነስ የሚታይ መሆኑን፣
- የ2009 የታወጀና የተተከለ በጀት ሳይኖር እና ዝውውር ሳይደረግ ከመደበኛ በጀት ብር 3,554,091.09 እና ከካፒታል በጀት ብር 1,344,497.50 በድምሩ ብር 4,898,588.59 ባልታወጀ በጀት እንደ ወጪ ተይዞ መገኘቱን፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት(ICMIS) መረጃዎችን ከክልሎች ጋር በመጣመር ለጀመረው ዝርጋታ ድጋፍ በማድረግ ሥርአቱ

እንዲጠቀሙ ባልተደረገበት እና እየሰራ መሆኑን ሳያረጋግጥ በድምሩ ብር 1,032,637.58 በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ መገኘቱን፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለገዛቸው ዕቃዎች ሞዴል19 በማንዋል እና በሲስተም እየተቆረጡ በመሆኑ የተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ሙሉ ለሙሉ እየተሠራበት አለመሆኑ፣

የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል፣

- ለ26 የመ/ቤቱ ሠራተኞች በቁጥር 51 ክፍል እና የመ/ቤቱ ሰራተኞች ላልሆኑ ለ40 ዳኞች በቁጥር 86 ክፍል የመኖሪያ ቤት በነጻ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ለሠራተኞቹ እና ለዳኞቹ የመኖሪያ ቤት እንዲሰጣቸው ከሚመለከተው አካል የተፈቀደበት ማስረጃ ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ እና ሠራተኞቹም ሆኑ ዳኞቹ የሚጠቀሙት የመብራት እና የውሀ ፍጆታ ቤቱን ከተረከቡት ጊዜ ጀምሮ ከመ/ቤቱ በጀት የሚሸፈን መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- ለማዕከሉ በመዋቅር ጥናት መሠረት የሠራተኛ ብዛት 237 ሆኖ ሳለ አሁን በማዕከሉ ያሉ ሠራተኛ ብዛት በቁጥር 88 ብቻ በመሆናቸው ክፍት የስራ መደብ ብዛት 149 መሆኑንና የኸውም በመቶኛ 63% መሆኑ፣
- በስልጠና ማዕከሉ ለቋሚ ሠራተኞች ለእያንዳንዳቸው የስራ መዘርዝር (Job Discription) የሚገልፅ ደብዳቤ ያልተሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- **የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ** በዩኒቨርሲቲው ለትምህርት የተላኩ 14 መምህራን በቀነ ገደቡ ያልተመለሱ ሲሆን ዩኒቨርሲቲውም በውሉ መሰረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣

- ዩኒቨርሲቲው የስጋት ምንጮች መለየት እና የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ፣
- የመረጃ ደህንነት አስተዳደር /approved IT security policy to ensure data confidentiality, integrity and availability/ የሌለ መሆኑ፣
- የአይ ሲቲ ቀጣይነት እና የመልሶ ማቋቋም ዕቅድ /disaster recovery plan/ የሌለ መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን፣

- መ/ቤቱ ከተፈቀደለት 161 የሥራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 133 ሲሆን 28 (17%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስጋት ምንጮች የመለየት እና የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ፣

የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ፣

- የውስጥ ኦዲቱ በተገቢው የስው ሀይል ያልተሞላ በመሆኑ፣
- አልፎ አልፎ የቫትና የተከፋይ ተቀናሽ ታክስ ደረሰኝ እንዲሁም የባንክ አድቫይስ ተቆርጦ ከባንክ ወጪ ማስመስከሪያው ጋር የማይያያዝ መሆኑ፣
- የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ ሂሳቡ ሲወራረድ ለምዝገባው መነሻ የሆነ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኝ ቁጥር የማይጠቃቀስ መሆኑ ለምሳሌ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 324511 ብር 10,000.00፣ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 324512 ብር 10,000.00 በድምሩ ብር 20,000.00 ያልተጠቃቀሰ መሆኑ፣
- ወደ ባለ መብቱ የሂሳብ ቁጥር ገንዘብ ዝውውር እንዲያደርግ ዩኒቨርሲቲው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚጽፍ ደብዳቤ አልፎ አልፎ ከባንክ ወጪ ማስመስከሪያው ጋር የማይያያዝ መሆኑ፣

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ፣

- የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ ለዩኒቨርሲቲው ሳይቀርብ የሠራተኛ ዝውውር የተፈፀመ መሆኑን፣
- ለዩኒቨርሲቲው በተፈቀደው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 13 የኦዲት ባለሙያዎች መመደብ ሲገባቸው 5 የኦዲት ባለሙያዎች ብቻ በሥራ ላይ የሚገኙ በመሆኑ 8 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ወይም በዝውውር ያልተሟሉ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከላይ የተዘረዘሩትን ልየ ልዩ የአሰራር ድክመቶችን በኦዲት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳቦች መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ ግልፅነትና ተጠያቂነት ማስፈን ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም ለወደፊት መሰል ስህተት እንዳይፈጣር ማንኛውም መ/ቤት እያንዳንዱን እንቅስቃሴዎች ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ

መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 28 ዩኒቨርስቲዎችና 1 ሚኒስቴር መ/ቤት በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡ በዕቅድ የተያዙት ተቋማት በሙሉ የኦዲት ሥራቸው ተጠናቋል ፡፡

ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የመውጫ ስብሰባ ተደርጎ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው መሥሪያ ቤቶቹ የሰጡትን ምላሾች መሰረት በማድረግ የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

1.1. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 28 ዩኒቨርስቲዎችና 1 ሚኒስቴር መ/ቤት የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ ነው፡፡

1.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት እና የበጀት ዓመቱን ሂሳብ የዘጉበትን ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ	1,796,958,921.60	1,130,516,683.64	2,927,475,605.24
2	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	967,728,363.84	920,194,053.00	1,887,922,416.84
3	ትምህርት ሚኒስቴር	1,447,412,056.05	2,440,898,251.30	3,888,310,307.35
4	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	1,463,937,512.22	1,125,194,733.45	2,589,132,245.67
5	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	1,245,815,374.45	969,911,952.56	2,215,727,327.01
6	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	1,229,750,166.20	830,000,000.00	2,059,750,166.20
7	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	983,224,718.08	1,033,779,096.82	2,017,003,814.90
8	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	903,036,291.70	1,097,690,074.35	2,000,726,366.05
9	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	881,483,711.16	805,000,000.00	1,686,483,711.16
10	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	478,498,573.09	659,734,505.26	1,138,233,078.35
11	ዲላ ዩኒቨርቲ	573,122,844.70	560,020,000.00	1,133,142,844.70
12	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	528,103,339.66	538,700,000.00	1,066,803,339.66
13	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ	495,494,015.48	570,676,557.85	1,066,170,573.33
14	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	523,560,780.90	523,560,780.90	1,047,121,561.80
15	ደ/ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	448,012,312.36	586,126,094.26	1,034,138,406.62
16	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	974,335,931.00	0.00	974,335,931.00
17	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	920,135,474.99	0.00	920,135,474.99
18	ደ/ብርሃን ዩኒቨርሲቲ	412,233,199.88	422,000,000.00	834,233,199.88
19	ድሬዳዋ የኒቨርሲቲ	369,052,420.60	380,000,000.00	749,052,420.60
20	ሠመራ ዩኒቨርሲቲ	375,196,132.04	338,083,000.00	713,279,132.04
21	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	342,406,370.00	344,500,000.00	686,906,370.00
22	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	112,306,970.93	525,563,791.62	637,870,762.55
23	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	324,021,988.19	279,236,713.76	603,258,701.95
24	አርሲ ዩኒቨርሲቲ	391,411,815.13	106,045,077.99	497,456,893.12

25	ራያ ዩኒቨርሲቲ	291,758,985.00	0.00	291,758,985.00
26	ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ	112,079,700.00	0.00	112,079,700.00
27	መቅደላ ዩኒቨርሲቲ	11,743,426.00	0.00	11,743,426.00
28	ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ	11,423,818.40	0.00	11,423,818.40
29	እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ	10,988,061.37	0.00	10,988,061.37
		18,625,233,275.2	16,187,431,366.76	34,812,664,641.78

1.3. የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ 1ዩኒቨርስቲ አስተያት መስጠት ያልተቻለ ሲሆን የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ19 መሥሪያ ቤቶች፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ9 መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዝርዝሩ አባሪ-1 ተመልክቷል፡፡

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡

2. የጥሬ ገንዘብ ፣ባንክ ሂሣብና የመክፈቻ ሂሳብ

2.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የመ/ቤት ስም	የጥሬ ገንዘብ ጉድለት	መግለጫ
በጎንደር ዩኒቨርሲቲ	30,852.31	(በሂሳብ መደብ 4202) የተመዘገበ
በጋምቤላ የዩኒቨርሲቲ፣	759,774.00	ከ2007 እስከ 2009 ዓ/ም
ድምር	790,626.31	

- የሳጥን ገቢና ወጪ ሲመዛዘን በማነስ የታየ ሲሆን ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

2.2. በሪፖርት የተመለከተውና በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ ልዩነት መኖሩ

ተቁ	የመ/ቤቱ ስም	በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገው	በገንዘብ ያዦች እጅ በቆጠራ የተገኘው	በቆጠራ የተገኘው በማነስ /በመብለጥ/
1	በጋምቤላ የዩኒቨርሲቲ፣	2,591,346.74	20,338.50	2,571,008.24
2	በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በኩልፎ ካምፓስ	12,296.35	**0.00**	12,296.35
3	በአዲስ አበባ የዩኒቨርሲቲ፣	0.00	370,317.37	370,317.37
ድምር		**2,603,643.09**	**390,655.87**	**2,953,621.96**

2.3. ባንኩ ብሎክ አድርጎ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ

ተቁ	የመ/ቤቱ ስም	ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ያልተደረገ
1	ዲላ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል	3,178,302.01
2	በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	145,845,772.14
3	አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ	1,941,004.89
ድምር		**150,965,079.04**

- በድምሩ ብር 150,965,079.04 ባንኩ ብሎክ አድርጎ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ማድረግ ሲገባ ሰኔ 30/2009 ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፣

2.4. በባለመብቱ የባንክ ሒሳብ በማስተላለፍ መከፈል ሲገባው በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ

ከብር 50,000.00 በላይ ለሆኑ ግዢዎች በባንክ ማስተላለፍ የክፍያ ዘዴ ወይም በተከፋዩ ድርጅት ስም በተዘጋጀ ቼክ ለዕቃ አቅራቢዎች እና አገልግሎት ሰጪዎች ክፍያ መፈፀም ሲገባው በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ለተለያዩ ዕቃዎች ግዢ ክፍያ ብር 4,429,978.05 በጥሬ ገንዘብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

- በጥሬ ገንዘብ መጠበቂያ ካዝና ውስጥ የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ በመቁጠር የቆጠራ ውጤቱ በእያንዳንዱ ገንዘብ ያዥ ስም ከተከፈተው የጥሬ ገንዘብ ተቀጽላ ሌጀር ጋር በማመሳከር ከወጪ ቀሪው ትክክል ለመሆኑ ወቅታዊ ቁጥጥር እንዲደረግ፤
- በጉድለት የሚታየው ጥሬ ገንዘብ እንዲተካ፣
- በበጀት አመቱ መጨረሻና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ድምር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተቀጽላ ሌጀር ከሚታየው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን የሥራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

2.4.1. የመክፈቻ ሂሳብ በተመለከተ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በ2009 በጀት ዓመት መክፈቻ ሂሳብ ከባለፈው ዓመት የዞረ ማለትም ቋሚ ሂሳቦች እንደ የባንክ እና ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣ የተከፋይ ሂሳብ፣ የተጣራ ሃብት እና የመሳሰሉት እንደ መነሻ ሂሳብ ተደርጎ ኮሌጁ ለመጠቀሙ እና የሂሳብ ምዝገባው ላይ ለማካተቱ ሲጣራ የዞረ እና መክፈቻ የሚሆን ሂሳብ በሂሳብ ምዝገባው ላይ በውስጥ ገቢ እና በፕሮጀክት ሂሳብ እንዲሁም በመደበኛ በጀት ከ2007 በጀት ዓመት በፊት ያለው በሂሳብ ሪፖርቱ ያልተመለከተ እና ለመካተቱም የሚገልፅ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ የመነሻ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

3. ተሰብሳቢ ሂሳብ

3.1. በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ፤

3.1.1.ግኝት፤

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በ24 መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው 1,172,375,148.70 ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ /ዝርዝር በአባሪ-6 ቀርቧል/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3.2. <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች</u>

<u>ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (በክሬዲት) የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ዓይደር ሪፈራል ሆስፒታል** በ4210 ሂሳብ መደብ ብር 6,937.43 በዴቢት የሂሳብ ሚዛን መታየት ሲገባው ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት የሚታይ መሆኑ፤
- **በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ** ብር 418,726.07 በዴቢት የሂሳብ ሚዛን መታየት ሲገባው ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት የሚታይ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ባልተለመደ የሂሣብ ሚዛን የሚታየው የሂሣብ ማስተካከያ እንዲሠራለት፤
- በውዝፍ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሳብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ በቅድሚያ የተወሰዱት ገንዘቦች በደንብና መመሪያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እዲያወራርዱ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4. ገቢ ሂሳብ፤

4.1. ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሣብ፤

4.1.1. በውለታው መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ፤

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግኝቱ መግለጫ	የገንዘቡ ልክ
1	አርሲ ዩኒቨርሲቲ	ከዱቤ ሕክምናና መድኃኒት ሽያጭ ያልተሰበሰበ ገቢ	160,795.60
2	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	ውዝፍ ኪራይ እና በውሉ መሰረት የተቀመጠ 15% ቅጣት ሂሣብ፣ እንዲሁም ከዱቤ ተጠቃሚዎች ያልተሰበሰበ	572,010.95
3	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	ከንግድ ቤቶች፣ ከሪፈራል ሆስፒታል እና ከዓይደር ሆስፒታል የዱቤ ተጠቃሚዎች	5,258,336.50
4	አ.አ ዩኒቨርሲቲ	ከንግድ ቤት ኪራይ	601,400.00
		ድምር	**6,592,543.05**

በአርሲ ዩኒቨርሲቲ አሰላ ሆስፒታል ከሀምሌ 1/2008 ጀምሮ ከሆስፒታሉ በዱቤ ሽያጭ አገልግሎት ካገኙ ሰባት /7/ ተቋማት መሰብሰብ የሚገባው ብር 160,795.60 ሂሳብ ሳይሰብሰብ የተገኘ መሆኑ፤

በአክሱም ዩኒቨርሲቲ ከ23 ንግድ ቤቶች ከ1 አመት በላይ ሳይሰበሰብ የቆየ ውዝፍ ኪራይ እና በውሉ መሰረት የተቀመጠ 15% ቅጣት ሂሣብ፣ እንዲሁም ከሆስፒታሉ የዱቤ ተጠቃሚዎች ያልተሰበሰበ ብር 572,010.95 መኖሩ፤

በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ከንግድ ቤቶች፣ ከሪፈራል ሆስፒታል እና ከዓይደር ሆስፒታል የዱቤ ተጠቃሚዎች ያልተሰበሰበ ሂሣብ ብር 5,258,336.50 መኖሩ፤

4.1.2. ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ፤

አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው እና ሥራ ተቋራጮች ህንፃዎች በውላቸው ላይ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው ላደረሱት የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 30,129,181.96 ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ዝርዝሩም፡-

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	ከዕቃ አቅራቢዎች ያልተሰበሰበ	ከተቋራጮች ያልተሰበሰበ	ድምር
1	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	71,973.44	0.00	71,973.44
2	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ	0.00	6,374,020.00	6374020
3	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	617,590.58	0.00	617,590.58
4	በመቀሌ ዩኒቨርስቲ	3,395,373.68	527,041.04	3,922,414.72
5	በአክሱም ዩኒቨርሲቲ	138,234.13	7,347,911.16	7,486,145.29
6	በትምህርት ሚኒስቴር	22,285.06	0.00	22,285.06
7	በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	3,480,091.25	8,120,679.96	11,600,771.21
8	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	33,981.66	0.00	33,981.66
	ድምር	**7,759,529.8**	**22,369,652.16**	**30,129,181.96**

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

- ከህክምናና መድኃኒት ሽያጭ የዱቤ አገልግሎት በወቅቱ ያልተሰበሰበው ገቢ እና ከንግድ ቤቶች ሳይሰበሰብ የቆየ ውዝፍ ኪራይ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡
- ከላይ የተመለከተውን ቅጣት አቅራቢዎቹና ሥራ ተቋራጮቹ እንዲከፍሉ እንዲደረግና ለወደፊቱም ዕቃ አቅራቢዎችና ሥራ ተቋራጮች በውሉ መሠረት እንዲፈጽሙ በየጊዜው ተገቢ ክትትል ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.1.3. ያልተሰበሰበ የሥራ ግብር፤የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ግብር ክፍያ፤

- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ዓ.ም አንቀጽ 53 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 ዓ.ም አንቀጽ 24 ተራ ቁጥር 1 እና 2 በገኘው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,238,761.73 ከተለያዩ ህንጻ ስራ ተቋራጮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ቀሪ ማድረግ ሲገባው እና የቅድመ ግብር ክፍያ (withholding tax) ብር 980,722.26

ያልተሰበሰበ እናብር 31,036,019.15 ከተከፈላቸው ደመወዝ ያልተቀነሰ የሥራ ግብር መሆኑ ታውቋል፡፡/ ዝርዝሩ በአባሪ-9 ተመልክቷል/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

- ተቀናሽ ያልተደረገው የሥራ ግብር፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድመ ግብር ክፍያ (withholding tax) ከሚመለከታቸው ሠራተኞችና ድርጅቶች ተመላሽ ተደርጎ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ እንዲደረግና ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢ ቁጥጥር እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.2. ለገ/ኢ/ት/ሚር ሪፖርት ያልተደረገ በማነስ ሪፖርት የተደረገ የውስጥ ገቢና ወጪ

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ሥም	ገቢ	ወጪ
1	ዲላ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሉ	6,532,519.00	5,000,608.14
2	በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፤በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በማሳነስ	14,656,731.02	8,887,522.68
3	በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የእርዳታ የገቢ	2,346,370.16	0.00
4	በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፤የህይወት ፋና ሆስፒታል የውስጥ ገቢ	6,545,352.58	0.00
5	በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፤የብድርና የእርዳታ ገንዘብ፡	6,618,783.82	0.00
6	በአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ (ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል፤ጤናሳይንኮሌጅ፤ቴክኖሎጅ ኢንስቲቲዩት፤አርክቴክቸርና ህንጻ ግንባታ) የዉስጥ ገቢና የፕሮጀክት ሂሳብ ከወጪ ቀሪ	317,456,321.70	57,733,714.72
ድምር ብር		**354,156,078.28**	**71,621,845.54**

ከላይ በሰንጠረዥ የተገለጸው በበጀት ዓመቱ ከተሰበሰበ ገቢና ወጪ የሂሳብ ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የማይቀርብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

ማንኛውም ገቢ እና ወጪ በህጋዊ የሂሳብ ምዝገባ ቫውቸሮች መከናወን እንደሚኖርበት እና ገቢ በመግስት ሂሳብ አያያዝ መሰረት ተመዝግቦ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.3. ከመቀጠር ከሚገኘው ገቢ ግብርና ከተለያዩ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በእርዳታ የተገኘው በሂሳብ መደብ 5002 ልዩ ልዩ ተከፋዮች የሚመዘገብ መሆኑ

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ

- በዋናው ግቢና በተለያዩ ካምፓሶች የተሰበሰበው በጠቅላላው ብር 17,174,150.64 ከቅጥር የተገኘ ገቢ በሂሳብ መደብ 1101 መመዝገብ ሲኖርበት በሂሳብ መደብ 5002 ልዩ ልዩ ተከፋዮች በሚል የተያዘ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በእርዳታ ያገኘው በድምሩ ብር 4,448,928.23 የፕሮጀክት ፈንድ በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት /Charts of accounts/ መሰረት ገቢው በገቢ አርዕስት ወጪውም በወጪ አርዕስት ተመዝግቦ መያዝ ሲገባው፡በተከፋይ ሂሳብ በዴቢትና በክሬዲት በማቀናነስ እየተመዘገበ መሆኑ፤

4.4. በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች

- **በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፤**

በውሉ መሰረት አቅራቢዎቹ ዕቃውን ገቢ ማድረግ ባለባቸው ቀኖች ስላላስገቡ ላዘገዩበት ከድርጅቶቹ የተቀነሰው ከዋናው ግቢ ብር 1,236.61፤ ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 337,408.28 በድምሩ ብር 338,644.89 የጉዳት ካሳ ተቀንሶ በ1489 ሂሳብ መደብ ላይ የተመዘገበ ቢሆንም የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ፤

- **በአክሱም ዩኒቨርሲቲ**

የነጭ ጤፍ አቅራቢ ከሆነ ሮማን ከበደው ከ01/09/09 ጀምሮ 5000.00 ኩንታል ጤፍ እንዲያቀርብ ውል የገባ ቢሆንም በውሉ መሠረት ባለማቅረቡ ያስያዙት ዋስትና ብር 1,049,500.00 ተወርሶ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ መደረግ ሲገባው በቀን 22/03/2010 ዓ.ም ለባንኩ በተፃፈ ደብዳቤ ያስያዙት ቦንድ እንዲታገድላቸው ብቻ የጠየቁ መሆኑ

- **በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ**

በአገር ዉስጥ ገንዘብ የሚሰበሰበው ገቢ በገቢ ደረሰኝ መሂ/1 ወይም ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ በሚታተም ደረሰኝ ብቻ መሆን እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ከሐምሌ

1/2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም በገቢ ሂሳብ ሂሳብ መደቦች 1443 እና 1489 ብር 4,623,489.88 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ የሰበሰበ መሆኑ፣

- **በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጥቁር አንበሣ ሆስፒታል**

መድሃኒት በመደበኛ በጀት የሚገዛ እና ከመድሃኒቱ ሽያጭ በበጀት ዓመቱ ብር 18,376,464.77 እንደተሰበሰበ በሂሳብ ሪፖርት ላይ የተመለከተ ሲሆን መድሃኒቱ በመደበኛ በጀት የተገዛ በመሆኑ በመልሶ መሸጥ የተገኘው ገቢ ሂሳብ ለበጀት መተኪያ ተደርጎ መመለስ ሲገባው አላግባብ ወደ ሆስፒታሉ የውስጥ ገቢ ሂሳብ አካውንት ገቢ የተደረገ መሆኑ፤

- በሂሳብ ሪፖርቱ መሰረት በገቢ ሂሳብ አርዕስት 1437 ከጤና ምርመራና ህክምና የተሰበሰበው ብር 11,690,474.40 የተለያዩ አገልግሎቶች ለተሰጠበት የተሰበሰበ ሂሳብ ሲሆን ገቢው በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ እንዲያስችል ለገቢ አይነቶቹ ሌጀር የሌለ በመሆኑ ትክከለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- ከግል ህክምና በበጀት ዓመቱ ብር 5,673,301.59 እንደሰበሰበ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የተመለከተ ሲሆን በመመሪያው መሰረት 14% ለሆስፒታል ገቢ መሆን እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም ከገቢው ላይ 14%ቱ ብር 794,262.22 (5,673,301.59*14%) ገቢ ለመሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ የሌለ መሆኑ

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ወደ መንግስት ካዝና ገቢ መደረግ ያለበት ገቢ እንዲደረግ
- ማስረጃ ለሌላቸው ማስረጃው እንዲቀርብ
- ሌጀር ለሌላቸው እንዲዘጋጅላቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

<u>በውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006 መሠረት ለቦርድ ቀርቦ ሳይፀድቅ የተከፈለ</u>

በውስጥ ገቢ መመሪያ ቁጥር 39/2006 መሠረት ገቢውን ለማመንጭት የሚወጣው ወጪ ከተገቢው ዝርዝር ጋር ለቦርድ ቀርቦ ሳይፀድቅ በበጀት ዓመቱ በ6 መ/ቤቶች ብር **39,648,133.82** ከውስጥ ገቢ በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የተደረገ መሆኑ፤/ዝርዝሩ በአባሪ-26 ተመልክቶል/

5.1. የግዥ ህግ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፤

5.1.1. ግኝት፤

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው እና ከታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በድምሩ ብር 198,603,552.67 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ግዥዎች ተፈጽመው ተገኝተዋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-21 ተመልክቷል/

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

- በአጠቃላይ ድምር የብር 23,744,152.98 የስጋ እንዲሁም የተለያዩ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጥንድ አልጋ፣ ሎከር፣ ቴብል ቼር፣ ጠረጴዛ ከዩኒቨርሲቲው ኢንተርፕራይዝ ያለውድድር ግዥው በቀጥታ የተፈጸመ መሆኑ፣
- ለኬሚካል፣ ለሲቪል ኢንጅነሪንግ፣ ለኤሌክትሪካል እና ለሜካኒካል ት/ክፍሎች የሚያገለግሉ በአንድነት በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም የሚገባቸው በድምሩ የብር 5,314,995.80 የላቦራቶሪ ዕቃዎች ተከፋፍለው በዋጋ ማቅረቢያ የተገዙ መሆኑ፣ በተጨማሪም፣እቃዎች በተፈላጊ ባህርያት ዝርዝር /Specification/ ለመቅረባቸው ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ወይም የጥራት አረጋጋጭ ኮሚቴ የጽሑፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ እቃዎቹ ገቢ የሆኑ እና ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

- ዩኒቨርስቲዎቹ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲፈጽም፣
- የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት በመሆኑ አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እድል እንዲኖራቸው በዙር ሁሉም ሊሳተፉ የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበትና የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑንና

ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.1.2. ዝቅተኛ ዋጋ ቀርቦ እያለ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ የተፈጸሙ ግዥዎች

- **በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ** ለግዥዎች ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ አቅራቢዎች እያሉ ግዥዎቹ ግን ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት በመፈጸማቸው በድምሩ ለብር 131,671.15 ተጨማሪ ወጪ እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህም ቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ የማቻል መሆኑ ታውቆ ከአዋጁ ውጪ ለተፈጸመዉ ግዥና አላግባብ ለወጣዉ ገንዘብ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት ሊቀርብ እና ለወደፊቱም በዚህ ረገድ ጥንቃቄ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.2. የዳሰሳ ጥናት ሳይደረግ የተወሰኑ አቅራቢዎችን ብቻ

በተደጋጋሚ በመጋበዝ የተፈጸመ ግዥ

- **በዲላ ዩኒቨርሲቲ** ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚዉል የጤፍ ግዥ ሲፈፅም በመመሪያው መሰረት የእህል ንግድ ድርጅት ወይም ሁለገብ የገቢያ ህብረት ስራ ዩኒየኖች የሚሸጡበትን ዋጋና አቅርቦት አስተማማኝነት ከሌሎች አቅራቢዎች የተሻለ መሆኑን የዳሰሳ ጥናት ለመደረጉ የሚገልፅ ማስረጃ ሳይኖር፣ በሀገሪቱ በርካታ ህብረት ስራ ማህበራት እና ዩኒየኖች እያሉ በተደጋጋሚ ሎሚ አዳማ የገበሬዎች ህ/ስ/ማ፣ ግዮን ሁለገብ የገበሬዎች ህ/ስ/ማህበር፣ የረር ህ/ስ/ዩኒየን እና ጎጎ ፅዮን ህ/ስራ ዩኒየን ብቻ በመጋበዝ በጠቅላላው ድምር የብር 12,773,400.00 ጤፍ በመመሪያው መሰረት ግዥው ያልተፈፀመ መሆኑና የተቋቋመው ኮሚቴ የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰብ እና የዳሰሳ ጥናት ማድረግ ሲኖርበት የዋጋ ማወዳደሪያውን ከሰበሰበ በሁዋላ እዛው የሚከፍት መሆኑ፣

የማሻሻያ ሀሳብ

- በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት በማድረግ እንዲሁም በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ከተሳተፉት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ያቀረበው

ዋጋ ጋር ተመሳክሮ ዋጋው የተጋነነ መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ግዥውን መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.3. መ/ቤቱ ለፈጸመው ግዢ በወቅቱ ክፍያ ባለመክፍሉ ምክንያት

ያለአግባብ የተከፈለ የወለድ ቅጣት፣

በትምህርት ሚኒስቴር ለከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎችን ለመግዛት የሚያማክር የግዥ አማካሪ መ/ቤቱ ክፍያውን ሳይከፍል በመቅረቱ ድርጅቱ ክስ በመመስረቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 13/01/2009 በዋለው ችሎት በጠቅላላው 5 ዓመት ከ7ወር ያልተከፈለውን ብር 963,577.48 እና 9% ህጋዊ ወለድ ብር 484,197.68 በድምር ብር 1,447,775.15 እንዲከፍል በፍርድ ቤቱ በመወሰኑ መ/ቤቱ አላግባብ ለብር 484,197.68 የክትትል እና የአሰራር ችግር ምክንያት መ/ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለወደፊቱ በመመሪያውና በውሉ መሰረት ግዥዎችን በመፈጸም ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ያለበት ሲሆን ከላይ የተጠቀሰውን ችግር በወቅቱ የተከናወነውን የግዥ ሂደትና ያለበትን ደረጃ ተከታትሎ ክፍያ እንዲፈጸም ባለማድረጉ መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጭ እንዲዳረግ ያደረጉ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

5.4. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፤

5.4.1. ግኝት፤

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ (የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ፤ በኮፒ ማስረጃ የተወራረደ፤ ለቀን ሰራተኞች የሰዓት መቆጣጠሪያ (Attendance sheet) የሌለው፤ የዕቃዎች ጥራት በቴክኒክ ኮሚቴ ወይም በሚመለከተው ባለሙያ የፅሁፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ፤ የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ሳይሞላ፤ በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ….) በ19 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **382,858,985.30** ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ፡ አባሪ-17 ተመልክቷል/

- በውጪ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ድጋፍ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዲፕሎማቲክ፤ ሚሲዮኖችና እና በዩኒቨርሲቲዎች የባንክ ሂሳብ ገቢ ለተደረገበት የባንክ ማስረጃ ቢኖርም ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው ላይ መሆናቸውንና የተላከው የኪስ ገንዘብ በትክክል

ለተማሪዎች መድረሱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳይቀርብ በድምር ብር 157,383,533.13 ክፍያ በመፈጸም በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፤

- **በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ** የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9/3 ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጅናል የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ተገለጸ ቢሆንም ለመኪና ጥገና ለኢትዮ ኒፖን አክ/ማህበር ለተከፈለ ብር 69,683.18 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ከወጪ ማስመስከሪያው ጋር ባለመያያዙ የተፈጸመዉ ክፍያ ዩንቨርሲቲዉ ላገኘዉ አገልግሎት መሆኑን ለማረጋገጥ ሳይቻል መቅረቱ፣

በአርባ ምንጭ

- በጠቅላላ ድምር ብር 3,066,428.88 በቂ ማስረጃ ሳይቀርብ መወራረዱ፣
- በዋናው ግቢ ለኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ አገልግሎት ግዥ ለኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ ደቡብ ሪጅን ብር 216,287.47 እና በአባያ ካምፓስ ለጽዳት ዕቃዎች ግዥ ብር 49,606.00፣ በድምሩ ብር 265,893.47 ከባንክ የወጪ ማስመስከሪያው ጋር የተያያዘው የክፍያ ማስረጃ ኮፒ መሆኑ፣

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

- በሪፈራል ሆስፒታል በድምሩ ብር 185,109.75 ለጤና ባለሙያዎች የተረኝነት አበል ክፍያ ሲከፈል ወሩን መሉ ቀንም ማታም የጤና ባለሙያዎቹ ስራ ገብተው ስለመስራታቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ ባለመቅረቡ የክፍያውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- አዲስአበባ ዩኒቨርስቲ ለአራዳ ክ/ከ/ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ብር 9,048,008.39 የካሳ ክፍያ ሲፈጽም በኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ቁጥጥር ባለሥልጣን እና በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በጋራ ተጠንቶ በከተማው ካቢኔ በሚጸድቅ ነጠላ ዋጋ መሠረት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ የተከፈለ ብር 36,950,514.06 የዕቃዎች ጥራት በቴክኒክ ኮሚቴ ወይም በሚመለከተው ባለሙያ የፅሁፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ የሚለው ይገኝበታል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ የዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር (Specification) መሠረት መቅረቡን ወይም

አገልግሎት መስጠቱን፣ ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ማረጋገጫውም ተጠያቂነትን በሚያስከትል መልኩ እንዲቀመጥ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር እርምጃ መውሰድ እንዳለበት፣

5.5. በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተመዘገበው ወጪ

ተ.ቁ	የመ/ቤቱስም	የገንዘቡ ልክ
1	በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	20,426,334.68
2	በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	8,926,290.16
3	በጎንደር ዩኒቨርሲቲ	3,155,087.83
4	በአርሲ የኒቨርሲቲ	2,873,129.51
5	በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ	1,804,585.61
6	በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	4,493,020.81
ድምር		**41,678,448.60**

የማሻሻያ ሃሳብ፣

አቅራቢዎቹ ህጋዊ ኦርጂናል ደረሰኝ እንዲያመጡ ማድረግ እንዳለባቸውና ከደንብና ከመመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸም የመንግስት በጀት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል በጻፍነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.5.1. ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈጸሙ ክፍያዎች፤

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ከፋይናንስ ደንብና መመሪያ ውጭ ለስፔሻሊስት ሐኪሞች ቶፕአፕ እና ክሊኒካል አበል፤ በዩኒቨርሲቲዎች ሥራ አመራር ውሳኔ ለሐኪሞች ማበረታቻ /ቶፕአፕና ለሌሎች ሰራተኞች አበል፤ መኖሪያ ቤት ላገኙ የአካዳሚክ ባለሙያዎች አላግባብ የተከፈለ የቤት አበል፤ ለተለያዩ የኮሚቴ አባላት ለማበረታቻ በሚል የተከፈለ፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ሚ/ር ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ለትርፍ ሰዓት ሥራና ለትራንስፖርት የተከፈለ፤ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር የተፈጸመ ክፍያ፤ ....) በ16 መ/ ቤቶች በድምሩ ብር 77,263,498.42 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ- 19 ተመልክቶል/

- ከዚህ ውስጥ እንደ ማሳያ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው በድምሩ ብር 880,800.00 የቤት ኪራይ

አበል የተከፈለ መሆኑ፣ ለግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ፤ ም/ስራ አስኪያጅ እና በጽ/ቤቱ ሥር ለሚገኙ ባለሙያዎች በየወሩ ብር 4000.00 የቶፕአፕ ክፍያ በድምሩ ብር **233,599.96** ከደንብና መመሪያ ውጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ኮሌጆች በአስተዳደር የሥራ መደቦች ላይ የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በተደራቢነት በመመደብ በስራ አመራር ውሳኔ መሠረት የአንዋላይዜሽን እና የኃላፊነት አበል በድምሩ ብር **973,595.00** የተከፈለ መሆኑ እና ለምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር 30,000.00 እና ለኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ተቋም ብር 100,000.00 በድምሩ **130,000.00** መንግስታዊ ለሆኑ መ/ቤቶች ከመመሪያ ውጭ ለድጋፍ በሚል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ለተለያዩ ኮሚቴዎች በድምሩ ብር 219,929.45 **በሠመራ ዩኒቨርሲቲ** በሰራተኞች ስነ ምግባር ለተሳተፉ አራት የኮሚቴ አባላት በድምሩ ብር 60,000.00 **በዲላ ዩኒቨርሲቲ** ዩኒቨርሲቲው የዲሲፕሊንና የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ፣ ሂሳብ ሰራተኛ፣ የተ/ዲሲ/ኮሚቴ፣ አስተባባሪ፣ የክሊኒክ ሰራተኞች ማበረታቻና አስተዳደር ሰራተኞች ቤት አበል፣ TDP ማበረታቻ እና ተከታታይ ትምህርት ማበረታቻ በሚል፣ የክረምት ዲግሪና ድህረ ምረቃ ፕሮግራም ስራ ላይ የተሳተፉ በሚል በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት በተወሰነው መሰረት በሚል ለፕሬዚዳንት ለስርዓተ ፆታ ጉዳይ ፅ/ቤት፣ የክረምት ፕሮግራም የአስተዳደር ሰራተኞች ክፍያ፣ ተከታታይና ርቀት ትምህርት ማበረታቻ፣ እና የክፍል ኃላፊዎችና ከፍተኛ ኃላፊዎች ማበረታቻ እና የመሳሰሉት በማለት በኦዲት ናሙና ከታዩት ውስጥ ብቻ በጠቅላላው ድምር ብር **8,379,468.42** አላግባብ በአስተዳደር ካውንስል ውሳኔ መሰረት ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ፣

- በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ለተማሪዎች ምግብ የሚውል የምግብ ዘይት ከሀማሬሳ የምግብ ዘይት አክሲዮን ማህበር በድምሩ ብር 231,731.40 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 ከሚያዘው ውጭ እና አስቀድሞ በተፈቀደ በጀት ሳይያዝ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ መከፈሉ፣
- በወሎ ዩኒቨርሲቲ የበጀት እጥረት በታየባቸው የሂሳብ መደቦች ከውስጥ ገቢ ወጪ እየሆነ እንዲከፈል የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድ በወሰነው መሰረት በኮምቦልቻ ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት ከውስጥ ገቢ ለመደበኛ ሥራዎች ግዥ ብር 793,916.70 የተከፈለ መሆኑ፤ ከተገለጹት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- አአ ዩኒቨርስቲ በእንስሳት ህክምና እና ግብርና ኮሌጅ ብር 39,375.00፤ በማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ ብር 163,981.20፤ መኖሪያ ቤት ላገኙ የአካዳሚክ ባለሙያዎች የሚከፈላቸው የቤት አበል ሙሉ በሙሉ መቆም /መቋረጥ/ ሲገባው አላግባብ የተከፈለ የቤት አበል መኖሩ፤

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ

- መምህራን ከሚሰሩበት ዩኒቨርሲቲ ተንቀሳቅሰው ሀገር ውስጥ ወደሚገኝ ሌላ ዩኒቨርሲቲ የሄዱ ሶስቱንም ድጋፎች (የቤት ኪራይ፤ የፅህፈትና የትራንስፖርት) እንደሚያገኙ እና በሚሰሩበት ዩኒቨርሲቲ የሚሰለጥኑ ደግሞ ከቤት ኪራይ ድጋፍ በስተቀር ሌሎች የድጋፍ ዓይነቶችን እንደሚያገኙ የተመለከተ ቢሆንም፣ በሠመራ ዩኒቨርሲቲ እየሰሩ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሰለጥኑ መምህራን የቤት ኪራይ ድጋፍ ተቀንሶ ክፍያ መፈፀም ሲገባ፤ በናሙና በታየው የሰኔ/2009 ደመወዝ መሰረት ለ10 መምህራን በድምሩ ብር 7,000.00 አላግባብ የቤት ኪራይ ድጋፍ የተከፈለ መሆኑ፤
- የጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ"MPH"' ድህረ ምረቃ ፕሮግራም በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ እንግዳ /ተጋባዥ/ መምህራንን /Guest lecturers/ በማስመጣት የተለያዩ ትምህርቶችን እንዲያስተምሩ ውል ያስገባ /ያሰረ/ ሲሆን፤ የተገባው ውለታ ላይ ለመምህራኑ የሚከፈለው ተመን /Rate/ በክሬዲት ሃወር /በሰዓት/ ምን ያህል እንደሆነ ውሉ ላይ ሳይገለፅ፤ ለአንድ እንግዳ መምህር በጥቅሉ 16,000.00፣ 24,000.00 እና 32,000.00 በማሰብ፣ በድምሩ ብር 224,000.00 አላግባብ ከመመሪያ ውጪ ከውስጥ ገቢ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በዲላ ዩኒቨርሲቲ

- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 5.4 (ለ) የውስጥ ገቢን በመጠቀም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ተሸከርካሪ መግዛት እንደማይቻል የተገለጸ ቢሆንም ለዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል የአምቡላንስ ግዥ ለማከናወን ብር **1,987,764.72** ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጤና ቢሮ ተራድኦ ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን ክፍያው ከመመሪያው ውጭ ከመሆኑም በተጨማሪ ሆስፒታሉ ላልተረከበው ንብረት የሂሳብ ምዝገባ ሲያከናውን በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የመዘገበ መሆኑ፣

- የመኖሪያ ቤት ለሰጣቸዉ በበጀት ዓመቱ አላግባብ ከመመሪያ ዉጪ ብር 224,585.33 እና እንግዳ ማረፊያ ለተሰጣቸዉ 6 ግለሰቦች አላግባብ በቀን ብር 200.00፣ በዓመት ደግሞ ለ6ቱ ብር 432,000.00 (200.00*30 ቀን*6 ሰው*12 ወር) እየተከፈለ እያለ አለአግባብ በየወሩ የቤት አበል ብር 69,600.00፣ በድምሩ ብር **294,185.33** ቤት ለተሰጠቸዉ የተከፈለ የቤት አበል ሂሳብ መኖሩ፤፡
- ለትምህርት ወይም ለስልጠና ከ1 ወር በላይ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ለሚላኩ በመመሪያው መሰረት ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ሳያካትት በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው ብቻ እንደሚከፈል የተገለጸ ቢሆንም ለመምህር ይርጋለም አበበ (ቱርክ)፣ ይልቃል ተስፋዬ እና ማርቆስ ፍሰሃ (ኔዘርላንድ)፣ አብይ ሰብስቤ (ህንድ) የቤት አበል ብር 37,800.00 እና Student Allowance ብር 9,450.00፣ በድምሩ ብር **47,250.00** ከመመሪያ ዉጪ የተከፈለ መሆኑ፣
- ክፍያ ከፍለው ቅዳሜ እና እሁድ የሚማሩ ተማሪዎችን ላስተማሩ መምህራን የትርፍ ሰአት የተከፈለው ሂሳብ ከተገቢው የክፍያ ምንጭ ከውስጥ ገቢ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር **4,091,988.70** ከመደበኛ በጀት ወጪ ሆኖ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
- ለትምህርቱ ጥራት ሲባል በወር ውስጥ ከ18 Crh መብለጥ እንደሌለበት የተቀመጠ ሲሆን ሰተለያዩ ሀኪሞች የደመወዝ ክፍያ ሲፈጸም አላግባብ በወር ውስጥ ከ160 Crh — 368 Crh መማር ማስተማር ሰርተዋል በሚል በአስተዳደር ካውንስል ውሳኔ ውል በመግባት ለአንድ ሰው ከብር 15,000.00 — 50,000.00 በመክፈል በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብቻ ብር **2,468,678.57** ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣

ሀዋሳ ኒቨርሲቲ

- ለትምህርት ወይም ለስልጠና ከ1 ወር በላይ ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ለተላኩ በመመሪያው መሰረት ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ሳያካትት በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው ብቻ እንደሚከፈል የተገለጸ ቢሆንም ውጭ ሀገር ትምህርት ላይ ላሉ ሰዎቹ ብር 11,517.00 የአኑዋላይዜሽን፣ ብር 2,000.00 የትራንስፖርት አበል፣ ብር 32,000.00 የቤት አበል እና ብር 7,500.00 የሃላፊነት አበል፣ በድምሩ ብር **53,017.00** ከመመሪያ ዉጪ የተከፈለ መሆኑ፣

- በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የቤት አበል ለማይገባቸው ለቴክኒካል አሲስታንስ I፣ II እና III በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ ብር 250.00 እና 239.81 ተመን በመፍቀድ በድምሩ ብር 281,046.31 የቤት አበል የተከፈለ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ክፍያዎችን ከደንብና መመሪያ ውጭ መፈጸም ተገቢ አለመሆኑን ገልጸን በመንግስት የፋይናንስ መመሪያ ያልተደገፉ ክፍያዎች እንዲቋረጡና አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.5.2. <u>በአንድ በተመሳሳይ ሰነድ ሁለት ጊዜ የተወራረደ እንዲሁም በድጋሚ የተከፈለ ሂሳብ</u>

- **በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ** ለኢትዮ ኒፖን የቴክኒክ ማህበር ለመኪና ጥገና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 54993 ብር 333,210.95፣ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 54963 ብር 45,489.42፣ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 91480 ብር 84,284.19 በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቀርቦ የተወራረደ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለእነዚሁ አገልግሎት በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ በመገኘቱ፣ በድምሩ ብር **462,984.56** በአንድ በተመሳሳይ ሰነድ ሁለት ጊዜ አለአግባብ መወራረዱ፣
- **በዲላ ዩኒቨርሲቲ** ለሁለት ዶክተሮች የጥር/2009 ክፍያ ብር 127,942.00 በድጋሚ የተከፈለ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፤

- ያለአግባብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ የተገኘው ብር **462,984.56** ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እና ይህ ሰነድ እንዲወራረድ ባደረጉ ሰራተኞች ላይ የዩኒቨርስቲው አስተዳደር አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡
- በድጋሚ የተፈጸመው ክፍያ በበጀት ዓመቱ ከተፈጸሙ ተመሳሳይ ክፍያዎች ክፍያዎዎች ጭምር በውስጥ ኦዲት ተሰልቶ ከግለሰቦቹ ላይ ተመላሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ በማድረግ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡

5.5.3. <u>በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር</u>፤

የኮንትራት/ጊዜያዊ ሠራተኞች በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት ሳይመደቡ ወይም ዘላቂነት ከሌለው የሥራ መደብ ላይ ሳይሰናበቱ እና ዩኒቨርሲቲው በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጠይቆ ሳያስፈቅድ በ6 መ/ቤቶች ብር 10,518,758.51 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 9/1 ተመልክቷል/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በቋሚ ሰራተኞች በውስጥ ደረጃ እድገት ወይም በውጭ ቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞቹ ሊመደቡ /ሊቀጠሩ/እንደሚገባ በቀን ሰራተኛነት እየተከፈለ ያለው ክፍያም እንዲቆም፡፡ ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንተራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ እንዳለበት እሳስበናል፡፡

5.5.4. <u>የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች፤</u>

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር (ተመራማሪዎች ጥናት ላቀረቡበት፤ ፤ ለድህረ ምረቃ (Msc and Phd) ተማሪዎች ፈተና ለፈተኑበት/ለገመገሙበት (Internal and External Examiner/Session) እና የማማከር አገልግሎት ለሰጡበት (Supervision) በጥቅሉ የHonorarium ክፍያ ከሚመለከተው አካል የጸደቀ የክፍያ ተመን ሳይኖረው በአስተዳደር ካውንስል በተወሰነው ተመን መሰረት፤ የመመረቂያ ጽሑፍ ለሚያማክሩ አማካሪ መምህራን፤ ፈተና ለማረም፣ አሳይንመንት ለማረም፣ ፈተና ለማዘጋጀት፣ ፈተና ሱፐርቫይዝ ለማድረግ፣ ለሞጁል ዝግጅት እና ለሞጁል ኤዲተር፤ ለተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ የሚያዘጋጁበት የፋይናንስ ድጋፍ፤ የተማሪዎች የመመረቂያ ፅሁፍ ለገመገሙበት፤ ሞጁል ላዘጋጁ፣ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ላስተማሩ፣ ፈተና ለፈተኑ እና ላማከሩ፤ ...ወ.ዘ.ተ) በ11 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 22,957,437.32 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ-9/2 ተመልክቷል/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

- በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ማስፈፀሚያ ተመን ውስን በመሆኑና ሁሉንም የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች የተማሪ ምርምር ስራን ማማከር፤ ፈተና ማውጣት፤ ፈተናና አሳይመንት ማረም፤ ሞጁል ማዘጋጀትና ኤዲት ማድረግ፤ የክትትል ስራ መስራትና ለመሳሰሉት በመንግስት የወጣ ተመን ባለመኖሩ ወይንም ባለመካተቱ ክፍያው በአብዛኛው ዩኒቨርስቲዎች የአከፋፈል ስርዓቱና የክፍያ መጠኑ የተለያየ በመሆኑ ለዩኒቨርቲው ተገቢነት ካለው ለትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በማቅረብ ሲፈቀድ ብቻ ሊከፈል ይገባል፡፡

ክፍያዎች በደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ለዩኒቨርስቲዎች ስራ አመራሮች አሳስበናል፡፡

- የዩኒቨርሲቲዉ አስተዳደር በመንግስት የወጡ ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና አዋጅ በተገቢዉ ተግባራዊ ለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚጠበቅበት እና አለአግባብ ከመንግስት መመሪያ ዉጭ የተከፈለ የማበረታቻ ክፍያ ተገቢ ባለመሆኑ ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ ሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

5.5.5. የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት፤

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግኝቱ መግለጫ	የገንዘቡ ልክ
1	**ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ**	ለግንባታ ሥራ አገልግሎት እንዲውሉ ሁለት ተሽከርካሪዎች (ቶዮታ ፒክአፕ) በብር 7,383,772.80 የተገዙ ሲሆን በዕቃ ገቢ ደረሰኝ (የሞዴል 19) ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ	7,383,772.80
2	**አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ**	ለብር 292,692.00 የህትመት ግዥ እና ለብር 57,500.00 የቁልፍ መያዣ ግዥ በአጠቃላይ ድምር የብር ክፍያ ሲፈፅም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተያየዘ መሆኑ፣	350,192.00
3	**ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ**	ዩኒቨርሲቲው ከGIZ ጋር በገባው ውል መሰረት ለመሰረተ-ልማት ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ገዝቶ ለተወራረደው ብር 1,662,342.75 ዕቃው ገቢ ስለመደረጉ የሚያመለክት ማስረጃ፣ ያልቀረበ መሆኑ፤	1,662,342.75
ድምር			9,396,307.55

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ዩኒቨርሲቲዎቹ በማንኛውም በግዥ የሚረከቧቸውን ንብረቶች ጥራታቸውና የተፈለገው ዕቃ ስለመቅረቡ በባለሙያ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት በንብረት ገቢ ደረሰኙ መሰረት ክፍያ ሊፈጸም እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.5.6. <u>በብልጫ የተከፈለ</u>፤

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ለደመወዝ፤ ለውሎ አበልና ትራንስፖርት፤ ለግንባታ ሥራዎች፣ ለተለያዩ የዕቃ ግዢ፣ የአገልግሎት ክፍያዎች በ12 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 6,955,326.20 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

<u>ማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በብልጫ የተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ ክፍያዎች በጥንቃቄ እንዲፈጸሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.6. <u>በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ፤</u>

5.6.1. <u>ግኝት</u>

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ሂሳቦች በተገቢው የሒሳብ መደብ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ በ14 መ/ቤቶች ብር 282,669,321.13 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ አባሪ-25 ተመልክቶል/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ማንኛውም ሂሳብ በትክክለኛ የሂሳብ መደብ (ኮድ) ለመመዝገቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5.7. ከመመሪያ ወጭ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ

5.7.1. ግኝት

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግኝቱ መግለጫ	የገንዘቡ ልክ
1	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	ዩኒቨርሲቲው ላቋቋማቸው የጃንተከል ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ ሰራተኞች ደመወዝ ብር 211,303.34 እና የብሩህ ሆቴልና መስተንግዶ ኢንተርፕራይዝ ሠራተኞች ደመወዝ ብር 501,073.00 የራሳቸውን ወጪ በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ ማድረግ ሲገባ፣በድምሩ ብር 712,376.34 በበጀት ዓመቱ ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ የተከፈለ መሆኑ፣	712,376.34
2	አአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	በሥራ ገበታቸዉ ላይ ላልነበሩ (ከሥራ ለለቀቁ)	12,273.00
		ለውጪ ሀገር መምህራን ትምህርት ሚኒስቴር ለሙያ መስክና ደረጃ ካስቀመጠው ጣሪያ (Scale) በላይ፤	$ 12,400.00
3	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	ለውጪ ሀገር መምህራን ትምህርት ሚኒስቴር ለሙያ መስክና ደረጃ ካስቀመጠው ጣሪያ (Scale) በላይ	$ 37,590.00
		በሀገር ውስጥ እና በውጪ ሀገር ትምህርታቸውን የሚከታተሉ መምህራን በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተመለሱ ሲሆን አካዳሚክ ባለሙያዎች ትምህርታቸውን ላለመጨረሳቸው ከሚማሩበት ተቋም ማረጋገጫ ሳይቀርብ የተከፈለ፤	499,693.50
4	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	በአባያ እና በኩልፎ ካምፓስ መምህራኑ ከዩኒቨርሲቲው ለቀው ሳለ ደመወዝ የተከፈላቸው መሆኑ፣	33,400.00

የማሻሻያ ሃሳብ፣

- የደመወዝ ክፍያ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

- ያለአግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ መመሪያው ተጠብቆ እንዲሰራ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.8. <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>፤

5.8.1. <u>ግኝት</u>፤

የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ11 ዩኒቨርሲቲዎችና በ1 መ/ቤት በድምሩ ብር 56,698,992.36 የ2005 እና 2008 በጀት ዓመት የወጪ ሂሳቦች በ2009 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ /ዝርዝራቸውም በአባሪ- 24 ቀርቧል፡፡/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.9. <u>የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ</u>፤

5.9.1. <u>ግኝት</u>፤

ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

ለጤና ሞያተኞች በቀረበው ጥናት መሰረት በተራ ቁጥር ስድስት ላይ የፀደቀ ሲሆን የተረኝነት አበል ክፍያ የሚያገኙ የስራ ክፍሎች ከሙያ ውጪ ያሉ ባለሙያዎች የተረኝነት አበል የማይገባቸው መሆኑን የተገለፀ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ቀናቶች የተረኝነት አበል ክፍያ ለማይገባቸው ክፍሎች በኦዲት ናሙና ከወደቁት ውስጥ በድምሩ ብር 248,497.22 በሆስፒታሉ ለሚሰሩ ለገ/ያዥ እና ለካርድ ክፍል ትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲከፍል ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛው ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ1.25 ተባዝቶ፣ ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛ ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ1.5 ተባዝቶ፣ በሳምንት የእረፍት ሰዓት ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛ ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ2 ተባዝቶ እንዲሁም በህዝብ በዓላት ቀን ለሚሰራ ትርፍ ሰዓት ለመደበኛ ስራው በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ2.5 ተባዝቶ ሂሳቡ ያልተሰላ እና በሰነዱ ላይ ሰራተኞቹ የሰሩበት ቀን ከላይ በቀረበው ዝርዝር መሰረት ሰዓቱ ተከፋፍሎ ሳይቀመጥ ለጤና ሞያተኞች በተፈቀደው የተረኝነት አበል ክፍያ ስሌት መሰረት በትርፍ ሰዓት የሰሩበት ቀን ብዛት ወደ

ሰዓት ተቀይሮ በሰራተኞች የአንድ ሰዓት ደመወዝ በማብዛት ሂሳቡ የተሰላ በመሆኑ የየትርፍ ሰዓት የክፍያው ስሌቱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉ ታውቋል፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የትርፍ ሰዓት ክፍያ በአግባቡ እንዲፈጸም በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.10. <u>ሳይጸድቁ የቀሩ ወጪዎች መሰረዝ የነበረባቸው አላግባብ በወጪ የተመዘገበ</u>

አአ ዩኒቨርስቲ የወጪ ምዝገባ ሲከናወን ሳይጸድቁ የቀሩ ወጪዎች መሰረዝ የነበረባቸው ቢሆንም በዋናው ግቢ ብር 2,399,856.25፣ በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ብር 128,602.60፣ በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ብር 200,709.58 ሳይሰረዙ በመቅረታቸው በድምሩ ብር 2,729,168.43 የወጪ የሂሳብ ሪፖርቱን መታየት ካለበት በላይ እንዲታይ ያደረገው መሆኑ፤

5.11. <u>የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ</u>፤

5.11.1. <u>ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ</u>፤

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ የግንባታ ሥራዎችን አጠናቀው ያስረከቡና ሥራውን ያቋረጡ ሥራ ተቋራጮች ተመላሽ ያላደረጉት የቅድሚያ ክፍያና የማቴሪያል ሂሣብ ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ብር2,283,138.16 እና ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ብር1,293,000.75 በድምሩ ብር 3,576,138.91 ተገኝቷል፡፡

- **በወላይታ ዩኒቨርሲቲ** የግንባታ ሥራዎች 80% ሲሆናቸው የሥራ ተቋራጮች የወሰዱትን ቅድሚያ ክፍያ ሙሉ በሙሉ መመለስ ሲኖርባቸው ከ7 (ሰባት) ሥራ ተቋራጮች በድምሩ ብር 2,283,138.16 የግንባታ ቅድሚያ ክፍያ በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ እና በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

5.12. <u>በትምህርት ሚኒስቴር 11 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስለተከፈለ የቅድመ ክፍያ ሂሳብ</u>

5.12.1. <u>ግኝት፡-</u>

በትምህርት ሚኒስቴር የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት የ11 ዩኒቨርሲቲዎች የግንባታና መሰረተ ልማት እስከ ሰኔ 30/2009 ለኦዲት በቀን 12/12/2009 በቀረበው ዝርዝር መግለጫ መሰረት የኦዳቡሉቱም ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ለማከናወን ከ11 ህንጻና የግንባታ ስራ ተቋራጮች ጋር በቀን 20/08/2008 እና ከአንድ የመሰረተ ልማት ተቋራጭ

ጋር በቀን 05/07/2009 ውል የተያዘ ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው ግንባታ የሚውል የቦታ ርክክብ ሳይደረግና ዩኒቨርሲቲው ለሚገነባበት አካባቢ ላሉ ተነሺዎች የካሳ ግምት ሳይቀርብና ካሳ ሳይከፈላቸው አስቀድሞ ውል ከመያዙ በተጨማሪ የህንጻ የስራ ተቋራጮች የቦታ ርክክብ ሳያደርጉና ወደ ስራ ሳይገቡ ቅድመ ክፍያ ለ9 ኮንትራክተሮች የዋናውን ውል 20% በ2008 በጀት ዓመት በድምር ብር 40,594,366.64 ከአንድ ዓመት በላይ እና ለአንድ ኮንትራክተር በ2009 15% ብር 31,442,798.11 ከሶስት ወር በላይ ምንም ዓይነት ስራ ሳይሰራ የተከፈለ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2009 በድምር ብር 72,037,164.75 የመንግስት ገንዘብ በህንጻ ግንባታና መሰረተ ልማት ስራ ተቋራጭ ድርጅቶች እየተጠቀሙበት መሆኑ

የማሻሻያ ሃሳብ

- ተቋራጭ ድርጅቶቹ ስራ የሚጀምሩበት ሁኔታ ሳይመቻች እና ስራውን ለመጀመር የተመቻቸ ሁኔታ ሳይኖርና ስራ ሳይጀምሩ ቅድሚያ ክፍያ መክፈል የመንግስት ገንዘብ ለግለሰቦች ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያስችል አሰራር በመሆኑ ለወደፊቱ እንዲህ ዓይነት ክፍተት እንዳይፈጠር ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡
- ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለገው ገንዘብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.12.2. **በአግባቡ ያልተመዘገቡ የግንባታ ክፍያዎች፤**

በጅማ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ፤

- በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 22,898,293.64 የግንባታ መያዣ ሂሰብ (Retention) ከህንጻ ስራ ተቋራጮች የተቀነሰ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ መደብ 5061 በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባዉ ምንም አይነት የሂሣብ ምዝገባ

ያልተከናወነና የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ተካቶ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

የግንባታ ክፍያዎች በአግባቡ እንዲመዘገቡና ለተጠቀሰው ሂሣብ ተገቢ የሂሣብ ማስተካከያ እንዲዘጋጅለት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5.13. መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ የተለዋጭ እና ተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ አላግባብ የተሠጠ፤

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ (ከውለታው በላይ የተፈፀመ ክፍያ፤ መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ የተለዋጭ እና ተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ አላግባብ የተሠጠ መሆኑ፤ ...ወ.ዘ.ተ) በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,304,780.05 የግንባታ ክፍያ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ፡-

የማሻሻያ ሃሳብ፡

- በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(11) መሰረት የለውጥ ሥራ ትዕዛዝ ተብሎ በተጨማሪነት ለተፈጸመው ክፍያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የውል ሥምምነት ካልተፈራረመ ክፍያው ተገቢነት ላይኖረው ስለሚችል በተጨማሪነት ለተፈጸመው ክፍያ በግዥው መመሪያው መሰረት ተጨማሪ ውል መፈረም እንዳለበት አሳስበናል

5.13.1 የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ፤

1	**በወላይታ ዩኒቨርሲቲ** በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 11 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
2	**በወለጋ ዩኒቨርሲቲ** በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ የሚገኙ 9 ፕሮጀክቶች (የግንባታ ሥራዎች) የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
3	**በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ** FE Construction የተባለ ተቋራጭ ቀድሞ የወሰዳቸውን ግንባታዎች በተሰጠዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ አጠናቅቆ ሳያስረክብ ሌሎች የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች በተደራራቢ የተሰጡት በመሆኑ ሥራዎቹ እየተጓተቱ ሲሆን በዚህም ምክንያት የካቲት/2007 እና መጋቢት/08 መጠናቀቅ የነበረባቸው ግንባታዎች እስከ የካቲት 30/2009 ዓ.ም ድረስ ያልተጠናቀቁና የውል ማረዘሚያ ጊዜ እየተጠየቀባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡
4	**በአርሲ ዩኒቨርሲቲ** አፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽ ለተለያዩ የግንባታ ስራዎች በቀን 28/08/2008 (06/05/16) ተጀምረው በቀን 26/08/2010 (04/05/18) ይጠናቀቃል ተብለው በብር 881,787,388.10 ውለታ ከተገባባቸው ሥራዎች ውስጥ (የአዲሱ ዋናው ግቢ የአስፋልት ሥራ) እስከ ሰኔ 30/09 የግንባታው ደረጃ 14.73% ላይ የሚገኝ መሆኑ
5	**በጎንደር ዩኒቨርሲቲ** የሥራ ተቋራጮች 4 ግንባታዎችን በውላቸው መሰረት ማጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ21 እስከ 187 ቀናት ያዘገዩ መሆኑ ታውቋል፡፡

6	**በአክሱም ዩኒቨርሲቲ** በዋናው ግቢ ቴዎድሮስ አበራ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር ለአስተዳደር ሕንፃ /Administration office building (Lot 24) ለማሰራት በዋናው ውል ብር 88,482,547.44 ለተለዋጭ ሥራ /variation Order/ ብር 1,134,144.46 በድምሩ በብር 89,616,691.90 ለመስራት ተዋውሎ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 22,602,258.11 የተከፈለው ሲሆን ሥራውን ያቋረጠ ቢሆንም በውሉ መሠረት በሕግ የተጠየቀበት እና ውሳኔ የተገኘበት ማስረጃ የተቋሙን ጥቅም ከማስከበር አንፃር በሥራ ተቋራጩ ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
7	**በሠመራ ዩኒቨርሲቲ፡-** ከአሽካ ኮንስትራክሽን የኮንክሪት ውሃ ማጠራቀሚያ ግንባታ ሥራ በቀን Sep16/2016 ይጠናቀቃል ተብሎ በብር 5,279,241.71 ውለታ የተገባበት ሥራ የግንባታው ደረጃ (Project status) 77% ላይ የሚገኝ መሆኑ፤
8	**አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፡-** በዩኒቨርስቲው በዋናው ግቢ የሚገኘውን የጋራዥ ዙሪያ አጥር የግንባታ ስራ ለማሰራት ቆርቆሮ በዩኒቨርስቲው እንደሚቀርብና የቆርቆሮ ዋጋ ብር 112,700.00 ከነኘቱ ወጪ እንደማይካተት በተገለፀው መሰረት ሳይሆን የጋራዥ ዙሪያ አጥር ሙሉ ለሙሉ ግብዓቶችን በማቅረብ ለመገንባት በሚል ውል ተገብቶ በ30/12/08፣ በ30/02/09 እና በ30/09/09 በቀረቡት የወጪ ማስመስከሪያዎች የቆርቆሮን ዋጋ በማካተት ክፍያ መፈጸሙ፣
9	• አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ • በቦክራ ህንጻ ተቋራጭ ከሚከናወኑ የጥገና እና የግንባታ ሥራዎች ውስጥ በዋናው ግቢ በብር 15,089,045.47 የተከናወነው የተማሪዎች ማደሪያ (ዶርሚቶሪ) ጊዜያዊ ርክክብ ተፈጸመ ቢሆንም ከተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት ጋር በ25/04/2010 በተደረገ የመስክ ኦዲት ቅኝት ወቅት የህንጻው መጸዳጃ ቤት የሚያፈስ መሆኑንና በአካባቢው መጥፎ ሽታ (ጠረን) የፈጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ ለተማሪዎቹ ልልብስ ማጠቢያ የተሰሩ ላውንደሪዎች እጅግ በጣም ጠባብ በመሆናቸው የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት በሚችሉ መልኩ ያልተሠሩ መሆኑ፤ • በዩኒቨርስቲው ሥር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ 7ቱ የባለ ይዞታና የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የሌላቸው መሆኑ፤ (የንግድ ሥራ ኮሌጅ፤ የኢት/አርክቴክቸር ህንጻ ግንባታና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፤ የሳይንስና ቴክ/ኢንስቲትዩት፤ ደ/ዘይት የእንስሳት ህክምና እና ግብርና ኮሌጅ፤ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ፤ የህግና አሰ/ትምህርት ኮሌጅ እና የኢት/ውሃ ሃብት ኢንስቲትዩት፤ ያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት) • የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በሚል የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የቀረበ ቢሆንም ዩኒቨርስቲው በባለቤትነት የተረከበው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ • ለኬኔዲና ለስድስት ኪሎ በራማ ኮንስትራክሽን የተገነባው ላይብረሪ የመስክ ኦዲት ቅኝት በታየበት ወቅት የላይብረሪዎቹ መስኮቶች እንደፍሪንች ዶር መስታወት በመስታወት የተሰሩና የጸሐይ ጨረር ለኮምፒዩተር አጠቃቀም የማያመቹ መሆኑ የህንጻው ዙሪያ ማፋሰሻ ያልተሰራለት በመሆኑ ፍሳሽ ወደ ላይብረሪው የሚገባ መሆኑ፤ • በጋዜጠኝነትና ኮምኒኬሽን ህንፃ ግንባታው በሚከናወንበት የቀድሞ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ይፈርሳሉ የተባሉ የቀድሞ ዋናው ህንጻ ጨምሮ ቢሮች ያልፈረሱ ከመሆኑም በተጨማሪ በአጥር የሚገናኙ (የተያያዙ) ቤቶች የድንበር ጉዳይ በቅድሚያ መፍትሄ ሳይሰጠው በቀጥታ ሥራው የተጀመረ መሆኑ፤

- በቅርስነት የተመዘገቡ የማደስና እንደገና የመሥራት ሥራ ሲሰራ በሚመለከተዉ አካል ፈቃድ ሳይሰጥ የሚፈርሱ መሆኑ፤
- በግንባታና ህንጻ ዲዛይን ድርጅት ክትትልና ቁጥጥር የተደረገበት ተጠገነ ተብሎ በ17/11/2007 ጊዜያዊ ርክክብ የተደረገው ሥራ (የጭንቅላት (የአንጎል)፤እና የሌሎችም ህሙማን ኦፕሬሽን የሚደረግበት የሥራ ክፍል አብዛኞቹ ክፍሎች የእጅ መታጠቢያዎች፤መጸዳጃ ቤቶች፤የመብራት ሶኬቶች፤በሰርጀሪ ወቅት የሚከሰቱ ቆሻሻዎች መድፊያ ሲንኮች፤እንደማይሰሩ፤የበረንዳው ወለል እየፈረሰ መሆኑና የጥገናው ሥራ በአግባቡ አለመከናወኑ ባለሙያዎቹ በሥራቸው ላይ ከፍተኛ ጫና እንደፈጠረባቸው፤ እንዲሁም ድራም (ላውንደሪ) ባለመኖሩ በቀን መቀበል በሚገባቸው መጠን ህሙማን መቀበል እንዳልቻሉና የሃኪሞቹ ማረፊያም እንደሌለ ከባለሙያዎቹ የተገለጸ መሆኑ፤
- ከተክለብርሃን አምባዬ የህንጻ ተቋራጭ ጋር ውለታ የተገባበት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ግቢ የድንገተኛ መድሃኒት ክፍል ህንጻ የግንባታ ለግንባታው ሥራ April2/2015 (24/07/2007) በተገባ ውል በ365 ቀናት ወይም በ23/07/2008 ይጠናቀቃል ተብሎ የተለዋጭ የሥራ ትዕዛዝ ጨምሮ በብር 255,895,301.82 ዉለታ የተገባበት ግንባታ ውለታ ከተገባበት ጊዜ በተጨማሪ 546 (149.59%) ቀናት (ከ1ዓመት ተኩል በላይ) ተጨምሮ ሰኔ30/2009 ላይ የሥራው ደረጃ (Project Status) 45.60% በመቶ ላይ መገኘትና የግንባታ ግዥው በ2007 በጀት ዓመት ግዥው ሲፈጸም ከነበው አስቸኳይነት አንፃር በውሱን ጨረታ የተፈጸመ እና አስቸኳይ ሆኖ ሳለ ከተጨመረው ጊዜና ሥራው ከሚገኝበት ደረጃ አንጻር እጅግ መጓተቱን የሚያመለክት መሆኑ እና ከተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት ጋር በመሆን በ09/05/010 በተደረገ የመስክ ኦዲት ቅኝት በግንባታው ቦታ ምንም ዓይነት የሥራ እንቅስቃሴ የሌለ ወይም የቆመ መሆኑ፤
- አምስት ኪሎ የተማሪዎች ማደሪያ በቦክራ ኮንስትራክሽን እና ትሬዲግ ኃ/የተ/የግ/ኩ በብር 20,411,642.10 የተገነባ እና ኮሜርስ በዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማ በብር 379,446,043.70 የተገነባ በተሽከርካሪ ወንበር ለሚጠቀሙ፣ ማየት ለተሣናቸው እንዱሁም በከፊል ለተጎዱ አካል ጉዳተኞች ወደ ህንፃው መዳረሻ ከእንቅፋት የፀዳ መንገድ ያልተዘጋጀላቸው በመሆኑ የህንጻ መመሪያውን ከመጣሱም በላይ በመማር ማስተማሩ እንዲሁም በቢሮ ሥራ ላይ ችግር የሚፈጥር እና እየፈጠረ ያለ መሆኑ፤

<u>የተሰጠው ማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

የግንባታ ሥራዎች በታቀደው መሠረት እንዲከናወኑ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ እንዲሁም አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6. በጀት

6.1. የበጀት አጠቃቀም፤

6.1.1 ግኝት

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን ከመደበኛ ብር 192,520,403.97ና ካፒታል በጀት ብር 10,354,863.43 ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ በድምሩ ብር 202,875,267.40 እና ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መደበኛ ብር 311,042,467.69 ከፒታል ብር1,246,835,297.43 በድምሩ ብር 1,557,877,765.12 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡

- **በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ** ከበጀት በላይ ከወጣው ብር **36,092,729.98** ውስጥ በወጪ ሂሳብ መደብ 6123 የወጣ ብር 387,440.33 እና በወጪ ሂሳብ መደብ 6256 የወጣ ብር 59,973.52፣ በድምሩ ብር 447,413.85 አስቀድሞ በጀት ባልጸደቀባቸው /ባልተፈቀደባቸው ወይም በጀት በሌላቸው/ የወጪ ሂሳብ መደቦች ወጪ የተደረገ መሆኑ፣

የማሻሻያ ሃሳብ

- ዩኒቨርስቲዎቹ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ፤ የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸውም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡
- ዩኒቨርስቲዎቹ የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7. ተከፋይ ሂሳብ፤

7.1.1 ግኝት

የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በወቅቲ ያልተወራረደ በ16 መ/ቤቶች ብር 561,748,905.23 ውዝፍ የተከፋይ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቶል/

የማሻሻያ ሃሳብ፣

የተከፋይ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ሌጀር የሌለው ተከፋይ ሂሳብ

የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 መሠረት የሂሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈፃፀም ሲታይ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 143,352.96 የተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

8. የዕቃና ንብረት አስተዳደር፤

8.1. ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፤

8.1.1 ግኝት፤

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

- ከውጭ ሀገር በእርዳታ የመጡ ዋጋ ሳይወጣላቸው የተመዘገቡ መሆኑ፤ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ
- ለቋሚ ዕቃች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸዉ መሆኑ፣የንብረት መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

- የዩኒቨርሲቲው የንብረት አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤

በዋናው ግቢ፣

- መወገድ የሚገባቸው እቃዎች ሳይወገዱ በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ምግብ ቤት ከ10 አመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ 4 (አራት) ፍሪጆች የሚገኙ መሆኑ፤

በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤

- የተለያዩ UPS በቁጥር 433፣ የኮምፒዩተር ጠረጴዛዎች በቁጥር 78 እና ወንበሮች በቁጥር 50 ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤የተለያዩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ የእንግዳ ወንበሮች እና UPS ሳይወገዱ በአሮጌ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ሳልቫጅ ስቶር) የሚገኙ መሆኑ፣

በስፔሻላይዝድ ሆስፒታልና በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ፤

- ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለዉ በአንድ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣

ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ

- የኮምፒውተር ነፀብራቅ መከላከያ ብዛት 1100 GPR የኮምፒውተር ቀለም ብዛት 206 ኮፒ ሆልደር ብዛት 127 ከ1 ዓመት በላይ በግምጃ ቤት የተቀመጡ መሆኑ፤ታውቋል፡፡

ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

- የዲሽ ሳህኖች፤ በርካታ የተማሪ ወንበሮች እና 580 የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች መወገድ ሲገባቸው በዋናው ግቢ ሜዳ ላይ ተጥለው የሚገኝ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡
- 153 የተለያዩ ኮምፒዩተሮች እና 20 ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፤

ሰላሌ ዩኒቨርሲቲ

- በሰኔ 30/2009 የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤
- ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- በዕቃ ግምጃ ቤት ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች ተለይተው ያልተጠበቁ መሆኑ፤
- አላቂና ቋሚ ዕቃዎች በቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ያልተመዘገቡ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ክሊኒክ መድኃኒቶችን የመረከብ፤ የማሰራጨት እና የምዝገባ ሥራዎች በአንድ ሠራተኛ የሚከናወኑ መሆኑ፤

ወላይታ ዩኒቨርሲቲ

በዋናው ግቢ፤

- ዩኒቨርሲቲው ሲመሰረት ከትምህርት ሚኒስቴር በእርዳታ የገቡ በርካታ ዘመናዊ የምግብ ማብሰያ እቃዎች አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በአላቂ ንብረት መጋዘን ንብረት የመያዝና የገቢና ወጪ ምዝገባ ሥራዎች በአንድ ሰራተኛ እየተከናወኑ የሚገኝ መሆኑ፣

- በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ፣ የመማሪያ ህንጻና የአስተዳደር ቢሮዎች እንደ ቋሚ ንብረቶች በተለየ መዝገብ አለመመዝገባቸው፤

የዩኒቨርሲቲው የመድሃኒት አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የህክምና ቋሚ ዕቃ መጋዘን ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ የሌላቸው ሲሆን እቃዎችም በአግባቡ ያልተቀመጡ መሆኑ፤
- የመድኃኒት ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መጋዘን በአንድ ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፤ ገቢ እና ወጪ የማድረግ ስራ እንደሚከናወንና ወቅታዊ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤
- መድሃኒት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ20% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ መሆን ሲገባው ሆስፒታሉ 30% የትርፍ ምጣኔ በማድረግ መድሃኒት ለተጠቃሚው ከመሸጡ ባሻገር የመድሃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በሚታይ መልኩ ለተጠቃሚው ያልተለጠፈ መሆኑ፣
- ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች ሳይወገዱ መቀመጣቸው፤ ታውቋል፡፡

አምቦ ዩኒቨርሲቲ

- በብዛት 179 የሚሆኑ 5450 DN Brother ሞዴል አዲስ ፕሪንተሮች ወደ የዩኒቨርሲቲው ከገቡ ከ5 ዓመት በላይ የሆናቸው ቢሆንም እስከ አሁን አገልግሎት ሳይሰጡ በእስቶር የተቀመጡ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ ዓመታዊ ቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ገቢ ሞዴል 19 እና ወጪ ሞዴል 22 የሚሰራው በአንድ ሰራተኛ ብቻ መሆኑ፤
- የእሰቶክ ካርድና የቢን ካርድን ጨምሮ ምንም ዓይነት ንብረት ምዝገባ የማይከናወን በመሆኑ ያለውን ባላንስ /ሚዛን/ ለማወቅ የማይቻል መሆኑ፤
- የበጀት ዓመቱ ዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤

አርሲ ዩኒቨርሲቲ

ቋሚና አላቂ ዕቃዎች፤

- በዋናው ካምፓስ የአዲስና የተመላሽ የቋሚ ንብረት ግምጃ ቤት ሠራተኛ ንብረት የመረከብ እና የገቢና ወጪ ደረሰኞች (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀት ሥራዎችን የሚያከናውኑ፣ በተጨማሪም የገቢና የወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ የሌለ መሆኑ፤
- ለሱቢ የጽህፈት መሳሪያና የቢሮ ዕቃዎች አቅራቢ በውለታው መሰረት ላልቀረቡ ወንበሮች ለአቅራቢው አላግባብ ብር 69,999.65 (35*1999.99) የተከፈለ መሆኑ፤
- ያልተጠገኑና ተጠግናው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የተማሪዎች የብረት አልጋ ያለምንም እርምጃ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

- 28፣ ታይፕራይተር ብዛት 29፣ ዴል ኮምፒዩተር ሲስተም ብዛት 128፣ ኤችፒ ሲስተም ብዛት 40፣ ኤችፒ ሞኒተር ሲስተም ብዛት 90፣ ኤችፒ ፕሪንተር ብዛት 50፣ የምግብ ቤት ማሽን ብዛት 15፣ የተለያዩ የመኪና ጎማዎችና ስፐር ፓርቶች፣ እስፖንጅ ፍራሾች ብዛት 818፣ ማርቲ በጣሳ ብዛት 1702፣ ቁጥራቸዉ የማይታወቁ ቁጥራቸዉ በርካታ የሆኑ የጣዉላ ሎከሮች እና የተለያዩ ብረታ ብረቶች (ወደ ስቴዲዮም አከባቢ)፣ ሚክሲድ ፎሲት ብዛት 152፣ የብሉኬት ማፍጫ የብረት ብዛት 196 ያሉ በርካታ ንብረቶች ተከማችተው የተቀመጡ መሆናቸው፤

ራያ ዩኒቨርሲቲ

- ለቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑን፤

መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ

- ለቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ U.P.S ተብሎ ሬጉላቶሬ (Regulator) በብር **773,232.96** ብዛት 297 በቀን 14/05/2007 ዓ/ም በሞዴል 19 ገቢ ቁጥር 36567 የተገዛ አገልግሎት ላይ ሳያውል በእስቶር ተቀምጦ እስከ አሁን ዩኒቨርሲቲው ያልተፈለገ ዕቃ የገባ መሆኑን እያወቀ አሰተዳደራዊ እርምጃ ሳይወስድ የተገኘ መሆኑ፤

- የቋሚ ዕቃ መጋዝን በውስጡ የሚገኙ ንብረቶች ያለ ዕቅድ በብዛት ተገዝተው የቆዩ በመሆኑ በወለል ላይ በመቀመጣቸው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤
- ከመድሃኒት ግምጃ ቤት ወደ መድሃኒት ስርጭት ክፍል (Dispensary) በሞዴል 22 መድሃኒት ወጪ ሲደረግ መጀመሪያ ከዋናው እስቶር የመጣው መድኃንት ገቢ ሆኖ ወጪ የማይደረግ እና ዋጋው የማይጠቀስ መሆኑ፤
- መወገድ የሚገባቸው ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች ያልተወገዱ መሆኑ፤

ትምህርት ሚኒስቴር

በቁጥር የማይታወቅ በጣም ብዛት ያላቸው ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፎቶከፒ ማሽኖች፣ ፋይል ካቢኔቶች፣ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ የተሽከርካሪ ጎማዎች እና ሌሎችም ቋሚ እቃዎች በተለያዩ ክፍሎች ታሽገው የተቀመጡ በመሆኑ ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፡

አክሱም ዩኒቨርሲቲ

- የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ከሌሎች ቋሚና አላቂ ንብረቶች ጋር በአንድ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- ብዛት ያላቸው የኮምፒውተር ወረቀቶች፤
- ብዛት ያላቸው ፍሊቶች ከ1 ዓመት በላይ በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ
- የቤተ-መጽሐፍት ንብረት ቆጠራ እና የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች በዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ውስጥ እንዳልተካተቱ፤

ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

- የአላቂ የገቢና ወጪ መከታታያ (ስቶክ ካርድ) ምዝገባ እየተከናወነ ቢሆንም የንብረቱ መነሻ ምዝገባ መሠረቱ የማይታወቅ እና እየተመዘገበ ያለውም ምዝገባው ወጥነት የሌለው መሆኑ፤የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች እንዲሁም ተብላሽተው የተቀመጡ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በአንድ የንብረት ክፍል ውስጥ ከመቀመጣቸው በተጨማሪ መሳሪያዎቹ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚችሉና እንደማይችሉ በባለሙያ ሳይለይና ሳይረጋገጥ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡ መሆኑ፣

ወሎ ዩኒቨርሲቲ

- በጣም ብዛት ያላቸው ቋሚና አላቂ እቃዎች(ወንበሮች ጠረጴዛዎች፤ሸልፎች----) እና አሮጌ ተመላሽ የተሸከርካሪ እቃዎች በወቅቱ መወገድ ሲገባቸው በክምችት የተቀመጡ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ምግብ ቤት አካባቢ የተረፈ ምግብ ማስወገጃ ቱቦ የተዘጋና ለማሰተላላፍ አሰቸጋሪ በመሆኑ ከፍተኛ ሽታ ስለፈጠረ እና አካባቢው ስለተበከለ ለተማሪዎችም ሆነ ለሰራተኞቹ ጤና ከፍተኛ ስጋት መሆኑ፤
- የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው መድሐኒቶች በወቅቱ መወገድ ሲገባቸው ከሌሎች መድኃኒቶች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ አብረው ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፡፡
- በክሊኒኩ የመድኃኒት ክፍል ሰራተኛ፤ሞ/19 እና ሞ/22 በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤

ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና የቋሚ ንብረቶች ከወጪ ቀሪ ቆጠራ (Inventory) ያልተደረገ መሆኑ፤በተማሪዎች ክሊኒክ ስቶር ገቢና ወጪ ለሚደረጉ መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ክሊኒክ ውስጥ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች ሳይወገዱ ተከማችተዉ የተቀመጡ መሆኑ፣

ሠመራ ዩኒቨርሲቲ

- በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ ቋሚ ንብረቶቹ የሚገኙበትን ሁኔታ ለማረጋገጥ ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤በ Laboratory equipment & consumables Store ውስጥ በብር 7,360.00 የተገዛ 32 ከረጢት መሰቦ ሲምንቶ፤ የብር 2,645.00 ጀሶ በከረጢት እና የብር 6,900.00 ኖራ በከረጢት ካለ አገልግሎት የተቀመጡና ከጥቅም ውጭ እየሆኑና ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤
- በባዮሎጂ የላብራቶር ሕንጻ (3) በቤተ-ሙከራ ዕቃ ግምጃ ቤት ውሰጥ 4 ፍሪጅ መረጃ የሌላቸውና ዋጋቸው የማይታወቅ ያለስራ ተቀምጠ የሚገኙ መሆኑ፤

- በፊዝክስ ዲፓርትመንት የትምህርት ክፍል ለመካኒክስ፣ ለኤሌክትሪክ ሲቲ እና ለኦፕቲክስ፤ ትምህርት አገልግሎት የሚውሉ በ2002 ዓ/ም ከትምህርት ሚኒስቴር በስጦታ በእርዳታ የተሰጡ በርካታ የተለያዩ ዕቃዎች መለየት በሚያስቸግር ሁኔታ ተቀላቅለው ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤
- ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ ወጪ የተደረገባቸው የምግብ ግብዓት ዕቃዎች፡- ቢንካርድ እንዲሁም የገቢና ወጪ መከታተያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ) የሌለ መሆኑ፤

አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ

- ከተገዙ ብዙ ጊዜ የሆናቸው የሻወር /የመታጠቢያ/ ቤት ሳህኖች ዩኒቨርስቲው ከሚያስገነባቸው ህንጻዎች ጋር የማይገጥሙ በመሆናቸው በሚል ያለመፍትሄ ተከማችተው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
- ቴብል ፋን (የጠረጴዛ ቬንቲሌተር) ካርቶን አዳዲስና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ብዛታቸውን ለመቁጠር ያልተቻለ ለብዙ ጊዜ የቆየ ምቹ ባልሆነና ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ የተቀመጡ መኖሩን፣ እንዲሁም ቶርኖ እና ከ1980 ጀምሮ ገባ የተባለ የውሃ ማሞቂያ ቦይለር በቁጥር 9 በመጋዘን ውስጥ አለአግባብ የሚገኙ መሆኑን፤
- ከዋናው ግቢ የተማሪዎች ክሊኒክ በስተቀር በሁሉም ካምፓሶች መድሃኒት ስርጭት/እደላ/ ክፍል የመደኃኒት ቆጠራ ያልተደረገ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምን ያህል መድሃኒት እንደቀረ የማይታወቅ መሆኑ፣

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

- 43 አልጋ እና 43 ፍራሽ በበጀት ተገዝተዉ በቋሚ ንብረት መጋዘን መቀመጥ ሲገባቸዉ ከሁለት ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሠጡ በአላቂ እቃዎቸ መጋዘን ውስጥ የተገኙ መሆኑ፣
- በፋርማሲ መጋዘን ወስጥ ብዛታቸው 29 አይነት የሆኑና ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 46,092.17 የሆነ ጊዜ ያለፈባቸው የተለያዩ መድሃኒቶች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፣በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀፅ 6/ለ የቋሚ ንብረት ምዝጋባ እንዲከናወን የተገለፀ ቢሆንም የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድ (ፋር) ያልተዘጋጀና ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣

<u>ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ</u>

- የአገልግሎት ጊዚያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች/የተበላሹ መድኃኒቶች/ 109 አይነት የተለዩ መድሃኒቶች ከ2002-2008 በጀት ዓመት ጀምሮ በተለያየ ጊዜ የገቡ መድሃኒቶች በአንድ መጋዘን ውሰጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

<u>አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ</u>

- የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ስራቸውን ሲለቁ በስማቸው የተረከቡትን/የወሰዱትን/ ንብረቶች ተመላሽ ማድረግ ሲገባቸው ተመላሽ የማያደርጉ መሆኑ እና ዩኒቨርስቲው የነበሩትን በርካታ ንብረቶች ሲያስወግድ በእርዳታ ከሰጣቸው ድርጅቶች መድረሱን የሚገልጽ የምስጋና ደብዳቤ እንጂ ምን ያህል እንደደረሳቸው የማያሳውቁ በመሆኑ ተሰጠ የተባለው በትክክል ለመድረሱ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በግዥ ወይም በርዳታ ተገኝተው ወደ መድኃኒት መጠበቂያ ክፍል ገቢ የሚደረጉ እና እንዲሁም ከመድኃኒት መጠበቂያ ክፍል ወደ ህክምና መስጫ ክፍል የሚተላለፉ መድኃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ ያለ ቢሆንም ንብረት መጠበቁ እና መመዝገቡን የምታከናው ግለሰብ አንድ መሆኗ፣የመጠቀሚያ ጊዜያቸው የተላለፈ ከሁለት መቶ ሃምሳ በላይ መድኃኒቶች /Expired medicine/ የሚገኙ ሲሆን አገልግሎት ከሚሰጡት ጋር በመድኃኒት መጠበቂያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ እና የመድሃኒት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ማመዛመኛ ያልተሰራ ስለሆነ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- የምግብ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ ንብረት መዝጋቢና ንብረት ጠባቂ ያልተለ የመሆኑ እና ስቶክ ካርድ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ በተለያዩ ተቋሞች በሚሄዱበት ጊዜ ከትምህርት ክፍሉ ለተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር የማሳወቂ ሥርዓት ያለ ቢሆንም ተማሪዎቹ ከሚሄዱበት ቀን ቀድሞ ማሳወቅ ሲኖርባቸው ተማሪዎቹ በሚሄዱበት ቀን እና ከሄዱ በኃላ የሚያሳውቁ የትምህርት ክፍሎች መኖራቸው፤
- ልደት ምግብ ቤት ለተማሪዎች ምግብ ቤት ለምግብ ዝግጅት አገልግሎት አስራ አምስት ሺ ሊትር ነዳጅ ይይዛል ተብሎ የሚገመት የነዳጅ ታንከር ያለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ያልተቆጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ ነዳጅ ከመሆኑ አንጻር የተሰራለት ቤት ለአደጋ የተጋለጠ መሆኑ እና ክዳኑም ጥረና ተጀምሮ ያልተጠናቀቀ

በመሆኑ መሆኑ እና ነዳጁም በአዲሲ ላይበራሪ እና ኬኔዲ ላይበራሪ ጀርባ ባለው የውሃ ማፋሰሻ ቦይ የሚፈስ ከመሆኑም በተጨማሪ የነዳጅ መከታተያ እና መቆጣጠሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤በ2008 በጀት ዓመት የገባ በኢሌክትሪክ የሚሰራ ቦይለር ሥራ ያልጀመረ መሆኑ እና ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ ለተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት የሚውል ጀኔሬተር በሰታርተር ችግር ምክንያት ተበላሽቶ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤

ዋናው ምግብ ቤት አምስት የወጥ መስሪያ ድስቶች የማይሰሩ መሆኑ፤ሞ/19 እና ሞ/22 ያለ በቂ ምክንያት ሳይሰራባቸው የሚዘለሉ መሆኑ እና የምግብ ቤቱ ጣሪያ ዝናብ ሲዘንብ የሚያፈስ መሆኑ፤

- 8.3.1 በግምጃ ቤቱ የሚገኙ በርካታ የተለያዩ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በዋናው ግምጃ ቤት የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) ተዘጋጅቶላቸው በቀጥታ ወደ ሚኒስቶር የተላለፉ ንብረቶች ምንም ዓይነት መከታተያ የሌላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ሠራተኛው ንብረቱን እንዲያንቀሳቅሱ የተመደቡ ሳይሆን ከሃምሌ1/2005 ጀምሮ በስፖርት ሜዳ ተንከባባቢትነት የተመደቡ መሆኑ፤ ለጂሚናዚየም አገልግሎት መስጫ እንዲያገለግሉ ብር 5,776,364.33 ውጪ ሆኖ ከተገዙ የተለያዩ ዕቃዎች፤ብር 3,877,500.42 ዋጋ ያላቸው ንብረቶች የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ሳይዘጋጅላቸው ከዋናው ዕቃ ግምጃ ቤት በሚኒ ስቶር ሰራተኛው በንብረት ወጪ መጠየቂያ (ሞ/20) ወጪ የተደረጉ መሆኑ፤
- ከተጠቀሰው ብር 3,877,500.42 ዋጋ ያላቸው የተለያዩ ዕቃዎች ብር 1,649,999.99 ዋጋ ያለው የትራክ መሮጫ አንድ ትሬድ ሚል (Tread mill) የንብረቶቹ አያያዝ በታየበት ወቅት ያልተገኘና በቃል ለፕሬዚደንቱ መኖሪያ ቤት የተሰጠ መሆኑን ከመገለጹ በቀር የጽሁፍ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ከ2000 በጀት ዓመት በፊት የነበሩና ሠራተኛው ያልተረከቡአቸው 5፤እና 1 ደግሞ ከ2 ዓመት የግምጃ ቤቱ ሰራተኛ የተረከቡት አዳዲስ የውሃ ማሞያዎች ያለአገልግሎት ለዓመታት በግምጃ ቤቱ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- ለ2008 የስፖርት ፌስቲቫል በሚል የተዘጋጀ የተገዙ (የተሰሩ) በርካታ ቲ-ሸርቶችና ኮፊያዎች ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

<u>የተሰጠው አስተያየት፤</u>

ዕቃዎች በአግባቡ ውስጥ በአግባቡ እንዲጠበቁ፤ የተበላሹ ዕቃዎች በወቅቱ እንዲጠገኑና መጠገን የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ፣ ወቅታዊ የንብረት ቆጠራ እንዲደረግ እና ዋስትና ማቅረብ የሚገባቸው ሠራተኞ ዋስትና እንዲያቀርቡ እንዲሁም ሌሎች በንብረት አያያዝ በኩል መስተካከል ያለባቸው ግድፈቶች እንዲስተካከሉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

10. <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም፤</u>

የመሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:- ሊቢሬ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው)፤በብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜያት የቆሙ ተሽከሪካሪዎችና ሌሎች የተሽከርካሪዎች አያያዝ ችግሮች እንዳሉ ተውቋል፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 35ተያይዟል)

<u>የተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በብልሽት ምክንያት የቆሙት ተሽከርካሪዎች እንዲጠገኑ፤ የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) የሌላቸው ሊብሬ እንዲወጣላቸው፤ ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎች ጌጅ እንዲቀየርላቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

11. <u>በባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፤</u>

በ12 መ/ቤቶች ቀደም ባሉት ኦዲት ሪፖርቶች መሰረት እርምጃ ያልወሰደባቸው ነጥቦች በዝርዝር ሪፖርቶች ተጠቅሷል፡፡
በመሆኑም አሁንም ክትትል በማድረግ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

12. <u>ልዩ ልዩ፤</u>

በሠመራ ዩኒቨርሲቲ የፕሮጀክት ሂሳብ ሁኔታ ሲታይ ዩኒቨርሲቲው ከሚያንቀሳቅሳቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶች ውስጥ 10ሩ በድምሩ ብር 970,488.80 ከወጪ ቀሪ እያላቸው የተጠናቀቁ (Phase out) ያደረጉ መሆኑ እና ከወጪ ቀሪያቸው ለሚመለከተው አካል ገቢ አለመደረጉ፣

<u>የማሻሽያ ሀሳብ፣</u>

- ዋስትና ማቅረብ በሚያስፈልጋቸው የስራ መደቦች ላይ ተቀጥረዉ የሚሰሩ ሠራተኞች ዋስትና እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

- የውለታ ጊዜያቸው በተጠናቀቀ የፕሮጀክት ሂሳብ ላይ የሚታየው ከወጪ ቀሪ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ /ገቢ/ እንዲደረግ የስራ አመራሩ በጉዳዩ ላይ እርምጃ መውሰድ እንደሚኖርበት እና ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት እንቅስቃሴያቸው ባበቃ የፕሮጀክት ሂሳቦች ላይ የሚታይ ከወጪ ቀሪ ገንዘብ ካለ ከስር በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ገቢ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ

መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የ35 መሥሪያ ቤቶችንና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት፣ ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት፣ ለጤና ጥበቃና ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ 11 መሥሪያ ቤቶችን በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ሂሳብ አቅራቢ መሥሪያ ቤት ኦዲት በዳይሬክቶሬቱ በተጨማሪነት እንዲሰራ ተደርጓል፡፡

1. <u>የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን</u>

1.1. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የሰላሳ አምስት መሥሪያ ቤቶችን የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

1.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት እና የበጀት ዓመቱን ሂሳብ የዘጉበትን ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ.	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት		
		ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
1.	የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር	639,091,943.49	2,345,448,926.87	2,984,540,870.36
2.	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	86,117,212.02	9,924,314.18	96,041,526.20
3.	የኢትዮጵያ ጤናመድኅን ኤጀንሲ	158,861,770.00		158,861,770.00
4.	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	115,013,250.0	1,133,115,833.0	1,248,129,083.00
5.	የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ. ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	80,440,787.79	104,200,000.00	184,640,787.79

6.	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚ/ር	334,794,653.36	5,203,864,710.71	5,538,659,364.07
7.	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	27,463,000.00		27,463,000.00
8.	የ ሆርቲካልቸርና ግ/ ኢ/ት ባ/ን			
9.	የማዕድን፣ነዳጅና ተ/ ጋዝ ሚ/ር	58,084,530.00	20,352,440.00	78,436,970.00
10.	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	604,398,663.83	669,402,563.58	1,273,801,227.41
11.	የኢትዮጵያ ምግብ ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን	106,517,200.00	10,404,860.00	116,922,060.00
12.	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	130,000,000.00		130,000,000.00
13.	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴ	129,268,443.98	896,958,240.67	1,026,226,684.65
14.	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	105,310,659.76	11,852,917.65	117,163,577.41
15.	ብሔራዊ የሜቲሮዎሮሎጂ ኤጀንሲ	66,435,483.00	60,000,000.00	126,435,483.00
16.	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	28,000,030.00	35,000,000.00	63,000,030.00
17.	የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር	332,093,467.34	121,453,966.23	453,547,433.57
18.	የአለርት ማዕከል	113,954,570.69	25,728,436.74	139,683,007.43
19.	የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር	149,945,535.00	546,861,445.00	696,806,980.00
20.	የስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	79,750,526.73	17,251,000.00	97,001,526.73
21.	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	83,059,096.11	10,000,000.00	93,059,096.11
	የሚዞር ድምር	**3,428,600,823.10**	**11,221,819,654.63**	**14,650,420,477.73**

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት		
		ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
	የዞረ ድምር	**3,428,600,823.10**	**11,221,819,654.63**	**14,650,420,477.73**
22.	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	12,376,019.19	10,000,000.00	22,376,019.19
23.	የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት	51,581,270.00		51,581,270.00
24.	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	11,000,000.00	50,000,000.00	61,000,000.00
25.	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	149,909,000.00	152,100,000.00	302,009,000.00
26.	የመንገድ ፈንድ የጽህፈት ቤት	7,869,580.00		7,869,580.00
27.	የፌደራል የተቀናጀ የመሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ	33,010,317.53		33,010,317.53
28.	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት	15,042,520.00		15,042,520.00
29.	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	96,067,371.00		96,067,371.00
30.	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክትማኔጅመንትኢንስቲትዩት	57,228,145.78	14,923,920.00	72,152,065.78
31.	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	38,529,534.33		38,529,534.33
32.	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣንን	16,748,841.18	20,000,000.00	36,748,841.18
33.	የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ	113,181,920.36		113,181,920.36
34.	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	67,939,605.00	16,636,500.00	84,576,105.00
35.	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	40,873,910.00	12,305,110.00	53,179,020.00
	ጠቅላላ ድምር	**4,139,958,857.47**	**11,497,785,184.63**	**15,637,744,042.10**

የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው የኦዲት አስተያየት መሰጠት ያልተቻለ ለ1 መሥሪያ ቤት፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ11 መሥሪያ ቤቶች፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ10 መሥሪያ ቤቶች፣ ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት ደግሞ ለ15 መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ-1 ተመልክቷል፡፡

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

2. የገቢ ሂሳብ

2.1. በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶች፤

2.1.1. ግኝት

1. ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ የሚጠቀሙበት ታሪፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 21 መሰረት በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ የተደረገ መሆኑን እና ገቢው በታሪፉ መሰረት መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-
2. ብሔራዊ የሜቲሮዎሮሎጂ ኤጀንሲ በበጀት ዓመቱ ለሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትንቢያ መረጃ አገልግሎት ለሰጠበት ለሰበሰበው ገቢ ብር **1,076,729.31** በሚመለከተው አካል የጸደቀ ታሪፍ ባለመኖሩ ምክንያት ገቢው በታሪፉ መሰረት ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን፣ ስለሁኔታው ባለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
3. የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን በበጀት ዓመቱ በናሙና ከታዩት የአገልግሎት ገቢዎች ውስጥ ከሰርተፊኬት አገልግሎት ለሰበሰበው ገቢ ብር 39,300.00 በሚመለከተው አካል የጸደቀ ታሪፍ የሌለ መሆኑ፤
4. የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማቱ፡-

- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት ከሚካሄድባቸው እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና አስተዋፅኦዎች የሚሰበስበው ገቢ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያልተደረገና ታሪፉ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሲጠቀምበት የነበረው መሆኑ፤
- የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ከእንስሳትን አባላዘር፣ የፈሳሽ ናይትሮጅን በሽያጭ የሚያቀርብ ሲሆን የምርት መሸጫ ዋጋ ተመን ሐምሌ 21 ቀን 1985 ዓ.ም ከምርት ማዳቀል አገልግሎት ዋና ክፍል ለአባላዘርና ፈሰሽ ናይትሮጅን ማምረቻና ማከፋፈያ ዋና ክፍል በተጻፈው ማስታወሻ መሰረት ተመኑ የማምረቻ ዋጋ ጥናት ተደርጎ የመሸጫ ተመን እስኪወሰን ድረስ ሥራ ላይ የሚውል መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ማዕከሉ ለሚያመርታቸው ምርቶች የማምረቻ ዋጋ ጥናት በማድረግ የሽያጭ ዋጋ ተመን ያላዘጋጀና በሚመለከተው አካል ያላጸደቀ መሆኑ፤

5. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር በጠ2/6/64 የሚሰበስቡትን ገቢ አስመልክቶ ለፌዴራል ሆስፒታሎች ባስተላለፈው መመሪያ ቁጥር 39/2006 መሰረት፡-
6. የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከግል ህክምና ከሰበሰበው ገቢ የሆስፒታሉን ድርሻ በበጀት አሲይዞ በመመሪያው በተፈቀደው አግባብ መጠቀም ሲገባው በጀት ሳያሲዝ በብር 1,735,033.88 ወጪ ያደረገ መሆኑ፣
7. **የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል** ከግል ህክምና ከሰበሰበው ገቢ የሆስፒታሉን ድርሻ በበጀት አሲይዞ በመመሪያው በተፈቀደው አግባብ መጠቀም ሲገባው በጀት ሳያሲዝ በብር 628,051.98 ወጪ ያደረገ መሆኑ፣
8. በፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት ላይ የመንግሥት ገቢ አሰባሰብና ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ገቢ ስለማድረግ በተቀመጠው መሰረት በመንግሥት ሥም የተሰበሰበና ቀጥታ ወደ መሥሪያ ቤቱ ወይም ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ ያለበት የመንግሥት ገንዘብ በተሰበሰበበት ዕለት እንደአግባብነቱ ወደ መሥሪያ ቤቱ ወይም ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ ያለበት መሆኑ እና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቀጥታ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ የሚያደርጉትን የመንግሥት ገንዘብ በአሳማኝ ምክንያት በባንክ ሂሳባቸው ማቆየት ካለባቸው ወር በገባ እስከ አምስተኛው ቀን ድረስ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሒሳብ ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የገፈርሳ የአዕምሮ

ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የሰበሰበውን ገቢ ብር 457,732.60 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ (ገቢ) ያላደረገ መሆኑ፤

9. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 30 ተራ ቁጥር 2(ሀ) መሰረት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግብር ነጻ መሆናቸው ተደንግጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1999 አንቀጽ 24 መሰረት በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታው ያልሆኑ ድርጅቶች የአገልግሎትና የእቃ ግዥ ሲፈጽሙ 2% የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንደሚያስቀሩ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ከደቡብ ምርጥ ዘር ድርጅት ጋር ምርጥ ዘርን ለማባዛት በገባው ውል ስምምነት መሠረት ካገኘው ገቢ ብር 609,226.87 ውስጥ ድርጅቱ 2% የቅድሚያ ግብር ብር 12,184.53 ቀንሶ ያስቀረ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

- ያለታሪፍ ለሚሰበሰበው ገቢ ታሪፍ እንዲወጣለትና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ መደረግ እንዳለበት፤
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሰረት ከውስጥ ገቢ የበጀት ጥያቄ ቀርቦ በመንግሥት እንዲታወጅ ሳይደረግ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን እና ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል ሆስፒታሎቹ በመመሪያው መሰረት መፈጸም እንዳለባቸው፤
- የመንግሥትን ገቢ በወጣው መመሪያ መሰረት ፈሰስ (ገቢ) አለማድረግ የገቢ አሰባሰቡን ተዓማኒነት እንዳይኖር ሊያደርግ እና ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል የሰበሰበውን ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በመመሪያው መሰረት ገቢ ማድረግ እንዳለበት፤
- ህግን ሳይከተሉ ክፍያ መፈጸም መንግሥት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ እና ለመንግሥት ገንዘብ አላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ኮሌጁ ህጉን

ሳይከተል የፈጸመውን የቅድሚያ ግብር ክፍያ ተመላሽ አስደርጎ ፈስስ ማድረግ እንዳለበት፤

አሳስበናል፡፡

3. ተሰብሳቢ ሂሳብ

3.1.በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ፤

3.1.1. ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በሃያ አንድ መሥሪያ ቤቶች እና በስምንት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 318,249,742.67 ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ቀጥሎ በአባሪ-6 ቀርቧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡት ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው በተደጋጋሚ አሳስበናል፡፡

3.2. መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፤

3.2.1. ግኝት

በጥሬ ገንዘብና በተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery ledger) ላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሂሳቦች ውጤት ከአጠቃላይ ሌጀሩና (General Ledger) በሂሳብ መግለጫው ጋር ከተመለከተው ሂሳብ ሚዛን ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን እና ተሰብሳቢ ሂሳቦቹም መደበኛ

ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ4 መ/ቤቶችን በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 30,296,253.83 ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-7/ ሀ ተመልክቷል፡፡/

የማሻሻያ ሃሳብ

በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ አጠቃላይ ሌጀሮቹ ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን እና የሂሳብ ምዝገባውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ስለሚችል የጥሬ ገንዘብና ተሰብሳቢ ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና፤ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. ተከፋይ ሒሳብ

4.1. ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ ሂሳብ፤

4.1.1. ግኝት

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል በተገባው ውልና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአሥራ ሁለት መሥሪያ ቤቶች እና በሰባት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው በጠቅላላው ብር 32,521,960.13 ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝ ሲሆን፣ የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ በአባሪ- 30 ቀርቧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ስለሚችሉ መሥሪያ ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳቦቹን ሁኔታ በማጣራት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ አሳስበናል፡፡

4.2. መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተከፋይ ሂሳብ፤

4.2.1. ግኝት

በተከፋይ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery ledger) ላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሂሳቦች ውጤት ከአጠቃላይ ሌጀሩና (General Ledger) በሂሳብ መግለጫው ጋር ከተመለከተው ሂሳብ ሚዛን ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን እና ተከፋይ ሂሳቦቹም መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ

መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአምስት መሥሪያ ቤቶች ከ2008 በጀት ዓመት ወደ 2009 በጀት ዓመት በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የዞሩት ከወጪ ቀሪ ሂሳቦች መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (Ending Balance) ብር 4,357,101.90 ዴቢት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ - 32 ሀ ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

በሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት ሂሳቦች መደበኛ የክሬዲት ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ከሆነ አጠቃላይ ሌጀሮቹ ትክለክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ሊሆን እና የሂሳብ ምዝገባውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ስለሚችል ተከፋይ ሂሳቦች መደበኛ የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና፤ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.3. በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት ሂሳብ፤

4.3.1. ግኝት

1. ስለ ከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 91/1995 አንቀጽ 7(1) ላይ በተገለጸው መሰረት ደንቡ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት የተከታተለን ሰው የሚቀጥር ማንኛውም አሠሪ በደንቡ ላይ በተቀመጡት ግዴታዎች መሰረት መፈጸሙን፤ እንዲሁም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በቀረበለት መረጃ እና በደንብ ቁጥር 91/1995 አንቀጽ 8(1) (ሐ) መሠረት ከተቀጣሪው ደመወዝ በየወሩ እየቀነሰ የማስተላለፍ ግዴታ እንዳለበት በተደነገገው መሰረት መፈጸሙን በናሙና ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አራት ሰራተኞች ከተቀጠሩበት ጀምሮ የወጪ መጋራት ክፍያ ያልተሰበሰበ ወይም ክፍያውን ለመፈጸማቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ለኦዲት ሥራ በናሙና ከተመረጡት ሰራተኞች ውስጥ ከአንድ ሰራተኛ ብር **2,841.60** የወጪ መጋራት ክፍያ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

2. ስለከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/2008 አንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሰረት ተጠቃሚው ከምረቃ በኋላ ሥራ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ወይም ከምረቃ በኋላ ከአንድ ዓመት በኋላ የሚፈለግበትን ክፍያ ተቀጣሪ ከሆነ ከወር ገቢው በየወሩ ቢያንስ አሥር

በመቶ (10%) ከገቢ ተከፋይ በሆነ መልክ እየቀነሰ ወይም በሙያው በግሉ የተሰማራ ከሆነ ከዓመት ገቢው በዓመቱ የሚፈለግበትን መጠን ተሰልቶ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በአዲሱ ደመወዝ መሰረት ብር 5,291.00 ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት መኖሩ፤

ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የመንግሥት የወጪ መጋራት ገቢ ላይሰበሰብ ስለሚችል እና መንግሥት ባወጣው ደንብ መሰረት ያለመሰብሰብ ደግሞ ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በደንቡ መሰረት የወጪ መጋራት ክፍያው የሚመለከታቸውን ሰራተኞች በመለየት ገንዘቡን በመሰብሰብ በወቅቱ ለሚመለከተው ክፍል ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

5.1.<u>በግዥ መመሪያው መሰረት ያልተፈጸሙ ግዥዎች</u>፤

5.1.1. <u>ግዥት</u>

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በ10 መ/ቤቶች ብር 16,680,513.56 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ መፈጸሙ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡/

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ግዥዎች የግዥ መመሪያውን ተከትለው የማይፈጸሙ ከሆነ፡-

- በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፣ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤

መሥሪያ ቤቶች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

5.2. በግዥ መመሪያው መሰረት ያልተፈጸመ የቢሮ ኪራይ ጨረታ ግምገማ፤

5.2.1. ግኝት

የፌዴራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ነሐሴ 3/2008 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባወጣው የቢሮ ኪራይ ማስታወቂያ መሰረት ሶስት ተወዳዳሪዎች ለቴክኒካል ግምገማ እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን፣ በተዘጋጀው የቴክኒካል ግምገማ ከ80% በላይ ያመጡ ተወዳዳሪዎች ብቻ ለፋይናንሻል ግምገማ እንደሚያልፉ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አቶ ሰለሞን ሹፌር የተባሉት ተጫራች የቴክኒካል ግምገማውን በብቸኝነት በማሸነፋቸው በአቀረቡት የመጫረቻ ዋጋ መሰረት በየዓመቱ በካሬ ሜትር ዋጋው ላይ 5% ጭማሪ እየተደረገ ለአምስት ዓመት የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ባቀረቡት ዋጋ ብር 43,921,920.00 መሰረት ከኤጀንሲው ጋር ጳጉሜ 3/2008 ዓ.ም ውል ተፈርሟል፡፡ ከመስከረም 2009 ዓም አስከ ሰኔ 2009 ዓ.ም ድረስ ያለው የአሥር ወራት የቤት ኪራይ ክፍያም የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር 6,624,000.00 ተፈጽሟል፡፡ ሆኖም የጨረታው ሂደት አግባብነት ሲጣራ፡-

1. በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 8(ለ) መሰረት እንዲሁም በግዥ መመሪያው ክፍል 2 አንቀጽ 5(10) መሰረት የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ውስብስብ ለሆኑ እና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ ለሚፈልጉ ግዥዎች ጊዜያዊ ገምጋሚ ኮሚቴ ማቋቋም እንደሚችል በተደነገገው መሰረት የቢሮ ኪራይ ጨረታውን ሂደት የሚገመግም 3 አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቁሞ ግምገማውን ለማከናወኑ እና የኮሚቴው አባላት በቴኪኒካልና በፋይናንሻል ውጤቱ ላይ የሚስማሙ ለመሆኑ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ነሐሴ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ለኮሚቴው አባላት በጻፉት ደብዳቤ ላይ በፊርማቸው አረጋግጠዋል፡፡ በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 8(ለ) መሰረት እንዲሁም በግዥ መመሪያው ክፍል 2 አንቀጽ 5(4) የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ እንዲቋቋም ባለመደረጉ በግዥ ገምጋሚ ኮሜቴው የተከናወነውን ግምገማ የኤጀንሲው ኃላፊ ያጸደቁት ለመሆኑ ከቀረበው ደብዳቤ ለመረዳት ተችሏል፡፡
2. ሰኔ 2002 ዓም በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16.5 መሰረት በኤጀንሲው የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ተዘጋጅቶ ተጫራቾች የቴክኒካል

መስፈርቱን ሞልተው አቅርበዋል። ሆኖም የቴክኒካል ግምገማው ሲደረግ ሁለቱ ተጫራቾች ዶ/ር ገ/እግዚሐብሄር አለበል ህንጻ እና ዘሪሁን ደስታ ኢንተርፕራይዝ በተራ ቁጥር 1 እና 2 እንዲሁም በተራ ቁጥር 3 ከተመለከቱት ዝርዝር የመገምገሚያ መስፈርቶች ውስጥ የመጨረሻውን የመገምገሚያ ነጥብ ሳይጨምር አሸናፊ ከሆኑት ተጫራች የተሻለና ተቀራራቢ የሆነ ውጤት ያመጡ ቢሆንም በተራ ቁጥር 3 ከተመለከቱት ዝርዝር መገምገሚያ መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ 20 የኤጀንሲውን መኪኖች ማስተናገድ የሚችል ፓርኪንግ ያለው ለሚለው ለመጨረሻው መገምገሚያ መስፈርት ከተቀመጠው 15% አሸናፊው ተጫራች 15% ሲሰጣቸው ለሁለቱ በቴክኒካል መስፈርቱ ለወደቁት ተጫራቾች ግን 0% ሊሰጥ ችሏል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ተጫራቾች ሞልተው ባቀረቡት የቴክኒካል መስፈርት ላይ ይህን እንደሚያሟሉ የገለጹ ከመሆኑም በተጨማሪ በኦዲቱ ወቅት ባደረግነው ማጣራት ሁለቱም ተጫራቾች በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታ እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ለፋይናንሻል ግምገማው እንዳያልፉ የተደረጉ መሆኑ፤

3. በግዥ መመሪያው ክፍል 4 አንቀጽ 16.18.3 መሰረት ጨረታው በሁለት ኤንቨሎፖች እንዲቀርብ የተጠየቀ ሲሆን፣ የቴክኒክ ግምገማ ተደርጎ የተገኘው ውጤት ሥልጣን በተሰጠው አካል ከጸደቀ በኋላ ወጤቱ በጨረታው ለተሳተፉ ተጫራቾች በሙሉ በተመሳሳይ ጊዜ በጽሁፍ መገለጽ እንዳለበት እና በተለይም የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉት ተጫራቾች የሚጻፈው ደብዳቤ በጨረታው የተሸነፉበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን እንዳለበት ተመልክaል፡፡ ሆኖም የቴክኒክ ግምገማውን ላላለፉት ተጫራቾች የተጻፈ ደብዳቤ ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

<u>**የማሻሻያ ሃሳብ**</u>

የግዥ አዋጁን እና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን ያለመፈጸም፡-

- የጨረታ ሂደቱን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ፣ግልጽ አሰራር እንዳይኖር እና የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፣
- ለጥቅም ትስስር መንገድ ሊከፍት ስለሚችል፣
- ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል፣

ኤጀንሲው የግዥ አዋጁና መመሪያውን ተከትሎ ግዥዎችን መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.3. የቤት ኪራይ የጨረታ ግዥ ቴክኒካል ግምገማ በአግባቡ ባለመከናወኑ ምክንያት አለአግባብ ከመንግሥት ካዝና ገንዘብ ወጪ ስለመደረጉ፤

5.3.1. ግኝት

የፌዴራል የተቀናጀ መሠረተ ልማቶች ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ነሐሴ 3/2008 ዓ.ም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የቢሮ ኪራይ ማስታወቂያ ያወጣ ሲሆን በማስታወቂያ ከተገለጹት ውስጥ ተጫራቾች በዋንኛነት ሊያሟሏቸው ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ "ህንጻው ጥራቱን ጠብቆ የተሰራና ያለቀለት፣ የፌዴራል የመሰረተ ልማት መሥሪያ ቤቶች (መብራት ኃይል፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ ቴሌ) በአካባቢ የሚገኝ፤ በቂ የሆኑ የቢሮ አገልግሎቶች ማለትም እንደ መጸዳጃ ቤት (ለወንድና ለሴት ለየብቻ)፣ ውሃ፣ መብራት፣ የስልክና የኢንተርኔት አገልግሎት እና ሌሎችም ያለው መሆን እንዳለበት" ተመልክቷል፡፡ ሆኖም፡-

1. ከላይ በተራ ቁጥር 4.2 ከቀረበው ግኝት ለመረዳት እንደተቻለው ጨረታውን ያሸነፉት ግለሰብ በቴክኒካል ግምገማ ብቸኛ አሸናፊ ከሆኑ በኋላ ኤጀንሲው ነሐሴ 1 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ መስከረም 6 ቀን 2016) በደብዳቤ ቁጥር FIDCA/025/16 ለግለሰቡ በጻፈው ደብዳቤ የመስክ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት የታዩትን ክፍተቶች በ30 ቀናት ያለምንም ዋጋ ለውጥ ድርጅቱ ራሱ እንዲያስተካክል ካልሆነ ግን ኤጀንሲው ወደ ውል ስምምነት እንደማይገባ የገለጸ ቢሆንም አከራይ ድርጅቱ ምንም አይነት ማስተካከያ ሳያደርግ ኤጀንሲው ነሐሴ 3 ቀን 2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ መስከረም 8 ቀን 2016) የውል ስምምነት ተፈራርሞ የአሥር ወራት የቤት ኪራይ ቅድሚያ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤
2. ኤጀንሲው የተከራየው ህንጻ የተፈለገውን የኤሌክትሪክ ኃይል ያላሟላ በመሆኑና የኢንተርኔት መስመር ዝርጋታው ያልተጠናቀቀ በመሆኑ የኤሌክትሪክ ኃይል ለመጨመር በሚል ብር 615,221.29 በህንጻ አከራዩ በአቶ ሰለሞን ሹፌር ሃብቴ ስም ለመብራት ኃይል ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤
3. ኤጀንሲው የኔት ወርክ ዝርጋታውን ለፈጸመው ድርጅት የሚከፈል በሚል ወደ አከራዩ አካውንት ብር 138,000.00 በማዘዋወር ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

በአጠቃላይ ኤጀንሲው በጨረታ ማስታወቂያ መሰረት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች ሳይሟሉ የኪራይ ውል በመፈጸሙ ለተጨማሪ ሥራዎች በድምሩ ብር 753,221.29 አላግባብ ከመንግሥት ካዝና ወጪ እንዲሆን ያደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ገንዘቡ ከአከራይ ድርጅቱ እንዲተካ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኤጀንሲው ባወጣው የቤት ኪራይ የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይሟሉ ግለሰቡ አሸናፊ እንዲሆኑ በመደረጉ ምክንያት የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ከመቻሉም በላይ የጨረታ ሂደቱ ተዓማኒነት የሌለው መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ስለሆነ በጨረታ ግምገማ ሂደቱ ላይ በተሳተፉት፣ ባጸደቁት እና አለአግባብ የመንግሥት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን በፈቀዱት ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም አለአግባብ ወጪ የተደረገው የመንግሥት ገንዘብ በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

5.4. <u>በግዥ መመሪያ መሰረት ያልተፈጸመ የግንባታ ክፍያ</u>፣

5.4.1. <u>ግኝት</u>

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከኮንስትራክሽን ድርጅቶች ጋር ባደረገው የህንጻ ግንባታና የዕድሳት ውል መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎች በውሉና በህጉ መሰረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ናእዳ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ በብር 1,955,807.60 የኦፕሬሽን ክፍል እና የኢንዶስኮፒ ህክምና ክፍል ጥገና ሥራ ለማከናወን ውል የፈጸመ ሲሆን፣ በተጨማሪም ኮሌጁ የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የብር 5,843,954.05 የተጨማሪ ሥራ ውል የተፈራረመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(3ለ) መሰረት በተጨማሪነት የሚታዘዘው የግንባታ ሥራ የገንዘብ መጠን ከመጀመሪያው ውል ጠቅላላ ዋጋ ከ30% (ሰላሳ በመቶ) የበለጠ መሆን እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም ለተጨማሪ ሥራዎች ተብሎ የተፈጸመው ውል ከመጀሪያው ውል ጋር ሲነጻጸር በ299% የጨመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በግዥ መመሪያው ከተፈቀደው በላይ ለለውጥ ሥራዎች ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት የሚሆን እና አሰራሩ ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል

መሆኑ ታውቆ ሂደቱ የግዥ መመሪያው በሚፈቅደው አግባብ መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.5. በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤

5.5.1. ግኝት

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ሂሳቦች በተገቢው የሒሳብ መደብ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአሥራ አንድ መሥሪያ ቤቶችና በአምስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ብር 4,427,922.71 መመዝገብ ባለባቸው የሂሳብ መደቦች ሳይመዘገቡ ተገኝቷል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ- 25 ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ወጪዎች በተገቢው ሂሳብ መደብ ካልተመዘገቡ በየሂሳብ መደቡ የተመለከቱት ሒሳቦች ትክክለኛውን ከወጪ ቀሪ እንዳያሳዩ ምክንያት ሊሆኑ እና የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት ሊያሳጡት የሚችሉ መሆኑን በመገንዘብ ወጪዎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በትክክለኛው (በተገቢው) የሂሳብ መደብ (ኮድ) መመዝገብ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.6. ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ የአበል ክፍያዎች፣

5.6.1. ግኝት

የውሎ አበልና የበረሃ ክፍያ የፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ባወጣው የመንግሥት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበልና የበረሃ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት መፈጸሙን እንዲሁም ለትምህርት እና ለትራንስፖርት ተብሎ በየወሩ የሚፈጸሙት አበሎች በሚመለከተው የመንግስት አካል የተፈቀዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በዘጠኝ መሥሪያ ቤቶችና በሶስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች 12,625,678.44 ከውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ ውጭ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን፣ ከፍተኛውን የክፍያ መጠን ከያዙት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ብር 11,990,000.50 ከወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ ውጪና በሚመለከተው

የመንግሥት አካል ሳይፈቀድ የራሱን የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ በማውጣት በተጨማሪ የፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ መሆኑ፤

2. የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አንድ ሰራተኛ የገራይሌ ብሄራዊ ፓርክ የህግ ክፍል ሰራተኛ ሆነው በየወሩ ብር 900.30 የበረሃ እየተከፈላቸው እንዲሰሩ ጥር 13 ቀን 2008 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ሠሀ43/22/08 የተመደቡ መሆኑ ተገልጾ ደብዳቤ የተጻፈላቸው ቢሆንም ሰራተኛው በትምህርት ላይ የሚገኙ እና በክርክር ላይ መሆናቸውን በመግለጽ ምደባውን ተቃውመው ጥር 22 ቀን 2009 ዓ.ም በጻፉት ማመልከቻ አሳውቀዋል፡፡ ሆኖም ግለሰቡ የሥራ ምድብ ቦታቸው ላይ ሳይገኙ ከመጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም እስከ ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ለዘጠኝ ወራት ያህል በወር ብር 900.30 በጠቅላላው ብር 8,102.70 የበረሃ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
3. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ጥቅምት 14 ቀን 1970 ዓ.ም በወጣው የመንግሥት ሠራተኞች የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያ መመሪያ ቁጥር 1/መ58/31 መሠረት የትራንስፖርት አበል የሚከፈለው አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በከተማ ክልል ውስጥ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ አዘውትሮ እየተዘዋወረ ለሚያከናውነው ሥራ ማስፈጸሚያ እንደሆነና ለሥራ መደቡ ሲፈቀድ ተግባራዊ እንደሚደረግ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ሜዲካል ኮሌጁ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴርን ሳያስፈቅድ ለኮሌጁ ፖስተኛ ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 500.00 የ10 ወር በጠቅላላው ብር 5,000.00 የትራንስፖርት አበል ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
4. የቀድሞው የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ሰኔ 10 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር ሲስሚ30/ጠ13/40/880 ባስተላለፈው ሰርኩላር በተለያዩ ተቋማት በሥራ ባህሪያቸው የተነሳ ለጤና ጠንቆች ተጋላጭ በሆኑ የሥራ መደቦች ላይ መደበኛ ሥራ ለሚያከናውኑ ሠራተኞች የሚፈጸመው የወተት አበል ክፍያ ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 30 ወደ ብር 80 ከፍ እንዲል በወሰነው መሠረት ክፍያ የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን ከሐምሌ 01/2008 እስከ ታህሳስ 30/2009 ድረስ ባለው ጊዜ በተላለፈው ሰርኩላር መሠረት ለ54 ሠራተኞች ለእያንዳንዱ ሠራተኛ በወር ብር 80 ለ54 ሰራተኞች ለሰባት ወራት ብር 30,240.00 ክፍያ

መፈጸም ሲገባው ብር 177,194.00 የወተት ግኘ የፈጸመ በመሆኑ በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ በብር 146,954.00 ከላሜ ዴይሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የወተት ግኘ የፈጸመ ሲሆን፣ በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ሁኔታው አግባብ አለመሆኑ ተገልጾ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድበት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምቱ ሳይወሰድ በዚህ በጀት ዓመት ወቅትም ግኘው የተፈጸመ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 19 እና በዚሁ ጽሁፍ አባሪ ለ ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት የወጡ መመሪያዎችን ተከትሎ ክፍያን ያለመፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ደንብና መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመው የአበል ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም የአበል ክፍያዎች የወጡትን መመሪያዎች ተከትለው መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.7. ከልዩ ልዩ የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር ስለመኖሩ፤

5.7.1. ግኝት

በገቢ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ….ወዘተ ከወር ደመወዝ ጋር እተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባሳወቀው መሠረት መፈጸሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በአምስት መሥሪያ ቤቶች ብር **226,943.41** ከቤት አበልና ከዓመት ፍቃድ ክፍያ ላይ ሥራ ግብር ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

መንግሥት ያወጣውን አዋጅ ደንብና መመሪያ ተከትሎ ያለመፈጸም ለመንግሥት ገቢ መቀነስ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ታውቆ በገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ

ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.8. ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ፤

5.8.1. ግኝት

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 34/2 መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የትርፍ ሰዓት ሥራ አከፋፈል መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደገና ጳጉሜ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/13/37/820 በተጻፈ ደብዳቤ የትርፍ ሰዓት ክፍያው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ ማሳወቁ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ሳይፈቀድ በአራት መሥሪያ ቤቶች ብር 475,543.58 የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 19 እና በዚሁ ጽሁፍ አባሪ ለ ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

መንግሥት ያወጣውን ደንብና መመሪያ ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም የመንግሥት ገንዘብን ለብክነት ሊያጋልጥ ከመቻሉም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል ስለሆነ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ በሚመለከተው አካል እንዳይፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.9. ከግዥና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰ እና ተቀንሶ ያልተመዘገበ ሂሳብ፤

5.9.1. ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ዓ.ም አንቀጽ 53 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 ዓ.ም አንቀጽ 24 ተራ ቁጥር 1 እና 2 በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ማንኛውም ወኪል በሚፈፅመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ እንዲያደርግ በተደነገገው መሠረት ተግባራዊ መደረጉን እንዲሁም ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በውሉና በህጉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና ተገቢው ምዝገባም የሚከናወን መሆኑን

ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-ከግዥና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰ እና ተቀንሶ ያልተመዘገበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ (ለዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ አባሪ ሐ ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

በሂሳብ አቀናነሱ እና በአመዘጋገቡ ላይ በታዩት ስሕተቶች ምክንያት፡-

- የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ ሊቀነስ የሚገባው ገንዘብ ሳይቀነስና መከፈል የሌለበት ገንዘብ ሊከፈል ስለሚችል፣
- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፣

ለታዩት ስህተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ፤ መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ እንዲሰበሰብ፤ መመዝገብ ያለበት ሂሳብ እንዲመዘገብ፤ ለወደፊቱም በግዥና በግንባታ ክፍያ አፈጻጸምና አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

5.10. በውል ስምምነት መሰረት ያልተፈጸመ ክፍያ፤

5.10.1. ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16(17) መሰረት ኮሌጁ ለፈጻሚቸው ግዥዎች ተገቢ ውል የሚፈጽም መሆኑንና የተፈጸሙት ክፍያዎችም በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

1. የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ከኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማኅበር (Construction Design S.C.) ጋር በፈጸመው የማማከር አገልግሎት ውል መሰረት ብር 1,857,181.90 ክፍያ መፈጸም ሲገባው ኮሌጁ እስከ ሰኔ 30, 2010 ዓ.ም ድረስ ብር 4,025,000.00 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 16 (14) (5ለ) መሰረት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል ጊዜው በመራዘሙ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከአስራ አምስት በመቶ (15%) የበለጠ መሆን እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም ኮሌጁ ለአማካሪው የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ብር ብር 2,167,818.10 ተጨማሪ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ተጨማሪ ክፍያው ከመጀመሪያው ውል ብር 1,857,181.90 ጋር ሲነጻጸር በ116.7% የጨመረ መሆኑ፣
2. በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(11) በአዋጁ አንቀጽ 51(1ሰ) እና 51(2) መሰረት ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጽመው ግዥ

የውል ሥምምነት መፈረም እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም ኮሌጁ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ በተጨማሪነት ለፈጸመው ክፍያ ብር 2,167,818.10 የተጨማሪ የማማከር ሥራ ውል ሥምምነት ያልቀረበለት መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ ለተጨማሪ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል በኮንስትራክሽን ክፍያ አፈጻጸም ላይ በመመሪያው መሰረት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ እሳስበናል፡፡

5.11. የግንባታ ሥራው በተቋረጠበት ጊዜ የተከፈለ የማማከር ክፍያ፤

5.11.1. ግኝት

የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የሚከፍላቸው ክፍያዎች መንግሥት ባወጣው ህግ ደንብና መመሪያው መሰረት ለመሆኑ በናሙና ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ከሳምሶን ገ/ዮሀንስ ጋር ተዋዉሎ የሚያሰራውን የሰራተኞች መኖሪያ ቤት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክስዮን ድርጅት የማማከሩን ስራ ያከናውን የነበረ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ኮንትራክተሩ የኮንስትራክሽን ስራዉን ሳይጨርስ አቋርጦ ከወጣ ከአመት ከስድስት ወር በላይ ሆኖት እያለ ድርጅቱ የማማከር አገልግሎቱን ላልሰጠበት ብር 115,469.70 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ኮንትራክተሩ የግንባታ ሥራዉን ሳይጨርስ ካቋረጠ ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በላይ የሆነው ሲሆን ግንባታው ተቋርጦ እያለ አማካሪው ድርጅት ማንን እንዳማከረ ባልታወቀበት ሁኔታ ለማማከር ስራ ተብሎ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ሁኔታው ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል ስለሆነ ኮሌጁ የማማከር አገልግሎት ዉሉን ማቋረጥ እንዳለበት እሳስበናል፡፡

5.12. በግዥ መመሪያው መሠረት ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ ያተቻለ የአጥር የጥበቃ ቤትና የፋይናንስ ቤት እድሳት፤

5.12.1. ግኝት

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ታህሣሥ 5/2008 ዓ.ም በሄራልድ ጋዜጣ በወጣው የአጥር፣ የጥበቃ ቤትና የፋይናንስ ክፍል እድሳት ግንባታ ግልጽ ጨረታ ሂደቱን አግባብነት በግዥ አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና ሰኔ 2002 ዓም በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኢንስቲትዩቱ በብር 3,592,281.08 ከዝናዬ ገብረ መድህን ሕንፃ ተቋራጭ ውል መፈጸሙ ታውቋል፡፡ ሆኖም ኢንስቲትዩቱ ጨረታውን በብር 2,074,854.04 አሸናፊ ከሆነው ዳንኤል ፍሰኃ ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር መጋቢት 23 ቀን 2008 ዓ.ም የውል ስምምነት የገባ ሲሆን ተቋራጩ ሚያዝያ 12 ቀን 2008 በደብዳቤ ቁጥር በጻፈው ደብዳቤ ዳ/ፍ/12/2008 የአጥር ግንባታው የሚሠራው በጥርብ ድንጋይ ሳይሆን በኖርማል ድንጋይ መስሏቸው ጨረታውን እንደተወዳደሩ በመግለጽ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው የጠየቁትን ጥያቄ ኢንስቲትዩቱ ውድቅ በማድረግ ተቋራጩ በሕግ እንደሚጠየቅ በደብዳቤ ቁጥር ኢ.አጤኢ.211/399 ግንቦት 18 ቀን 2008 ዓ.ም ለተቋራጩ አሳውቋል፡፡ በሌላ በኩል በግዥ መመሪያው አንቀጽ 16.25.3 መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ አቅራቢው በውሉ መሠረት አለመፈጸሙን ሲያረጋግጥ አቅራቢው ያሲያዘውን የውል ማስከበሪያ መውረስ እንደሚኖርበት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ የውል ግዴታውን ሳይፈጽም የቀረውን ሥራ ተቋራጭ የውል ዋጋውን ብር 2,074,654.04 10% ብር 207,465.48 የውል ማስከበሪያ ወደ ኢንስቲትዩቱ ገቢ እንዲሆን ለመደረጉ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የውል ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረው ሥራ ተቋራጭ የውል ዋጋውን ብር 2,074,654.04 10% ብር 207,465.48 የውል ማስከበሪያ ለኢንስቲትዩቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃው እንዲቀርብ መደረግ እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

5.13. በግንባታ ሥራዎች ላይ የታዩ ክፍተቶች፤

5.13.1. ግኝት

የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ ከተለያዩ የግንባታ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎችን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን የተጠናቀቁት የግንባታ ሥራዎች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ኮሌጁ ከአሊ ሞሚን ጠቅላላ የውሀ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ጋር ለውሀ መስመር ዝርጋታ ግንባታ በብር 7,379,375.32 ውል የፈጸመና ሥራውም ተጠናቆ ከተቋራጩ ጋር ጊዜያዊ ርክክብ የፈጸመ ቢሆንም፡-

1.1. በውሀ መስመሩ ላይ ተዘርግተው የነበሩት በርካታ የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች ከመሀል የተነሱና በገዋኔ ከተማ በሚገኘው ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ግቢ ውስጥ ሜዳ ላይ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን፣ በውሀ መስመሩ ላይ የቀሩት የውሀ ማስተላለፊያ ቧንቧዎችም ቢሆኑ አልፎ አልፎ የወላለቁ መሆኑ፤

- ኮሌጁ የውሃ መስመሩን ዝርጋት ርክክቡ ከፈጸመበት ከመስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 60,000.00 የውሀ ማመላለሻ ቦቴ መኪና ተከራይቶ በድምሩ ብር 540,000.00 ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ ከመሆኑም በላይ ወጪው አሁንም የቀጠለ መሆኑ፤

1. ኮሌጁ ከሁሴን ኢብራሂም ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር በብር 9,221,913.25 የመኖሪያ ቤት ግንባታ ውል የፈጸመና ሥራው ተጠናቆ ርክክብ የተከናወነ ቢሆንም ለግንባታው የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ማስወገጃ አብሮ ስላልተገነባለት ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመታት በላይ ተቆልፎ የሚገኝ መሆኑ፤
2. ኮሌጁ ኤፍ ኤ ዋይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር በብር 5,468,710.00 የህንጻ ጥገና ግንባታ ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ጥገናው ከመጋቢት 2006 ዓ.ም ጀምሮ በስምንት ወራት ውስጥ ማለቅ እንዳለበት ቢጠቀስም ግንባታው ከመዘግየቱም በተጨማሪ የጥገናው ሥራ ተቋርጧል፡፡ ሆኖም ኮሌጁ በተቋራጩ ላይ ምንም ዓይነት ህጋዊ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶባቸው እየተገነቡና እየተጠገኑ ያሉ ግንባታዎች ላይ የተከሰተው ችግሩ ምንጩ ተጣርቶና ታውቆ መጠገን ያለባቸው ተጠግነው ተጨማሪ ግንባታ ለሚፈልጉትም አስፈላጊው ግንባታ ተደርጎላቸው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ካልተደረገ የግንባታው ወጤታማነት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ እና በግንባታው የክትትልና የቁጥጥር ሥራው ላይ ክፍተት መኖሩን ከማመልከቱም በተጨማሪ መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ ኮሌጁ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ሁሉ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

2. በኪራይ መኪና ለቢሮ ኃላፊዎችና ለዳይሬክተሮች

2.1. የሚሰጥ የሰርቪስ አገልግሎትን በተመለከተ፤

2.1.1. <u>ግኝት</u>

1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሰኔ 27 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ/1/2/47 የፌዴራል የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ሥምሪት እና አጠቃቀምን በተመለከተ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 32/2004 አንቀጽ 6(2) መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በመሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት ሥር ያሉ ተሽከርካሪዎች በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ የሚያስችል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት እንዳለባቸው፤ እንደመሥሪያ ቤቱ የሥራ ባሕሪ ለጋራ አገልግሎት፣ በልዩ የሥራ ባሕሪያቸው ተሽከርካሪ ለሚያስፈልጋቸው የሥራ ኃላፊዎች፣ ለፕሮጀክት፣ ለሥራ ክፍሎች እና እንዲሁም ለመስክና የከተማ አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን ለይተው ሊመድቡ እንደሚችሉ፤
2. ጥቅምት 14 ቀን 1970 ዓ.ም በወጣው የመንግሥት ሠራተኞች የልዩ ልዩ አበሎች ክፍያ መመሪያ ቁጥር 1/መ58/31 መሠረት የመደበኛ የትራንስፖርት አበል ለከፍተኛ ባለሥልጣኖችና ለመመሪያ ኃላፊዎች ወይም ተመሳሳይ ማዕረግ ላለው የተቀመጠው የነዳጅ መጠን ወይም በመመሪያው እንዲሰጥ የተወሰነው ገንዘብ ብቻ እንዲሰጥ፤
3. መንግሥት ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ለመንግሥት ሰራተኞች የሰርቪስ አገልግሎት መመቻቸቱ፤

በወጡት መመሪያዎች ላይ ተመልክቷል፡፡ መሥሪያ ቤቶች ለዳይሬክተሮች አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ካሏቸው ከላይ በተራ ቁጥር አንድ በተገለጸው አግባብ፣ በቂ ተሽከርካሪዎች ከሌሏቸው ደግሞ ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት በተገለጸው አግባብ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ሚኒስቴርን ወይም የሚመለከተውን የመንግሥት አካል ለትራንስፖርት የሚሆን አበል ማስፈቀድ ወይም በተራ ቁጥር 3 የተመለከተውን አማራጭ መጠቀም ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም፡-

- የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከላይ ከተዘረዘሩት አማራጮች ውጭ በበጀት ዓመቱ ለቢሮ ኃላፊዎችና ለጽህፈት ቤት ዳይሬክተሮች አገልግሎት የሚውሉ ለሰርቪስ አገልግሎት የሚሆን የመኪና ኪራይ ግዥ በብር 1,278,549.30 ከሞሰስ የመኪና ኪራይ እና አስጎብኚ የፈጸመ መሆኑ፣
- በተመሳሳይ ሁኔታ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ከፒልካን የመኪና አከራይ ለአንድ መኪና በቀን 750.00 ሂሳብ 8 ቶዮታ ኮሮላ አውቶሞቢሎችን ከግንቦት 21 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ለመከራየት የኪራይ ውል ገብቶ እና ለሶስት ወር ብር 540,000.00 የቅድሚያ ክፍያ ፈጽሞ ተሽከርካሪዎቹ ለስምንት ዳይሬክተሮች እንዲሰጡ ያደረገ ሲሆን በተጨማሪም የኢንስቲትዩቱ አንድ ዳይሬክተር በግላቸው መኪና ላይ ነዳጅ ተሞልቶ እንዲጠቀሙ በመወሰኑ ከግንቦት 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ብር 4,200.00 የሚያወጣ 600 ሊትር ነዳጅ በኩፖን እንዲሞላላቸው የተደረገ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ኢንስቲትዩቱ ለመስክ ሥራ አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር በከፍተኛ ወጪ ተሽከርካሪዎችን በመከራየት ለዳይሬክተሮች እንዲሰጡ ማድረጉ ህጋዊ መሰረት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ እና የመንግሥትን በጀት ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት ለመደገፍ በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ መሥሪያ ቤቶቹ የመኪና ኪራይ አገልግሎቱን እንዲቆም በማድረግ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ሚኒስቴርን ወይም የሚመለከተውን የመንግሥት አካል ለትራንስፖርት የሚሆን አበል ማስፈቀድ እንዳለባቸው እናሳስበናል፡፡

3. **መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ለመኝታ አገልግሎት የተፈጸመ ክፍያ፤**

3.1. **ግኝት**

የፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሰኔ 2004 ዓ.ም ባወጣው የመንግሥት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ ክፍል 2 አንቀጽ 5/1 መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ በሥራ በቆየባቸው ቦታዎች በተተመነው ከሙሉ አንድ ቀን የዉሎ አበል ተመን ዉስጥ 10% ለቁርስ፣ 25% ለምሳ፣ 25% ለእራት እና 40% ለአልጋ በመመደብ መከፈል እንዳለበት በተቀመጠው መመሪያ መሰረት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩቱ፡-

1. በአዲስ አበባ በሚገኘው በሲያን ሲቲ ሆቴል ከሰኔ 6 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 20 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ለምርጥ ተሞክሮ ቅመራ እና ሰነድ ዝግጅት ላይ ለተሳተፉ 18 የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ከአዲስ አበባ ሳይወጡ ለአልጋ በቀን ለአንድ ሰው የተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ ብር 1,597.39 በጠቅላላው ብር 330,378.42፤
2. ለኢንስቲትዩቱ ለ16 የሥራ አመራር አባላት ግንቦት 4 ቀን 2009 ዓ.ም አዝማን ሆቴል በእስትራቴጂክ እቅድ ዙሪያ ለተደረገው ውይይት ለተሳታፊዎች የአልጋ አገልግሎት ብር 25,549.44፤ በድምሩ ብር 355,927.86 ከመመሪያ ውጭ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለውሎ አበል የሚፈጸሙ ክፍያዎች መንግሥት ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ የማይፈጸም ከሆነ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል መሥሪያ ቤቱ አሰራሩን በውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያው መሰረት ማስተካከል እንዳለበት እናሳስበናል፡፡

4. **በህግ ሳይፈቀድ የተፈጸመ የኢንሹራንስ ክፍያ፤**

4.1. **ግኝት**

የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በመንግሥት ሳይፈቀድ እና ክፍያውን የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይኖር ለኤጀንሲው ሰራተኞችና ለቤተሰቦቻቸው የጤና ኢንሹራንስ (Health Insurance) ብር 203,210.36፤ የግሩፕ የህይወት ዋስትና (Group Life Insurance) ብር 2,195,303.61 እንዲሁም ለገንዘብ ዋስትና (Money &

Fedelity Guarantee) ብር 18,498.00 በድምሩ ብር 2,417,011.97 ለተለያዩ የኢንሹራንስ ድርጅቶች ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተፈቀደ ክፍያን መፈፀም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል ስለሆነ ኤጀንሲው ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ከሚመለከተው አካል ፍቃድ ማግኘት እንደሚገባው፤ ነገር ግን ክፍያውን የሚደግፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሳይኖር ክፍያ መፈጸም አግባብ ስላልሆነ አሰራሩ መቆም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.2. አለአግባብ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ፤

4.2.1. ግኝት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በጀት ዓመቱ የተከፈለውን የደመወዝ ሂሳብ ክፍያ አግባብነት፣ የምዝገባውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ በሶስት መሥሪያ ቤቶች ከሥራ ከለቀቁ በኋላና መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ ብር 4,994,688.65 የተገኘ ሲሆን አለአግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ፡-

1. ለግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ.13/ጠ48/46/1049 ባስተላለፈውና በጸደቀው የኤጀንሲው የሥራ መደቦች ደረጃ፣ የደመወዝ ስኬል እና የተፈላጊ ችሎታዎች መመሪያ መሰረት ክፍያ መፈጸም ሲገባው ኤጀንሲው ከሐምሌ 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ባለው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ከብር 3,499.00 ዝቅተኛው የደመወዝ ስኬል እስከ ከፍተኛው የደመወዝ ስኬል ብር 5,535.00 በተፈቀደው መሰረት ብር 1,351,701.00 መከፈል ሲገባው ባልተፈቀደ ዝቅተኛው የደመወዝ ስኬል ብር 15,539.00 እስከ ከፍተኛው የደመወዝ ስኬል ብር 50,035.00 ድረስ ብር 6,120,444.00 ክፍያ በመፈጸሙ ምክንያት ከተፈቀደው በላይ ብር 4,768,743.00 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

2. በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውና ላኪና ተቀባይ መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ሠራተኛው ሲስማሙ አንድን የመንግሥት ሠራተኛ እኩል በሆነ ደረጃና ደመወዝ ተመሣሣይ ወደ ሆነ የስራ መደብ ኤጀንሲውን በማሳወቅ አዛውሮ ማሰራት እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሰረት በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በዝውውር የመጡ ሠራተኞች ተመሳሳይ ባልሆነ የስራ ደረጃ እና ደመወዝ የተመደቡ በመሆኑ ከተዛወሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ብር 125,445.63 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላና ያልተፈቀደ የደመወዝ ክፍያ መፈጸም፤ እንዲሁም መንግሥት ያወጣውን አዋጅ ተከትሎ ዝውውር ያለመፈጸም የክፍያውን ተገቢነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ፣ የዜጎችን ተወዳድሮ የመቀጠር መብት ሊገድብና ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ከስራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለው ደመወዝ እንዲሁም ከተፈቀደው የደመወዝ ስኬል በላይ የተፈጸመው የደመወዝ ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ እንዲሁም የሠራተኞች ዝውውር መፈጸም ያለበት በአዋጁ መሠረት በነበሩበት ደረጃና ደመወዝ መሆን ስላለበት ሰራተኞች ሲዛወሩም ሆነ ሲመደቡ ህጉን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.3. ተገቢው ማስረጃ ያልቀረበለት የወጪ ሂሳብ፤

4.3.1. ግዥ

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ብብር ሚኒስቴር የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለወጪ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ ቀርቦላቸው የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤ ለተፈጸመው ክፍያ ብር 259,472.31 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ፣ በብር 37,506.00 ለተፈጸሙት ግዥዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው መሆኑ፣ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ -22 ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

ለክፍያዎቹ የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ስለማይቻል፣ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ሊሆንና ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ስለሚችል የወጪ ማስረጃ ላልቀረበላቸው ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብላቸው ማስረጃ ሊቀርብላቸው ካልቻለ ግን ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.4. በድጋሚ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤

4.4.1. ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት ነሐሴ 1999 ዓ.ም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ለሰራተኞች ፓራትሩፐር ጫማ ከካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ በብር 97,019.48 ገዝቶ ክፍያውን ባንክ በኩል ወጪ በቀጥታ ፈጽሞ በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ ሲሆን፣ ይህው ሂሳብ ወጪን ዴቢት፣ ተሰብሳቢ ሂሳብን በድጋሚ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የወጪ ሂሳብን በድጋሚ መመዝገብ የሒሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው የወጪና የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛውን ሂሳብ እንዳያመለክቱ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው የሚችል በመሆኑ በድጋሚ ለተመዘገበው ሂሳብ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራለት፤ ለወደፊቱም በአመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.5. ለስፖንሰርሺፕ ተብሎ የተፈጸመ ክፍያ ስለመኖሩ፤

4.5.1. ግኝት

የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በአንቀጽ 6(1) ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈጸመው ወይም ወጪ የሚደረገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ እንደሆነ በመመሪያው ላይ ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ለስፖንሰር ተብሎ የሚያዝ በጀት እንደሌለ እየታወቀ በሁለት መሥሪያ ቤቶች ብር 75,000.00 ለስፖንሰርሺፕ ተብሎ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩም፡-

1. የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር የወይን ጋዜጣ አርባ ሁለተኛ ዓመት ምክንያትን በማድረግ ብር 50,000.00 ስፖንሰር ያደረገ መሆኑ፣
2. የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን
3. ለብሄረ አማራ ዴሞክራሲ ንቅናቄ (ብአዴን) 36ኛ ዓመት የምስርታ በዓል በሚል ብር 5,000.00፣
4. ለአርባ ምንጭ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በባንክ ቁጥር 1000021677047 ብር 20,000.00፣

በድምሩ ብር 75,000.00 ለእስፖንሰር ሺፕ ተብሎ በጀቱ ከተያዘለት ዓላማ ወጪ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የመንግሥት በጀት የሚፈቀደው በእቅድ ለተያዙ ጉዳዮች ብቻ ስለሆነ እና ለስፐንሰርሺፕ ተብሎ የሚፈቀድ በጀት እንደሌለ እየታወቀ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት የሚሆንና ተጠያቂነትን የሚያስከትልና አሰራሩም አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.6. በመረጃ ያልተደገፉ የሂሳብ ማስተካከያዎች፤

4.6.1. ግኝት

የምዝገባ ለውጦች ሲደረጉ የፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያን መሰረት በማድረግ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያዎች የተሰራላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች የሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ (ጆርናል ቫውቸር) የተዘጋጀላቸው ቢሆንም፡-

- ስህተቱ በየትኛው የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀመ፣
- የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት፣

ማስተካከያ በተሰራበት የሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ ላይ የሚገለጽ መሆኑን የማስተካከያውን ምዝገባ ተገቢነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰባት መሥሪያ ቤቶች እና በሁለት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ለብር 12,728,064.14 በዴቢትና በክሬዲት የተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች በተገለጸው አግባብ የተፈጸሙ ባለመሆኑ የተሰራው ማስተካከያ ትክክለኛ መሆን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

(ለዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ አባሪ ሀ ተያይዟል)

4.6.2. ***ሥጋት***

መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ ማስተካከያ ሲሰሩ የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት እንዲሁም ስህተቱ በየትኛው የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀመ ሳይገለጽ (ሳይታወቅ) እንዲሁም የተዘጋጀው ጆርናል ቫውቸር በሚመለከተው ሰራተኛና ኃላፊ ሳይፈረምና ሳይጸድቅ የሚሰሩ የሂሳብ ማስተካከያዎች ለጥፋትና ለጉድለት መንገድ ሊከፍቱ እና የሒሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጣቸው ስለሚችል በፋይናንስ ሥርዓትና መመሪያው መሰረት ለተሰሩት የሂሳብ ማስተካከያዎች ተገቢው መረጃ ሊቀርብላቸው እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.7. **ከመመሪያው ውጪ የተከፈለ የቤት አበል፤**

4.7.1. **ግኝት**

1. **በዋና እና በምክትል ዋና ዳይሬክተር ደረጃ ተሹመው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ለሚመሩ ኃላፊዎች የሚሰጥ ጥቅማጥቅምን በተመለከተ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ሚያዝያ** 16 **ቀን** 2004 **ዓ.ም በቁጥር መ**80-899/62 **በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት የቤት አበል በወር** 1,500.00 **እንዲያገኙ ውሳኔ ተላልፏል፡፡ ሆኖም በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ሆነዉ ለተመደቡት ኃላፊ ከመጋቢት** 1 **ቀን** 2008 **ዓ.ም እስከ ሰኔ** 30 **ቀን** 2009 **ዓ.ም ድረስ በወር ብር** 1,500.00 **በጠቅላላው ብር** 24,000.00 **የቤት አበል ተከፍሏቸዉ የተገኘ መሆኑ፤**
2. **የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሰኔ** 17 **ቀን** 2005 **በቁጥር መ**200-8/3/6 **በተጻፈ ደብዳቤ ለጤና ሙያተኞች ከፈቀደው የተሻሻለ የተረኝነት አበል እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ውስጥ አንዱ ለመኖሪያ ቤት ኪራይ ማካካሻ የሚሆን እንደ ኃላፊነታቸው የሚከፈል የቤት አበል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁንና የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጁ መመሪያውን ባልተከተለ ሁኔታ ለሶስት የአቤት ሆስፒታል ዶክተሮች ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት የሚደርስ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል በየወሩ በብር** 10,000.00 **ተዋውሎ ከሶስት ወር እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ በጠቅላላው ብር** 270,000.00 **የመኖሪያ ቤት የቅድሚያ ኪራይ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤**

የማሻሻያ ሃሳብ

በመንግሥት የወጣውን የቤት አበል መመሪያ ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም ለመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ ክፍያው በአስቸኳይ እንዲቆምና በመመሪያው መሰረት እንዲፈጸም ወይም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ሆነ ሜዲካል ኮሌጁ የሚመለከተውን አካል ማስፈቀድ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.8. ያለአግባብ የተከፈለ የዓመት ፈቃድ ክፍያ፤

4.8.1. ግኝት

1. በፌዴራል የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅ 515/1999 ምዕራፍ ሁለት አንቀጽ 39:-

    1.1. ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ምክንያት መሥሪያ ቤቱ ለሰራተኛው የዓመት እረፍት ፍቃዱን ሊሰጠው ያልቻለ እንደሆነ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከሁለት የበጀት ዓመት ላልበጠ ጊዜ ሊያስተላልፈው እንደሚችል እና ሆኖም ያልተጠቀመበት የዓመት እረፍት ፍቃድ በሶስተኛው በጀት ዓመት ለሰራተኛው መሰጠት እንዳለበት፤

    1.2. ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 36(3) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የዓመት ፍቃዱ ለሚተላለፍበትና ፍቃዱ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ ሰራተኛ በጀት በቅድሚያ በማሲያዝ ከተላለፈው የዓመት ፍቃድ ውስጥ የመጀመሪያውን የአንዱን ዓመት የሥራ ቀናቶች ብቻ በማሰብ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠው መደረግ እንዳለበት፤

ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ለዓመት እረፍት ሥራ የፈጸመው ክፍያ አግባብነትን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዋጁ መሰረት የ2007 በጀት ዓመት የአመት ፍቃድ በገንዘብ የተቀየረ ሲሆን የ2008 በጀት ዓመት ፈቃድ ወደ 2010 በጀት ዓመት መዞር ወይም ፍቃዱ ለሰራተኛዉ ፈቃድ መስጠት ሲገባው ያለአግባብ ብር 88,497.60 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የመንግሥት ሰራተኞች አዋጅን ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል እና ተጠያቂነትንም የሚያስከትል በመሆኑ ያለአግባብ የተፈጸመው የዓመት ፈቃድ ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም የዓመት እረፍት ፍቃድ በገንዘብ ሲቀየር በአዋጁ መሰረት መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.9. ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው መገዛት ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት የተፈጸመ ግዥ፤

4.9.1. ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/3 መሰረት፣ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የስትራቴጂ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ በ2009 ዓ.ም. 1000 የጠረጴዛ ካሌንደር በስሙና አርማው ለማሳተም በሰበሰበው የዋጋ ማወዳደሪያ መሰረት ብሉዳን ህትመት ማስታወቂያ ያንዱ ዋጋ ብር 46.50 በጠቅላላው ብር 46,500.00፤ ማስተር ማተሚያ ቤት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ደግሞ ያንዱን ዋጋ ብር 87.27 በጠቅላላው በብር 87,270.00 ያቀረበ ሲሆን፣ ኤጀንሲው ያለምንም ተጨባጭ ምክንያት ግዥውን ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ከማስተር ማተሚያ ቤት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግዥ በመፈጸሙ ምክንያት ብር 40,770.00 ተጨማሪ ገንዘብ ወጪ እንዲሆን የተደረገ መሆኑ፤
2. **የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**
   - 2.1. መሥሪያ ቤቱ ሶፋ እና የቡና ጠረጴዛ ከሰንሜት ኢታሊ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ግዥ ሲፈጽም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት ምናየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ብር 162,949.99 ሆኖ እያለ ያለምንም ተጨባጭ ማብራሪያ ግዢው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ሰንሜት ኢታሊ በብር 194,600.00 እንዲፈጸም በመደረጉ በብር 31,650.00 በብልጫ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣
   - 2.2. መሥሪያ ቤቱ በብር **108,000.00** ለሚኒስቴሩ አጃቢዎች፣ ሾፌሮችና ፕሮቶኮሎች የደንብ ልብስ ግዥ ሲፈጸም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት አምባሳደር ኃ/የተ/የግ/ማህበር ብር 26,459.88 ሆኖ ሳለ ነገር ግን ተጠቃሚ

ሠራተኞቹ በመሩጡት ተብሎ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ከትሩ ፋሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በብር 108,000.18 በመግዛቱ በብልጫ ብር 81,540.30 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 153,960.30 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቶቹ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥው የሚፈጸም ከሆነ፡-

- በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ስለሚያደርግ፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥው ለምን እንደተፈጸመ ሁኔታውን በማጣራት ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም ግዥ በመንግሥት የወጣውን አዋጅና መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.10. <u>ጨረታውን በዝርዝር ካሸነፈው ድርጅት መግዛት ሲገባው በጥቅል ካሸነፈ ድርጅት የተፈጸመ ግዥ</u>፤

4.10.1. <u>ግኝት</u>

ለኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በ2009 በጀት ዓመት ለፈጸማቸው የእቃ ግዥዎች የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 16.8 መሰረት፡-

ሀ/ ለግዥው ተቀባይነት ያለውን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት በመወሰን ዝቅተኛ የቴክኒክ መመዘኛውን ካàሉት ተጫራቾች መካከል አነስተኛ ዋጋ ያቀረበውን ተጫራች መምረጥ፣ ወይም

ለ/ ግዥዉ የሚኖረውን ጠቀሜታ ወይም ኢኮኖሚያዊ ዕሴት ሊወስኑ የሚችሉ መስፈርቶች እና እያንዳንዱ መስፈርት የሚኖረውን አንጻራዊ ክብደት በግልጽ በጨረታ ሰነዱ ላይ በማሳየትና በነዚህ መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ ግምገማ በማካሄድ በአጠቃላይ ውጤት ከፍተኛ ውጤት ያገኘውን መምረጥ፣ እንዳለበት

ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ኢንስቲትዩቱ የሴኩሪቲ ካሜራ ግዥ በጨረታ ሲፈጸም የግዥ ኮሚቴው እያንዳንዱን ዕቃ እና አገልግሎት በዝርዝር አወዳድሮ አነስተኛ ዋጋ ካቀረቡ ድርጅቶች በጠቅላላ በብር 280,255.00 መግዛት ሲገባው ግዥውን በጥቅል ዋጋው በብር 368,115.00 በመፈጸሙ ምክንያት ብር 87,860.00 ለተጨማሪ ክፍያ እንዲወጣ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ግዥዎች የግዥ አፈጻጸም መመሪያውን ተከትለው የማይፈጸሙ ከሆነ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለዉን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ካለማስገኘቱም በተጨማሪ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆንና ለብክነትም ሊዳረግ ስለሚችል ኢንስቲትዩቱ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን መከተል እንዳለበት፣ ያለአግባብ ክፍያ እንዲፈጸም ምክንያት የሆኑ ኃላፊዎችና ሰራተኞችም ተጠያቂ እንዲሆኑ እና ለወደፊቱ ተመሳሳይ የሆነ ስህተት እንዳይፈጠር ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.11. <u>ተመላሽ ባልተደረጉ የሞባይል ቀፎዎችና በስልክ ቁጥሮቹ ክፍያ እየተፈጸመ የሚገኝ ስለመሆኑ</u>፣

4.11.1. <u>ግኝት</u>

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስልክ ክፍያ የሚፈጽመው በመሥሪያ ቤቱ ለሚገኙ ኃላፊዎችና ሰራተኞች መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

1. አቶ መኮንን ማንያዘዋል ከሐምሌ 2005 ዓ.ም ጀምሮ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተዛወሩ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም እሳቸው ሲጠቀሙበት የነበረው የሞባይል ስልክ ቁጥር 0911-204404 ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ስለመደረጉ ማስረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ በ2009 በጀት ዓመት በናሙና ከታዩት ክፍያዎች ውስጥ በስልክ ቁጥሩ ብር 8,655.22፣
2. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚኒስቴር ደኤታ ተሹመው ሲያገለግሉ የነበሩት ክብር አቶ ታደሰ ኃይሌ ህዳር 6 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር መ/10-830/4 በተጻፈ ደብዳቤ ከህዳር 15 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ከኃላፊነት የተነሱ መሆኑን የተገለጸ ቢሆንም እሳቸው ሲጠቀሙበት የነበረው የሞባይል ስልክ ቁጥር 251-911-22-53-83 ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ስለመደረጉ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ

ከመሆኑም በተጨማሪ በ2009 በጀት ዓመት በናሙና ከታዩት ክፍያዎች ውስጥ በስልክ ቁጥሩ ብር 4,523.35 ፣

በድምሩ ብር 13,178.57 አለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የሞባይል ቀፎዎቹና ቁጥሮቹ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ካልተደረጉ በስልክ ቁጥሮቹ ለሚደረጉ ማንኛውም እንቅስቃሴዎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተጠያቂ ሊሆን ከመቻሉም በተጨማሪ አላስፈላጊ ክፍያ እየተፈጸመ የሚገኝ ስለሆነ የሞባይል የስልክ ቀፎዎቹና ቁጥሮቹ እንዲሁም አለአግባብ የተፈጸመው ክፍያም ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጠር ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.12. <u>በፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት ያልተደረገ ጥቅም ላይ ያልዋለ የነዳጅ ሂሳብ</u>፣

4.12.1. <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረግ ሂሳብ ከመንግሥት ግምጃ ቤት የገንዘብ ምንጭ ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃ በቅድሚያ በሰነድ ተከፍሎ ሳይወራረድ በየዓመቱ መጨረሻ በሣጥን ከተቆጠረው ውስጥ ክፍያው በበጀት ዓመቱ የተፈጸመና አገልግሎቱ በተከታዩ በጀት አመት ውስጥ የሚሰጥ አላቂ ንብረት ሂሳብ በፈሰስ ሂሳብ ሊመዘገብና ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ፈሰስ ሊደረግ እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ ሆኖም፡-

የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም በጆርናል ቫውቸር ቁጥር 0050603 እና 0050604 ብር 100,000.00 የነዳጅ ግዥ ፈጽሞ በወጪ እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ በቅድሚያ ለነዳጅ ግዥ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 13,860.32 መሥሪያ ቤቱ ነዳጁን ለመጠቀሙ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ ስለመዋሉ ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 86,139.68፣

1. የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ ያልዋለና በቆጠራ የተገኘና መተማመኛ የተፈረመበት የሞባይል ካርድ ብር 23,845.00፣ በድምሩ ብር 109,984.68 በውስጥ ኦዲት በፈሰስ ሪፖርት እንዲካተት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በመመሪያው መሰረት በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ ያልዋለው ነዳጁ በፊስስ ሪፖርት ያለማካተት ተጠቂነትን ሊያሥከትል ስለሚችል በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ ያልዋሉት ነዳጅና የሞባይል ካርዶች ፊሰስ እንዲደረጉ፣ ለወደፊቱም በበጀት ዓመቱ ጥቅም ላይ ያልዋሉ እቃዎች እየተቆጠሩ በፊሰስ ሪፖርት ተካተው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5. በጀት

5.1 ሥራ ላይ ያልዋለ የመደበኛና የካፒታል በጀት፣

5.1.1. ግኝት

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፡- በድምሩ ብር 1,328,728,991.66 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 33 ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የመሥሪያ ቤቶቹን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ስለሚችል መሥሪያ ቤቶች ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በኃላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደረጉ እንደሚገባ እና በተጨማሪም መሥሪያ ቤቶቹ የበጀት አጠቃቀማቸው ላይ ተገቢ የሆነ ክትትል በማድረግና የማይጠቀሙበትን በጀት ለይተው በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

5.2. <u>ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ ሂሳብ</u>፤

5.2.1. <u>ግኝት</u>

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲመዛዘን፡- በድምሩ ብር 6,729,691.39 ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶቹ) ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 33 ተያይዟል)

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይጠየቅ ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ስለሚችል መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸው በቅድሚያ የበጀት ሕጉን ተከትለው የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

6. <u>ንብረት</u>

6.1. የመሥሪያ ቤቶች የንብረት አስተዳደር መንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በርካታ የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ -34 ተያይዟል)

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የአሰራር ክፍተቶቹ የመንግሥት ንብረቶችን ለብክነት የሚያጋልጡ እና ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት መስተካከል እና መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6.2 የመሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:- ሊቢሬ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው)፤በብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜያት የቆሙ ተሽከሪካሪዎችና ሌሎች የተሽከርካሪዎች አያያዝ ችግሮች እንዳሉ ተውቋል፡፡

(ለዝርዝሩ አባሪ -35 ተያይዟል)

የማሻሻያ ሃሳብ

- በወጣው የተሸከርካሪዎች መመሪያ መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ስለሚችል፣
- የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሆኑ እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች የመሥሪያ ቤቶቹ ንብረቶች ናቸው ብሎ ለመቀበል ሊያስቸግር ስለሚችል፣
- ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ካልተደረገ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት ደግሞ እንዲወገዱ ካልተደረገ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ ስለሚችል፣

መሥሪያ ቤቶቹ በተሽከርካሪዎቹ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ላይ የታዩትን ክፍተቶች በመመሪያው መሰረት ማስተካከል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

7. ልዩ ልዩ

7.1 በውሉ መሰረት ላልቀረበ ጤፍ የተፈጸመ ክፍያ፤

7.1.1 ግኝት

የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ለሚገዛቸው እህሎች ተገቢውን ውል መግባቱንና በውሉ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውል ጤፍ ከየሱፍ ሂርጶ ለመግዛት መስከረም 29 ቀን 2008 ዓ.ም ውል የተዋዋለ ሲሆን በውሉ ተራ ቁጥር 6 አቅራቢው የምግብ ጥሬ እቃዎቹን በውድድር ወቅት ባቀረበው ናሙና መሰረት በሚፈለገው ጥራት 1ኛ ደረጃ ለግዢ ፈጻሚው ለማቅረብ ግዴታ ገብቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በውሉ ተራ ቁጥር 11 ደግሞ አቅራቢው የገባውን ግዴታ ባለመወጣቱ የምግብ ጥሬ እቃዎቹን በገባው ውል በሚፈለገው ጥራት ባቀረበው ናሙና መሰረት ባለማቅረቡ በግዢ ፈጻሚው ላይ ጉዳት ካደረሰበት የተያዘው የዋስትና ገንዘብ ለግዢ ፈጻሚው ገቢ እንደሚደርግ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተዋል፡፡ ነገር ግን የሱፍ ሂርጶ በ2008 ዓ.ም. በተለያዩ ጊዚያት ካቀረባቸው 1,565.69 ኩንታል ጤፍ ውስጥ 325 ኩንታል የሚሆን የተበላሸ ወይም ከአሸዋ ጋር የተቀላቀለ ጤፍ ቢሆንም ኮሌጁ ጤፉን ለአቅራቢው በጊዜው መመለስ አሊያም መወሰድ ያለበትን እርምጃ መወሰድ ሲገባው ኮሌጁ ብር 416,325.00 በውሉ መሰረት ላልቀረበለት ጤፍ ክፍያ የፈጸመ

ሲሆን በዚሁ ምክንያት 325 ኩንታል ጤፍ ያለአገልግሎት በኮሌጁ ወፍጮ ቤት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ተከማችቶ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ክፍያዎች በውሉ መሰረት የማይፈጸሙ ከሆነ መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪና ለገንዘብ ብክነት ሊዳርግ የሚችል በመሆኑ ኮሌጁ በውሉ መሰረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢውን ክትትልና ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

7.2 በብድር ተሰጥቶ ተመላሽ ያልተደረገ ሽቀጣ ሽቀጦችና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች፤

7.2.1 ግኝት

በኮሌጁ ለሚማሩ ተማሪዎች ምግብ ለማዘጋጀት የሚውሉ ግብአቶች ለታለመለት አላማ የሚውሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ለተማሪዎች የምግብ እቃ ግምጃ ቤት ሚኒ እስቶር (Mini Store) እና ወፍጮ ቤት ገቢ ከሆኑት ውስጥ በጠቅላላው ዋጋቸው ከብር 203,495.00 በላይ የሆኑ ሽቀጣ ሽቀጥና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በሞዴል 22 ወጪ ተደርገው በራሱ ገቢ ለሚንቀሳቀሰው ለኮሌጁ የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ (Cafeteria) በብድር የተሰጡ ቢሆንም ሽቀጣ ሽቀጦቹና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በብድር የተሰጡት ሽቀጣ ሽቀጥና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በወቅቱ ተመላሽ የማይደረጉ ከሆነ የመንግሥት በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ እንደማይቻል እና ሁኔታው ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ በብድር የተሰጡት ሽቀጣ ሽቀጦችና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በአስቸኳይ ተመላሽ እንዲደረጉ አሳስበናል፡፡

7.3 በብድር የተሰጠ ሰንጋዎች፣ በጎችና የእርባታ እንስሳትን በተመለከተ፤

7.3.1 ግኝት

ኮሌጁ ብር 184,923.00 የሚያወጡ ለሽያጭ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ እንስሳቶችንና የእንስሳት ውጤቶችን ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ለኮሌጁ የሰራተኞች ክበብ (ካፍቴርያ) በብድር የሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በብድር የተሰጠው ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር እና በንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር የሚችል በመሆኑ በብድር የተሰጡት ሰንጋዎች፣ በጎችና የእርባታ እንስሳት ዋጋ መሰረት ገንዘቡ በአስቸኳይ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

7.4 እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

7.4.1 ግኝት

1. በአሥራ ሶስት መሥሪያ ቤቶችና በሶስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች አለአግባባ የተፈጸሙ ለውሎ አበል፣ ለትራንፖርት፣ ለማበረታቻ እና ለመሳሰሉት የተፈጸመው ክፍያ ብር 1,341,,327.03 ተመላሽ እንዲደረግ፣
2. በአራት መሥሪያ ቤቶች ሰራተኞች ከሥራ ከለቀቁ (ከተዛወሩ) በኋላ የተከፈለው ደመወዝ ብር 104,591.77 ተመላሽ እንዲደረግ፣
3. በአራት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ለብር 4 9,507,494.05 የወጪ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣
4. በስድስት መሥሪያ ቤቶች ሳይፈቀድ ለትርፍ ሰዓት ሥራ የተፈጸመው ክፍያ ብር 2,716,444.96 ተመላሽ እንዲደረግ፣
5. በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ብር 5,138.52 ያልተሰበሰበ የህክምና መዋጮ እንዲሰበሰብ፣

6. በሚዛን የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ከተጨማሪ ዕሴት ታክስና ከቅድሚያ ግብር የተቀነሰው ብር 863,09.74 ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት በመሆኑ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ እንዲቀርብለት፣

በተሰጠው አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መሥሪያ ቤቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፤ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤ መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰዱ፤ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለባቸው በድጋሚ እሳስበናል፡፡

<u>መደበኛ የመነሻ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች፤</u>

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ክሬዲት ሚዛን የሚያሣይ የጥሬ ገንዘብ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ	ዴቢት ሚዛን የሚያሣይ የተከፋይ ሂሳብ ሂሳብ
1.	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት ተጠሪ ተቋማት	27,733,641.74 293,367.62	2,458,260.74
1.1	በሚኒ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	5,038,380.71	2,216,491.67
1.2	በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ ቤት	20,335,184.59	239,721.61
1.3	በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	2,054.55	2,047.46
1.4	በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	2,358,021.89	
1.5	በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	293,367.62	
2.	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	5,631.87	321,089.78
3.	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	158,523.22	
4.	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	2,398,457.00	
5.	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ		1,577,751.38
	ጠቅላላ ድምር	30,589,621.45	4,357,101.90

* የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ነው፡፡

አባሪ-ለ

አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ እና የተለያዩ የአሰራር ክፍተቶች ዝርዝር፤

ተራቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ	ከመመሪያው ውጭ የተፈጸመ የውሎ አበል እና የበረሃ አበልT የትራንስፖርት አበል L የወተት አበል	ከግዥ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰና ተቀንሶ ያልተመዘገበ				ያልተመዘገበ እና በብልጫ የተመዘገበ የግንባታ ወጪ	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ እና መመሪያውን ሳይከተል የተፈጸመ የደመወዝ
				የተጨማሪ ዕሴት ታክስ	የቅድሚያ ግብር	ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ እና ተመላሽ	ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ ያልተመዘገበ		
1.	ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እና ከተጠሪ ተቋማቱ	172,198.09	70,861.50	491,115.68	16,408.30	5,318,289.22 * 2,835,538.85	392,974.88 *237,770.00	2,317,345.94 *1,444,970.18	19,593.65
1.1	ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	172,198.09	13,443.00						
1.2	የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ			33,990.14		138,751.10	31,180.31		
1.3	የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ		17,754.00			4,838,275.62			
1.4	የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ			457,125.54	16,408.30	341,263.20	361,794.57	2,317,345.94	9,250.33

	ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ					*2,835,538.85	*237,770.00	*1,444,970.18	
1.6	የአላጌ ግብርና ቴክኒክ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ								4,728.32
1.7	የሚዛን ግብርና ቴክ/ኮሌጅ		39,664.50						5,615.00
2.	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን		4,456.20 * 8,102.70						6,714.00
	የሚዞር ድምር	172,198.09	83,420.40	491,115.68	16,408.30	8,153,828.77	630,744.88	3,762,316.12	26,307.65

ተራ ቁጥ ር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ	ከመመሪያው ውጭ የተፈጸመ የውሎ አበል እና የበረሃ አበል T የትራንስፖርት አበል L የወተት አበል ክፍያ	ከግዥ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰና ተቀንሶ ያልተመዘገበ				ያልተመዘገበ እና *በብልጫ የተመዘገበ የግንባታ ወጪ	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ እና መመሪያውን ሳይከተል የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ
				የተጨማሪ ዕሴት ታክስ	የቅድሚያ ግብር	ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ እና ተመላሽ ተደርጎ ያልተመዘገበ	ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ ያልተመዘገበ		
	የዞረ ድምር	172,198.09	83,420.40	491,115.68	16,408.30	8,153,828.77	630,744.88	3,762,316.12	26,307.65
3.	የኢትዮጵያ ጤናመድኅን ኤጀንሲ								4,289.60
4.	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር								2,162.60
5.	የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ. ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል								8,298.50
6.	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር								1,421.80
7.	የማዕድን፣ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር								3,174.80

8.	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ		66,494.34 T 5,000.00						
9.	የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን		6,358.00 L 146,954.00						7,446.73
10.	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን								3,953.77
11.	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር								2,300.00
12.	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ								9,133.67
13.	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	55,123.42	10,878.72						414.33
	የሚዞር ድምር	227,321.51	319,105.46	491,115.68	16,408.30	8,153,828.77	630,744.88	3,762,316.12	42,595.85

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ	ከመመሪያው ውጭ የተፈጸመ የውሎ አበል እና የበረሃ አበል T የትራንስፖርት አበል L የወተት አበል ክፍያ	ከግዥ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰና ተቀንሶ ያልተመዘገበ				ያልተመዘገበ እና በብልጫ የተመዘገበ የግንባታ ወጪ	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ እና መመሪያውን ሳይከተል የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ
				የተጨማሪ ዕሴት ታክስ	የቅድሚያ ግብር	ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ እና ተመላሽ ተደርጎ ያልተመዘገበ	ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ ያልተመዘገበ		
	የዞረ ድምር	227,321.51	319,105.46	491,115.68	16,408.30	8,153,828.77	630,744.88	3,762,316.12	42,595.85
14.	በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር								
14.1	የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል				5,226.53				
15.	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር								2,854.17
16.	የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት								9,450.00
17.	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	229,294.07							
18.	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት		316,716.85						
19.	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር				1,217.40				*125,445.63

20.	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንትኢንስቲትዩት	18,928.00	7,424.16						
21.	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን		152,488.12						* 45,600.00
22.	የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ		11,990,000.55						*4,768,743.00
	ጠቅላላ ድምር	475,543.58	12,785,735.14	491,115.68	22,852.23	8,153,828.77	630,744.88	3,762,316.12	4,994,688.65

አባሪ-ሐ

<u>**አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ እና የተለያዩ የአሰራር ክፍተቶች ዝርዝር፤**</u>

ተራ ቁጥ ር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ከቤት አበል ከዓመት ፍቃድ ላይ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር	ክፍያው ለመፈጸሙ ደረሰኝ (ማስረጃ) ያልቀረበለት	በማስረጃ ያልተደገፈ እና ተገቢው ማስተካከያ ያልተሰራለት የወጪ ሂሳብ	ለተገዙት ንብረቶች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው
1.	ከእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እና ከተጠሪ ተቋማቱ	43,500.00	315,228.33	6,844,554.93	37,506.00
1.1	ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	43,500.00			
1.2	በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት		315,228.33		37,506.00
1.3	በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ			82,954.55	
1.4	የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ			6,761,600.38	
2.	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	5,750.56	19,975.51	1,016,072.55	
3.	የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል			172,062.03	
4.	የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን		92,408.47		
5.	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	5,684.00			
6.	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር			1,784,568.55	
7.	የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር			258,194.76	
8.	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር			2,554,478.00	
	የሚዞር ድምር	54,934.56	427,612.31	12,629,930.82	37,506.00

ተራ ቁጥ ር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ከቤት አበል ከዓመት ፍቃድ ላይ ያልተቀነሰ ሥራ ግብር	ክፍያው ለመፈጸሙ ደረሰኝ (ማስረጃ) ያልቀረበለት	በማስረጃ ያልተደገፈ እና ተገቢው ማስተካከያ ያልተሰራለትየወጪ ሂሳብ	ለተገዙት ንብረቶች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው
	የዞረ ድምር	**54,934.56**	**427,612.31**	**12,629,930.82**	**37,506.00**
9.	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን			96,600.00	
10.	የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ምክር ቤት እና ሴክሬታሪያት	171,457.50			
11.	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣንን	551.35			
12.	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት			1,533.32	
	ጠቅላላ ድምር	**226,943.41**	**427,612.31**	**12,728,064.14**	**37,506.00**

አባሪ- መ

እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	መመሪያን ሳይከተሉ ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርት ለማበረታቻ እና ለመሳሰሉት የተፈጸሙ ክፍያዎች	ከሥራ ከለቀቁ (ከተዛወሩ) በኋላ የተከፈለ ደመወዝ	የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት የወጪ ሒሳብ	ለትርፍ ሰዓት ሥራ የተፈጸመ ክፍያ
1.	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር				
1.1	የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	1,550.00			
1.2	የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ			736,561.85	
2.	በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር				
3.	የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል	9,330.21			
4.	የብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት	54,538.00			
5.	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	354,843.50			117,062.20

6.	**የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት**	**10,100.00**			**9,580.00**
7.	**የትራንስፖርት ሚኒስቴር**	**9,966.00**			
8.	**የአለርት ማዕከል**	**191,925.35**			
9.	**የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**			**686,785.25**	
10.	**የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ**	**3,385.00**			
11.	**የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ**			**3,093,359.00**	
	የሚዞር ድምር	**635,638.06**		**4,516,706.10**	**126,642.20**

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	መመሪያን ሳይከተሉ ለውሎ አበል፣ ለትራንስፖርት ለማበረታቻ እና ለመሳሰሉት የተፈጸሙ ክፍያዎች	ከሥራ ከለቀቁ (ከተዛወሩ) በኋላ የተከፈለ ደመወዝ	የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት የወጪ ሒሳብ	ለትርፍ ሰዓት ሥራ የተፈጸመ ክፍያ
	የዞረ ድምር	635,638.06		4,516,706.10	126,642.20
12.	የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	318,845.00	15,442.17		41,397.35
13.	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	18,582.25			
14.	የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	1,375.25			15,597.75
15.	የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን				2,476,314.76
16.	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	146,200.00			56,492.90
17.	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	5,728.69	1,137.86		
18.	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	204,292.23	76,294.15	4,987,564.59	
19.	የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	10,665.55	11,717.59	3,223.36	
ጠቅላላ ድምር		**1,341,327.03**	**104,591.77**	**9,507,494.05**	**2,716,444.96**

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2008

በጀት አመት ኦዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

1. ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በጀት

ተራ ቁጥር	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
		መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	11,982,382,531.79		11,982,382531.79
2	የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	2,344,606,833.41	172,737,130.00	2,517,343,963.41
3	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	548,626,440.33	498,167,415.57	1,046,793,855.90
4	ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት	480,390,790.48	31,703,675.00	512,094,465.48
5	ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	49,654,569.46		49,654,569.46
6	ፌዴራል ፖሊስ ኮምሽን	1,915,658,995.46	348,582,798.35	2,264,241,793.81
7	ጠቅላይ ፍ/ቤት	277,414,227.20	51,446,306.69	328,860,533.89
8	የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሱ	104,504,528.15		104,504,528.15
9	የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ	43,135,320.00		43,135,320.00
10	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	763,532,832.04	351,107035.00	1,114,639,867.04
11	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ	91,798,622.55		91,798,622.50
12	የፌዴራል የከተማ መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	31,197,110.00	120,006,000.00	151,203,110.00
13	የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	10,600,240.00		10,600,240.00

14	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	55,895,067.95		55,895067.95
15	የኢትዮጵያ አፅምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት	17,022,008.43		17,022,008.43
16	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ልማት ኢንስቲትዩት	41,336,070.34		41,336,070.34
17	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር	72,812,736.67		72,812,736.67
18	የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቢ ህግ	196,377,164.06	45,444,068.43	241,821,232.49
19	የፌዴራልና የአርብቶ አደር ጉዳዮች ልማት ሚኒስቴር	85,158,457.45		85,158,457.45
20	ንግድ ሚኒስቴር	111,764,328.44	13,630,000.00	125,394,328.44
21	የደረጃዎች ኤጀንሲ	25,830,720.00	5,000,000.00	30,830,720.00
22	ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	98,155,560.00	-	98,155,560.00
23	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ	56,441,990.00	45,000,000.00	101,441,990.00
24	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	220,734,543.85	9,896,251.71	230,630,795.56
25	የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	41,853,806.00	-	41,853,806.00
26	የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን	31,334,902.86		31,334,902.86
27	ፌዴራል ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮምሽን	55,677,288.73	-	55,677,288.73
28	ሕገመንግሥት አጣሪ ጉባኤ	15,311,570.00		15,311,570.00
29	የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን	62,603,598.00		62,603,598.00
30	የታላቁ ህዳሴ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ም/ቤትጽ/ቤት	12,054,515.00		12,054,515.00
		19,843,867,436.65	**1,692,720,680.75**	**21,536,588,117.40**

1.2 የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው የኦዲት አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ለ4 መ/ቤቶች ፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ6 መሥሪያ ቤቶች፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የኦዲት አስተያየት ለ12 መሥሪያ ቤቶች፣ ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት ደግሞ ለ8 መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-1 ተመልክቷል፡፡/

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ

የጥሬ ገንዘብ ጉድለት .... ብር 120,125.00

በጉድለት የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ትኩረት ተሰጥቶት ክትትል ሊደረግና ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባና በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

1.2 ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በካዝና ውስጥ እንዲያዝ ከተፈቀደው በላይ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፤

ማዕከላዊ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ክ/ሂመ39/7/19 በቀን 30/07/2007 አዲስ ባሻሻለው መመሪያ መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በካዝና እንዲይዙ የሚፈቅደዉ የገንዘብ መጠን ከብር 100,000 ያልበለጠ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡በመሆኑም የጥሬ ገንዘብ አያያዝ በወጣው መመሪያ መሠረት መሆኑ ሲጣራ፡ ሐምሌ 1 ቀን 2009 ዓ.ም በከፍተኛ የበታች ሹም ማሰልጠኛ ት/ቤት ብር 309,080.89፤ በዚህም በብለጫ ብር 209,080.89 ፤በሜ/ጀ/ኃ/አ/ወታ/አካዳሚ ብር 227,248.10 በብልጫ ብር 127,248.10፤በአየር ኃይል በዋና ገንዘብ ያዥ በካዝና ብር 230,068.71 በቆጠራ በብልጫ ብር 130,068.71 ተገኝቷል ፡፡

በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

በኢምግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መመሪያ ሰኔ 30/2009 የተቆጠረ ጥሬ ገንዘብ ብር 136,961.14 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ከመመሪያው በላይ ብር 36,961.14 ተገኝቷል፡፡እንዲሁም በውጭ መረጃ ዋና መምሪያ ሐምሌ 1 ቀን 2009 ዓ.ም ብር 107,644.75 በካዝና ውስጥ በቆጠራ ተገኝቷል፡፡በመሆኑም በካዝና መቀመጥ ከሚገባው በላይ የተቆጠረ ብር 7,644.75 ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተገለጸው ከፍተኛው በሀገር መከላከያ የተገኘው ሲሆን የቫትና ዊዝሆልዲንግ ሂሳብም ቢሆን ሰኔ 30 ለገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ፈሰስ ተደርጎ እንደገና ከገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ጠይቆ በማምጣት መክፈል ስለሚቻል የጥሬ ገንዘብ መመሪያ ከሚፈቅደው በላይ በሳጥን መቆጠር ስለሌለበት ለወደፊትም በጥሬ ገንዘብ መመሪያ መሰረት ሊሰራ እንደሚገባና በተጨማሪም የሥራውን ባህሪ በማስረዳት ለሰኔ ወር ብቻ የሚያስፈልገውን የጥሬ ገንዘብ መጠን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር (ለገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር) ማስፈቀድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.3 <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አመዘጋገብ ችግሮች</u>

ጠቅላይ ፍ/ቤት

- በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሳጥን ሂሳብ 4101 በተቀጽላ ሌጀር (01) ብር 138,993.98፣በተቀጽላ ሌጀር (03) ብር 855.00 እና በተቀጽላ ሌጀር(10) ብር 35,406.91 የሂሳብ ሚዛን በዴቢት መመዝገብ ሲገባው በክሬዲት ተመዝግቦ መገኘቱ፡፡-በዚህም የሳጥን ሂሳቡ በተገለጸው የገንዘብ መጠን ድምር በብር 175,255.89 ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፡
- በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በባንክ ሂሳብ መደብ 4103 በተቀጽላ ሌጀር (0001) ብር 20,236,660.66 የሂሳብ ሚዛን በዴቢት መመዝገብ ሲገባው በክሬዲት ተመዝግቦ መገኘቱ፡- በዚህም የባንክ ሂሳቡ በብር 20,236,660.66 ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፡

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ

ብሔራዊ ምክር ቤት በጽ/ቤት "

- ጽ/ቤቱ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ሂሳብ ገቢ እንጂ ወጪ የማያስተናግድ ዝግ የባንክ ሂሳብ / "D" /አካውንት ብቻ ማንቀሳቀስ ሲገባው በናሙና ከታየው ሂሰብ ውስጥ በB የባንክ ሂሳብ መደብ ገቢ የተደረገ ብር 3,392,482.72 ተገኝቷል፡፡

- የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት በጽ/ቤት ” ስም መደቡ “D” የሆነ ገቢ እንጂ ወጪ የማያስተናግድ ዝግ የባንክ የሂሳብ ቁጥር 0171553550700/1000000984896 የተከፈተ ሲሆን በተጠቀሰው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ የሆነውን ሂሳብ የገቢ አድቫይስና የባንክ እስቴትመንት በመጠየቅ ምዝገባ በማካሄድ በየወሩ ከምዝገባ ጋር በማገናዘብ በሂሰብ ሪፖርት ተካቶ እንደማይቀርብ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመሆኑም የጠቅላይ ፍ/ቤትን በተመለከተ የፍርድ ቤቱ ሂሳብ ክፍል ሂሳብ ከመዘጋቱ በፊት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቋሚ ሂሳቦች ተቀጽላ ሌጀር ቁጥሮች ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን የታየባቸውን የሂሳብ እንቅስቃሴ ምክንያት በማጣራት ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት በትክክል ማለፋቸውን እንዲሁም ተቀጽላ ሌጀሮች ከጀነራል ሌጀር ሳይገናዘብና ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ክትትል ማድረግ እንደሚገባ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤትን በተመለከተ ደግሚ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ሂሳብ በሂሳብ መደቡ ‹‹D›› ገቢ ሊያደርግና ወደ ባንክ ሂሳብ መደብ ‹‹B›› ገቢ የተደረጉትን ገቢዎች በማጣራት ትክክለኛውን የፕሮጅቶች ሂሳብ ሊታወቅ እንደሚገባና ጽ/ቤቱም በመመሪያው መሰረት ዋና የተቋቋመለት አለማ ሀብት ማሰባሰብ በመሆኑ ከዚህው ጋር በተያያዘ ተገቢውን ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ እንዲሁም የጽ/ቤቱ ሂሳብ ክፍል የየወሩን የባንክ ሰቴትመንት ከምዝገባ ጋር በማገናዘብ የሂሳብ ማስታረቂያ ሊሠራና በሂሳብ ሪፖርት ተካቶ ሊቀርብ እደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 የተሰብሳቢ ሂሣብ የቆይታ ጊዜ ትንተና

በተሰብሳቢ የተመዘገቡት ሂሣቦች በትክክለኛ ማስረጃዎች መደገፋቸውንና በደንቡ መሠረት የተወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ17 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 100,289,401.19 በደንቡ መሠረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/

በመሆኑም የተሰብሳቢ ሂሳቡ እንዲሰበሰብ ተገቢ የሆነ ጥረትና ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል ፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች

ጠቅላይ ፍ/ቤት

- በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሂሳብ መደብ 4210 በተቀጽላ ሌጀር ብር 115,569.25 የሂሳብ ሚዛን በዴቢት መመዝገብ ሲገባው በክሬዲት ተመዝግቦ መገኘቱ ፡-በዚህም የተሰብሳቢ ሂሳቡ በብር 115,569.25 ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፡
- በሂሳብ መደብ 4203 በተቀጽላ ሌጀር (0000) ብር 471.15የሂሳብ ሚዛን በዴቢት መመዝገብ ሲገባው በክሬዲት በመመዝገቡ፤- በመጀመሪያ ፍ/ቤት በሂሳብ መደብ 4211 በተቀጽላ ሌጀር (02) ብር 5052.09 እንዲሁም በተቀጽላ ሌጀር (01) ብር 919.16 የሂሳብ ሚዛን በዴቢት መመዝገብ ሲገባው በክሬዲት በመመዝገቡ ሊሰበሰብ የሚገባውን ሂሳብ በብር 5971.25 ዝቅ አድርጎት ተገኝቷል፡፡

ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

- 4253 (ለዕቃ አቅራቢዎች የቅድመ ክፍያ) ሂሳብ መደብ በተቀጽላ ሌጀር (001) ብር 21,597.00 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት፤- ፡-በዚህም የተሰብሳቢ ሂሳቡ ተቀጽላ ሌጀር ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፡፡

2.3 በተሰብሳቢ ተመዝግቦ የተገኘ እና ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ

በተሰብሳቢ የተመዘገቡ ሂሳቦች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ በ8 መ/ቤቶች ብር 1,281,305,600.46 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የተሰብሳቢ ሂሳቦች በተገቢው ማስረጃ ሊደገፉና ማስረጃዎችም በአግባቡ ሊያዙና ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግላቸው እንደሚገባና ማስረጃ የሌላቸው ሂሳቦች ለይቶ ማውጣት ለሚመለከተው አካል በማቅረብአስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.4 የተጣራ ሀብትን ዴቢት ተሰብሳቢን ክሬዲት በማድረግ በማጣፋት መነሻ ሰነድ ሳይቀርብለት አለ አግባብ የተከናወነ ምዝገባ

- ውጭ ጉዳይ ሚኒቴር ብር 500,231.72

አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሳብ

3.1 ማስረጃ ባለመሟላቱ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፤

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

- አስተዳደሩ በሂሳብ መደብ 1441 ከተለያዩ ምርቶች ሽያጭ ገቢ የሰበሰበውን ብር 8,569,423.09 የገቢ ተመን ያልቀረበለት በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡

የሚሰበሰበው ገቢ ተመን ወጥቶለት በሚመለከተው አካል ጸድቆ ከማስረጃዎቹ ጋር በአባሪነት ለኦዲት ስራ ሊቀርብና የሚመለከተው የስራ ክፍልም በትመናው መሰረት ስለመሰብሰቡ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.2 በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ(ያልተቀነሰ የገቢ ግብር)

የተለያዩ ገቢዎች በሕጉ መሰረት መሰብሰባቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ5 መ/ቤቶች ብር 364,533.44 በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ(ያልተቀነሰ የገቢ ግብር)መኖሩ ተረጋግጦል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-9(ለ)ተመልክቷል/

3.2 በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች፤

በንግድ ሚኒስቴር

- በዋናው በሚ/ር ቤ/ትም ሆነ በልደታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተለያየ የገቢ አርዕስት በሂሳብ መደብ 1412(Registration of Foreigners) የውጭ አገር ዜጎች ምዝገባ እና 1417 (Business and Professional Registration and License Fees) የንግድ ድርጅቶችና የባለሙያዎች ምዝገባና ፍቃድ ክፍያ በየሂሳብ መደቡ ፣ በሲስተም ያልተገለጸ መሆኑ፤

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

- የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ አዲስ ፓስፖርት ለማውጣትም ሆነ ለማሳደስ የሚመጣው በትክክል ስሙንና የመኖሪያ አድራሻ የሚገልጽበት ቅጽ(Form) አንዱን በብር 10.00 ተገልጋዩ ገዝቶ መሆኑ ታውቋል፡፡ መምሪያው ለተቀበለው ሂሳብ የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ እንደማይሰጥ በተጨማሪም ከዚህ ቅጽ(Form) ሽያጭም የሚሰበሰበው ገቢ ዋና መምሪያው በሚያዘጋጀው የገቢ የሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ

መሆኑን እና የተሰበሰበዉንም ገንዘብ ማወቅ የማይቻል መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በንግድ ሚኒስቴር ከአይቲ ዳይሬክቶሬት የገቢ ደረሰኝ ማመሳከርያ ዝርዝር ሪፖርት በሲስተሙ በሶፍት ኮፒ (Soft Copy) ተመዝግቦ የቀረበው በአገልግሎት ዓይነት እንጂ በየሂሳብ መደብ (Account Code) ስለአልተመዘገበ ሰኔ 30/2009 በቀረበው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 1412 እና በሂሳብ መደብ 1417 የተመዘገበውን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በመንግሥት ሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት መሠረት የሂሳብ መደቡ ሊገለጽ እንደሚገባናዋና መምሪያው በመንግሥት ወጪ የታተመውንና ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት ከሚሞሉት ቅጾች ሽያጭ የሚሰበሰበውን ገቢ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ሲገባ ከህግና ከመመሪያ ውጪ ያለ ደረሰኝ መሰብሰቡና በሂሳብ ሪፖርት አለመካተቱ አግባብ የሌለው በመሆኑ ስለሆነም ገቢው በህጋዊ ደረሰኝ ገቢ ሆኖ በሂሳብ ሪፖርት መካተት እንዳለበት አሳስበናል፡፡እንዲሁም በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በኢሚግሬሽን ዋና መምሪያ በመንግሥት ወጪ የታተመውንና ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት ከሚሞሉት ቅጾች ሽያጭ የሚሰበሰበውን ገቢ በህጋዊ ደረሰኝ ገቢ ሆኖ በሂሳብ ሪፖርት አሊካተት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት

- ጽ/ቤቱ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ሂሳብ ገቢ እንጂ ወጪ የማያስተናግድ ዝግ የባንክ ሂሳብ ፤ / "D" /አካውንት ብቻ ማንቀሳቀስ ሲገባው በናሙና ከታየው ሂሰብ ውስጥ በB የባንክ ሂሳብ መደብ ገቢ የተደረገ ብር 3,392,482.72 ተገኝቷል፡፡

ጽ/ቤቱ የፕሮጀክት ማሰፈጸሚያ ሂሳብ በሂሳብ መደቡ ‹‹D›› ገቢ ሊያደርግና ወደ ባንክ ሂሳብ መደብ ‹‹B›› ገቢ የተደረጉትን ገቢዎች በማጣራት ትክክለኛውን የፕሮጅቶች ሂሳብ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ጽ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት ዋና የተቋቋመለት አለማ ሀብት ማሰባሰብ በመሆኑ ከዚህው ጋር በተያያዘ ተገቢውን ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

የወጪ ሂሳብ ምዝገባ የተከናወነው ማስረጃ ቀርቦ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣ በ7 መ/ቤቶች ብር 110,033,859.03 ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሁለተኛው የዲስፖራ በዓል ዝግጅት ለመስተንግዶ አገልግሎት የወጣ እንዲሁም ለ28ተኛው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ እና ለ10ኛው የጡት ጫፍና የማህጸን ካንሰር ስብሰባ ዝግጅት አስመልክቶ ለፌደራል ፖሊስ የተሰጠ ይገኙበታል፡፡ ለወጪው ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብለት ሂሳቡን በወጪ መመዝገብ ለመንግስት ንብረት መባከን መንስዔ በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትና የተጠቀሰው ሂሳብ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ገንዘቡ ለታቀደለት ዓለማ ለመዋሉ መረጋገጥ እንዳለበት በተጨማሪም መረጃ የማይቀርብበት ሂሣብን በተመለከተ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመነጋገር ማስፈቀድ እንዳለባቸውና ይህ ካልሆነ የወጪ ሂሣቡ ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ ማስረጃዎቹ ቀርበው ኦዲት የሚደረጉበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.2 የተሟላ ደጋፊ የወጪ ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

ክፍያዎች የተፈጸሙት የተሟላ ማስረጃ ቀርቦላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-በ9 መ/ቤቶች ብር 29,127,762.78 የተሟላ ደጋፊ የወጪ ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ተገኝቶል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሰነዓ ፎረም መዋጮ በሚል የተፈጸመ ክፍ ይገኝበታል፡፡ ማስረጃዎቹ ሊቀርቡና በኦዲት ሊረጋገጡ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡ ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ ክፍያ ሲፈፅሙ በፌዴራል መንግስት የክፍያ መመሪያ መሰረት ሊሆን እንደሚገባ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ አለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ወጪ ሆነው የተከፈሉት ወጪዎች ደንብና መመሪያ የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ14 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 3,546,031.80 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ አለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች መሆኑ ታውቆል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለመ/ቤቱ ሠራተኞች የትርፍ ሰዓትና ቅዳሜ ቀን ገብተው የሰሩበት በሚል ለፍል ዉሃ አገልግሎት ድርጅት የምሳ እና እራት የተጋበዙበት የተፈጸመ ክፍያ፣ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ለሽልማት የተፈጸመ ክፍያ እንዲሁም በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የመንግስት ሠራተኞች የውሎ አበል ቅጽ በአግባቡ ሳይሞላ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ሠራተኞቹ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ የሰሩ መሆኑ እየተረጋገጠ የምሳ እና የእራት አበል እንደ ደመወዛቸው መጠን በፐርሰንት እየተሰላ ክፍያ ሊፈጽም እንደሚገባ ፣ለሠራተኞች የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም ለመንግስት ሠራተኞች በተዘጋጀው የውሎ አበል መሙያ ፎርም በአግባቡ በመሙላት የውሎ አበል ሊከፈል እንደሚገባና ያለአግባብ የተከፈለው አበል ተመላሽ መደረግ እንዳለበትና በአጠቃላይ የክፍያ መመሪያና ደንብ ተጠብቆ ክፍያዎች እንዲፈጸሙ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

እንዲሁም የውሎ አበል ሲከፍል በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተዘጋጀው የአበል መክፈያ ቅጽ (ፎርማት)መሠረት በአግባቡ በመሙላት መከፈል እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.4 በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች

የውሎ አበል አከፋፈሉ ስርዓቱ ሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ.ም በወጣው የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

• የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	ብር	189,550.00
• የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	ብር	388,008.35
ድምር	ብር	**577,558.35**

ከፍተኛው የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ሲሆን በ2008 ኦዲትም አስተያየት ተሰጥቶበት እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል

እንደሚገባና ባልጸደቀ መመሪያ የፈቀደና የከፈለ ሰራተኛ ተጠያቂ ሊሆን እንደሚገባ አሳስበናል ፡፡

4.5 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸሙ ግዥዎች፤

በበጀት ዓመቱ የተፈጸመው ግዢ በመንግሥት የግዢ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ18 መ/ቤቶች ብር 45,048,311.30 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ግዥ ፈጽመው ተገኝተዋል፡፡/ዝርዝር በአባሪ- 21 ተመልክቶል/

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው ግዥ የተከናወነው በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ሲሆን ግዥዎች ሲከናወኑ በግዥ ህጉ መሰረት ፍትሃዊ የሆነ ውድድር ሊደረግና ለመንግስት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል መልኩ መፈፀም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡በተጨማሪም በፌዴራልና አርብቶ አደር ጉዳዮች ሚኒስቴር በቂ ተወዳዳሪዎች ሳይቀርቡ የተፈጸመ የቢሮ ፈርኒቸሮች ግዥ እና በውስን ጨረታ ውስጥ ካልተሳተፈ ድርጅት የተፈጸመ የኔት ወርክ ዝርጋታ ግዥ ፣ በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ህንጻ ኪራይ ፣ በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት እና በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የመኪና ጥገና አገልግሎት ያለዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ፣ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር የመኪና መለዋወጫ እንዲሁም በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የላፕቶፕ ግዥ አነስተኛ ዋጋ ያቀረበ ድርጅት እያለ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት የተፈጸመ ግዥ፤ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ፣ በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ፣ በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም፣በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር፣ በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያለዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ እና ውል ሳይገባ የተፈጸመ ግዥ ይገኙበታል፡፡

ለወደፊቱ ማንኛውም ግዥ በግዥ አዋጅ ፣ደንብና መመሪያ መሠረት ሊፈጽም እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.6.1 በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መሰረት ክፍያዎች የተፈፀሙት ሥልጣን ባለው አካል እየፀደቁ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፣ በ5መ/በቤቶች ብር17,985,419.23

በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ወጪው ሳይፈቀድ(ሳይጸድቅ) ተገኝቷል ።/ዝርዝሩ በአባሪ-26 ተመልክቷል/

ወጪ መፈጸም ያለበት በሚመለከተው ኃላፊ ሲፈቅድ በመሆኑ ማንኛውም የወጪ ሂሣብ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ መፈቀዱ መረጋገጥ እንደሚኖርበትና ያዘዘው ኃላፊ ሳይፈርም ለተፈጸመው ክፍያ ወጪው ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉ በውስጥ ኦዲት ሊጣራ እንደሚገባ በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

4.6.2 ከተሰጠ የውክልና ገደብ በላይ የጸደቀ ወጪ

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት

- በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ላይ ፤ የግዥ ወሳኔ ሀሳብና ውል መፈራረምን ጨምሮ በድምሩ ብር 1,434,648.86 ከተሰጠ የውክልና ገንዘብ መጠን በላይ አጽድቀው ተገኝቷል፡፡
- የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ወጪ ሂሳብ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ላይ በድምሩ ከተሰጣቸው የውክልና ገንዘብ መጠንብር 6,244,711.68 በላይ አጽድቀው ተገኝቷል፡፡

ድምር 7,679,360.54

ወጪዎች በተሰጠው የስልጣን ገደብ መሠረት ሊፈጸም እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

• ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	ብር	277,143.47
• ፌዴራል ፖሊስ		2,677,569.04
	ድምር	2,954,712.51

በመሆኑም ቅድሚያ ክፍያዎችን በተሰብሳቢ ሂሳብ በመመዝገብ ስራው በውሉ መሰረት ተጠናቆ ሲያልቅና ንብረቱን ገቢ ተድርጎ ቀሪ ክፍያ ሲከፍል በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘውን ብር በመቀነስ አጠቃላይ በወጪ መመዝገብ እንዳለበትና በወጪ የተያዘው ቅድሚያ ክፍያ በተሰብሳቢ እንዲያዝ ወጪውም በዚሁ መጠን ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.8 በብልጫ የተከፈሉ የተለያዩ ወጪዎች

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፣ በ4 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች ግዥ ብር124,767.85 እና በ2 መ/ቤቶች ብር 215,852.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብ ከውሎ አበል ተመን በላይ መክፈል፣ በመስክ ላይ ከቆዩበት ቀናት በላይ የውሎ አበል መክፈልና ለስልጠና አገልግሎት ከውል በላይ መክፈል ይገኙባቸዋል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ ለመንግስት ሀብት መባከን የሚዳርግና ለሙስና በር ሊከፍት ይችላል፡፡ በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱን ተከትለውና የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ተከትለው መስራት እንዳለባቸውና በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግና በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.9 ከበጀት ዓመቱ ውጭ በጀት ሳይያዝለት በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ የተገኘባቸው፤

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች ብር 2,608,992.14 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2009 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህም የበጀት ዓመቱን የበጀት አፈጻጸም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት ዓመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በተላከው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በትክክለኛው ሂሳብ መደባቸው የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ11 መ/ቤቶች ብር 24,710,611.64 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ወጪውን በተገቢው አርዕስት አለመመዝገብ የበጀት እጥረትን ለመሸፈንና አለአግባብ በጀትን ለመጠቀም መንገድ ስለሚከፍት የመንግስት የሂሳብ አወቃቀር ስርዓትን ተከትሎ

በተገቢው የሂሣብ መደብ ሂሳቦች እንዲመዘገቡ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እና ለተጠቀሱት ሂሳቦች ማስተካከያ ሊሠራ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል ፡፡

4.11 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ፤</u>

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 29,702.67
- ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት <u>212,426.59</u>

ድምር <u>242,129.26</u>

የተገዙ ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ሂሳቡን በወጪ መመዝገብ ለመንግስት ንብረት መባከን መንስዔ በመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.12 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ላይ የዕቃው ብዛትና ዋጋ ሳይመዘገብ የተገኘ፤</u>

- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 309,477.84

በንብረት ገቢ ደረሰኙ ላይ የእቃው ብዛት እና ዋጋ አለመመዝገብ ለንብረቱ መባከን መንስዔ ሊሆን ስለሚችል በንብረት ገቢ ደረሰኙ ላይ የዕቃው ብዛትና ዋጋ ሊጠቀስ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳበናል፡፡

4.13 <u>ፎቶ ኮፒ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የቀረበበት</u>

- ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 77,745.75
- የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮምሽን ብር <u>1,261,040.00</u>

ድምር **<u>1,338,785.75</u>**

ከፍተኛው የፌዴራል ስነምግባርና ጸረ ሙስና ኮምሽን ሲሆንዳታ እስቶሬጅ ብዛት አንድ እንዲሁም ዲስክ ድራብ አንድ በወጪ ሲመዘገብ የቀረበው የንብረት ገቢ ደረሰኝ /ሞ/19/ ቁጥር 486507 ፎቶ ኮፒ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ዖጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት አስፈላጊው ደጋፊ ዋናው (ኦሪጂናል) ማስረጃ ሊቀርብ እንደሚገባ በፎቶ ኮፒ የሰነድ ማስረጃ ከአንድ ጊዜ በላይ ለማወራረጃነት ሊውል ስለሚችል ዋናው (ኦሪጂናሉ) የንብረት ገቢ ደረሰኝ(ሞ/19) ሊቀርብና ትክክለኛነቱ በውስጥ ኦዲቱ ሊጣራ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.14 <u>በተፈላጊ ባህሪያ ዝርዝርመሠረት ገቢ ስለመደረጉ ማስረጃ ያልቀረበለት</u>

• ፌዴራል ፖሊስ	ብር	589,000.00
• የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስ/ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት	ብር	275,719.40
• የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	ብር	1,364,859.58
ድምር		**2,229,578.98**

ግዥ ፈጻሚው አካል ባዘጋጀው ባህሪያት ዝርዝር (Specification መሰረት ገቢ ከመደረጋቸዉ በፊት በማረጋገጥ ገቢ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.15 <u>በወጪ ሂሳብ ላይ የታዩ ዋና ዋና የአሰራር ድክመቶች</u>

<u>ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር</u>

- ባልጸደቀ የክፍያ ምስክር ወረቀት ብር922,870.36 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ሚ/ር መ/ቤቱ ለተላከለት የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው ምላሽ ግኝቱ ትክክለኛ መሆኑንና በሚመለከተው አካል ሳይፈረም የቀረበ የምስክር ወረቀት በአግባቡ ባለመመርመር የተፈጠረ ክፍተት እንደሆ ግኝቱ በአስተማሪነት እንደሚወስዱት እና በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ወጪው ለመስሪያ ቤቱ ስራ ስለመዋሉ በውስጥ ኦዲት እንዲረጋገጥ የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡በመሆኑም የተከፈለው ክፍያ ለጠቅላይ መምሪያው በትክክል ለተሠራው ሥራ ለመሆኑ በሚመለከተው አካል የተረጋገጠ ሰነድ ሊቀርብና በውስጥ ኦዲት ሊጣራ እንደሚገባ ለወደፊቱም ማንኛውንም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የክፍያ ማስረጃዎች በሚመለከተው አካል መጽደቃቸውን መረጋገጥ እንዳለበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በኢንፎርሚሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ</u>

- ከኤጀንሲው የመዝናኛ ክበብ አገልግሎቱ እንደተገኘ በማስመሰል የኤጀንሲው መዝናኛ ክበብ ባልሆነ ነገር ግን የመከላከያ ወታደራዊ መደብሮችና ክበቦች አስተዳደር መምሪያ በሆነ የክፍያ ደረሰኝና የክፍያ ማስረጃ ዝርዝር ብር 414,951.00 ተወራርዶ መገኘቱ፡፡

- በበጀት ዓመቱ ኤጀንሲው ካለቁ ፕሮጀክቶች/ገቢ/ ላይ ምን ያህል ገንዘብ እንደተጠቀመ የሚገልጽ ዝርዝር ሪፖርት የሌለ መሆኑን ታውቋል፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ መዝናኛ ክበብ የሚጠቀመው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የመከላከያ ወታደራዊ መደብሮችና ክበቦች አስተዳደር መምሪያ ደረሰኝ የሚል በመሆኑ ወጪው ለመ/ቤቱ አገልግሎት የዋለ ለመሆኑ ለማረጋገጥ አያስችልም ፡፡ በመሆኑም ከመዝናኛ ክበቡ ጋር የሚደረጉ ሌሎች አገልግሎቶች በዚህ ደረሰኝ ማወራረድ ተቀባይነት እንደሌለውና የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት በኩል ተጣርቶ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

ኤጀንሲው ያለቁ የፕሮጀክት ሂሳቦች ሪፖርትን በሚመለከት ግልጽ የሆነ መመሪያ ሊያስቀምጥና ተግባራዊነቱን ሊያረጋግጥ እንደሚገባና፡፡ እንዲሁም ካለቁ ፕሮጀክቶች ላይ የሚደረጉ የክፍያ ትዕዛዞች መነሻችው እነዚሁ ሪፖርቶች ሊሆን እንደሚገባ በተጨማሪ የፕሮጀክት በጀት ክፍሉም የክፍያ ትዕዛዝ ሲመጣ በጀት ስለመኖሩ ተገቢውን የማረጋገጥ ስራ ሊሰራ እና ካለው ሚዛን በላይ እንዳይወጣ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደለት ጣሪያ ባላይ ወጪ ስላለማደረጉ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ሪፖርት ሊዘጋጅ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>

- የግንባታ ውሎች ላይ የውሉ ቀን የማይጻፍ መሆኑን በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡
- ግንባታው ወቅቱን ጠብቆ ለመጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ በግንባታ ውሉ ላይ የውሉ ቀን ሊገለጽ እንደሚገባ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

<u>በፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር</u>

- የፋይናንስና ግዥ ዳይሬክተር ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ብር 600,000.00 ወጪ አፅድቀው መገኘታቸው፡፡

<u>በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

- በዋናው መ/ቤት በድምሩ ብር 300,002.99 የማስተካከያ ሂሳቡ ምዝገባ መነሻ ማስረጃም ሆነ ማጣቀሻ የሌለው በጥቅሉ የማስተካከያ ምዝገባ በሚል ተመዝግቦ ተገኝቷል፤

- በኢ.ፌዲሪ ኤምባሲ ዋሽግተን ሰራተኛ የሆኑት Mr Anton kanishka የታህሳስ ወር ደሞዝ ብር 29,568.00 ስለመውሰዱ ሳይፈርም በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በኢ.ፌዲሪ ኤምባሲ ዋሽግተን በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 253512 በቀን 26/10/2009 ላይ የጡረታ ክፍያ ማስተካከያ ምዝገባ በሚል ብር 18,767.51 የተመዘገበ ሲሆን የማስተካከያው ምዝገባ መነሻ ማስረጃም ሆነ ማጣቀሻ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም</u>

- በኦሮሚያ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የወጪ ሒሳብ በሂሳብ መዝገብ መሠረት ብር 6,337,406.95 ሲሆን በሂሳብ ሪፖረቱ መሠረት ብር 5,429,878.50 በመሆኑ የሂሳብ ሪፖርቱ በብር 907,528.45 አንሶ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የሀዋሳ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የወጪ ሂሳብ በሂሳብ መዝገብ መሠረት 4,824,002.34 ሲሆን በሂሳብ ሪፖርቱ መሠረት ብር 4,542,650.97 በመሆኑ የሂሳብ ሪፖርቱ በብር 281,351.37 አንሶ ተገኝቷል፡፡

<u>ፌዴራል ፖሊስ</u>

- ለወንጀል መከላከል ዘርፍ ከዉጪ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ለአፍሪካ ህብረትና ለተለያዩ ዓለማአቀፋዊና አህጉራዊ ስብሰባዎች ፀጥታ ለማስከበር ለፌዴራል ፖሊስ የተላከዉ የአደራ ገንዘብ በዘርፉ ሥር ለሚገኙት የተለያዩ ክፍሎች ከተወራረዱት ሂሰቦች ብር 14,692,293.59 በናሙና ከታዩት ውስጥ ከተላከበት ዓላማ ውጭ ለመስተንግዶ አገልግሎት በድምሩ ብር 158,082.25 ተከፍሎ የተገኘ ሲሆን በጀት ዓመቱ የተጠቀመበት /ከተወራረዱት ሂሰቦች/ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የታየው ብር 269,135.78 ስለአፈጻጸሙ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሪፖርት የማይቀርብበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምዝገባዎች ሲከናወኑ ለምዝገባው መነሻ የሆነ ተገቢው የሆኑ ማብራሪያዎችና ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባ፡፡እንዲሁም የሂሳብ ምዝገባዎች ከመነሻ ሰነዶቹ ወደ ሂሳብ ምዝገባ ከመከናወናቸው በፊት የሚመለከተው የአይቤክስ የምዝገባ ባለሙያ ሰነዶቹ በሚመለከተው አካል የጸደቀ ስለመሆኑ ተገቢውን ቁጥጥር ሊደርግ እንደሚገባ ፤ወጪ የሚፈቅዱ የሥራ ኃላፊዎች በተሰጣቸው ኃላፊነት ብቻ ወጪ ማፅደቅ እንደሚገባቸውና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሥህተት እንዳይፈጠር ጥንቃቄና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ ፤ማንኛዉም ክፍያ

ሲፈጸም ክፍያ የሚፈጸምለት ሰራተኛ በትክክል ገንዘቡን ስለመቀበሉ የሚረጋገጥበት ስርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ፤ እንዲሁም ክፍያው የተፈጸመለት ሠራተኛ ገንዘቡን ለመቀበሉ በፊርማ እንዲያረጋግጥ፤ መ/ቤቱ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብና በሂሳብ ሪፖርቱ ለታየው ልዩነት ማስተካከያ ሊሰራና የመ/ቤቱ ሂሳብ ሪፖርት ታርሞ ሊቀርብ እንደሚገባ፤ ዘርፉ በአደራ ለሚላክለት ሂሳቦች ለታለመላቸው አላማ ብቻ ወጪ በማድረግ የወጪውንና ከወጪ ቀሪ ያለውን ሂሳብ ለባለበጀቱ መ/ቤት ሊያሰውቅ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.16 <u>በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ኃላፊ ሳይረጋገጥ የተፈጸመ ክፍያ</u>

- በውጭ ጉዳይሚኒስቴር ብር 191,113,989.03
- በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም <u>559,709.52</u>

በድምሩ <u>191,673,698.55</u>

ማንኛውም ሂሳብ ወጪ ከመደረጉና በመዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው አካል መፈረም (መረጋገጥ) እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.17 <u>በኦዲት ያልተሸፈኑ ወጪዎች</u>

4.17.1 የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ሚያዚያ 2006 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 809/06 አንቀጽ 7(3)ን መሠረት አድርጎ በሚንስትሩ በወጣው መመሪያ ቁጥር መከ-መ803 መሠረት ኦዲት የማይደረጉ የወጪ ሂሳቦች ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው ኦዲት ያልተደረጉና የወጪዎቹን ትክክለኛነት ማረጋጥ ያልተቻለ ሂሳብ ከአጠቃላይ ወጪው ብር11,318,454,186.83 ውስጥ 7,472,151,130.27 በተጨማሪም ከመመሪያው ውጪ ለኦዲት ያልቀረበ የሲቪል ሠራተኞች ደመወዝ ብር 19,336,823.34 ሲሆን በድምሩ ብር **7,491.487,953.61** (66.18%) ለኦዲቱ ያልቀረበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

4.17.2 ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አልግሎት በአገልግሎቱ ማቋቋያ አዋጅ ቁጥር 804 /2005 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) ለዋና ዳይሬክተር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት እንዲሁም በደብዳቤ ቁጥር ብመደአ1/8964 ጥር 10 ቀን 2009 ዓ.ም በተገለጸው መሠረት ከአጠቃላይ ወጪው ብር 463,339,212.56 ውስጥ (85.10%) ሚስጥር በመሆኑ በኦዲቱ አልታየም፡፡

4.17.3 የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ የኤጀንሲውን አዋጅ ለማስፈጸም በተቋሙ በፀደቀው የሚስጠራዋ ሃብቶች ምደባ መመሪያ ክፍል 3 የሃብት ምዝገባ ምደባ ጥበቃ ሂደት በሚለው ስር ሰነዶች እና መዛግብትን በሚመለከት የሰው ሃይል ፕሮፋይል/ቅጥር፣ እድገት

ዝውውር የመሳሰሉት የያዙ ሰነዶች ሚስጥራዊ በመሆናቸው ምክንያት ከጠቅላላ የበጀት ዓመቱ ወጪ በድምሩ ብር 237,259,030.01(29.65) በኦዲቱ አልታየም፡፡

5. ተከፋይ ሂሣብ

5.1. የተከፋይ ሂሣብ የቆይታ ጊዜ ትንተና

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል በተገባው ውልና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 340,571.66 በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-30 ተመልክቷል/

የተከፋይ ሂሳቡ ለሚመለከተው አካል ክትትል ተደርጎ ክፍያው እንዲፈጸም በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

• ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	ብር	551,907.71
• የሀገር መከለከያ ሚኒሰስቴር	ብር	95,816,056.39
• ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን		20,986.25
• ኢንቨስትመንት ኮሚሽን		13,340.00
ድምር		**96,402,290.35**

ከፍተኛው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴ ሲሆንማስረጃ ያላቸውን ተከፋይ ሂሳቦች ማስረጃቸውን በማጣራት ለሚመለከተው አካል መክፈል፣ ማስረጃ የሌላቸውን ሂሳቦች ለይቶ ማውጣት እና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አስፈላጊው እርምጃ እዲወሰድ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.3 በተከፋይ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ

- የተከፋይ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በሂሳብ መደብ 5054 የተቀጽላ የሂሳብ ቋት /subsidiary ledger/ ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) በድምሩ ብር 33,860,883.91 ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡

- የተከፋይ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በሂሳብ መደብ 5058 ከ2008 በጀት ዓመት የዞረ ብር 15,379,981.89/Cr/ ፤እንዲሁም በ 2009 በጀት ዓመት ኤጀንሲው የሰበሰበው ብር 4,130,982.07/Cr/ በድምሩ ብር 19,510,963.96 እንዲሁም በምዝገባ ከግኸ ላይ የተቀናነሰና በምዝገባ የሚታይ ብር 2,385,180.02/Dr/በድምሩ ብር 17,125,783.94 የተጨማሪ እሴት ታክስ ለገቢዎችና ጉምሩክ መተላለፍ ሲገባው ሳይተላለፍ ተገኝቷል፡፡

<u>በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ዋሽንግተን በቀን 24/04/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 254470 ብር 1,093,964.48 በቂ ማስረጃ ሳይቀርብለት ከሂሳብ መደብ 5002 (ልዩ ልዩ ተከፋይ) ወደ ሂሳብ መደብ 1489 /ልዩ ልዩ ገቢ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሀራሬ ኢ.ምባሲ ለውሎ አበል የተከፈለ ገንዘብ በስህተት ድጋሚ በተከፋይነት የተመዘገበ በመሆኑ ስህተቱን ለማስተካከል ተብሎ ያለማስረጃ ተከፋይ(5002) ብር 4,918.00 ዴቢት እንዲሁም ልዩልዩ ገቢ(1489) ብር 4,918.00 ክሬዲት ተመዝግቧል
- ለገዳሪፍ ቆንፅላ በተከፋይነት የተያዘ ብር 558,748.15 ለማጥፋት በሚል ተከፋይ(5002) ብር 558,748.15.00 ዴቢት እንዲሁም ልዩ ልዩ ገቢ(1489) ብር 558,748.15 ክሬዲት ተመዝግቦ ተገኝቷል፣በሆኑም ፊሰስ የተደረገበት ማስረጃ አልቀረበም፡፡
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ካርቱም ከተፈቀደው የግንቦት ሃያ በዓል ያልተጠቀሙበት ብር 447.30 ለማጥፋት በሚል በተከፋይ (5028) ብር 447.30 ዴቢት እንዲሁም ልዩ ልዩ ገቢ(1489) ብር 447.30 ክሬዲት በማድረግ ምንም መነሻ ሰነድ ሳይቀርብለት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ቆንፅላ ጄነራል ፑንትላንድ የመረጃና ደህንነት የመከታተያ ክፍያ በሚል (በዶላር 800.00) በብር 17,920.00 በተከፋይ (5028) ዴቢት እንዲሁም (4101) ክሬዲት በማድረግ ምንም መነሻ ሰነድ ሳይቀርብለት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ ጅቡቲ የቫት ተመላሽ የተደረገ ምዝገባ በሚል በተከፋይ የተያዘ ብር 47,803.68 ለማጥፋት (5002) ብር 47,803.68 ዴቢት እንዲሁም ልዩ ልዩ ገቢ(1489) ብር 47,803.68 ክሬዲት የተመዘገበው በቫት ሂሳብ መደብ መመዝገብ

ሲገባው 5002 ሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፣በተጨማሪ ገንዘቡን የሚመለከተው አካል ተመላሽ ማድረግ ሲገባው እንደ ልዩ ልዩ ገቢ ገቢ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

- የኢፌዲሪ ኤምባሲ ብራሰልስ ለረጅም ጊዜ የተከንባለለ ለማወራረድ የተደረገ ምዝገባ ብር 189,743.52 ለማጥፋት በሚል (5028) ብር 189,743.52 ዴቢት እንዲሁም ልዩ ልዩ ገቢ (1489) ብር 189,743.52 ክሬዲት በማድረግ ምንም መነሻ ሰነድ ሳይቀርብለት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ብር 113,952,340.72 ውስጥ ብር 98,480,182.11 ለተከፋይ ሂሳቡ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን ቀሪው ብር 15,472,158.61 ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ብር 113,952,340.72 ውስጥ የ2009 በጀት ዓመት ኦዲት እስከተጠናቀቀበትቀን ድረስ ብር 58,518,178.69 የተወራረደ የተከፋይ ሂሳብ ተብሎ ኦዲት ግኝት ላይ ቢጠቀስም ማስረጃ ቀረቦለት የተወራረደ ብር 2,167,903.26 ሲሆን ቀሪው ብር 56,350,275.43 ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳብን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ኢንቨስትመንት ኮምሽን</u>

- 5054 (በሌሎች መያዣዎች) ሂሳብ መደብ በተቀጽላ ሌጀር (01) ብር 347,047.71. ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በዴቢት--
- በ5055 (የውል ማስከበሪያ መያዣዎች) ሂሳብ መደብ በተቀጽላ ሌጀር (01፣ 05፣ 07) በድምሩ ብር 12,536.53 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ዴቢት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በዚህም የተከፋይ ሂሳቦቹ ተቀጸላ ሌጀር ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፤

<u>ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>

- በጠቅላይ ፍ/ቤት የተከፋይ ሂሳብ መደብ 5005 በተቀጽላ ሌጀር (0002፤0001) ብር 226,604.90 የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት መመዝገብ ሲገባው በዴቢት ተመዝግቦ በመገኘቱ የተከፋይ የሂሳቡ በብር 226,604.90 አንሶ ተገኝቷል፡፡
- በሂሳብ ሂሳብ መደብ 5002 በተቀጽላ ሌጀር(0000) ብር 2912.09 በክሬዲት መመዝገብ ሲገባው በዴቢት በተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በዚህም የተከፋይ የሂሳቡ በብር 2912.09 ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፡

- ከተከፋይ ሂሳብ መደብ 5055 በተቀጽላ ሌጀር(0000፤0001፤0002፤0033) ብር 391,102.07 የሂሳብ ሚዛን በክሬዲት መመዝገብ ሲገባው በዴቢት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡በዚህም የተከፋይ ሂሳቡ በብር 391,102.07 ዝቅ ብሎ ሊታይ ችሏል፡፡

ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

- በአስተዳደር ዘርፉ በሂሳብ መደብ 5061 የተለያዩ የተቋራጮች የሪቴንሽን ሂሳብ በድምሩ ብር 50,744,529.11 በየተቋራጩ ስም (በተቀጽላ ሌጀር) ያልተያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን የታየባቸውን የሂሳብ እንቅስቃሴ ምክንያት በማጣራት ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት በትክክል ማለፋቸውን እንዲሁም ተቀጽላ ሌጀሮች ከጀነራል ሌጀር ሳይገናዘብና ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ክትትል ማድረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6. የበጀት አጠቃቀም

6.1.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ(መደበኛ በጀት)

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	ብር 330,099,679.28
የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም	791,444.38
ድምር	330,891,123.66

ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

6.1.2 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ካፒታል በጀት

- ፌዴራልፖሊስ ብር15,329,347.23

መ/ቤቶቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ የበጀት ዝውውር በማድረግ አስፈቅደው ስራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

ኦዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2009 በጀት ዓመት ከመደበኛ ብር **502,972,929.34** እና በ4 መ/ቤቶች ብር156,926,283.26 ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፡- ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ 33 ተያይዟል)

መ/ቤቶቹ በጀቱን በተጨባጭ ሊሰሩ ካቀዱት ተግባር ጋር በማገናዘብ እና ያለፉትን ዓመታት አፈፃፀም በመገምገም የበጀት ዝግጅት የሚሻሻልበትን ሁኔታ ማመቻቸትና መከታተል እንደሚኖርባቸው በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.የዕቃና ንብረት አስተዳደር

7.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት

- የመሥሪያ ቤቶች የንብረት አስተዳደር መንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በርካታ የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ- 34 ተያይዟል)

7.2 ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች

በንግድ ሚኒስቴር

ንብረቶች ተገዝተው በሞዴል 19(የዕቃ ወይም የንብረት ገቢ) እንዲሁም በሞዴል 22 (የንብረት ወጪ) ሲደረጉ የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) በሁለቱም ገቢም ሆነ ወጪ ሲደረጉ መመዝገባቸውን ኦዲት ሲደረግ በተለያየ ጊዜ የተገዙት ኮምፒውተር እና ፕሪንተር በማለት ብቻ የተፃፉት በሞዴል 19(የዕቃ ወይም የንብረት ገቢ) ከቁጥር 92450 ፣ 92904 እስከ ቁጥር 922950 ከጳጉሜ/2008 እስከ ግንቦት 30/2009 እንዲሁም በሞዴል 22 (የንብረት ወጪ ደረሰኝ) ከተመዘገበበት ከሀምሌ 8/2008 ዓ.ም እስከ ግንቦት 27/2009 ዓ.ም ከቁጥር 942402 እስከ ቁጥር 942956 ባሉት በገቢ የተመዘገቡት በድምሩ 76 ላፕቶፖች ፣ ዴስክቶፖች ፣ ካሴት ሪከርደር እና ሬዲዮ መገናኛ እንዲሁም በሞዴል 22 ወጪ የሆኑት 66 ላፕቶፖች እና ዴስክቶፖች እንዲሁም 5 ፕሪንተሮች የመ/ቤቱ ንብረቶች ተገዝተው በገቢም ሆነ በወጪ ምዝገባ ሲከናወን የተመረቱበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡

በመመሪያው መሠረት የመንግስት ቋሚ ንብረቶች ተገዝተው እንደመጡ ሂሳቡ ከመወራረዱ በፊት በሞዴል 19(በዕቃ ወይም በንብረት ገቢ) ገቢ ሲሆኑ በጅምላ ሳይሆን ለቁጥጥርና ክትትል ያመች ዘንድ እያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የተመረቱበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) እነዲሁም በሞዴል 22 ወጪ ሲሆኑም በሞዴል 19 በትክክል የተመዘገበው የተመረተበትን የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥሩን) ተመሳክሮ ተስተካክሎ ሊመዘገብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

በፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር

- በንብረት ክፍል ውስጥ በሞዴል19 ገቢ ሳይደረግ የተቀመጠ በጣቃ የተገዛ የደንብ ልብስ መገኘቱ፤
- የቋሚ ዕቃዎች፣ የአላቂ እቃዎች፣ አዲስ እና አሮጌ እንዲሁም የሚወገዱ ዕቃዎች ጭምር በአንድ ስቶር ውስጥ በአንድ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ፤
- ብዛታቸው 6 model C-EXV 32 የሆኑ የፎቶ ኮፒ ማሽን ቀለም ያለአገልግሎት በእስቶር ውስጥ ተቀምጦ መገኘቱ፤
- 92A የፕሪንተር ቀለም ብዛት 4፣ GPR-34/C-EXV 32/NPG-50 TONER ብዛት 20፣ የፕሪንተር ቀለም 15A ብዛት 4 ፣ 53 A ብዛት 2 ፣ 29 A ብዛት 1 እና 49 A ብዛት 1፣ በእስቶር ውስጥ ከ2007 ዓ.ም ከተገዙበት ጊዜ ጀምሮ ለ3 አመታት ያለምንም ጥቅም ተቀምጠው ተገኝተዋል፡፡
- ከ300 በላይ የሚሆኑ ብዛት ያላቸው ጎማዎች፣ የመኪና ባትሪዎች፣ የቤት ቆርቆሮ እና ሚስማር መወገድ ሲገባቸው ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ምንም አይነት እርምጃ ሳይወሰድ ግቢ ውስጥ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት

- የጽ/ቤቱ መጋዘን ውስጥ ከየቢሮው ተመላሽ ሆነውና ቢጠገኑ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የባለሙያ ተሽከርካሪ ወንበሮች፤ባለመሳቢያ ሼልፎች፤የእንግዳ ወንበሮች ያለ አገልግሎት ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡
- ለመገናኛ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መተላለፍ የነበረባቸው አሮጌ ኮምፒውተሮች ሲስተም ዩኒታቸው ብቻ ተወስዶ ቀፎው ብቻ አላግባብ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

አዲስ አበባ ቀጠሮ ማረፊያ ቤት አስተዳደር

- የስቶክ ወጪ መጠየቂያ ተጠቃሚ የስራ ክፍሎች ወይም ሰራተኞች ለስራ የሚያስፈልጋቸውን ንብረት በሚፈልጉበት ወቅት የዕቃ መጠየቂያ ቅጽ በተገቢው ሁኔታ በመሙላትና በሚመለከተው ኃላፊ ተፈቅዶ ወጪ መደረግ እንዳለበት መመሪያው ቢገልጽም ነገር ግን በተወሰኑ ወጪ በተደረጉ ዕቃዎች ላይ በመጠየቂያው ላይ ያሻሻለው ባለስልጣን በሚለው ላይ ሳይፈረም

ተገኝቷል፡፡በተጨማሪም ተፈርመው ያሉትም በጠያቂው የስራ ክፍል ኃላፊ መፈረም ሲገባው በንብረት አስተዳደር ኃላፊ የሚፈረም መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- የምግብ ማከማቻው/ስቶር/በያንዳንዳቸው የምግብ አይነት ተለይተው የተያዙ የስቶክ መመዝገቢያ ካርዶች ያለመኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ዋናው መ/ቤት

- በሰኔ 30,2009 በጀት ዓመት ላይ በአላቂ ዕቃ ቆጠራ ሪፖርት ላይ ላለማካተት በሞዴል 22 ቁጥር 45977 እና 45978 በድምሩ ብር 610,487.41 የጽ/መሳሪያና ጽዳት ዕቃዎች በንብረት ክፍል ጠያቂነት ወጪ ተደርገው ተገኝተዋል፡፡
- ለቋሚ ንብረት ተጠቃሚዎች የንብረት ምዝገባ ካርድ ያለ ቢሆንም የቋሚ ንብረት መለያ ቁጥር ተሰጥቶ ያላለቀ በመሆኑ የሚያስፈልገው መረጃዎች በሙሉ ወደ ተጠቃሚ ካርድ ያልገባ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- የንብረት መመዝገቢያ ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ በአግባቡ የማይመዘገብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- የላፕቶፕ ኮምፒውተሮች ወጪ ሲደረጉ በተጠቃሚው ካርድ ላይ የፋብሪካ ቁጥር/ሲሪያል ቁጥር የማይመዘገብ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ተሰጥቶ ያላለቀ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ጋራዥ

- ለያንዳንዱ ተሽከርካሪ አስፈላጊውን መረጃ የያዘ የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ
- የመለዋወጫ ዕቃዎች በዓይነታቸው /Part Number/ተስተካክለው መቀመጥ ሲገባው በአግባቡ ተለይተው ያልተቀመጡና ቢን ካርዳቸው ላይ በጥቅል የተመዘገበ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡
- የመለዋወጫ ዕቃዎችን ስቶክ የመመዝገብና የመረከብ ስራው በአንድ ባለሙያ እየተሰራ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

- የንብረት መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ የማይጠቀም መሆኑ፤
- ለቋሚ ዕቃዎች ሙሉ በሙሉ ተከታታይ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

ንብረት የመመዝገብና የመረከብ ስራ በተለያዩ ሰዎች እንዲሠራና የንብረት አስተዳደር ስራን የሚያከናውነው የስራ ክፍል የንብረቱን ተጠቃሚ ሰዎችን የንብረት ምዝገባ ካርድ

ሊመዘግብና ወቅታዊ ሊያደርግ እንደሚገባ፤አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች በመለየት በመንግስት የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ደንብ መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ፣ ለእያንዳንዱ የቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር መሰጠት እንዳለበት እንዲሁም ይህ የመለያ ቁጥርም በቋሚ ንብረት ላይ መለጠፍ እንዳለበት በአጠቃላይ መ/ቤቶቹ በመንግስት ንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ መሠረት ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት</u>

- በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውስጥ ኦዲት ከተገኘ የንብረት ጉድለት ከብር 134,668.59 ውስጥ ብር 45,636.10 ተመላሽ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 89,032.49 ከደመወዛቸው ተቀንሶ ተመላሽ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

<u>የፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ልማት ኤጀንሲ</u>

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ፊሰስ እንዳይደረግ **የብር 226,379.01** ዋጋ ያላቸው አላቂ ዕቃዎች ከዕቃ ግምጃ ቤት ወጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ቆጠራ እና ማመዘዛኛ ሊሠራ እንደሚገባ ፣ እንዲሁም ከቋሚ ገንዘብ ሰብሳቢዎች ውጪ ገንዘብ መሰብሰብ ህጉ ስለማይፈቅድ የማይመለከታቸው ሠራተኞች ገንዘብ እንዳይሰበስቡ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በኩል ያልተሰሩ ሥራዎች በመዳሰስ እንዲሁም 49 የሚ/ር መ/ቤቱ ሠራተኞች ገንዘብ የሰበሰቡበት መሂ/1 እና የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በሙሉ ቆጠራ ተካሂዶ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ፤ እንዲሁም ገንዘብ የመሰብሰብ ኃላፊነት ተሰጥቶአቸውና በሥራ መዘረዝራቸው ተካቶ ተጠያቂነት ጭምር የሚኖርበት ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በንብረት ክፍል የሚገኙ አላቂ ዕቃዎች ተቆጥረው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊደረግና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ባሉት ቀናት ከንብረት ክፍል እንደወጣ ፈቀድ የሰጠው ኃላፊ ሊጠየቅ እንደሚገባ በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

7.3 በነዳጅና የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች

የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን

- የነዳጅ፤የዘይት እና ቅባት በመጠየቂው ቅጽ የጠያቂውን ስም ብቻ በመግለጽ በጠያቂው ሳይረጋገጥና የተጠየቀበት ቀን ሳይገለጽ በፈቃጅ ስም ብቻ ተፈርሞ የብር 3,399.17 የነዳጅ ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ነዳጅ በሚመለከተው ሠራተኛ በመጠየቅ በፈቃጁ ሊረጋገጥና የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር ላይ ተገቢው ክትትልና ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

7.4 የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ አጠባበቅና አያያዝ በ ተመለከተ

ንግድ ሚኒስቴር

- የ2009 በጀት ዓመት የንግድ ሚኒስቴር የውስጥ ኦዲት ሥራ በዓመቱ መጨረሻ የውስጥ ገቢ ደረሰኝ መሂ/1 እና ኤሌክትሮኒክስ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በትክክል ለመቆጠሩና ሚዛን ተሰርቶ መቅረቡ ሲጣራ 49 የሚ/ር መ/ቤቱ ሠራተኞች ገንዘብ የሰበሰቡበት መሂ/1 እና የኤሌክትሮኒክስ ገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በሙሉ በቆጠራ ያልተካተተ መሆኑ፤
- የገቢ ደረሰኞች ሥርጭትን በተመለከተ ሲረከቡ ፣ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሲሰራጭ እና እንዲሁም ከየቅርንጫፉ ገንዘብ ሲሰበሰብ ለእያንዳዳቸው ሰራተኛ(የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ) በየስማቸው ሌጀር ያለመዘጋጀታቸው ፣
- የተሠራባቸው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች መሂ/1 ወደ ንብረት ክፍል ወይም ወደ ሰነድ ያዥ ክፍል ሙሉ በሙሉ ተመላሽ የማይደረግ መሆኑ ፣
- የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ከንብረት ክፍል በሞዴል 22 ወጪ የሆነው በገንዘብ ያገዦች ብቻ መሆኑን ኦዲት ሲደረግ የሚ/ር መ/ቤቱ ዋና ገንዘብ ያገዥ ወይም ረዳት ገ/ያዥ በድምሩ 6 ብቻ መሆናቸውን ከፋይናንስና ከሰው ኃይል ሲረጋገጥ 49 የሚ/ር መ/ቤቱ ሠራተኛች በገንዘብ አሰባሰብ ላይ መገኘታቸው፤

በብሔዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት

- የገቢ ደረሰኞች ሥርጭትን በተመለከተ ሲረከቡ ፣ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሲሰራጭ እና እንዲሁም ከየቅርንጫፉ ገንዘብ ሲሰበሰብ ለእያንዳዳቸው ሰራተኛ(የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ) በየስማቸው ሌጀር ያለመዘጋጀታቸው፣

- ያልተሠራባቸው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች መሂ/1(የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ) መሂ/2(የውጭ ምንዛሬ የገቢ ደረሰኝ) ንብረት ክፍልም ሆነ በሰነድ ያዥ እጅ ያለመቀመጣቸው ፡፡
- የተሠራባቸው የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ወደ ንብረት ክፍል ወይም ወደ ሰነድ ያዥ ክፍል ተመላሽ የማይደረግ መሆኑ፤

እያንዳንዱ ገንዘብ ያዥ የወሰደውን የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ (መ/ሂ/1 ፣ መሂ/2 እና ሌሎችም ደረሰኞች) በደረሰኙ (በጥረዙ) ልክ ከ--እስከ የተሰራበትንና ያልተሰራበትን የጥራዝ ብዛትና የገቢውን ትክክለኛነት የሚያሳይ ምዝገባ መካሄድ እንዳለበት፡፡ በየቦታው ያሉ የተሠራበትና ያልተመለሱ ጥራዞች ከ6ቱም ቅ/መ/ቤቶች እንዲሁም የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት ቦታ ተዘጋጅቶላቸው በዋናው መ/ቤት መመለስ እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

7.5 <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም</u>

7.5.1 የመሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:- ሊብሬ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው)፣በብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜያት የቆሙ ተሽከሪካሪዎችና ሌሎች የተሽከርካሪዎች አያያዝ ችግሮች እንዳሉ ተውቋል፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ -35 ተያይዟል)

በብልሽት የቆሙት ተሽከርካሪዎች ከመቆም ብዛት መንግስት ለተጨማሪ ወጪ ከመዳረጉ በፊት አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ሥራ የሚገቡበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባና፣ ይህ ካልሆነም በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ ወይም ለሚመለከው አካል ርክክብ እንዲደረግ አስፈላጊው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.5.2 <u>ሌሎች የተሽከርካሪ አያያዝና አጠባበቅ ድክመቶች</u>

<u>ንግድ ሚኒስቴር</u>

- ኒሳን አውቶሞቢል የባለቤትነት መታወቂያ E023252 ፣ የሰሌዳ ቁጥር 4-03123 ፣ የሞተር ቁጥር ፣ OG13233181 ፣ የሻንሲ ቁጥር JNICEAN 1620002354 የሆነ ተሽከርካሪ በቁጥር 01.1.22.7/10696 ግንቦት 23/2009 ዓ.ም የሚ/ር ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ዝውውር እንዲፈጸምላቸው ተስማምተው ከንግድ ሚ/ር በሞዴል 22 ወጪ ሆኖ ወደ ቡናና ሻይ ገቢ ሲሆን በሞዴል 19(የዕቃ ወይም የንብረት ገቢ ደረሰኝ) ገቢ የሆነበት ዝርዝር መረጃ ርክክብ ሳይኖር መኪናው ተዛውሮ ተገኝቷል፡፡

- ያለምንም ማስረጃ የተሰጠውም ተሸከርካሪ ትኩረት ተሰጥቶት ርክክብ ተካሂዶ ማስረጃው ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት

- የሰሌዳ ቁጥር 4-20867 ላንድ ክሮዘር ዳብል ጋቢና ለአፋር ክ/ቅ/ጽ/ቤት በሚል የጽ/ቤቱ ሰራተኛ ላልሆነ ግለሰብ ንብረቱ ወጪ ሆኖ ተሰጥቶ ተገኝቷል፡፡
- ከፍተኛ ኃላፊዎች በይዞታቸው ስር ሆኖ የሚጠቀሙበት አንድ መኪና እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው አገልግሎት የሚውል አንድ አውቶሞቢል እንደሚመደብላቸው ፤ ለሚመደቡትም ተሽርካሪዎች መመሪያው በሚፈቅደው የነዳጅ መጠን መሠረት መጠቀም እንደሚችሉ ይገልጻል ፡፡ ነገር ግን የቦርዱ ሰብሳቢ መመሪያው የሚፈቅድላቸው 2 ተሽከረካሪዎች እየተጠቀሙ ቢሆንም 3 መኪኖችን በግል ይዞታቸው ስር ሆነው በተጨማሪ እንደሚጠቀሚበት ታውቋል ፡፡

የቦርዱ ሰብሳቢ መመሪያው የሚፈቅድላቸውን በይዞታቸው ስር ሆኖ የሚጠቀሙበት ከግልና ከቤተሰብ ተሽከረካሪ ውጭ አላግባብ የተያዙት ተሽከርክሪዎች ለጽ/ቤቱ አገልግሎት እንዲውሉ እንዲደረጉ የነዳጅ አጠቀቀምም በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ፤ንብረትነቱ የምርጫ ቦርድ ጽቤት የሆነውን ንብረት የጽ/ቤቱ ሰራተኛ ላልሆነ ግለሰብ እንዲጠቀሙበት ማድረጉአግባብነት የሌለው በመሆኑ አሠራሩ ሊቆም እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ጠቅላይ ፍ/ቤት

- በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አገልግሎት የማይሰጡ የሰሌዳ ቁጥር 4-03888፤ 4-01862 ፤4-07627፤ 4-07831፤ እነዲሁም በከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ሴሌዳ ቁጥር 4-01093፣ 4-14469፣ 4-08024፣ 4- 04167፣ 4-03230፣ 4-03213፣ 4-11498፣ 4-03217፣ 4- 07678 በሜዳ ላይ ለዝናብና ለፀሐይ ተጋልጠው ተገኝተዋል፡፡ፍ/ቤቱ መኪኖቹ የከፋ ብልሽት እንዳያገናቸው ሊወገዱ የሚገባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

7. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፓርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ

ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት በቀረበው የኦዲት አስተያየት በተሰብሳቢ ሂሳቦች፤ በተከፋይ እና ማስረጃ ሳይቀርብላቸው በወጪ የተመዘገቡ በርካታ ሂሳቦች በተሰጠው የማሻሻያ ሀሰብ መሰረት በ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት እርምጃ ያልተወሰደባቸውና ማስተካከያ ያልተደረገባቸው መሆኑ ተረጋግጠል፡፡ ቀጥለው የተመለከቱት መ/ቤቶች በበርካታ ነጥቦች ላይ እርምጃ ያልወሰዱ ናቸው፡፡

- የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ
- የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር
- ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር
- የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር
- የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ
- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳዳር
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ፌዴራል ፖሊስ
- በፌዴል ጠቅላይ ፍ/ቤት
- የፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ
- የፌዴራል ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን
- የበጎ አድራጎትና ድርጅቶች ማህበራት ኤጀንሲ
- ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
- የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት በጽ/ቤት

ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ በቂ፣ባለ መሆኑ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ አሳስበናል፡፡

9.<u>ልዩ ልዩ</u>

9.1 የሴቶች ዳይሬክቶሬት የሌላቸው መ/ቤቶች

- ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ
- ፌዴራል ፖሊስ

10. የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት በጽ/ቤት

ለጉዳዩ ባለቤት ኖሮትና አስፈላጊ በጀት ተመድቦለት እንዲሰራ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አሳስበናል፡፡